# በምዕራብ ሸዋ ዞን አደአ በርጋ ወረዳ የአምስት ግለሰቦች የጌረርሳ /Geerarsaa/ ክዋኔና ይዘት አውዳዊ ትንተና ገጠመኞቻቸውን ከመግለፅ አንፃር

በግርማ አዱኛ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ጥቅምት 2005

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

# በምዕራብ ሸዋ ዞን አደአ በርጋ ወረዳ የአምስት ግለሰቦች የጌረርሳ /Geerarsaa/ ክዋኔና ይዘት አውዳዊ ትንተና ገጠመኞቻቸውን ከመግለፅ አንፃር

በግርማ አዱኛ

አማካሪ፡

አቶ ሙሉጌታ ነጋሳ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

**በምዕራብ ሸዋ ዞን አደአ በርጋ ወረዳ የአምስት ግለሰቦች የጌረርሳ /Geerarsaa/ ክዋኔና ይዘት አውዳዊ ትንተና ገጠመኞቻቸውን ከመግለፅ አንፃር**

በግርማ አዱኛ

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

<u>አማካሪ</u>

ስም [illegible] ፊርማ

<u>የፈታኝ (የውስጥ)</u>

ስም [illegible] ፊርማ

<u>የፈታኝ (የውጪ)</u>

ስም [illegible] (ዶ/ር) ፊርማ

<u>የትምህርት ክፍሉ ሊቀመንበር</u>

ስም ፍርማ

# ምስጋና

በመጀመሪያ ደረጃ ጥናቴን ከመጀመሪያ አንስቶ እስከ መጨረሻ ድረስ በትህግስት አንብበው በማረምና በማስተካከል የምክር አገልግሎት ለሰጡኝ ለአቶ ሙሉጌታ ነጋሳ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። በመቀጠል ጥናቴ ከግቡ እንዲደርስ ጥናቱ የሚካሄድበትን ገንዘብ በመስጠት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላደረገልኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን በጣም አመሰግናለሁ

በተጨማሪም ከመረጃ ሰጪዎቼ ጋር በማገናኘት ለጥናቱ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላደረጉልኝ መንገድ መሪዬ ለነበሩ ለአቶ ሥዩም አዱኛና ሳይታክቱ ለጥናቱ አጥጋቢ የሆነውን መረጃ ለሰጡኝ ለአምስቱ መረጃ ሰጪዎቼ ምስጋናዬ የላቀ ነው። ወረዳውን በተመለከተ ሳይታክቱ መረጃ ለሰጡኝ ለአደአ በርጋ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊ ለአቶ በለጠ ታደሰ ምስጋናዬን ሳላቀርብ አላልፍም።

ለጥናቴ መረጃ ለማሰባሰብ መስክ በነበርኩበት ጊዜ መኝታና ምግብ በመስጠት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላደረጉልኝ ለአባቴ ለአቶ አዱኛ ጅማና ለናቴ ለወ/ሮ ጥሩነሽ ኪዳኔ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ። እንዲሁም በቤታቸው ተገኝቼ ለጥናቴ መረጃ ለመሰብሰብ ለፈቀዱልኝ ለአቶ አዱኛ ጅማ፣ ለአቶ ድርባ ጅማ፣ ለአቶ ድሪባ ዋሚና ለአቶ ድዳ ዳዲ ከነባለቤቶቻቸው እጅግ በጣም አድርጌ አመሰግናለሁ።

በመጨረሻም የጥናት ጽሑፌን ለተየበችልኝ ወ/ሪት ፋሲካ ዘውዱን እጅግ በጣም አመሰግናለሁ።

## ማውጫ

ምስጋና .......... i

ማውጫ .......... ii

የካርታዎች ዝርዝር .......... vi

የፎቶዎች ዝርዝር .......... vi

አጠቃሎ .......... vii

ሙዳየ ቃላት .......... viii

ምዕራፍ አንድ .......... 1

1.መግቢያ .......... 1

1.1.የጥናቱ ዳራ .......... 1

1.2.የጥናቱ ዓላማ .......... 4

1.2.1.የጥናቱ ዋና ዓላማ .......... 4

1.2.2.የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች .......... 4

1.3.የጥናቱ አስፈላጊነት /ጠቀሜታ/ .......... 4

1.4.የጥናቱ አደረጃጀት .......... 5

1.5.የጥናቱ ወሰን .......... 6

1.6.የአጠናን ዘዴ .......... 7

1.7.የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች .......... 8

1.8.ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች .......... 9

1.8.1.ያጋጠሙ ችግሮች .......... 9

1.8.2.የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች .......... 10

1.9.የአዳአ በርጋ አካባቢያዊ ዳራ .......... 10

1.9.1.የወረዳው ስም ስያሜ .......... 10

1.9.2.የወረዳው አቀማመጥ....10
1.9.3.የወረዳው አየር ንብረት....11
1.9.4.የወረዳው ህዝብ ብዛት....11
1.9.5.የወረዳው ሕዝብ መተዳደርያ....12
1.9.6.በወረዳው ውስጥ የሚገኙ የቱርዝም መስዕቦች....13
1.9.7.በወረዳው ውስጥ የሚገኙ ተፈጥሮአዊ፣ ሰው ሰራሽና ባህላዊ ሀብቶች....14
ምዕራፍ ሁለት....17
2.ክለሳ ድርሳናት....17
2.1.የጽንሰ ሃሳብ ቅኝት....17
2.1.1.ስነ-ቃል....17
2.1.1.1.የቃል ግጥም....17
2.1.1.2.የቃል ግጥም ዓይነቶች....18
2.1.1.2.1. የጌረርሳ ምንነት....18
2.1.1.3.የቃል ግጥም ባህሪያት....19
2.1.1.3.1. ክዋኔ....20
2.1.1.3.1.1.አውዳዊ ጥናት /Contextual Study/....23
2.1.1.3.1.1.1.ባህላዊ አውድ / cultural context /....26
2.1.1.3.1.1.2.ማህበራዊ አውድ /Social Context/....27
2.1.1.3.2.ተለዋዋጭነት....30
2.1.1.3.3.ድግግሞሽ....31
2.2.የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት....31
ምዕራፍ ሦስት....36
3.የመረጃ ሰጪዎች ፕሮፋይል....36
3.1.የአቶ አባተ ኤጀርሳ ህይወት ታሪክ....36
3.2.የአቶ ብርሃኑ አዱኛ ህይወት ታሪክ....38

3.3.የአቶ ቸሩ ድንቁ ህይወት ታሪክ......40
3.4.የአቶ ድሪባ ለታ ህይወት ታሪክ......43
3.5.የአቶ መኰንን ደሜ ህይወት ታሪክ......45
ምዕራፍ አራት......48
4.መረጃ ሰጪዎች የከወኑት ጌረርሳ ላይ የተደረገ የይዘት ትንተና......48
4.1.አቶ አባተ ኤጀርሳ የከወኑት ጌረርሳ ላይ የተደረገ ትንተና......48
4.1.1.በሰው ላይ ጉዳት አድርሰው ስለ መታሰር......50
4.1.2.በእስራቱ የተነሳ ስለንብረታቸው በወጪ ማለቅ......55
4.1.3.ስለጠመንጃ መሸጥ......58
4.1.4.ንብረታቸው በማለቁ የተከሰተው ማህበራዊና ስነ-ልቡናዊ ቀውስ......60
4.2.አቶ ብርሃኑ አዱኛ የከወኑት ጌረርሳ ላይ የተደረገ የይዘት ትንተና......63
4.2.1.ስለ መጠጥ ጎጂነት......64
4.2.2.ስለ አዶ ሻክሶ ጉዞ......66
4.2.3.ወሬ ትቶ በርትቶ ስለመስራት......69
4.2.4.ስለ አባት ምክር......73
4.2.5.ስለልማት ሥራ......74
4.3.አቶ ቸሩ ድንቁ የከወኑት ጌረርሳና የይዘት ትንታኔው......75
4.3.1.ብድር መመለስ ባለመቻል ስለመሰደብ......75
4.3.2.ስለ ድህነት አስከፊ ገጽታ......77
4.3.2.1.ወደ ሞጆ ሥራ ፍለጋ ስለመሄድ......78
4.3.3.አቶ ቸሩ ንብረት በማፍራት ክብር ስለማግኘታቸው......79
4.3.4.ስለልማት ሥራ......81
4.3.5.ስለ አባታቸው ሞት......82
4.4.አቶ ድሪባ ለታ የከወኑት ጌረርሳ ላይ የተደረገ ትንተና......84

4.4.1.ስለ ባለቤታቸው ሞት ....................84
4.4.2.በባለቤታቸው ሞት የተነሳ ስለልጆቻቸው መበተን ....................86
4.4.3.ስለ ድህነት ....................89
4.4.4.ከኤድስ በሽታ ራስን ስለመጠበቅ ....................91
4.4.5.ሁለተኛ ባለቤታቸውን ያገኙበት አጋጣሚ ....................93
4.4.6.ስለልማት ሥራ ....................95
4.5.አቶ መኮንን ደሜ የከወኑት ጌረርሳ ላይ የተደረገ ትንተና ....................97
4.5.1.አቶ መኮንን ጠመንጃ መታጠቅ አትችልም ስለመባል ....................98
4.5.2.ስለ ወንድማቸው ሞት ....................100
4.5.3.እናታቸው ወደ ጎንደር እንዲሄዱ አቶ መኮንንን ያዘዙበት ሁኔታ ....................101
ምዕራፍ አምስት ....................104
5.የአምስቱ ግለሰቦች ጌረርሳ የአከዋወን ሂደት ....................104
5.1.የጌረርሳ ክዋኔ አጀማመር ....................108
5.2.የታሚያን ሚና ....................110
ማጠቃለያ ....................114
ዋቢዎች ....................116
አባሪዎች

## የካርታዎች ዝርዝር

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ካርታ ..........................................................15

የምዕራብ ሸዋ ዞን ካርታ........................................................................15

የአደኣ በርጋ ወረዳ ካርታ......................................................................16

## የፎቶዎች ዝርዝር

ፎቶ1. በ19/06/2004 ዓ.ም ለአቶ አባተ ኤጀርሳ በቤታቸው ቃለ መጠይቅ ሲደረግ.....................................................................................36

ፎቶ2. በ15/06/2004 ዓ.ም ለአቶ ብርሃኑ አዱኛ በቤታቸው ቃለ መጠይቅ ሲደረግ.....................................................................................38

ፎቶ3. በ15/06/2004 ዓ.ም ለአቶ ቸሩ ድንቁ በቤታቸው ቃለ መጠይቅ ሲደረግ.....................................................................................41

ፎቶ4. በ20/06/2004 ዓ.ም ለአቶ ድርባ ለታ ቃለ መጠይቅ ሲደረግ................44

ፎቶ5. በ18/06/2004 ዓ.ም ለአቶ መኮንን ደሜ በቤታቸው ቃለ መጠይቅ ሲደረግ.....................................................................................46

ፎቶ 6. አቶ ብርሃኑ አዱኛና አቶ ቸሩ ድንቁ በ21/06/2004 ዓ.ም በአቶ አዱኛ ጅማ ቤት ጌረርሳ አብረው ሲከውኑ....................................105

ፎቶ 7. አቶ ድሪባ ለታና አቶ መኮንን ደሜ በ21/06/2004 ዓ.ም በአቶ አዱኛ ጅማ ቤት ጌረርሳ አብረው ከከወኑ በኋላ ከመዳላ ስጠጡ............106

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዓላማ የጌረርሳ ከያንያን ጌረርሳ በመከወን ገጠመኞቻቸውን በአጠቃላይ ግላዊም ይሁን ማህበራዊ እሴቶቻቸውን እንዴት እንደሚገልፁ ማሳየት ነው፡፡ ለዚህ ጥናት የተመረጡት የመረጃ ምንጮች በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ምዕራብ ሸዋ ዞን አደአ በርጋ ወረዳ የሚኖሩ አምስት ግለሰቦች ናቸው። እነዚህ ግለሰቦች አቶ አባተ ኤጀርሳ፣ አቶ ብርሃኑ አዱኛ፣ አቶ ቸሩ ድንቁ፣ አቶ ድርባ ለታና አቶ መኮንን ደሜ ናቸው። ግለሰቦቹ ለዚህ ጥናት የተመረጡበት ምክንያት ጌረርሳ በመከወን ከፍተኛ ብቃትና ልምድ ያላቸው በመሆናቸው ነው።

የጥናቱ መረጃ የተሰባሰበው ጥናቱ ያተኮረባቸው እነዚህ አምስቱ ግለሰቦች ጌረርሳ በሚከውኑበት አውድ በመገኘት ጌረርሳውን ሲከውኑ ምልከታ በማድረግ ሲሆን ግለሰቦቹ ጌረርሳ እንዲከወኑ ያነሳሳቸውን ጉዳዮችና ምን ማህበራዊና ግለሰባዊ ጉዳዮች ለማስተላለፍ እንደከወኑ ለማወቅ ለግለሰቦቹ ቃለመጠይቅ በማድረግ ነው። ይህ መረጃ በመቅረፀ ድምፅ፣ በፎቶ ካሜራ በመቅረፅና ማስታወሻ በመያዝ የተሰበሰበ ሲሆን በመስክ ላይ ከግለሰቦቹ ጋር በተደጋጋሚ በመገናኘት በመረጃው ላይ የይዘት ትንተና ተደርጓል። ግለሰቦቹ የከወኑትን ጌረርሳ ከህይወት ታሪካቸው ጋር በማገናዘብ ወይንም በማስተያየትና የኑሮአቸውን ሁኔታ በጥልቀት በማጥናት ከህይወታቸው ጋር ግንኙነት እንዳለው ታይቷል። በመሆኑም ግለሰቦቹ ጌረርሳን በመከወን በሕይወት ዘመናቸው ያጋጠማቸውን ጉዳዮች፡ ደስታም ሆነ ሀዘን፣ ክፉም ሆነ በጎ፣ ምቾትም ሆነ ጭንቀትና የመሳሰሉትን ገጠመኞቻቸውን ገልጸዋል። ከያንያኑ ኑሮአቸውን ለማሸነፍ በጉልበት ሠራተኛነት በመቀጠርና ከመንደራቸው ርቀው በመስራት ያገኙት ውጤት ገልፀዋል። በሄዱበት ቦታ የገጠማቸውን ችግር በጌረርሳቸው አንጸባርቀዋል። በጥረታቸው ኑሮቸቸውን ያሸነፉ ግለሰቦች የገኙትን የኑሮ መሻሻል ሲገልፁ ያልተሳካላቸው ደግሞ ያሉበት የኑሮ ጉስቁልናና ለዚህ አስከፊ ኑሮ ያበቃቸውን አጋጣሚዎች በጌረርሳ ገልጸዋል።

በተጨማሪም የግለሰቦቹን የጌረርሳ ክዋኔ ለማገዝና ድምቀት ለመስጠትና ከዋኞች የማህበረሰቡን እሴት እንዲያከብሩ ለማድረግ ታዳሚያን ያደረጉት አስተዋፅኦና በከዋኞችና ታደሚያን መካከል የነበረው ተግባቦት በጥናቱ ውስጥ ተመላክቷል።

## ሙዳየ ቃላት

ቱሩምቡሌ /Turumbullee/- በልጅ ኢያሱ ዘመነ ንግስና የተቋቋመው የከተማ ዘበኛ /Modern Municipal Police/

ዋሮ /Waaroo/- ዋሮ ባርኖስ ወይም ካባ ሳይሆን አዶ ሻክሶ የሚኖሩ ባህላዊ ወርቅ አውጪዎች ከእንጨት፣ ከፕላስቲክ፣ ከልብስና ከመዳበሪያ ከረጥት ሠርተው የሚኖሩበት ጎጆ ነው። የጎዳና ተዳዳሪዎች የሚኖሩበት ዓይነት

ቦሴቶ /Booseettoo/- ተቆፍሮ ወርቅ የሚወጣበት ጉድጓድ

ዋርሳ /Waarsaa/- ዋርሳ የባል ወንድም ሳይሆን በአደአ በርጋ ወረዳ በሙሽራው የሚለመን በሠርግ ጊዜ የሙሽራ አጃቢ፣ ለሙሽራው ሳር የሚቆርጥ፣ ፈረስ የሚይዝ፣ ዳቦ የሚሸከምና የሙሽሪት ቁሳቁሶችን ተሸክሞ ወደ ሙሽራ ቤት የሚወስድ ሰው

እኚ ማረስ /Inyii Qotuu/- አንድ በሬ ብቻ ያለው ሰው ሌላውን አንድ በሬ ከሰው ወስዶ ለራሱ ሁለት ቀን እያረሰ ለባለ በሬው ደግሞ አንድ ቀን በማረስ መተዳደር /የመቀናጆ እርሻ/

ሽጋ /Shiggaa/- ታርሶ የማያውቅ መሬት በማሳ ዳር ላይ የሚገኝ /እዳሪ መሬት/

ክታ /kitaa/- እንደሸሚዝ የሚለበስ በድሮ ጊዜ በእጅ የሚሰፋ

አፍራሳ /Afraasaa/- ከአራቱ ወቅቶች አንዱ ሆኖ ጥር፣ የካቲትና መጋቢት ወራትን የሚሸፍን

ብራ /Birraa/- ከአራቱ ወቅቶች አንዱ ሆኖ መስከረም፣ ጥቅምትና ህዳር ወራትን የሚሸፍን

ጉሊሻ /Guulliishaa/ - በውሃ ርሶ የተድቦለቦለ አፈር

ጬካ /Ceekaa/ - ቆላ የሚበቅል የእንጨት ዓይነት

ቦሶ /Boosoo/- ይህ ቃል ቦሴቲ /Boosettii/ ከሚለው ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙ ሙያ የሌላት ሴት /ፅዳት የሌላት፣ የተስረከረከች ሴት/

ኮሞ Koomoo/- ይህ ቃል ካሜቲ /Kaamettii/ ከሚለው ቃል የመጣ ሲሆን ሙያ ያላት ሴት (ባለሙያ ሴት)

መዳላ /Madaala/- መዳላ ሚዛን የሚለውን ትርጉም የሚይዝ ሳይሆን በአደአ በርጋ ወረዳ የጌረርሳ ከዋኞች የሚጠጡበት ዋንጫ፣ ኩባያ፣ ብርጭቆ፣ ስኒ ወይም መለኪያ ነው። ማንኛውም በወቅቱ የሚጠጣ ነገር ተሞልቶበት የጌረርሳ ከዋኞች የሚጠጡበት ነው። እርስበርስ ከዋኞች ጌረርሳ እየከወኑ በነገር ከተነካኩ እንዳይጣሉ ከመዳላ ያጠጡዋቸዋል። መዳላው ስለሚያስታርቃቸው ከመዳላ ከጠጡ በኋላ በከዋኞች መካከል ጥል አይኖርም ።

ቀያ /Qayyaa/- ጥሩ መአዛ ያላቸው እንደ ቀረፋና ሌሎች እንጨቶችን የቀያ ጉድጓድ ቆፍረው በማዘጋጀትና በጉድጓዱ ውስጥ በማቀጣጠል ሴቶች ጥሩ ውበትና መአዛ እንድኖራቸው የሚታጠኑት ነው።

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

ይህ ጥናት በአደአ በርጋ ወረዳ የጌረርሳ ከያንያን በሚከውኑት ጌረርሳ ውስጥ እንዴት አድርገው ገጠመኞቻቸውን ወይም ህይወታቸውን ይገልፃሉ? የሚለውን አጥንቶ ማሳየት ላይ ያተኮረ ነው። ጥናቱ ያነጣጠረው በአምስት ግለሰቦች የጌረርሳ ክዋኔ ላይ ነው። እነዚህ አምስት ግለሰቦች (ከያንያን) አቶ አባተ ኤጀርሳ፣ አቶ ብርሃኑ አዱኛ፣ አቶ ቸሩ ድንቁ፣ አቶ ድሪባ ለታና አቶ መኮንን ደሜ ናቸው። ግለሰቦቹ የተመረጡት በተለያዩ አውዶች ጌረርሳ በመከወን ገጠመኞቻቸውን የመግለፅ ከፍተኛ ብቃትና ልምድ ስላላቸው ነው።

እነዚህ አምስቱ ከያንያን የከወኑት ጌረርሳ በሚከወንበት ተፈጥሮአዊ መቸት የተሰበሰበ ሲሆን ጥናቱ መረጃ ለመሰብሰብ ሥራ ላይ የዋለው የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ምልከታና ቃለመጠይቅ ናቸው። መረጃው የተሰበሰበው መቅረፀ-ድምፅ፣ የፎቶ ካሜራ በመጠቀምና በማስታወሻ በመያዝ ነው። በተሰበሰበው መረጃ ላይ የይዘት ትንተና የተደረገ ሲሆን ግለሰቦቹ የከወኑት ጌረርሳ ከሕይወታቸው ጋር እንደሚገናኝ ደግሞ ከሕይወት ታሪካቸው ጋር በማገናዘብና አኗኗራቸውን በጥልቀት በማጥናት ታይቷል።

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

በማያቋርጠው የሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ስነ-ቃላት የአኗኗር ገፅታን ያንፀባርቃሉ። ባህላዊና ማህበራዊ የሆኑ ጉዳዮችን እያነሱ የተለያዩ የህይወት መልኮችን ያሳያሉ። ቃላዊ የግጥም ዓይነቶች ደግሞ ይህንን ተግባር ከሚያከናውኑት ውስጥ የሚመደቡ ናቸው። እንደሌሎቹ የስነ-ቃል ዘርፎች (genres) ሁሉ የማህበረሰቡን እድገትና ውድቀት፣ ምኞትና ተስፋ ማጣት፣ ጥላቻና ፍቅር በአጠቃላይ የደስታም ሆኑ የሀዘን ስሜቶች ይገለፁባቸዋል። ከዚህም ባለፈ የማህበረሰቡ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፓለቲካዊ ጉዳዮች ይተላለፉባቸዋል። በአጠቃላይ በሰው ልጅ የኑሮ ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙ ውጣ ውረዶች ይገለፁባቸዋል (ዘሪሁን፣ 2000)። በመሆኑም የኔ ጥናት ግለሰቦች የስነ-ቃል ዘውግ የሆነውን ጌረርሳን በመከወን ገጠመኞቻቸውን እንዴት እንደሚገልፁ ማሳየት ነው።

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥናት ለማካሄድ ያነሳሱኝ ምክንያቶች አንዱ የኦሮሞ ማህበረሰብ እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ማህበረሰቦች የሚታወቅበት የራሱ የሆኑ ማህበራዊና ባህላዊ አኗኗር አሉት። ከዚህም ጋር ተያይዞ በማህበራዊ ሕይወት ውስጥ ማህበረሰቡ እርሰበርሱም ሆነ ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋር በሚያደርገው ተራክቦ የሚፈጠሩትን መስተጋብሮች የሚመራበት ልማዳዊ ደንቦችም አሉት። እነዚህን ባህላዊም ሆኑ ማህበራዊ ደንቦችና የማህበረሰቡ የአኗኗር ስልቶች የሚገለፁባቸው በርካታ የፎክሎር ዘውጎችም አሉት።እነዚህ የፎክሎር ዘውጎች እንጉርጉሮ፣ እንቆቅልሽ፣ አፈታሪክ፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ቅኔያት /Ciigoo/፣ ጌረርሳና የመሳሰሉት ናቸው። ከነዚህም የፎክሎር ዘውጎች ውስጥ ከቃል ግጥም ዓይነቶች አንዱ የሆነው ጌረርሳ የማህበረሰቡን እሴት በመግለፅ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። የኦሮሞ ማህበረሰብ በጌረርሳ ጀግንነቱን፣ ታታሪነቱን፣ ውድቀቱን፣ አሸናፊነቱን፣ ሀዘኑን፣ ደስታውን በአጠቃላይ ረጅም የታሪክ ሂደት ውስጥ ያጋጠሙትን (በማህበረሰቡ የተከሰቱ በጎም ሆኑ በጎ ያልሆኑ ክስተቶችን) ሲገልፅበት ኖሯል፣ እየገለፀበትም ይገኛል። በህይወት ዘመኑ ያሳለፋቸውን የሕይወት ውጣ ውረዶችን፣ ሀዘንና ደስታውንና ተጠቦ ያመጣቸውን የሕይወት ፍልስፍና ያንፀባርቅበታል። ከዚህም ባለፈ የማህበረሰቡን ጀግኖች በጌረርሳ በማወደስ ተከታዩን ትውልድ ይቀርፅበታል። እንዲሁም በሕይወት ዘመኑ ያካበታቸውን የህይወት ተሞክሮ ያኖርበታል። በተጨማሪም ማህበረሰቡ አስተሳሰቡንና አመለካከቱን፣ ድጋፍና ተቃውሞውን ይተነፍስበትና እፎይታን ያገኝበታል። ጌረርሳ የማህበረሰቡን ስነ-ልቡናም ጭምር የማሳየት አቅም አለው።

በማህበረሰቡ ደግሞ ግለሰቦች ጌረርሳን በየአጋጣሚው እየከወኑ እነዚህን የህይወት ገጠመኞች በመግለፅ የማይናቅ ሚና ይጫወታሉ። ታሪካቸውንና በሕይወት ዘመናቸው ያጋጠሟቸውን ሁሉ ይገልፁበታል። ያልተመቻቸውን የማህበረ-ባህሉን ሥሪት ይኮንኑበታል። እንዲለወጥም ማህበረሰቡን ለማንቃት እንደፕሮፓጋንዳም ይጠቀሙበታል። ይህ ሆኖ እያለ በጌረርሳ ላይ በበቂ ሁኔታ ጥናት አልተደረገም። ከዚህ በፊት በጌረርሳ ላይ ጥቂት ተማሪዎች ለመጀመሪያና ለሦስተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፅሑፋቸውን ቢያቀርቡም በአጠቃለይ ጉዳዮች ላይና የጌረርሳውን ግጥሞች ብቻ በመሰብሰብ ይዘቱን መተንተን እንጂ ጌረርሳ በሚከወንበት ተፈጥሮአዊ አውድ

ተገኝተው ከላይ የተገለፁትን ማህበራዊ እሴት አጥንተው በማሳየት ላይ ያተኮሩ አልነበሩም። በተለይ ያገኘሁዋቸው ስድስት በጌረርሳ ላይ የተሰሩ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች አራቱ ትላልቅ አራዊትን የገደሉ የገዳዮች ሙገሳ ግጥሞችን ይዘት መተንተን ላይ ብቻ ያተኮሩ ናቸው። ከተቀሩት ሁለቱ አንዱ በንጉስ ኩምሳ ሞሮዳ ዘመን ጌረርሳ ላይ የተሠራ ሲሆን ሁለተኛው ከብቶችን ለቦሊ የሚያሰማራ ሰው የሚከውነውን የቦልቱ ጌረርሳ ግጥሞች ጥናት ላይ ያተኮረ ነው። ስድስቱም ጥናቶች ግለሰቦችን ትኩረት አድረገው የግለሰቦችን ሕይወት በማሳየት አንፃር አልተሰሩም። የአዲሱ ቶለሳ የፒ.ኤች.ዲ (Ph.D) ጥናትም የኦሮሞ ማህበረሰብ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ሁኔትዎች ቢያሳይም ግለሰቦች ላይ ትኩረት ያደረገ አይደለም። በዚህ ምክንያት የግለሰቦችን ሕይወት ለማሳየት ግለሰቦች ጌረርሳን በመከወን ገጠመኞቻቸውን እንዴት እንደገለፁ ለማጥናት ፍላጎት አበረብኝ። ሁለተኛው ምክንያት በየአጋጣሚው ግለሰቦች ጌረርሳንና የተለያዩ የስነ-ቃል ዘውጎችን (genres) በመከወን ማህበረሰቡን ለሥራና ለሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ሲያነሳሱ ይታያሉ። ይህንን የግለሰቦች ሚና በተለያዩ አጋጣሚዎች በማየቴ ጉዳዩን በጥልቀት ለማጥናት መነቃቃቱን ፈጥሮልኛል።

ስለሆነም ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው የጌረርሳ ከያንያን ጌረርሳን ከውነው ገጠመኞቻቸውን (ህይወታቸውን) የሚገልፁበትን ሁኔታዎች አጥንቶ ማሳየት ላይ ነው። ይህም የተደረገው ጌረርሳን በየአጋጣሚው በመከወን ገጠመኞቻቸውን የመግለፅ ችሎታ ያላቸውን አምስት ግለሰቦች በመምረጥ በማጥና ነው። ግለሰቦቹ በየአጋጣሚው የሚከውኑት ጌረርሳ ምን ያህል ከህይወታቸው ጋር እንደሚስምር ጥናቱ ያሳያል። በመሆኑም ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል።

- ግለሰቦቹ ጌረርሳውን እንዲከውኑ ያነሱዋቸው አጋጣሚዎች (አውዶች) ምን ይመስላሉ?
- ግለሰቦቹ ጌረርሳውን በመከወን ገጠመኞቻቸውን እንዴት ገለፁ?
- ግለሰቦቹ የከወኑት ጌረርሳ ምን ያህል ህይወታቸው ይገልፃል? የሚሉት ናቸው፡፡

## 1.2. የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት የሚከተሉት አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች አሉት

### 1.2.1. የጥናቱ ዋና ዓላማ

ጥናቱ ያተኮረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምዕራብ ሸዋ ዞን አደአ በርጋ ወረዳ የሚኖሩ እነዚህ የተመረጡት አምስት ግለሰቦች በተለያዩ አጋጣሚዎች (አውድ) ጌረርሳን በመከወን ገጠመኞቻቸውን እንዴት እንደሚገልፁ አጥንቶ ማሳየት ነው።

ስለዚህ የጥናቱ ዋና ዓላማ

- እነዚህን አምስት ግለሰቦች በመከታተል ጌረርሳ በመከወን ገጠመኞቻቸውን በአጠቃላይ ግላዊም ሆነ ማህበራዊ እሴቶቻቸውን የገለፁበትን ሁኔታዎች ማሳየት ነው።

### 1.2.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

ጥናቱ የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች አካቷል።

- ግለሰቦቹ ጌረርሳውን እንዲከውኑ ያነሳሳቸውን /ምክንያት የሆናቸውን/ አጋጣሚዎች መለየት፣
- ግለሰቦቹ ገጠመኞቻቸውን ጌረርሳ በመከወን እንዴት እንደገለፁ ማሳየት፣
- ከዋኞች ከሕይወት ገጠመኞቻቸው ጋር በማያያዝ በከወኗቸው ጌረርሳዎች ውስጥ ያነሷቸውን አበይት ጉዳዮች መለየት፣
- ግለሰቦቹ የከወኑት ጌረርሳ ምን ያህል ከህይወታቸው ጋር እንደሚሰምር መግለፅ ናቸው፡፡

## 1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት /ጠቀሜታ/

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታ ይኖሩታል የሚል እምነት አለኝ።

- በጌረርሳ ላይ ከዚህ በፊት ሲደረጉ የነበሩ ጥናቶች የጌረርሳውን ግጥሞች /text/ ከነክዋኔያቸው ወይንም ያለክዋኔ በመሰብሰብና አደራጅቶ በመተንተን የተደረጉ ቢሆኑም እስካሁን ድረስ ለግለሰቦች ትኩረት በመስጠት

ገጠመኞቻቸውን በጌረርሳ እንዴት እንደሚገልፁ ግለሰቦቹን በመከታተል ጥናት በማድረግ ያሳየ አጥኚ የለም። በመሆኑም ይህ ጥናት በግለሰቦች ላይ ትኩረት በማድረግ እንደተጠና ሁሉ በተመሳሳይ ርዕስ ወደፊት ሰፊ ጥናት እንዲደረግ አጥኚዎችን ያነቃቃል ተብሎ ይታመናል።

- በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ግለሰቦች የማህበረሰቡን እሴት በማስጠበቅና ለቀጣይ ትውልድ በማስተላለፍ ረገድ ያላቸው ሚና የጎላ ነው። በተጨማሪም ግለሰቦች ዓላማቸውን ለማስፈፀም በማህበረሰቡ ላይ የሚያሳድሩት ተፅእኖም ቀላል አይደለም። ጥናቱ ለማህበረሰቡ እነዚህ ግለሰቦች ያላቸውን ማህበራዊ ሚና ያሳያል። ስለዚህ ጥናቱ ወደ ፊት በዚህ ርዕስ ዙሪያ ጥናት ለሚያደርጉ ለሌሎች አጥኚዎች የመረጃ ምንጭም ሆኖ ያገለግላል።
- የጥናቱ አቅራቢም በዚህ ርዕስ ጉዳይ ላይ ጥናቱን በማካሄድ ሰፊ የመስክ ልምምድ በማግኘት ጥናት የማድረግ ዕውቀቱን አዳብሯል።

## 1.4. የጥናቱ አደረጃጀት

ጥናቱ አምስት ምዕራፎች አሉት፡፡ የመጀመሪያ ምዕራፍ መግቢያ ሲሆን በዚህ ክፍል ውስጥ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የአጠናን ዘዴ፣ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች፣ ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸውና የአደአ በርጋ አካባቢያዊ ዳራ በቅደም ተከተል ተካተዋል፡፡ በምዕራፍ ሁለት የክለሳ ድርሳናት የቀረቡ ሲሆን በዚህ ርዕስ ሥር የንድፈ ሀሳብ ቅኝት ስለፎክሎር ጥናት የቀረቡ ንድፈ ሀሳባዊ ጉዳዮች ማለትም የክዋኔና የአውዳዊ ጥናት ንድፈ ሀሳቦችና የጌረርሳ ምንነት ቀርበዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ  ውስጥ የተካተተው የተዛማጅ ጥናት ቅኝትም ተካቷል፡፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር በጌረርሳ ላይ የተሰሩ የመጀመሪያና የሦስተኛ ዲግሪ ጥናቶች ተቃኝተው ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ተመሳስሎና ልዩነት ተመላክተዋል፡፡ በምዕራፍ ሦስት ውስጥ ጥናቱ ያተኮረባቸው የአምስቱ ግለሰቦች የህይወት ታሪክ በአጭሩ የተካተተ ሲሆን የህይወት ታሪካቸው ሲጻፍ በቀጥታ ግለሰበቦቹ የተናገሯቸው ንግግሮችም ተካቷል፡፡ ለግለሰቦቹ የቃለ መጠይቁ ጥያቄ የቀረበላቸው በኦሮሚኛ ሲሆን እነሱም የጥናቱን መረጃ የሰጡት በኦሮሚኛ ነው፡፡ መረጃው በዚህ ጥናት ውስጥ የተካተተው ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ነው፡፡  በምዕራፍ አራት ውስጥ ደግሞ አምስቱ ግለሰቦች የከወኑት ጌረርሳዎች ከነትንታኔያቸው የት፣ መች፣ በምን አጋጣሚ እንደተከወኑ የቀረበ ሲሆን ምዕራፍ አምስት ውስጥ የቀረበው

ግለሰቦቹ የከወኑት ጌረርሳ የአከዋወን ሂደቱ ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ሥር የጌረርሳ አጀማመርና የታዳሚያን ሚና ተካቷል፡፡ የጥናቱ ማጠቃለያ በመጨረሻ ላይ ተለይቶ ቀርቧል።

በጥናቱ ውስጥ የጌረርሳ ግጥሞች የኦሮምኛና የአማርኛ ትርጉሙ ጎን ለጎን እንዲቀመጡ ተደርገዋል፡፡ የአማርኛ ትርጉሙን በግጥም መልክ ለማስቀመጥ የተሞከረ ሲሆን አልፎ አልፎ ደግሞ በግጥም መልክ ቢቀመጡም ቤት እንዲመቱ ተደርጐ ለማስቀመጥ አስቸጋሪ በመሆኑና ትርጉሙንም ስለሚያዛባ ተተርጉሞ ብቻ እንዲቀመጡ

ተደርገዋል፡፡ በመጨረሻም አምስቱ ከያንያን የከወኑት ትንታኔ ውስጥ ያልገቡ የጌረርሳ ግጥሞች በኦሮምኛና የአማርኛ ትርጉሙ አባሪ ተደርገው ቀርበዋል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ እንደ መረጃ ምንጭ የተጠቀኩት አምስት ግለሰቦችን ነው። ከስነ-ቃል ዘውግም /genres/ ጌረርሳ ላይ ብቻ ያነጣጠረ ነው። ስለዚህ ጥናቱ አምስቱ ግለሰቦች በተለያዩ አጋጣሚዎች አነሳሽነት ጌረርሳ ከውነው ገጠመኞቻቸውን እንዴት እንደገለፁ ከግለሰቦቹ ጋር በመዋል፣ በማደርና በመከታተል በጥልቀት አጥንቶ ማሳየት ላይ የተወሰነ ነው። ጥናቱ ያተኮረባቸው ግለሰቦች /ከያንያን/ አቶ አባተ ኤጀርሳ፣ አቶ ብርሃኑ አዱኛ፣ አቶ ቸሩ ድንቁ፣ አቶ ድሪባ ለታና አቶ መኮንን ደሜ ናቸው፡፡

አራቱ ግለሰቦች (አቶ አባተ፣ ብርሃኑ፣ ቸሩና መኮንን) በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምዕራብ ሸዋ ዞን አደኣ በርጋ ወረዳ ደኩ ቀርሣ ቀበሌ ገ/ማህበር ውስጥ የሚኖሩ ሲሆኑ አቶ ድሪባ ለታ ግን በዚሁ ዞንና ወረዳ ውስጥ በምትገኘው በሬጂ ከተማ ይኖራሉ።

ግለሰቦቹ ጌረርሳ እንዲከውኑ ያነሳሳቸው ግላሰባዊ ወይም ማህበራዊ ጉዳዮች የተለያዩ ናቸው። ከግለሰብ ግለሰብም ይለያያሉ። ስለዚህ የጥናቱ ትኩረት እነዚህ ግለሰቦች በየአጋጣሚዎቹ  የሚከውኑትን ጌረርሳ በመቅረፅ ወይም በመቅዳት መተንተን ነው። ጥናቱ የጌረርሳው የአከዋወን ሂደቱና የይዘት ትንተና ያካተተ ነው።

## 1.6. የአጠናን ዘዴ

ስነ-ቃል በተለያዩ አውዶች ሊሰበሰብ ይችላል። በባህል ወይም በተለምዶ በሚከወንበት ጊዜና ቦታ በመገኘት በተፈጥሮአዊ መቼት መሰብሰብ አንደኛውና ዋነኛ ዘዴ ነው (ፈ.ቃደ፣ 1991)። ስለዚህ ለዚህ ጥናት የተመረጡ አምስቱ ግለሰቦች በተለያዩ አጋጣሚዎች ጌረርሳውን ከውነው ገጠመኞቻቸውን በሚገልፁበት አውድ /natural setting/ በመገኘት ጥናት ተደርጓል። ይህ ጥናት የአይነት ጥናት /Qualitative Research ሲሆን የአይነት ጥናት የተተኮረባቸውን ጉዳዮች ወይም የጥናቱን ናሙና በጥልቀት በመግለፅና በመተንተን የሚያሳይ የጥናት ዓይነት ነው ። በዚህ የጥናት ዓይነት የሚመረጠው ናሙና የተወሰነ ወይም ጥቂት በመሆኑ ስለ ጉዳዩ ወይም ናሙናው በቂ መረጃ በማቅረብ በስፋትና በጥልቀት ለማሳየት ያስችላል። ጥናቱ አሃዛዊ ባለመሆኑ ስለሚጠናው ጉዳይ ባህሪም በወኑ ለመግለፅ አቅም ይፈጥራል /Venderstoep and Johnston, 2009; Creswell, 2007) ። የአይነት ጥናት የጥናቱን ተሳታፊዎች ስሜትና አመለካከት /feeling and perception/ በበቂ ሁኔታ ለማጥናትም ይረዳል (Lodico etal., 2010)።

ጥናቱን ከግብ ለማድረስ አገልግሎት ላይ የዋለው የጥናቱ ዘዴ ደግሞ ገላጭ ውሱን ጥናት /Descriptive Case Study/ ነው። ይህ ዘዴ የተወሰነ ጉዳይ፣ አንድ ግለሰብ ወይም የተወሰኑ ግለሰቦችን በመከታተል በጥልቀት ለማጥናት አገልግሎት ላይ የሚውል ነው። በጥናቱ ጊዜ የታዩትን ጉዳዮች ሁኔታና ባህሪ በጥልቀት ለመግለፅና ለመተንተን ያስችላል (አለም፣ 1997፣ Creswell, 2007 , Lodico etal., 2010)። ገላጭ ውሱን አውድ ተኮር ኢትኖግራፊያዊ የአጠናን ዘዴ በመጠቀሜ የጌረርሳ ከያንያን ያዜሟቸውን ጌረርሳ ከተከወነበት ማህበረ-ባህላዊ መቼት አንፃር ለመተንተንና ለመግለፅ አግዞኛል። በመሆኑም ከያንያን (ግለሰቦች) ባዜሟቸው ጌረርሳ ውስጥ የመጡትን መልዕክቶችና ለኪናዊ ቅርፆች መፈጠር መንስኤ የሆኑ ማህበረ-ባህላዊ አውዶችን ለመመልከትና ለመመርመር እንደአቅጣጫነት ሥራ ላይ ውሏል። ግለሰቦቹ የከወኑት ጌረርሳ ከሕይወታቸው ጋር ያለውን ግንኙነት በጥልቀት ለማጥናትም አስችሏል። በመሆኑም በአጋጣሚዎች አነሳሽነት በግለሰቦቹ (ከያንያኑ)

የተከወኑትን ጌረርሳዎች ከግለሰቦቹ ጋር በመቆየት ጥናት በማድረግ ተሰብስቦ በአውዱ የይዘት ትንተናንም /content analysis/ ተደርጓል።

## 1.7. የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች

MacDonald (1972) "Systematic field work usually begins at the desk, in the library and the archive" እንዳለው ይህ ጥናት በመስክ ምርምር ላይ የተመሠረተ በመሆኑ በመጀመሪያ ደረጃ ከቤተ መጻሕፍት ስለፎክሎር ጥናትና የጥናቱ ባህሪያት ላይ በመስኩ ሰፊ ምርምር ያደረጉ ምሁራን የሰጡትን ንድፈ ሃሳቦች ከተለያዩ መጻሕፍት፣ መጻሕፍት፣ መዛግብትና መጣጥፎች በማንበብ መረጃ ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል።

በተጨማሪም ጥናቱን በመረጃ ለማጠናከር ቀደም ሲል በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ የተሠሩ ጥናቶች ለመዳሰስ ተሞክሯል። የተዳሰሱት ጥናቶች አንድ የፒ.ኤች.ዲ ጥናት /Ph.D dissertation/ና ስድስት የመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ ጥናቶች ጠቅለል ባለመልኩ ታይተው ከዚህ ጥናት ርዕስ-ጉዳይ ጋር ያላቸው ተመሳስሎና ልዩነት ተመላክቷል። በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ሁሉም ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ብፈልግም በጌረርሳ ላይ የተሠሩ የማስተርስ ድግሪ (M.A) ማሟያ ጥናቶችን ለማግኘት አልቻልኩም።

ከቤተ መጻሕፍት ምርምር በኋላ ደግሞ በጥናቱ ላይ ወደ ተጠቀሰው አካባቢና ግለሰቦች በመሄድ ትላልቅ ከሆኑ የመስክ መረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች መካከል ምልከታ/observation/፣ ቃለመጠይቅ/interview/ በመጠቀምና በማስታወሻ በመያዝ ግለሰቦቹ ጌረርሳውን በሚከውኑበት ተፈጥሮአዊ አውድ ግለሰቦቹ የከውኑት ጌረርሳዎች ከነመከሰቻ ምክንያታቸውና ክዋኔአቸው ተሰብስበዋል። ግለሰቦቹ የከወኑት ጌረርሳ ምን ያህል ከህይወታቸው ጋር የተቆራኘ እንደሆነም በጥልቀት ታይተዋል።

በምልከታ አምስቱ ግለሰቦች ጌረርሳውን ሲከውኑ የሚያደርጉትን ነገሮች፣ በቦታው የተከሰቱ ክስተቶችና ሁኔታዎች ከነ መከሰቻ አውዳቸው በጥንቃቄ በመከታተል የተመዘገቡ ወይንም የተቀረፁ ሲሆን ግልፅ ያልሆኑ ነገሮች/ጉዳዮችን ደግሞ በቃለ መጠይቅ ግለሰቦቹን በመጠየቅ መረጃዎቹ ተሰብስበዋል።

አምስቱ ግለሰቦች የከወኑት ጌረርሳ የተሰበሰበው በ16/06/2004፣ 19/06/2004፣ 21/06/2004፣ 12/07/2004ና 21/07/2004 ዓ.ም ነው። ነገር ግን የጥናቱን አላማ ከማሳወቅ ጀምሮ የህይወት ታሪካቸውንና ግለሰቦቹ የከወኑትን ጌረርሳ ከነአውዱ ለመሰብሰብና የከወኑት ጌረርሳ ምን ያህል ከከዋኞች ህይወት ጋር እንደሚሰምር ለማየት ከመረጃ ሰጪዎች ጋር የቆየሁት ከ01/06/2004-30/07/2004 ዓ.ም ለ60 ቀናት ነው። ከግለሰቦቹ የተገኘውን መረጃ ስተነትን ጥያቄ ያነሱብኝን ጉዳዮች ለማጣራትና የጎደሉኝን መረጃዎች ለማሟላት ደግሞ ከ 01/08/2004-15/08/2004 ዓ.ም ድረስ ለ15 ቀናት ከግለሰቦቹ ጋር እየተገናኘሁ በማሟላት ትንተና አድርጌአለሁ፡፡ በዚህ ጊዚያት ውስጥ መረጃ ሰጪዎች የከወኑት ጌረርሳ ከህይወታቸው ጋር እንደሚሰምር በጥልቀት ታይቷል።

## 1.8. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች

### 1.8.1. ያጋጠሙ ችግሮች

የጥናቱ መረጃ በሚሰበሰብበት ጊዜ ያጋጠሙ ችግሮች፣

- መረጃ ሰጪዎች የጥናቱን ዓላማ ቶሎ አለመረዳት፣
- አራቱ መረጃ ሰጪዎች በደኩ ቀርሳ ቀበሌ ቆላማ ስፍራ ስለሚኖሩና በአካባቢው ያለው አየር በጣም ሞቃታማ በመሆኑ እንደተፈለገው በመንቀሳቀስ መረጃን ለመሰብሰብ አስቸጋሪ መሆን፣
- መረጃ ሰጪዎች ከ01/06/2004 ዓ.ም እስከ 30/07/2004 ዓ.ም የሚቆይ በመንግስት የተነደፈ የልማት ሥራ ላይ ስለነበሩና በሳምንት አራት ቀን /እሁድ፣ ሰኞ፣ ማክሰኞና ረቡዕ/ ከ3፡00 እስከ 6፡00 /ከሶስት ሰዓት እስከ ስድስት ሰዓት/ ስለሚሠሩ እንደአስፈላጊነቱ አግኝቶ መረጃ ለመሰብሰብ አለመመቸት፣
- አብዛኞቹ መረጃ ሰጪዎች ጌረርሳውን የሚከውኑት በማንኛውም ቀን ሳይሆን ማህበረሰቡን አንድ ማህበራዊ ጉዳይ በሚያገናኛቸው ጊዜያት (በዓመት በዓላት፣ በሰርግ፣ በደቦና ማህበረሰቡ በሚሰበሰቡበት ሌሎች አጋጣሚዎች) ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሁል ጊዜ የማይከሰት በመሆኑ እነዚህን አጋጣሚዎች መጠበቅ የግድ አስፈልጓል፤ በመሆኑም እነዚህ ችግሮች በጊዜ መረጃው እንዳይሰበሰብ እንቅፋት ሆኗል፡፡

### 1.8.2. የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች

ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመፍታት የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች፣

- የጥናቱን ዓላማ ጊዜ ወስዶ መረጃ ሰጪዎችን በማስረዳትና መረጃውን በመሰብሰብ፣
- በአካባቢው ከሰዓት በኋላ ጀምሮ አየሩ ስለሚቀዘቀዝና መረጃ ሰጪዎችም ከልማት ሥራው ስለሚያርፉ ይህን ጊዜ በመጠበቅ መረጀ በመሰብሰብ፣
- ከሰዓት በኋላና ሌሎች የሳምንቱ ሦስት ቀናት /ሐሙስ፣ እርብና ቅዳሜ/ ሙሉ ቀን በመጠቀም መረጃዎችን በመሰብሰብ፣
- መረጃ ሰጪዎች ጌረርሳውን የሚከውኑበትን አጋጣሚዎች በትእግስት ጠብቆ መረጃዎችን በመሰብሰብ ችግሮቹ ተቃለዋል፡፡

## 1.9. የአዳአ በርጋ አካባቢያዊ ዳራ

### 1.9.1. የወረዳው ስም ስያሜ

አደአ በርጋ ወረዳ "አደአ በርጋ" የሚለውን ስያሜ ያገኘው ወረዳው ውስጥ ከሚኖሩት "አደአ" ከተባለ የጎሣ ስምና በወረዳው ውስጥ ከሚገኘው "በርጋ" ከተባለ ወንዝ ስም በማጣመር ከ1910-1920 ዓ.ም በሚንሊክ ዘመነ መንግሥት መሆኑን ከወረዳው የቱሪዝምና ባህል ጽ/ቤት የተገኘ ርዕሱ "Seenaa Ada'aa Bargaa/ የአደአ በርጋ ወረዳ ታሪክ" የሚል በ2004 ዓ.ም ተባዝቶ የተጠረዘ ያልታተመ ሰነድ ያሳያል። ይህ ጎሳ የቱለማ ጎሳ የዘር ሀረግ ሥር ከሚገኘው ከስድስቱ የገላን ልጆች (Ja'an hortee Galaan) አንዱ ነው። ስድስቱ የገላን ጎሳ ልጆች ሊበን፣ ጅዳ፣ አቡ፣ አደአ፣ ወረ ጃርሶና ጋዱላ ናቸው (Alamaayyoofaa, 1998)። ከተጠቀሰው ዘመን በፊት ወረዳው እንደ ወረዳ የቆመ እንዳልነበረ ሰነዱ ያመለክታል።

### 1.9.2. የወረዳው አቀማመጥ

አደአ በርጋ ወረዳ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በምዕራብ ሸዋ መስተዳደር ዞን ሥር ከሚገኙ ወረዳዎች አንዱ ሲሆን ከአዲስ አበባ 64 ኪሎ ሜትር፣ ከዞኑ ዋና ከተማ ከአምቦ ደግሞ 117 ኪሎ ሜትር ርቆ ይገኛል። የወረዳው

ዋና ከተማ እንጭኒ ሲሆን ወረዳውን በምስራቅ የሙሎ ወረዳ፣ በሰሜን የደገም፣ የሱሉልታ፣ የያያ ጉላሌና የኩዩ ወረዳዎች፣ በምዕራብ የሜታ ሮቢ ወረዳና በደቡብ የወልመራና የኤጀሬ ወረዳዎች ያዋስኑታል። ከላይ የተጠቀሰው ከወረዳው የቱሪዝምና ባህል ጽ/ቤት የተገኘ ሰነድ እንደሚያመለክተው የወረዳ ስፋት 79,835 ሄክታር ሲሆን 36 የቀበሌ መስተዳድሮች አሉት። ከ36ቱ ቀበሌዎች መካከል 34ቱ የገጠር ቀበሌ ገበሬ ማህበራት ሲሆኑ ሁለቱ ደግሞ የከተማ መስተዳድሮች ናቸው። ወረዳው $09^0$-$16^0$N እና 38-$23^0$E መካከል ይገኛል። የመሬቱ አቀማመጥ 30% ተራራማ፣ 45% ውጣ ውረድና 25% ሜዳማ ነው።

### 1.9.3. የወረዳው አየር ንብረት

ይህ ከላይ የተመለከተው ሰነድ እንደሚያመለክተው የወረዳው አየር ንብረት 29% ደጋ፣ 34% ወይናደጋ፣ 37% ቆላ ሲሆን የሙቀት መጠን በአቬሬጅ ከ10-$25^0$C ነው። በዓመት የሚያገኘው የዝናብ መጠን በአማካይ ከ918-1368 ሚሊ ሊትር ነው። ከባህር ጠለል በላይ 3169 ሜትር ላይ ይገኛል። በወረዳው የሚገኘው የአፈር ዓይነት ጥቁር አፈር 44%, ቀይ አፈር 39% ና አሸዋማ አፈር 17% ነው። ከነዚህም መካከል 6% በደን የተሸፈነ፣ 27% የግጦሽ መሬት፣ 0.05% በውሃ የተሸፈነ፣ 1.45% በከተሞች የተያዘና 13% በሌሎች ነገሮች ማለትም በፋብሪካዎች፣ በገደላገደልና በመሳሰሉት ነገሮች የተሸፈ ሲሆን የተቀረው 52.5% ለእርሻ የዋለ መሆኑን ሰነዱ ያመለክታል።

### 1.9.4. የወረዳው ህዝብ ብዛት

በ2010 ዓ.ም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፑብሊክ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ "The 2007 population and Housing Census of Ethiopia Result for Oromiya Region: Statistical Report on Population Size and characterstics" በሚል ርዕስ ባወጣው መረጃ መሠረት የወረዳው ሕዝብ ብዛት 60,366 ወንዶች፣ 60,288 ሴቶች በአጠቃላይ 120,654 ናቸው፡፡ ከነዚህ ውስጥ በከተማ የሚኖሩ ደግሞ 7,690 ወንዶች፣ 8,250 ሴቶች በአጠቃላይ 15,940 ሲሆኑ በገጠር ቀበሌዎች የሚኖሩት ደግሞ 52,676 ወንዶች፣ 52,038 ሴቶች በአጠቃላይ 104,714 ናቸው። በወረዳው

ውስጥ ከሚኖሩት ህዝቦች መካከል 97% ኦሮሞ፣ 2.7% አማራ፣ 0.1% ጉራጌና 0.25 ሌሎች ብሔረሰቦች ናቸው።

ስታቲስቲክስ ኤጀንሲው ባወጣው መረጃ መሰረት ካላይ ከተጠቀሱት የወረዳው ሕዝብ ውስጥ 53,522 ወንዶች፣ 53,307 ሴቶች በአጠቃላይ 106,829 የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ሲሆኑ 3,162 ወንዶች፣ 3,222 ሴቶች አጠቃላይ 6,384 ሰዎች የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ናቸው። የካቶሊክ እምነት ተከታዮች ደግሞ 8 ወንዶች፣ 10 ሴቶች በአጠቃላይ 18 ሰዎች ናቸው። በተጨማሪም 105 ወንዶችና፣ 89 ሴቶች  በድምር 194 የሙሲሊም እምነት ተከታዮች ናቸው። የባህላዊ እምነት ተከታዮች ደግሞ 3,367 ወንዶች፣ 3,514 ሴቶች አጠቃላይ 6,881 ናቸው። የተቀሩት 202 ወንዶችና 146 ሴቶች በአጠቃላይ 348 የሌሎች ሃይማኖቶች ተከታዮች ናቸው (C.S.A, 2010)።

### 1.9.5. የወረዳው ሕዝብ መተዳደርያ

የወረዳው ህዝብ በእርሻና በከብት እርባታ የሚተዳደር ሲሆን እ.አ.አ በ2003 "Ethiopia Agricultural Sampiing Enumeration, 2001/02 (1994 E.C) Result for Oromia Region: Statstical Report on Area and Production of Temporary Crops/ በኢትዮጵያ የግብርና ናሙና ቆጠራ የቦታና ቋሚ ያልሆኑ ሰብሎች አሃዛዊ ርፖርት" በሚል ርዕስ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፑብሊክ የማዕከላዊ የግብረና ናሙና ቆጠራ ኮሚሽን ባወጣው መረጃ መሠረት በወረዳው ከሚመረቱት እህሎች መካከል ማሽላ፣ ዘንጋዳ፣ ጤፍ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ ባቄላ፣ ዓያ፣ ሽንብራ፣ ተልባ፣ ኑግ፣ አተርና ምስር ዋና ዋናዎች ናቸው። ከሚመረቱት አትክልትና ፍራፍሬዎች መካከል ደግሞ ሙዝ፣ ብርቱካን፣ ሎሚ፣ ቡና፣ ቆስጣ፣ ጥቅል ጎመን፣ ቃሪያ፣ የተለያዩ የሽንኩርት ዓይነቶችና ካሮት የሚጠቀሱ ናቸው።

"Statstical Report on Livestock and Livestock Products/ የቤት እንስሳትና የቤት እንሰሳት እርባታ አሃዛዊ ርፖርት" በሚል ርዕስ እ.አ.አ በ2003 ከላይ የተጠቀሰው አካል ባወጣው መረጃ መሠረት በወረዳው ከሚረቡት የቤት እንስሳት መካከል የቀንድ ከብቶች፣ ፍየል፣ በግ፣ በሬ፣ ላም፣ የጋማ ከብቶች ደግሞ ፈረስ ፣ በቅሎ፣ አህያና ሌሎች የቤት እንስሳት ናቸው።

### 1.9.6. በወረዳው ውስጥ የሚገኙ የቱርዝም መስዕቦች

በወረዳው ውስጥ የተለያዩ የቱሪዝም መስዕቦች አሉ። እነሱም አንደኛው በኢትዮጵያ፣ በዝንባቡዌና በደቡብ አፍሪካ ብቻ የምትገኝ የወፍ ዝርያ ሲትሆን በአካባቢው አጠራር የበርጋ ወፍ/ simbira Bargaa/ ትባላለች። ይቺ ወፍ በበርጋ ወንዝ በሚገኙ ሳሮች ውስጥ ከሰኔ እስከ መስከረም ቆይታ የምታደርግ ስትሆን እንቁላል ጥላ ፈልፍላ ከመስከረም በኋላ ወደ ዝንባቡዌና ደቡብ አፍሪካ የምትመለስ ነች። ይቺህ ወፍ በኢትዮጵያ ውስጥ በዚህ ወረዳ ብቻ እንደምትገኝ የወረዳው ሰነድ ያመለክታል። የወፏ ትክክለኛ ስያሜ የምትታወቅበት “white-winged fluftail /የበርጋ ወፍ” ነው። ወፊቷ ወደዚህ አካባቢ ስትመጣ ጥብቅ ጥበቃ የሚደረግላት ሲሆን “Norwegian Orinthological society /የኖርዌይ የአዕዋፋት ጥናት ማህበር” እና “Norwegian Agricultural Agency /የኖርዌይ የግብርና ኤጀንሲ” ከ“Ethiopian wild life Hisotry Society /የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ጥናት ማህበር” ጋር በወፊቷ ላይ ጥናት እያካሄዱ እንደሚገኙ ሰነዱ ያሳያል።

ሌላው በዚህ ወረዳ የሚገኝ የቱሪዝም መስዕብ የበሮ ዋሻ (Holqa Baroo) ነው። ይህ ዋሻ ከፍተኛ ስፋት ያለው ሲሆን በጣሊያን ወረራ ጊዜ የአካባቢው ህዝብና አርበኞች በዋሻው ውስጥ ንብረታቸውን በመሸሸግ፣ ራሳቸውም በዋሻው ውስጥ በመደበቅ ከጥቃቱ እንደተረፉና ከዋሻው እየወጡ ወራሪ ሃይል ላይ ጥቃት ያደርሱ እንደነበር ከወረዳው የተገኘ መረጃ ያመለክታል። በንጉሣውያን ዘመነ መንግስት ( በተለይ በኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት) ጊዜ የሥርዓት ለውጥ የፈለጉ የአካባቢ ሰዎች በዋሻው ውስጥ በመሸሸግ ከነበረው መንግስት ጋር ይዋጉ እንደነበርም ሰነዱ ይገልፃል።

ሌሎች በወረዳው ውስጥ የሚገኙ የዓይን ማረፊያዎች መካከል የቀርሣና የወርቄ ወንዞች ፏፏቴዎች ናቸው። በተጨማሪም መስከረም 17፣ ጥቅምት አምስትና 27፣ በጥምቀትና በሌሎች ባህላዊ ክብረ በዓላት የሚካሄዱት የፈረስ ጉግሶችና ሌሎች ባህላዊ ጫወታዎች ሳቢና አዝናኝ ናቸው። እሬቻ ባህላዊ አከባበርም በብረቴ፣ በቀርሣና በበርጋ ወንዞች ላይ ከመስቀል በኋላ ባለው የመጀመሪያ እሁድ የሚካሄድ ሲሆን ከቱሪዝም መስዕቦች መካከል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ነው።

የጉማ ባህላዊ ሥርዓትም /sirna Gumaa/ በወረዳው ውስጥ የቆየ ታሪክ ያለውና ማህበረሰቡ በሰላም፣ በመከባበር አብሮ እንዲኖር ከሚያደርጉት ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች መካከል አንዱ ነው።

### 1.9.7. በወረዳው ውስጥ የሚገኙ ተፈጥሮአዊ፣ ሰው ሰራሽና ባህላዊ ሀብቶች

በወረዳው ውስጥ ሁለት የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ይገኛሉ። አንደኛው በ1976 ዓ.ም የተቋቋመው በኢትዮጵያ ደረጃ በጣም የሚታወቀው ግዙፉ የሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ ሲሆን ሁለተኛው ቤድሮክ የሚባል የቻይና ባለሃብቶች በ2003 ዓ.ም ያቋቋሙት የሲሚንቶ ፋብሪካ ነው።

በወረዳው ውስጥ ሙገር፣ ቀርሣ፣ በርጋ፣ ወርቄና ሌመን የሚባሉ ትላልቅ ወንዞች ይገኛሉ። በወረዳው ውስጥ የሚገኙ የዱር እንስሳት መካከል ጥርኝ፣ ጦጣ፣ ዝንጅሮ፣ ድኩላ፣ ሚዳቋ፣ ሰስና ቀበሮ የሚጠቀሱ ናቸው። 143 ዓይነት አእወፋት እንዳሉ በወረዳው የተገኘው ሰነድ ያመለክታል። ከማዕድናት መካከል ጀሶ፣ እብነበረድ፣ የድንጋይ ከሰል፣ የግንባታ ድንጋዮችና አሸዋዎች ይገኛሉ።

በወረዳው ውስጥ የማህበረሰቡን አብሮነት የሚያጠናክሩ እንደ እድርና የዕዋ ማህበራት አሉ። እነዚህ ተቋማት የራሳቸው የመተዳደሪያ ደንቦችና ባህላዊ ሥርዓት ያላቸው በመሆናቸው ማህበረሰቡ በሰላም አብሮ እንዲኖር ያግዛሉ። ከዚህም ባለፈ በችግር ጊዜ ማህበረሰቡ እንዲረዳዳና ደስታንና ሀዘንን አብሮ እንድካፈል ያደርጋሉ። ለምሳሌ አንድ ግለሰብ በሬ ከሞተበት በእድርና በማህበራት ገንዘብ እያዋጡ ይገዙለታል። ሀዘን ካጋጠመው ያስተዛዝኑታል። ከታመመና መታከሚያ ካጣ ከእድርና ከማህበራት ወጭ አድርገው ያስክሙታል።

ሌላው የማህበረሰቡን አባላት አንድነት የሚያጠናክሩ ደግሞ በደቦና በጅጌ የመስራት ልምዳቸው ነው። ማህበረሰቡ በእርሻ ጊዜያት አብረው ይሰራሉ። ያርሳሉ፣ ያርማሉ፣ ያጭዳሉ። በሠርግ ጊዜያትም በመረዳዳት ይደግሳሉ። በመስተንግዶውም አይለያዩም።

በመሆኑም በዚህ ማህበረሰቡ በሚገናኝበት በደስታ ጊዜያት የተለያዩ የሥራ፣ የሠርግ፣ የአመት በዓላትና የፍቅር ዘፈኖች ይከወናል። በሀዘን ጊዜያት ደግሞ ሙሾ

ይሟሻል። ጌረርሳ በአብዛኛው በደስታ ጊዜያት ይከወናል። ግለሰቦችም በዚህ አጋጣሚ ጌረርሳን በመከወን ገጠመኞቻቸውን ይገልፃሉ።




Source: http://www.ocha-eth.org

ካርታ 1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ካርታ




Source: http://www.ocha-eth.org

*ካርታ 2. የምዕራብ ሸዋ ዞን ካርታ*




Source:OEB & JICA,1998 E.C

ካርታ 3. የአዳአ በርጋ ወረዳ ካርታ

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ ሥር ሁለት ትላልቅ ጉዳዮች ተቃኝተዋል። እነዚህ ጉዳዮች የጽንሰ ሃሳብና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ናቸው። በጽንሰ ሀሳብ ቅኝት ሥር የስነ-ቃል ምንነት፣ የቃል ግጥም ዓይነትና ባህሪያት፣ የጌረርሳ ምንነትና የፎክሎር ጥናት የሚመለከቱ ጽንሰ ሀሳባዊ ጉዳዮች፣ የክዋኔና የአውዳዊ ጥናት ጽንሰ ሀሳቦች የተቃኙበት ሲሆን በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ሥር ደግሞ ከዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ቀደምት ጥናቶች ተቃኝተዋል።

### 2.1. የጽንሰ ሃሳብ ቅኝት

#### 2.1.1.ስነ-ቃል

ስነ-ቃል በቃል ተደርሶ በቃልና በክዋኔ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ የፎክሎር ዘውግ ነው (ፈ.ቃደ፣1991)። ስነ-ቃል የማህበረሰብ ሀብት በመሆኑ የማህበረሰቡን ልማድ፣ ፍልስፍና፣ ሀዘን፣ ደስታ፣ በአጠቃላይ የማህበረሰቡን ስሜትና አስተሳሰብ የሚገልፅ ቅርፅ ነው (Dorson, 1972) ።

ስነ-ቃል በሁለት መንገድ የሚከፈል ወይም የሚቀርብ ነው። እነሱም በዝርው የሚተረኩና በግጥም የሚቀርቡ (የሚዘፈኑ) ናቸው። በዝርው የሚቀርቡ የስነ-ቃል ዓይነቶች ውስጥ ተረታ ተረት፣ ቀልዶች፣ አፈ-ታሪክና የመሳሰሉት በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው። በግጥም የሚቀርቡና የሚዘፈኑ የስነ-ቃል ሀብቶች ደግሞ የሥራ፣ የሠርግ፣ የፍቅር፣ የበዓላት ዘፈኖችና የመሳሰሉት ናችው። እነዚህ ባህላዊ ዘፈኖች የማህበረሰቡን ውስጣዊ ስሜት ለመግለፅ በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚከሰቱ ናቸው (ዘሪሁን፣ 2000)።

##### 2.1.1.1. የቃል ግጥም

ቃል ግጥም የስነ-ቃል ዘርፍ ሆኖ በቃል ተደርሶ በቃልና በክዋኔ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ነው። "ቃል ግጥም ማለት አደራረሱ፣ አከዋወኑ፣ ተስተላልፎው እና አቀራረቡ ብዙውን ጊዜ በቃልና በዜማም የሆነ በዘፈን፣ በሙሾ፣ በእንጉርጉሮና በሌሎች ተመሳሳይ ዜማዊ ቅርፅ ውስጥ የሚገኝ ህዝባዊ ግጥም ነው (ፈ.ቃደ፣1991)።

Finneganም በበኩሏ የቃል ግጥም ብያኔ ስትሰጥ ቃል ግጥም ማለት በቃል የሚፈጠርና የሚከወን ነው ትላለች (1970) ።

ዘሪሁንም የቃል ግጥም ምንነት ሲገልፁ፣

> *በግጥም ከሚቀርቡትና ከሚዜሙት የስነ-ቃል ዓይነቶች አንደኛው ወገን ባህላዊ ዘፈኖችን ያጠቃልላል። ባህላዊ ዘፈኖች በተለያዩ አጋጣሚዎች ላይ የሚዘፈኑ የማህበረሰቡን ልዩ ልዩ መልኮች ሊያሳዩ የሚችሉ አስደሳች የስሜት መግለጫዎች ናቸው። እያንዳንዱ ማህበረሰብ እንደ የባህሉና እንደ የአኗኗር ስልቱ ዘፈኖችና እንጉርጉሮዎች አሉት። በነዚህ ዘፈኖችና እንጉርጉሮዎች የማህበረሰቡ አባላት ደስታቸውንና ብሶታቸውንና ምኞትና ፍላጎታቸውን ይገልፁባቸዋል (2000) ።*

በአጠቃላይ ቃል ግጥም የሚዜምና በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ በማንኛውም ማህበረሰብ የሚገኝና የማህበረሰቡን እሴት፣ ታሪክ፣ ማንነት የሚገልፅ የስነ-ቃል ዘውግ ነው፡፡

### 2.1.1.2. የቃል ግጥም ዓይነቶች

የቃል ግጥም ዓይነቶች ከላይ እንደ ተገለፀው በግጥም የሚቀርቡና የሚዘፈኑ የስነ-ቃል ሀብቶች የሆኑ እንደ የሥራ፣ የሠርግ፣ የፍቅር፣ የበዓላት ዘፈኖች፣ ጌረርሳና የመሳሰሉት ናቸው። እነዚህ የስነ-ቃል ሀብቶች በተለያዩ አጋጣሚዎች በሥራ፣ በሠርግ፣ በዓመት በዓላትና በመሳሰሉት የሚከሰቱና የማህበረሰቡን አስተሳሰብ የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡

#### 2.1.1.2.1. የጌረርሳ ምንነት

ጌረርሳ ከስነ-ቃል ዘውጎች በቃል ግጥም ዓይነት ውስጥ የሚመደብ ነው፡፡ የቃል ግጥም ዓይነቶች ደግሞ የማህበረሰቡን ወግና ልማድ፣ አስተሳሰብና ተሞክሮ ከትውልድ ወደ ትውልድ ያስተላልፋሉ፡፡ በመሆኑም የኦሮሞ ማህበረሰብ በቃል ግጥም የአኗኗር ስርዓቱን፣ ልምዱንና ታሪኩን ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲያስተላልፍበት ኖሯል፤ እያስተላለፈበትም ይገኛል፡፡ ከነዚህ የቃል ግጥሞች አንዱ የሆነው ጌረርሳ የኦሮሞ ማህበረሰብን አስተሳሰብና አመለካከት በመግለፅ ከፍተኛ

ሚና ይጫወታል፡፡ ጌረርሳ የስነ-ቃል ዘውግ ስለሆነ የስነ-ቃልን ሚና ማየቱ ጌረርሳን በወጉ ለመረዳት ያግዛል፡፡ ዘሪሁን አስፋው የስነ-ቃልን ሚና ሲገልፁ፡

> *...ስነ-ቃል በተወሰኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ የሚከወን ቃላዊ ፈጠራ ሲሆን የአንድን ማህበረሰብ ባህል፣ ወግ፣ ልማድ እንዲሁም ታሪክ ማስተላለፍያና ልዩ ልዩ ክስተቶችንና የህይወት መልኮችን መግለጫ ኪነጥበብ ነው፡፡ ይህ ኪነጥበብ ማህበረሰቦች በረጅም ዘመን ታሪካቸው ያጠራቀሙትና የሚያጠራቅሙት ቅርስ ከመሆኑም በላይ ለህልውናቸው ሲሉ በሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ምክንያት የሚከሰት ከአካባቢያቸውና ተፈጥሮ ጋር ካላቸው መስተጋብርና ትግል የሚፈጠር የአያሌ ገጠመኞች ጥርቅምና የገጠመኞቹም ማንጸባረቂያ ነው ይላሉ (ዘሪሁን፣2000)፡፡*

አምሳሉ አክሊሉም የስነ-ቃልን ሚና ስገልፁ "አፋዊ ሥነጽሑፍ እንደ ጽሑፋዊ ሥነጽሑፍ ያንድን ህብረተሰብ አስተሳሰብና ፍልስፍና በጠቅላላ ባህሉን፣ ወጉን የሚያንፀባርቅ ከተጻፈ ሥነጽሑፍ የማያንስ ዋጋ ያለው የባህል ሀብት ነው" ይላሉ (አምሳሉ፣ 1976) ፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው ሁለት ጥቅሶች ለመረዳት እንደሚቻለው ስነ-ቃል በተወሰኑ አጋጣሚች ላይ ማለትም በሠርግ፣ በዓመት በዓላት፣ በደቦና በሌሎች አጋጣሚዎች ተከውኖ የማህበረሰቡን ባህል፣ ወግ፣ ልማድ፣ ታሪክና ሌሎች ማህበራዊና ግላዊ ጉዳዮችን ከትውልድ ትውልድ ያስተላልፋል፡፡

ጌረርሳም የሰነ-ቃል ዓይነት በመሆኑና ምንጩ የማህበረሰቡ ገጠመኝ በመሆኑ ከላይ በቀረበው ጥቅሶች እንደተመለከተው ማህበረሰቡ ባህሉን፣ ወግ ልማዱን፣ ሀዘን ደስታውን፣ ተሞክሮውን በአጠቃላይ በህይወቱ ውስጥ የሚያጋጥሙትን ሁሉ ያንጸባረቅበታል፡፡ ስለዚህ ጌረርሳ የማህበረሰብ ህይወት ማሳያ ኪነጥበብ ነው፡፡

### 2.1.1.3. የቃል ግጥም ባህሪያት

የቃል ግጥም እንደማንኛውም የስነ-ቃል ዘውግ የሚከተሉት ባህሪያት አሉት፡፡ እነሱም፡

### 2.1.1.3.1. ክዋኔ

ክዋኔ ጥበባዊ ድርጊት፣ የንግግር ክሂል፣ የሰውነት እንቅስቃሴና የገፅታ መለዋወጥ የሚታይበት ሆኖ ተደጋግሞ በጊዜና በቦታ የሚከወን የግለሰብና የቡድን ማንነት መገለጫ ነው (Kapchan, 1995; Bauman, 1992)። ክዋኔ ፎክሎር ህይወት ዘርቶ የሚንቀሳቀስበት ወይንም ህያውነትን የሚላበስበት ነው። ለፎክሎር ውበት መፍጠርያው በመሆኑ ከዋኙ አንድን የፎክሎር ቅርፅ ሲከውን ተውኔታዊ በሆነ መልኩ በማቅረብ የተደራሲያኑን ስሜት ቆንጠጥ አድርጎ በመያዝ አጋጣሚውን የሚገልፅበት ነው (Finnegan, 1970)። ክዋኔ በጊዜና በቦታ የሚደረግ ተግባቦታዊ ድርጊት ነው (Finnegan, 1992)።

በውማን (Bauman, 1975) ስለ ክዋኔ ሲገልፅ ክዋኔ ቋንቋን የመጠቀም ክሂል፣ የንግግር ስልት ነው። ከዋኞች የመከወን ኃላፊነት ተቀብለው ለተደራሲያን ግልፅ በመሆን የመከወን ብቃታቸውን በማሳየት ተግባቦት የሚፈጥሩበት ነው በማለት ያስረዳል። ፊኔጋንም (Finnegan) ክዋኔ የስነቃል (ቃላዊ ኪን) ትርጉም መፍጠሪያ፣ ውበት መከሰቻ ነው። የአንድ ቃላዊ ኪን ፍቺ ከቃላት ብቻ ሳይሆን ከከዋኙ ድምፀት፣ የድምፅ ከፍታና ዝቅታ፣ የሰውነት እንቅስቃሴ ጭምር መሆኑን ትገልፃለች። ቀጠል አድርጋም የቃላዊ ኪን መገለጭያው ክዋኔ ነው። ያለክዋኔ የስነቃል ኑረት በራሱ አይታወቅም ትላለች (1992፣ 1977፣ 1970)። አቶ ዘሪሁን አስፋውም "የስነጽሁፍ መሰረታውያን" በሚለው መጽሐፋቸው ስለ ክዋኔ ስገልፁ፣

> *የአንድ ስነቃል አቀንቃኝ ወይም ከዋኝ በተሳታፊዎቹ ፊት ሲቀርብ ባህሉ የሰጠውን የአከዋወን ስልት ሳይለቅ በራሱ የፈጠራ ችሎታ ለስነቃሉ ተገቢ ድባብ ለመፍጠርና የተሳታፊዎቹን ስሜት ለመሳብ ተስማሚ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን ያደርጋል፣ አይኑን ያጉረጠርጣል፣ ፊቱን ያጨማድዳል፣ አፉን ይከፍታል፣ እጆቹን የወናጭፋል፣ ወይ ይዘላል፣ ቁጭ ብድግ ይላል፣ይውረገረጋል ይላሉ (ዘሪሁን፣2000) ።*

ከላይ እንደተገለፀው የክዋኔ ዋነኛ ነገር የሚያርፈው በተግባቦታዊ ነገሮች፣ በግለሰቦች ብቃትና በተሳታፊዎች ሚና ላይ ነው። ክዋኔ በወቅቱ በሚከሰቱ አውዳዊ አጋጣሚዎችና ሁኔታዎች ላይ ይመሠረታል። በዚህ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ክዋኔውን ለመተግበር የሚያግዙ የክዋኔ አካሄዶች፣ ገቢሮች፣ ክስተቶች፣ የአከዋወን

ደንቦችን በማህበረሰቡ ተቀባይነት ያላቸው የአከዋወን ሥርዓቶች ናቸው (Bauman, 1992) ።

ክዋኔ የፎክሎር የጥበብ አላባዊያን ማማከያ /center/ ነው። ክዋኔ ከሌለ በተለይ የፎክሎር ዘርፍ የሆነው ስነ-ቃል ጥበባዊ ተግላጭነት የለውም (Finnegan, 1970)። ክዋኔ ድርጊት በመሆኑ ብዙውን ጊዜ ከተውኔት ጋር የተቆራኘ የሰው ልጅ ተግባራት ሆኖ በባህል ውስጥ የሚከሰት ለፎክሎር ትርጉም/ፍቺ/ መፍጠሪያ መሰረታዊና ቁልፍ ጉዳይ ነው (Bauman, 1975)። ክዋኔ የሚካሄድበት ቦታና ጊዜ፣ ክዋኔው የተዘጋጀበት ምክንያትና ጉዳይ፣ በክዋኔ ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎች (ህፃን፣ አዋቂ፣ ወንድ፣ ሴት) እና የሚኖራቸው ሚና፣ የከዋኞች ጥበባዊ አቀራረብና የታዳሚያን ምላሽ እነዚህ ሁሉ በክዋኔ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ አላቸው።

በሌላ በኩል ደግሞ በውማን (Bauman, 1975) ክዋኔን 'Frame' የሚያደርጉ ቁልፍ የሆኑ ነገሮችን ሲገልፅ፣

> *1. Special Codes: archaic or esoteric language, reserved for and diagnostic of performance, (2) special formulae that signal performance, such as conventional openings and closing, or explicit statements announcing or asserting performance, (3) figurative language, such as metaphor, methonymy, (4) formal stylistic devices such as rhyme, vowel harmony, other forms of parallelism, (5) special prosodic patterns of tempo, stress, pitch, (6) special paralinguistic patterns of voice quality and vocalization፣ (7) appeal to tradition and (8) disclaimer of performance በማለት ያስቀምጣል።*

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩ የክዋኔ መገለጭያ ጉዳዮች የከዋኙንና የተደራሲያንን ተግባቦት የሚፈጥሩ፣ የክዋኔን ኪናዊ ውበት የሚያጎሉ ናቸው። በተጨማሪም እነዚህ ጉዳዮች በፎክሎር የአከዋወንና የተግባቦት ሥርዓት ውስጥ ስለ አንድ ማህበራዊ እውነታና ባህላዊ ሥርዓት ማህበረ-ባህሉ በሚፈቅዱለት አካሄድ በማስጓዝ ትርጉም የሚፈጥሩና በተገቢ ቦታቸውና በበቂ ክህሎት እንዲከወኑ ለማድረግ የሚያስችሉ ናቸው።

የፎክሎር ክዋኔ አጀማመር ከዋኙንና ተሳታፊዎችን ወደ ክዋኔ የማስገቢያ ዘዴ ነው። አንድ የፎክሎር ቅርፅ የመግቢያ ቀመር በከዋኙ፣ በተሳታፊዎችና በታዳሚያን መካከል ስምምነት መኖሩን ማሳያ፣ መላሹ ለቀረበው ክዋኔ ተገቢውን መልስ እንዲሰጥ፣ ታዳሚያን ክዋኔውን በአግባቡ እንዲከታተሉ ማንቂያ፣ በጨወታ ውስጥ ፈቃድ የማግኛ ዘዴ ነው። ይህ ዘዴ /ቀመር/ በከዋኙና ታዳሚያን መካከል ግንኙነት መፍጠሪያ መንገድ ነው።

ሌሎች እንደ ስልተ ምት፣ ድምፀት፣ የገፅ መለዋወጥ፣ የክዋኔው ባህላዊ መሠረትና የቃላዊ ኪን የቋንቋ አጠቃቀም ትርጉምን በመፍጠር ከዋኙንና ተደራሲያንን የበለጠ የሚያግባቡ ናቸው።

ክዋኔ በከዋኙ ብቃት ላይ የሚመሠረት ነው። በሚከሰተው እያንዳንዱ ክስተት ላይ ከዋኙ ሁኔታዎችን እየተመለከተ ሁኔታዎቹ ወይንም አውድና የፎክሎር ጉዳይ /text/ በሚፈቅዱት መሠረት የመለወጥ ኃላፊነት አለበት። ይህንን አስመልክተው ባውማን (1992) እንዲህ ብሏል።

> *The relative dominance of performance, then, will depend on the degree to which the performer assumes responsibility to the audience for a display of communicative skill and effectiveness as against other communicative functions.*

አንድ ከዋኝ በክዋኔ አላፊነቱን ወስዶ ለታዳሚያን ታማኝ በመሆን በአግባቡ ክዋኔውን ማካሄድና ብቃቱን ማሳየት እንዳለበት ይገልፃል። ክዋኔ ለፎክሎር ትርጉምና ውበት ፈጣሪ በመሆኑ ለአንድ ፎክሎር ቅርፅ መከሰት ምክንያት የሆኑ ሁኔታዎችን የመግለጽ ብቃት እንዲኖረው ተደርጎ መከናወን አለበት (Bauman, 1992) ። ይህ ካልሆነ የአንድ የፎክሎር ቅርፅ ክዋኔ ትርጉም ያጣል። ምክንያቱም የፎክሎር ቀዳሚ ህልውናው በሰዎች ተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ የተመሰረተና ሥረ መሠረቱ ማህበረ-ባህላዊ ህይወት ነው (Bauman, 1992) ።

ከዋኙ በትክክለኛው አውድ ውስጥ ትክክለኛውን ስሜት በማምጣት ክዋኔውን መፈፀም ይኖርበታል። በተጨማሪም ክዋኔውን ግርማ ሞገስ አላብሶ ውበት ባለው መልኩ መከወን አለበት። ምክንያቱም ባውማን (Bauman) "The emergent quality of performance resides in the interplay between communicative resources,

individual competence, and the goals of the participants, with in the context of particular situations" (1975) ይላል። ስለዚህ አንድ ከዋኝ አንድ የፎክሎር ቅርፅ ሲከውን ክዋኔው ላይ ትኩረት ሰጥቶ ትርጉሙ ጎልቶ እንዲወጣ በማድረግ መከወን አለበት።

አብዛኞቹ የፎክሎር አጥኚዎች የፎክሎር ክዋኔ ሲጠና ለአውድ ትኩረት መሠጠት እንዳለበት ይመክራሉ (Berger & Negro, 2002, Kopchan, 1995, Hufford, 1995)። አውድ ክዋኔው የሚቀርብበት ሰበበ ነገር፣ ጉዳይ፣ ሁኔታ፣ አነቃቂና አነሳሽ ጉዳይ ነው። በፎክሎር ጥናት ውስጥ መረጃዎቹም የሚሰበሰቡት በአውድ ነው። ምክንያቱም ፎክሎርን በበቀለበት ማህበረ ባህላዊ ቀዬ የማጥናት፣ የመቅረፅ ተግባር ፎክሎርን በጥልቀት እንድንረዳ አጋዥ የሆኑትን ፎክሎርን ህያው ያደረጉትን፣ ቅርፁን የሰጡትንና ትርጉም ያስገኙለትን ግለሰባዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎችን በጥናቱ ለማካተት ያስችላል።

በተጨማሪም አጥኚው የሰበሰበው አውዳዊ መረጃ ስለክዋኔ ለመረዳት አጋዥ ነው። ምክንያቱም በማህበረ ባህሉ ውስጥ ፎክሎርን የፈጠረው ሰው ስሜቱንና ማንነቱን የገለፀበትን ሁኔታ ለመረዳት ፎክሎር በሚከወንበት አውድ በቦታው ተገኝቶ መሰብሰቡ ከፍተኛ ግምት ሊሰጠው ይገባል። ስለአንድ ክስተት፣ ክስተቱ ስለፈጠራቸው አጋጣሚዎች፣ አጋጣሚዎቹ የፈጠሩአቸው ሁኔታዎችን ማወቅና መረጃውንም በዚሁ አንጻር መሰብሰብ የፎክሎርን ሚና፣ ውበት፣ የፈጠራቸውን ማህበራዊ ተግባቦት ማወቅ ያስችላል። የአንድ ማህበረሰብ ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ምን ፍቺ እንደሚሰጡ በሰዎች የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ የሚያሳድሩትን ተፅእኖና ጫናዎች ለማወቅ ክዋኔውን ከነ አውዱ በሚከወንበት ተፈጥሮአዊ መቸት ማጥናት ትልቅ ግምት የሚሰጠው ነው። ስለዚህ እነዚህን ለፎክሎር ጥናት ቁልፍ የሆኑትን የአውድ መልኮችን ማየት አስፈላጊ በመሆኑ እንደሚከተለው እመለከተዋለሁ።

#### 2.1.1.3.1.1. አውዳዊ ጥናት /Contextual Study/

አውድ /context/ የሚለው ቃል ምንጩ "contexere" ከሚለው የላቲን ቃል ሲሆን ትርጉሙም ማጠናቀር፣ ማዋሃድ፣ ማስማማት፣ መሸመን ነው። የፎክሎር

ተመራማሪዎች የተለያዩ የስነ ማህበረሰብ ትወራዊ ዘዴዎችን በማቀናጀት፣ በማጠናቀር ፎክሎርን በስነ ጎሣዊ ዘዴ፣ በስነ ክዋኔ ጥናቶች (performance studies)፣ በሐቲት ትንተና ወዘተ ያካተቱ ዘዴዎች በማጠናቀርና በማደራጀት ማጥናት ጀመሩ (Hufford, 1995)።

ይህ የፎክሎር ጥናት አቅጣጫ በ1960 ዎቹ በአሜሪካ ሀገር የተጀመረ የጥናት መስክ ሲሆን ጥናቱ ትኩረት ያደረጋቸው አበይት እሳቤዎች ፎክሎርን በበቀለበት ማህበረ ባህላዊ አውድ ማህበረሰቡን ባሳተፈ መልኩ ማጥናት ነው (Dorson, 1972)። ትኩረ ሊሰጥባቸው የሚገቡ ወሳኝ የአውድ መልኮች ከዋኝ፣ ታዳሚ፣ የሚከወነው ጉዳይ፣ መቸት፣ በድርጊት ወይንም በክዋኔው የሚተላለፈው መልዕክት፣ ክዋኔው ሥርዓቱን ጠብቆ የሚካሄድበት Frame line, የክዋኔው አጀማመርና አዘጋግ /Formula/ እና ልዕለ ትረካ (meta narrative) ናቸው (Dorson, 1972)፡፡

በአውዳዊ የጥናት ትወራ ጉዳይ (text) ብቻ ሳይሆን ባክቲን /Bakhtin/ እንደሚለው በአውድ ውስጥ የተወሳሰቡ ማህበራዊ ክስተቶችም መጠናት አለባቸው። ይህ የሚያተኩረው በሁለት ጉዳዮች (events) ላይ ነው። ይኸውም የሚከወነው ጉዳይ (events) እና የክዋኔ ተሳታፊዎች (ከዋኝ ወይም አድማጭ)ና ክወኔው (ጉዳዩ) የሚተገበርበት ጊዜያትና ቦታዎች ናቸው። በዚህ ጥናት ከላይ እንደተጠቀሰው ጉዳይ (text)፣ የከዋኝ ታዳሚያን ተግባቦት፣ ጉዳይ የሚከወንበት መቸት እና የአከዋወን ጥበብ ትኩረት የሚሰጥባቸው ጉዳዮች ናቸው (Hufford, 1995)።

ሲምስና ስቴፈንስ (Sims and Stephens, 2005) "Living Folklore፡An Introduction to the Study of People and Thier Tradition" በሚለው መጽሐፋቸው አውድን አካላዊ መቸት (physical setting) እና ማህበራዊ ሁኔታዎች (social situations) በማለት ከፋፍሎ ማህበራዊ ቡድን የጋራቸው የሆነውን ጉዳይ የሚጋሩበት፣ በከዋኝ እና ታዳሚያን መካከል ተግባቦት የሚፈጠርበት ነው ይላሉ። ቀጠል አድርጎ አውድ ማለት ማንኛውም በክዋኔ ዙሪያ ያሉ ነገሮች እንደሆኑ ይገልፃሉ።

አካላዊ መቸት ክዋኔ የሚተገበርበት አካባቢ ወይንም ቦታ እና ጊዜን ያጠቃልላል። ከዋኙና ታዳሚያን የሚገናኙበት ቦታና ጊዜ፣ ከዋኙ የተጠቀመበት መሣሪያ፣ ክዋኔ

የተደረገበት ቦታ ቤት ውስጥ ከሆነ በቤቱ ውስጥ የሚገኙ ለክዋኔው አስተዋፅኦ ያደረጉ ቁሳቁሶች (ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎችና የመሳሰሉት) ናቸው ይላሉ።

ማህበራዊ አውድን ሲገልፁ ደግሞ ማህበራዊ አውድ የክዋኔው ሰፊ አውድ ሲሆን የፎክ ቡድን /folk group/ ወይንም ከዋኙንና ታዳሚያን ያገናኛቸው ጉዳዮች፣ በቡድኑ መካከል ተግባቦት እንዲፈጠር ያደረጉ ማህበረ-ባህላዊ ጉዳዮችን ያጠቃልላል ይላሉ። ይህ አውድ ማህበራዊ ተግባቦት እንዲፈጠር ያደረጉ ጉዳዮች፣ ከዋኝ፣ ተደራሲያንና ክዋኔው የተደረገበትን ጊዜና ቦታ ላይ የራሳቸውን ተፅእኖ ያሳረፉ ክስተቶችንም የሚጨምር ነው ይላሉ።

የክዋኔ አካላዊ አለባዊያን በራሳቸው የአውድ ክፍሎች ናቸው። አውድ የከዋኙ የገፅ መለዋወጥ፣ ድምፀት፣ ስልተምትና የመሳሳሉት ጭምር ናቸው። አንድ የፎክሎር አጥኚ ለእነዚህ ነገሮች ትኩረት መስጠት አለበት። እነዚህ ጉዳዮች በፎክሎር ክዋኔ ላይ የራሳቸውን ተፅእኖ ማሳደር የሚችሉ ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው። የአውድ ጉዳዮች አንድ የፎክሎር ዘውግ የሚከወንበት አጋጣሚዎችን ይጨምራል (Finnegan, 1970, 1977, 1992)። አንድ የፎክሎር ዘውግ በሚከወንበት ጊዜ የሆነውን ሁሉ መግለፅ የተደረገውን ድርጊት ብቻ ሳይሆን ድርጊቱ ለምን እንደተደረገ፣ በድርጊቱ ጊዜ ምን ክስተቶች እንደተደረጉ፣ ክስተቶች ያመጧቸው ውጤቶች (Sims & Stephens, 2005)፣ የከዋኙና የተደራሲያን ምላሽ፣ በተደራሲያንና በከዋኝ መካከል የተፈጠሩ ግንኙነቶች የሚያሳዩ ናቸው (Finnegan, 1992)። አለን ደንደስ (Alan Dundes, 1964) አውድ ክዋኔ የሚተገበርበት መቸት ነው ይላል።

በአንፃሩ ቤን አሞስ (Ben-Amos) ደግሞ አውድን በሁለት ትላልቅ ጎራዎች ይከፍላል። እነሱም ባህላዊና ሁኔታዊ አውድ ናቸው። ባህላዊ አውድ በጣም ሰፊው አውድ በመሆኑ ከዋኞቹ የሚጋሩት እውቀት /እሴት/፣ ባህላዊ ስምምነት፣ ሥርዓት-አምልኮ፣ የቋንቋ ዘይቤና የንግግር ዘውግ/genre/፣ ታሪካዊ እውቀት፣ ስነ ምግባርና ህጋዊ እንድምታዎች በውስጡ ያቀፈ ነው ይላል። በመቀጠል ሁኔታዊ አውድ ደግሞ ጠባብና ቀጥተኛ የፎክሎር ክዋኔ አውድ ነው ይላል (Ben-Amos, 1993)።

ባህላዊ ሁኔታ /cultural situation/ በውስጡ የማህበረሰቡን አስተሳሰብ /world view/፣ ባህል፣ ሥርዓት /system/፣ ባህላዊ ቅንብብ /cultural framework/ እና ሀቲት /discourse/ አቅፎ የያዘ ነው (Hufford, 1995)።

ባውማን (Bauman,1983) በበኩሉ አውድን በሰፊው የተነተነው እንደሚከተለው ተቃኝቷል። በውማን (Bauman) አውድን ባህላዊ አውድ /ፍቻዊ አወድንና ተምሳሌታዊ ግንኙነትን የሚያካትት/ እና ማህበራዊ አውድ (ማህበራዊ መዋቅርና ማህበራዊ ግንኙነትን የያዘ/ በማለት በሁለት ከፋፍሎ ያያል።

### 2.1.1.3.1.1.1. ባህላዊ አውድ / cultural context /

ባውማን (Bauman, 1983) እንዳስቀመጠው ባህላዊ አውድ ፍቻዊ አውድ፣ ተቋማዊ አውድንና ተግባቦታዊ ሥርዓት አውድን በውስጡ የያዘ ነው። በዚህ ርዕስ ሥር ግን ከባህላዊ አውድ መካከል ለዚህ ጥናት ወሳኝ የሆኑትን ፍቻዊ አውድና ተግባቦታዊ ሥርዓት አውድን እንቃኛለን።

1.ፍቻዊ አውድ / context of Meaning /፡- ፍቻዊ አውድ በባህላዊ አውድ ሥር የሚጠና ሲሆን አንድ የፎክሎር ዘውግ ለማህበረሰቡ ያለውን ፍቺ የሚያሳይ ነው። የአንድ የፎክሎር ይዘት ወይንም ለማህበረሰቡ ያለውን ትርጉም ለማወቅ አንድ ሰው አንድ የፎክሎር ዘውግ በሚከወንበት ማህበረ ባህል ምን ማወቅ ወይም መረዳት አለበት? ምን ዓይነት የማህበረሰቡ የአኗኗር ሁኔታዎች በፎክሎሩ ውስጥ ተንፀባርቀዋል? ምን ዓይነት የማህበረሰቡ የእምነት ሥርዓት፣ የአብሮነት ሁኔታዎች፣ የመረዳዳት እሴት፣ ምክንያትና ውጤት፣ ምርጫና ፍላጎት፣ ድርጊት /mode of action / ተምሳሌታዊና ዘይቤአዊ ተግባቦት ለፎክሎር ዘውጉ ፍቺና ቅርፅ ሰጥተዋል? አንድ የፎክሎር ዘውግ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ትርጉም ምን እንደሆነ የሚጠናበት አውድ ነው።

በተጨማሪም በዚህ አውድ የሚጠናው የፎክሎር ባለቤቶች ፎክሎሩ ስለሚያነሳቸው ጉዳዮች ወይንም ስላነጣጠረባቸው ልምዶች እና ግንዛቤዎች ምን እውቀት እንዳላቸው እና እያንዳንዱን የፎክሎር ይዘት እንዴት እንደሚረዱ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ከዋኙ አንድን የፎክሎር ቅርፅ ከሌሎች መርጦ በዚያች መቼት ውስጥ

ይከውን ዘንድ የቀሰቀሱ፣ ያነቃቁ ጉዳዮች፣ ፎክሎሩ በሚከወንበት ማህበራዊ ወይንም ግላዊ ምክንያቶች መካከል ያሉ ተምሳሌታዊና ዘይቤያዊ ዝምድናዎች ምን እንደሆኑ የሚጠናበት አውድ ነው።

2.ተግባቦታዊ ሥርዓት አውድ / Context of Communicative System /፡- በዚህ አውድ ውስጥ የሚጠናው ጉዳይ ደግሞ አንድ የፎክሎር ቅርፅ በማህበረሰቡ አባላት መካከል ተግባቦትን እንዴት ፈጠረ? የተፈጠረው ተግባቦት ከማህበረሰቡ ባህል ወግ ልማድ ጋር ይሰምራል ወይ? በከዋኝና ታዳሚያን መካከል የተፈጠረው ተግባቦት ከዘወትራዊ ንግግር በምን ይለያል? የሚሉት ጉዳዮች ናቸው።

2.1.1.3.1.1.2. ማህበራዊ አውድ /Social Context/

በውማን ማህበራዊ አውድ ሥር ማህበራዊ መሠረት አውድ፣ ግለሰባዊ አውድ፣ ሁኔታዊ አውድና ተፈጥሮአዊ አውድ እንዳሉ አመላክቷል።

1. ማህበራዊ መሠረት /Social Base/፡- ፎክሎር የአንድ ማህበረሰብ የጋራ ሀብት፣ የጋራ መገለጭያ ነው። ፎክሎርን የማህበረሰቡ የጋራ መገለጭያ ሀብት አድርጎ ማየቱ ለሁለት መቶ አመታት የቆየና አሁንም በጥናቱ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ እያሳደረ ያለ ጉዳይ ነው። በልዩ ልዩ ማህበረሰቦች ውስጥ ልዩ ልዩ የአደረጃጀት መርሖዎች አሉ። ፎክሎር በእነዚህ የአደረጃጀት መርሖዎች ውስጥ አገልግሎት መስጠቱ ማህበራዊ ያደርገዋል። ስለዚህ ይህ አቀራረብ ፎክሎር በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ሚና ምንድነው? የማህበረሰቡን የአሁኑን ወግ፣ ልማድ በጠቃላይ ባህልና ማህበራዊ ደረጃ አንፀባርቋል ወይ? የትኛውን ማህበራዊ ማንነት አንፀባርቋል? የሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ የሚያገኙበት አውድ ነው።

2. ግለሰባዊ አውድ /Individual Context/፡- ፎክሎር የማህበረሰቡ መገለጫ እንደሆነ ሁሉ የግለሰቦች የማንነት መግለጫም ጭምር ነው። ግለሰቦች በማህበራዊ ቡድን ወይንም ማህበራዊ ህይወት አውድ ውስጥ ፎክሎርን ይማራሉ፣ ይከውናሉ። እንዲሁም ግለሰቦች ስሜታቸውንና ሃሳባቸውን የሚገልፁበት ጥበብ ነው። ማህበራዊ ሁኔታዎች ግለሰቦች ፎክሎርን የሚማሩበት እና የሚከውኑበት አውድ እንደሚያስገኙ ሁሉ የአንድን ከዋኝ የህይወት ታሪክ እንዲሁም የሰውየውን ሀብተ-ኪንና ተውህቦ

እንዴት እንዳደገ ማጥናት ፎክሎር በሰዎች ህይወት ውስጥ ያለውን ቦታ ለመረዳት ያግዛል።

በዚህ አውድ በፎክሎር ክዋኔ ውስጥ ግለሰቦች መቼና እንዴት ፎክሎር እንደተማሩ፣ ጥበቡን ከማን እንደተማሩ፣ ጥበቡን እንዲማሩና ከዋኝ እንዲሆኑ ያነሳሱዋቸው ግለሰባዊና ማህበራዊ ምክንያቶች /ጉዳዮች ምን እንደሆኑ፣ በከዋኝነት በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ቦታ ወይንም ደረጃ ምን እንደሆነ ይጠናበታል።

ሌላው በዚህ አውድ የሚታየው ጉዳይ ምን ዓይነት ማህበራዊና ግለሰባዊ ጉዳዮች በፎክሎር ክዋኔ ላይ ተፅእኖ አሳርፈዋል? እነዚህ ማህበራዊና ግለሰባዊ ጉዳዮች በፎክሎር እንዴት ተገለፁ? ምን ዓይነት ግለሰባዊና ማህበራዊ ጉዳዮች /factors/፣ መርሖዎች /principles/ የግለሰቦችን የፎክሎር ክዋኔ ቅርፅ አስያዙ? የሚከውኑ የፎክሎር ቅርፆች ምን ያህል የግለሰቦችን ህይወት ያሳያሉ የሚሉት ጥያቄዎች ናቸው።

3.ሁኔታዊ አውድ /Situational Context/፡- ሁኔታዊ አውድ በቡድኑ መካከል ተግባቦት የሚፈጠርበት አውድ ነው። የአንድ የፎክሎር ቅርፅ ትርጉም ወይንም ፋቹ የሚከሰትበትና የማህበረሰቡ አባላት ማህበራዊ ተግባቦት የሚፈጥሩበት አጋጣሚ ነው። ምክንያቱም በዚህ ማህበራዊ አጋጣሚ ፎክሎር ይፈጠራል፤ ይከወናል። ክዋኔው የተሟላ እንዲሆን ኪናዊና ባህላዊ ገፅታ ማላበስ አስፈላጊ ነው። ይህ ሁሉ የተሟላ እንዲሆን አካላዊ መቼት፣ የተሳታፊና የታዳሚያን ማንነት፣ በክዋኔው ውስጥ የሚኖራቸው ሚና፣ ክዋኔው መከተል ያለበት ማህበራዊና ባህላዊ ህግጋት፣ በከዋኙና በታዳሚያን መካከል ያለው ተግባቦት፣ የድርጊቶቹ ቅደም ተከተል፣ ፎክሎር እንዲከወን ያደረጉት ማህበራዊ አጋጣሚዎች፣ በአጋጣሚዎቹ ውስጥ የተከሰቱ ክስተቶች፣ የክስተቶቹ ምክንያትና ውጤት… ወዘተ አስፈላጊዎች ናቸው። ይህንን ሁኔታ አስመልክቶ በውማን (Bauman,1983) ሲገልፅ፡

> *The structure of folkloric events is a product of interply of numerious situational factors, including physical setting, participants' identities and roles, cultural ground rules fore performance norms of interaction and interpretation, and the sequence of actions, making up the conventional scenario of the event itself as a cultural scens* ይላል።

ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው ለአንድ የፎክሎር ቅርፅ ክዋኔ ግብ መምታት የሚወስኑ ሁኔታዎች አካላዊ መቸት፣ የታዳሚያን ማንነትና ሚና፣ የአንድ ፎክሎር ቅርፅ ክዋኔ ባህላዊ ህጋጋት፣ ተግባቦታዊ ሥርዓትና አረዳድ፣ የድርጊቶቹ ቅደም ተከተልና የመሳሰሉት ባህላዊ መልኮች ወሳኞች ናቸው።

ሁኔታዊ አውድ አንድ የፎክሎር ቅርፅ በአንድ አጋጣሚ እንዲከወን ያደረጉ ማህበራዊ ሁኔታዎች ምንድ ናቸው? በዚህ ሁኔታ ውስጥ መከወኑ ምንን ለመግለፅ ነው? ተከውኖ ሁኔታውን በመግለፁ ምን ጥቅም አስገኘቷል? ሁኔታዎችን ለመግለፅ እንዴትስ ተተገበረ ወይንም ተከወነ? የሚሉትን ጥያቄዎቹ ይመልሳል።

4.ተፈጥሮአዊ አውድ /Natural Context/፡- ተፈጥሮአዊ አውድ ለፎክሎር መከሰት ምክንያት የሆኑ ማህበረ-ባህላዊ ሁኔታዎች፣ ፎክሎር ለማህበረሰቡ ምን እንደሆነ ወይንም ቡድኑ በፎክሎር እንዴት ተግባቦት እንደሚፈጥር አጥኚው በቦታው በአካል ተገኝቶ  መረጃውን በበቀለበት መንደር ወይንም አውድ የመሰብሰብ፣ በማህበረሰቡ አተያይ የመተንተን አቅም የሚፈጥለት አውድ ነው (MacDonald in Dorson, 1972)። ተፈጥሮአዊ አውድ በፎክሎር ክዋኔ ላይ ለሚከሰቱት ተለዋውጦዎች ምክንያት ምን እንደሆነ፣ በምክንያቱ መነሻነት የተከሰቱ ክስተቶችና የውጤታቸውም እንዴትነት ለመረዳት ያስችላል። በተፈጥሮአዊ መቼት በፎክሎር ክዋኔ ውስጥ ግለሰቦች ያላቸው ሚናና ግለሰቦቹ አጋጣሚዎችን ለመግለፅ አንድን የፎክሎር ቅርፅ እንዴት እንደሚከውኑ (Bauman, 1983, Bronner, 1988) ለማወቅ ከፍተኛ አጋዥነት አለው።

በአሁኑ ጊዜ በከዋኝና ታዳሚያን መካከል ያለው ተግባቦት ምን ይመስላል? ማህበረሰቡ የራሱን ፎክሎር እንዴትስ ይረዳል? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ፎክሎርን በበቀለበት ማህበረ-ባህላዊ አውድ /ተፈጥሮአዊ አውድ/ ማጥናት አስፈላጊ ነው።

በአጠቃላይ በውማን (Bauman) እና ሌሎች ምሁራን ያስቀመጡዋቸው ከላይ የተዘረዘሩት የአውድ መልኮች የፎክሎርን ክዋኔ በምልኣት ለመረዳት የሚያስችሉ ናቸው። አንድ የፎክሎር ቅርፅ የት? ለምን? እንዴት? እንደተከወነና እነማን? እንደከወኑት፣ የክዋኔው ጥበባዊ ተገላጭነት እስከምን እንደሆነ፣ የከዋኝ ብቃትና

የታዳሚያን ምላሽ ምን መልክ እንዳለው፣ የፎክሎር ቅርፅ የተከወነበት ማህበረ-ባህላዊ አጋጣሚ፣ በክዋኔ ሂደት ውስጥ የተከሰቱ ክስተቶችና ሁኔታዎች ወዘተ ያስገነዝባሉ።

በተጨማሪም የአንድን ማህበረሰብ ፎክሎር ለማጥናት በሚሞከርበት ጊዜ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ነጥቦች ናቸው። እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ነጥቦች የሚጠናውን የማህበረሰቡን እምነት፣ አስተሳሰብና አመለካከት ሳይጓደልና ሳይዛባ ለማካተት የሚያስችሉ፣ በጥናቱ ቦታ በአካል ተገኝተው መረጃውን መሰብሰብና በጥናቱ ላይ የአካባቢውን ማህበረሰብ ማሳተፍ፣ በቂ ጊዜ ወስደው ትክክለኛውን መረጃ ለመያዝ የሚያስችሉ፣ የትንተናውን አቅጣጫ ከዚያ ማህበረሰብ አኗኗር፣ አካሄድ፣ ስነ-ልቡና፣ ወግና ልማድ መነሳት እንዳለበት ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ናቸው። እንዲሁም የፎክሎር ህያውነት የሚገለፅባቸው፣ ተለይተውና ተወስኖ የሚቀርብባቸውን አጋጣሚዎች፣ በአከዋወኑ ሂደት የፎክሎርን መምጣት ምክንያት የሚወስኑ ሁኔታዎችና ሌሎች የአከዋወን ሥርዓቶችን ለማወቅና በጥናቱ ውስጥ ለማካተት፣ እያንዳንዱ የፎክሎር ቅርፅ የተለያዩ ተምሳሌታዊ ፍችዎችን ስለሚይዝ ይህን ጉዳይ በሚከወንበት ማህበረ-ባህል ለመረዳት አቅም ይፈጥራሉ።

የኔ ጥናትም ጌረርሳ በሚከወንበት ማህበረ-ባህላዊ አውድ ውስጥ በመሰራቱ ከላይ የቀረቡትን ንድፈ ሃሳቦች መሠረት አድርጓል። እነዚህ ንድፈ ሃሳቦች የግለሰቦች የጌረርሳ ክዋኔ ያነጣጠረበት ማህበራዊና ግለሰባዊ ጉዳዮችን ለመረዳት አግዞኛል። ጥናቱን በማካሄድበት ጊዜ ምን ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለብኝ አቅጣጫውን በማሳየት አስተዋፅኦ አድርጎልኛል። በተጨማሪም በክዋኔው ሂደት ውስጥ ታዳሚያን ያላቸው ሚና ምን እንደሆነና ለነሱም ትኩረት መስጠት እንዳለብኝ መንገድ አሳይቶኛል።

#### 2.1.1.3.2. ተለዋዋጭነት

ሌላኛው የቃል ግጥም ባህያት ተለዋዋጭነት ነው። የቃል ግጥም በግለሰብ ተፈጥሮ በተላያዩ አጋጣሚዎች እየተከወነ ለሚቀጥለው ትውልድ በቃል የሚተላለፍ በመሆኑ እንደ ከዋኙ ብቃት ሊጨመርበትና ሊቀነስበት ስለሚችል በየጊዜው ሊለዋወጥ ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እንደአውዱ ሁኔታ ለአውዱ እንዲመች ከዋኙ ለቦታውና ለሁኔታው የሚስማማውን በመጨመር የማይስማማውን በመቀነስ

ይከውናል። ምክንያቱም ፎክሎር የማህበራዊ ቡድን መገለጫ በመሆኑ ለቡድኑ እንዲመች ተደርጎ እንደገና ይፈጠራል (Bauman, 1975) ። ይህ ሁኔታ እንዲለወጥ በር ይከፍትለታል።

በተጨማሪም የቃል ግጥም የመለዋወጫ ምክንያት ደግሞ ቃል ግጥሞችን ከዋኙ በቃል ይማራል፤ መልሶ በቃል የስተላልፋል። በዚህ ጊዜ ያስታወሰውን ሲያዜም የረሳውን ወይም የጎደለውን በራሱ ይሞላበታል። በአጠቃላይ በከዋኙ የማስታውስና እንደገና መልሶ የመፍጠር ችሎታ ላይ ሊመሰረት ይችላል። የሚለወጡት የቃል ግጥም ስንኞች፣ ሀረጋት ወይም ቃላትና ከዚህ ያለፈ ልሆኑ ይችላሉ (Finnegan, 1970; ዘሪሁን፣ 2000) ።

#### 2.1.1.3.3. ድግግሞሽ

ከቃል ግጥሞች መሰረታዊ ባህሪያት አንዱ ድግግሞሽ ነው (Finnegan, 1977) ። ፎክሎር የመለወጥ ባህሪ እንዳለው ሁሉ ራሱን ይደግማል፤ እየተደጋገመ ይከወናል። ስለዚህ ቃላዊ ፎክሎር የመለወጥ ባህሪ እንዳለው ሁሉ እየተደጋገመ የመከወን /continuity) አለው (Finnegan, 1992) ።

በአጠቃላይ ቃላዊ ግጥም ከላይ የተጠቀሰውን ዋና ዋና ባህሪያት አሉት።

### 2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ርዕስ ሥር ከጥናቱ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተዛማጅነት ያላቸው የሦስተኛ ዲግሪ ጥናት /Ph.D Dessertaion/ እና የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ተቃኝተዋል። እነዚህ ጥናቶች አንደኛው በ "Indiana University" በ1990 እ.ኤ.አ የተሠራው የአዲሱ ቶለሳ የፒ.እች.ዲ ጥናት ሲሆን ሌሎች ስድስት /6/ ጥናቶች ደግሞ በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናቶች ናቸው። በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ሁሉም ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ብፈልግም በጌረርሳ ላይ የተሠሩ የማስተርስ ድግሪ (M.A) ማሟያ ጥናት ለማግኘት አልቻልኩም።

የአዲሱ ቶለሳ የፒ.እች.ዲ /Ph.D/ ጥናት " The Historical Transformation of a Folklore Genre፡ The 'Geerarsa' as a National Literature of The Oromo in The Cotnext of Amhara Colonization in Ethiopia" በሚል ርዕስ የተሠራ ሲሆን

በዚህ ርዕስ ሥር "ፎክሎር እንደ ኦሮሞ የታሪክ ምንጭ፣ የኦሮሞ ኢትኖግራፍያዊ ዳራ፣ የጌረርሳን ክዋኔ (poetic performance), ጌረርሳ እንደ ኦሮሞ የጀግንነት መገለጫ፣ ጌረርሳ በኢትዮጵያ የአማራ የበላይነት አውድ ውስጥ፣ ጌረርሳ በኢትዮጵያ የለውጥ ሁኔታዎች ውስጥና ጌረርሳ እንደ ኦሮሞ ብሔራዊ ስነ-ጽሑፍ የሚሉት ንዑስ ርዕሶች የተከፋፈለ ነው።

አዲሱ "ፎክሎር እንደ የኦሮሞ ታሪክ ምንጭ" በሚለው ርዕስ ሥር ጌረርሳ ኦሮሞ ከአማራ ነገስታትና የፓለቲካ ካድሬዎች ግፍ አገዛዝ በፊት፣ በኋላና በግፍ አገዛዝ ጊዜ ያለውን ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፓለቲካዊ ሁኔታዎች የሚያሳይ ነው በማለት ያብራራል። ጌረርሳ ኦሮሞ ከግፍ አገዛዝ ለመውጣት ያደርግ የነበረውን ተጋድሎ የሚገልፅ ነው። በተጨማሪም የአማራ ነገስታት የኦሮሞን መሬት እንዴት በሃይል እንደያዙና ኦሮሞን "Gabbarii" እንደዳረጉም ያሳያል። በዲያስፖራ ያሉትንም የኦሮሞ ማህበረሰብ ህይወት ማሳየቱና የኦሮሞ ማህበረዊ እሴት በመግለፁ ጌረርሳን የኦሮሞ የታሪክ ምንጭ ያደርገዋል በማለት ይተነትናል።

"የኦሮሞ ኢትኖግራፍያዊ ዳራ" በሚለው ርዕስ ሥር ደግሞ የኦሮሞ ኢትኖግራፍያዊ ዳራ ኦሮሞ በሚለው ስም ላይ ይመሰረታል። የኦሮሞ ተቋማዊ መርሖዎችና እንቅስቃሴዎች፣ የኦሮሞ የጋብቻ ስነ-ሥርዓት፣ የኦሮሞ የገዳ /Gada/ ማህበረ-ፓለቲካዊ ተቋምና እነዚህ ማህበራዊ ተቋማት ከጌረርሳ ጋር ያላቸው ግንኙነትም በጥልቀት ተብራርቷል።

በፊውዳል የአገዛዝ ሥርዓት ጊዜ ጌረርሳ የኦሮሞን ጭንቀቶች፣ ራሃብ፣ ሌሎች ችግሮችና የኦሮሞ የራሱን ግዛት /መሬት/ ማጣትና ከክብሩ ማዋረድ የሚያንፀባርቅ መሆኑንና የጌረርሳ ከዋኞች ይህን ግፍ በተለያዩ አጋጣሚዎች ጌረርሳን በመከወን ያሳዩ መሆኑ በጥናቱ ተገልጿል።

እንዲሁም ጌረርሳ የኦሮሞን ጀግንነት፣ ኦሮሞ ከነፍጠኞች ጋር ያደርጋቸው የነበረውን ተጋድሎ፣ የአማራ ነገስታት ትጥቅ ከአውሮፓዊያን አግኝተው ኦሮሚያን ሙሉ በሙሉ ቁጥጥራቸው ሥር ከማስገባታቸው በፊት ያደረጋቸውን የአልሸነፍ ባይነት ትግል እንደሚያሳይ አመላክቷል።

በተጨማሪም ጌረርሳ በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው የፓለቲካ ሁኔታዎች መለወጥ በተለይ የአማራ የበላይነት መከሰት፣ ለሥራና ትምህርት ፍለጋ የኦሮሞዎች ወደ ከተማ መሰደድን ያሳያል። በመቀጠልም የሥራ ቋንቋ ወደ አማርኛ መለወጥና

የአማራነት ስሜት መስፋፋት፣ የኦሮሞ የራሱን ማንነት እንዲያጣ መደረግና የኦሮሞ የራሱን ስነ-ጽሑፍ መከልከል ጌረርሳ እንደሚያሳይ አመላክቷል። የኦሮሞዎች በራሳቸው ማንነት እንዲያፍሩ መደረግ፣ በኦሮሚያ ውስጥ ያሉ የቦታ ስሞች መለወጥ፣ የኦሮሞ ሕዝብ በግድ የክርስትና ሃይማኖት እንዲቀበሉ መደረግ (የኦርቶዶክስ ሃይማኖት የበላይነት ማግኘት)፣ የኦሮሞዎች ነፍጠኞችን በጉልበት እንዲያገለግሉ መደረግና ታክስ በግድ የመስከፈል ሁኔታዎችና ሌሎች በኦሮሞ ላይ ይደርሱ የነበሩ ግፎች በጌረርሳ እንደሚነፀባረቁ አብራርቷል።

ስለዚህ ጌረርሳ በኢትዮጵያና በዲያስፓራ የሚኖሩ የኦሮሞዎች ህይወት ጭምር የሚያሳይ በመሆኑ የኦሮሞ ታሪክ ምንጭና የኦሮሞ ብሔራዊ ስነ-ጽሑፍ ለመሆን እንደሚያስችሉት በጥናቱ አመልክቷል።

ይህ ጥናት በአጠቃላይ ሲታይ ጠንካራና ሰፋ ያለ ትንተና ቢያቀርብም በአብዛኛው በዲያስፓራ የተሰበሰበ መረጃ ላይ መመስረቱ በሀገር ውስጥ ያሉ የኦሮሞዎች ህይወት ማሳየቱ ላይ ጥርጣሬ ውስጥ የሚከት ነው። በተለይ ከ1974-1976 እ.ኤ.አ የተሰበሰበ መረጃ አጥኚው እንደሚለው ከግፍ አገዛዙ በኋላ ያለውን የኦሮሞ ህይወት ማሳየቱ ላይ ደካማ እንደሚሆን አያጠራጥርም።

የአዲሱ ቶለሳ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ያለው ተመሳስሎና ልዩነት ሲታይ ደግሞ ጌረርሳ የኦሮሞን ህይወትና እሴቶች ማሳየቱን በጥናቱ ለማሳየት መሞከሩ ተመሳሳይ የሚያደርግ ሲሆን የአዲሱ ቶለሳ ጥናት አጠቃላይ የማህበረሰቡን ማህበራዊና ፖለቲካዊ ህይወትና እሴት ማሳየቱን ያየ ሲሆን የኔ ጥናት ግን ግለሰቦች ላይ ትኩረት ያደረገ ሆኖ የግለሰቦችን ህይወትና እሴት ማሳየቱ ላይ ያተኮረ ነው። ስለዚህ ግለሰቦችን በመምረጥ የተመረጡትን ግለሰቦች በመከታተል የሚከውኑት ጌረርሳ ከህይወታቸው ጋር እንዴት እንደሚሰምር ማሳየት ላይ ያነጣጠረ በመሆኑ ልዩ ያደርገዋል።

ሌሎች ከዚህ ጥናት ጋር ተዛምዶ ያላቸው ጥናቶች ደግሞ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቀረቡ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ናቸው። እነሱም እንደሚከተለው ተቃኝተዋል።

ወርቁ ደቻሳ (1978)፣ ገመቹ ገላልቻ (1986)፣ ሽጉጤ ተሾመ (1986)፣ ካባ መኮንን (1996)፣ ሀይደር አማን (1998 እና እውነቱ አድማሱ (2002) ጌረርሳ (Geerarsa) ላይ የድግሪ መሟያ ጥናት ያደረጉ ሲሆን እነዚህ ጥናቶች የጌረርሳ ግጥሞች ይዘት

ትንተና ላይ ያተኮሩ ናቸው። ጥናቶቹ የይዘት ተመሳሳይነት የሚታይባቸው ናቸው። የወርቁ ደቻሳ፣ የገመቹ ገላልቻ፣ የካባ መኮንንና የሀይደር አማን ጥናቶች በአዳኞች ጌረርሳ ላይ ያተኮሩ ሲሆን አዳኞች ለአደን ከመነሳታቸው በፊት የሚያደርጉትን አካላዊ፣ ቁሳዊና መንፈሳዊ ዝግጅት ለአደን የሚወጡበት ዓላማ፣ ጎሽ፣ አንበሳና የመሳሰሉትን እንሰሳት ገድሎ ሲመጡ ለአዳኞች የሚደረግላቸውን አቀባበል የሚያቀርቡ ናቸው። ጥናቶቹ ጀግናን የሚያወድሱ፣ ፈሪን የሚነቅፉና የጀግናን ቤተሰቦች የሚያወድሱ በማለት የጌረርሳን ግጥሞች ከፋፍለው አቅርበው ትንታኔ የሰጡ ሲሆን አዳኞች ለአደን የሚወጡት ከማህበረሰቡ ከበሬታን፣ ሀብትና ንብረት ለማግኘት እና ዝናን ለመጎናፀፍ መሆኑን አመልክተዋል።

የተሾመ ሽጉጤና የእውነቱ አድማሱ ጥናቶች ደግሞ ከላይ ከተጠቀሱት ጥናቶች የተለየ ሃሳብ የያዙ ናቸው። የተሾመ ሽጉጤ ጥናት "በጉጂ ጎሣ የቦሊቱ ጌረርሳ ግጥሞች" በማለት የቀረበ ሲሆን ጥናቱ የቦሊቱ ጌረርሣ ማህበራዊ ልማዶችና እሴቶች የሚያቀርብ ነው። ጥናቱ ቦሊቱ (ከብቶችን ለቦሌ የሚያሳምረው ግለሰብ) የሚያደርገውን አካላዊ፣ ቁሳዊና መንፈሳዊ (ሃይማኖታዊ) ዝግጅት፣ ቦሊቱው የሚከውናቸውን የጌረርሳ ግጥሞችና ከብቶችን ለቦሌ ማሠማራት የሚያስገኘውን ማህበራዊ እሴት አቅርቧል። ጌረርሳዎቹንም ቦሊቱን በተመለከተ፣ የቦሊቱን ቤተሰብ በተመለከተ፣ ከብቶችን ማሞገስና ቦሌንና አባያን በተመለከተ በማለት ከፋፍሎ ይዘታቸውን ተንትኗል።

እውነቱ አድማሱ ደግሞ "Xiinxala Geerarsa Bara Mootii Kumsaa Morodaa" በማለት ያቀረበ ሲሆን ትርጉሙ የንጉሥ ኩምሳ ሞሮዳ ዘመን ጌረርሳ ትንተና" ማለት ነው። ይህ ጥናት ጌረርሳውን ስለሀገር፣ ስለ ኢኮኖሚ፣ ስለፓለቲካ፣ ገበሬዎች ላይ በገዢዎች ሲደርስ ስለነበረው ግፍ የሚያቀርቡ በማለት በመከፋፈል ይዘቶቹን የሚተነትን ነው።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የዲግሪ ማሟያ ጥናቶች በአጠቃላይ ሲታዩ ጠንካራ የንድፍ ሀሳብ ቅኝት የሌላቸውና ያቀረቡትም የይዘት ትንተናም ደካማ ነው። የሚከወኑበት አውድም በወጉ አላቀረቡም።

ጥናቶቹ ጌረርሳ ላይ ከመሠራታቸው ውጪ ከዚህ ጥናት ጋር ምንም ተመሳስሎ የሌላቸውና አጠቃላይ ነገሮች ላይ ያተኮሩ ናቸው። ማለትም ግለሰቦቹ ላይ ትኩረት

ያላደረጉ ሲሆን ያቀረቡት ጌረርሳ አሁን በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን ሁኔታ የማያሳይና በድሮ ጊዜ ማንም ገዳይ የሚከውናቸው ጌረርሳዎች ናቸው።

የኔ ጥናት ግን በግለሰቦች ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን ግለሰቦች በተለያዩ አጋጣሚዎች አነሳሽነት ጌረርሳን ከውነው ህይወታቸውን ወይም ገጠመኞቻቸውን የሚደልፁበትን ሁኔታዎች ማሳየት ላይ ያነጣጠረ ነው።

## ምዕራፍ ሦስት

# 3. የመረጃ ሰጪዎች ፕሮፋይል

## 3.1. የአቶ አባተ ኢጀርሳ ህይወት ታሪክ

አባተ ኢጀርሳ ከአባታቸው ከአቶ ኢጀርሳ ፈይሳና ከእናታቸው ከወ/ሮ ፈለቁ ማሞ ተወለዱ፡፡ የትውልድ ቦታቸው አደአ በርጋ ወረዳ ደኩ ቀርሳ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ሂንኔ ሰሪቲ (Hinnee Sariitii) በተባለ ቦታ ነው፡፡ የትውልድ ዘመናቸው 1966 ዓ.ም ሲሆን አሁን ዕድሜያቸው 38 ዓመት ነው፡ በልጅነት ዘመናቸው በጥሩ ሁኔታ ያደጉ ሲሆን ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በ1978 ዓ.ም የኢሉ ደንሴ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ገብተው የአንደኛ ክፍል ትምህርት ለተወሰኑ ወራት ብቻ ተከታትለው አቋርጠዋል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ለወላጆቻቸው የመጨረሻ ልጅ በመሆናቸው አባታቸው ከብቶች እንዲያግዱላቸው በመፈለግ መሆኑን መረጃ ሰጪው አቶ አባተ ኢጀርሳ ነገረውኛል፡፡



*ፎቶ1. በ19/06/2004 ዓ.ም ለአቶ አባተ ኢጀርሳ በቤታቸው ቃለ መጠይቅ ሲደረግ*

አቶ አባተ በልጅነት ዘመናቸው ከብት በመጠበቅ፣ በግብርና የተለያዩ የእርሻ ስራዎች በመሥራት ወላጆቻቸውን ሲያገለግሉ በእንክብካቤ ያደጉ ሲሆን በ1990 ዓ.ም በሚያዝያ ወር ውስጥ ታላቅ ወንድማቸው አቶ ገርማ ኢጀርሳ የኢሉ ደንሴ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ዘበኛ በነበሩበት ጊዜ ከትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ከመምህር በለጠ ነጋሳ ጋር በመጣላታቸው አባተና ሌሎች ስድስት ወንድሞቻቸው ለአቶ ገርማ ኢጀርሳ በመደረብ መምህር በለጠ ነጋሳን በመደብደብ ከፍተኛ የአካል ጉዳት

በማድረሳቸው ተከሰው ተፈርዶባቸው ከ1991-1996 ዓ.ም ለሰባት ተከታታይ አመታት በአምቦ ማረምያ ቤት ቆይተዋል፡፡ ከእስራቱ በኋላም ለረጅም አመታት ከሰባት ወንድሞቻቸው ጋር ፍርድ ቤት በመመላለሳቸው የነበራቸውን ንብረት ሸጠው ጨርሰዋል፡፡ አባተና ሰባቱ ወንድሞቻቸው የነበራቸውን በሬዎች፣ ላሞች፣ በጎች፣ ፍየሎች፣ የተከሉት ባህር ዛፎችና ሌሎች ንብረቶች ተሸጠው ለተጎጂው ግለሰብ ካሳ እንዲከፈል በመደረጉ አቶ አባተ በጉልበት ሥራና ለሰዎች እየተላላኩ እንዲተዳደሩ አድርጓቸዋል፡፡ እስራቱና ወደ ፍርድ ቤት መመላለሱ የአቶ አባተ ንብረት ብቻ አንድ ጥማድ በሬ፣ አራት ላሞች፣ አንድ ጊደር፣ ስምንት በጎች፣ ከአንድ ሄክታር በላይ የተተከለ ባህርዛፍ እንዲሸጥ ተደርገዋል፡፡ ሌሎች ለተጎጂው ካሳ እንዲከፈል ከካሳ የተረፈው ደግሞ በትራንስፖርትና በሌሎች ወጪዎች እንዲያልቅ ምክንያት ሆኗል፡፡ በዚህ የተነሳ አቶ አባተ በድህነት ኑሮአቸውን እየገፉ እንዲኖሩ ተደርገዋል፡፡

አቶ አባተ አሁን ያላቸው ንብረት አንድ በሬ፣ አንዲት በግ፣ ከአባታቸው የተሰጣቸው ስድስት ጥማድ የሚያውል አንድ ማሳና አንዲት አንገት ማስገቢያ ትንሽ ጐጆ ቤት ብቻ ናቸው፡፡ አቶ አባተ በ1998 ዓ.ም ትዳር የያዙ ሲሆን የአንድ ሴት ልጅ አባት ናቸው፡፡

አቶ አባተ ኤጀርሳ መዝፈንና ጌረርሳ መከወን ይወዳሉ፡፡ ዘፈኑንና ጌረርሳውን የሚከውኑት በዓመት በዓላት፣ በሰርግ፣ ለሥራ ሰዎች በሚሰበሰቡበት ጊዜ ሁሉ ነው፡፡ አንዳንዴ ብቻቸውን በመሆን ይከውናሉ፡፡ በጌረርሳው ገጠመኞቻቸውን ይገልፃሉ፡፡

አቶ አባተ ጌረርሳ መከወኑን የተማሩት አምቦ ማረሚያ ቤት በነበሩበት ከ1991-1996 ዓመተ ምህረት ባሉት ተከታታይ ዓመታት ነው፡፡ በወቅቱ እስር ቤቱ ውስጥ ከነበሩት እስረኞች መካከል ጌረርሳ የመከወን ችሎታ ያላቸው ጥቂት እስረኞች ነበሩ፡፡ እነዚህ እስረኞች አብዛኛውን ጊዜ ጌረርሳውን በመከወን ያሳለፉትን ህይወት እየገለፁ ራሳቸውንና እስረኞችን ያዝናኑ ነበር፡፡ በእስር ቤቱ ውስጥ የሚያጋጥማቸውንም ሁሉ በጌረርሳ ያሳዩ ነበር፡፡ እነዚህ ከያንያን በአቶ አባተ ላይ ተፅእኖ አሳድረዋል፡፡ የነሱን አርአያ በመከተል አቶ አባተ በተለያዩ አጋጣሚዎች ላይ ጌረርሳ በመከወን ችሎታቸውን አዳብረዋል፡፡ አሁን በየትኛውም ማህበረሰቡ

በሚገናኙበት አጋጣሚዎች ላይ ጌረርሳ ይከውናሉ። ማንኛውንም ማህበራዊም ሆነ ግላዊ ጉዳዮችን ይገልፃሉ (አባተ፣ 19/06/2004፣ 3:30)።

### 3.2. የአቶ ብርሃኑ አዱኛ ህይወት ታሪክ

አቶ ብርሃኑ አዱኛ ከአባታቸው ከአቶ አዱኛ ጅማና ከእናታቸው ከወ/ሮ ጥሩነሽ ኪዳኔ ጥቅምት 21 ቀን 1969 ዓ.ም ተወለዱ። የትውልድ ቦታቸው አደአ በርጋ ወረዳ ደኩ ቀርሳ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ አይሉ /Hayyiluu/ በተባለ ቦታ ነው። አቶ ብርሃኑ አዱኛ ለወላጆቻቸው አራተኛ ልጅ ሲሆኑ አምስት ወንድሞችና ሁለት እህቶች አሏዋቸው።



*ፎቶ2. በ15/06/2004 ዓ.ም ለአቶ ብርሃኑ አዱኛ በቤታቸው ቃለ መጠይቅ ሲደረግ*

አቶ ብርሃኑ አዱኛ ወላጆቻቸው በጥሩ ሁኔታ ያሳደጉዋቸው ሲሆን ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በ1980 ዓ.ም ኢሉ ደንሴ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ገቡ። ትምህርታቸውን እስከ አምስተኛ ክፍል የተከታተሉ ሲሆን በ1985 ዓ.ም ትምህርታቸውን አቋርጠው ወደ ግብርና ተመለሱ። ትምህርታቸውን ያቋረጡበት ምክንያት ሲገልፁ፡

> እስከ አምስተኛ ክፍል ከተማርኩኝ በኋላ የትምህርትን ጥቅም ባለማወቴ ትምህርቴን አቋረጥኩ። በትምህርት ቤት እያለሁ ራሱ ትምህርቴን ወደ ጉን ትቼ አረቄ እነገድ ነበር። በወረዳችን ከምትገኘው ኦለንኮሚ ከተባለች ትንሽዬ ከተማ አረቄ እያመጣሁ እሸጥ ነበር። ወላጆቼ ትምህርቴን እንድቀጥል ቢፈልጉም የኔ ፍላጎት ስላልነበረ አቋረጥኩኝ /ብርሃኑ፣ 15/06/2004፣ 7:00/።

አቶ ብርሃኑ አዱኛ አረቄውን ለአንድ ዓመት ነግደው ባገኙት ትርፍ ፍየሎችን በመግዛት ማርባት ጀመሩ። በኋላ ፍየሎቹን በመሸጥ አንድ በሬ ለመግዛት ችለዋል።

አረቄውን መነገድ ካቆሙ በኋላ በ1987 ዓ.ም ደግሞ ኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ጉጂ ዞን ኦዶ ሻክሶ ወደሚባል ቦታ ለወርቅ ቁፋሮ ሄዱ፡፡ ኦዶ ሻክሶ እንደጠበቁት አልሆነችላቸውም፡፡ ምክንያቱም እዚያ እንደደረሱ ለጊዜው ስራ ሊያገኙ አልቻሉም፡፡ ከጓደኛቸው ጋር ለሳምንታት ተንገላተዋል፡፡ ስራውን ከጀመሩ በኋላም ጓደኛቸው ይታሟል፡፡ ቆፍረው ባገኙት ብር ጓደኛቸውን አሳክመው አዳኑ፡፡ ነገር ግን ወደ ስራው ተመልሰው ለዘጠኝ ወራት ከሠሩ በኋላ እሳቸውም ይታመሙና ወደ ትውልድ ቀዬአቸው ተመለሱ፡፡ ኦዶ ሻክሶ የነበረውን ሁኔታ ሲገልፁ፡

> ኦዶ ሻክሶ ወርቅ የሚቆፈርበት ቦታ ቤት የለም። ሰዎች ዋሮ (Waaroo) ሰርተው ይኖራሉ፡፡ ዋሮው ከፕላስቲክ፣ ከማዳበሪያና ከተቀዳደዱ ልብሶች የሚሠራ ጎጆ ነው። ምግብ የሚነግዱ ሰዎችም ዋሮ ሰርተው ነው የሚኖሩት፡፡ ለኑሮ የሚስማማ አይደለም፡፡ ሰውን ለማኖር የሚያስችል አይደለም፡፡ በየቀኑ ትላልቅ ጉድጓድ ቆፍረን አፈሩን አውጥተን በማጠብ ወርቅ እንፈልጋለን፡፡ ተቆፍሮ አፈሩ የሚወጣበት ጉድጓድ "ቦሶቶ (Boosoottoo)" ይባላል፡፡ ጥልቅ ጉድጓድ ነው፡፡ ይህን ሁሉ ለፍተን ወርቁን ማግኘትም ማጣትም እንችላለን፡፡ በጣም አድካሚ ነው፡፡ ይህ ሁሉ ለፍተን ማታ የምንተኛው ዋሮ ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህ እኔም ታመምኩ፤ ጓደኛዬም ታመመ፡፡ ከዚያ በኋላ ቁፋሮውን ትተን ወደ ትውልድ ቁዬአችን ገባን (ብርሃኑ፣ 15/06/2004፣7፡00/፡፡

ቆፍረው ወርቁን አውጥተው ሽጠው ያገኙትን ብር ለህክምና በማዋላቸው በቂ ገንዘብ ይዘው ወደ ትውልድ ቀዬያቸው አልተመለሱም፡፡ ነገር ግን ከገቡ በኋላ ትንሽ በእጃቸው ላይ በቀረችው ገንዘብ ፍየሎችን ገዙ። እነዚህ ፍየሎች ካረቡ በኋላ ሽጠው፣ ከኦዶ ሻክሶ መልስ ያረሱትንም እህል ጨምረው ሽጠው በሬ በመግዛት ያላቸውን በሬዎች ሁለት አደረሱ፡፡ በሬ ጠምደው አባታቸው ከሰጧቸው ሁለት ማሳ መሬት በተጨማሪ መሬት በኮንትራት በመግዛት በማረስ ኑሯቸውን ማሻሻል ጀመሩ፡፡ አቶ ብርሃኑ አዱኛ በ1996 ዓ.ም ትዳር ያዙ። አሁን ሁለት ሴት ልጆች አባት ናቸው፡፡

አቶ ብርሃኑ አዱኛ በቀበሌው ውስጥ በሰላሳ ሰዎች በተደራጀ ጐጥ ውስጥ ፀሐፊ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡ ለአካባቢው ማህበረሰብ የዕድሮች ፀሐፊ፣ ገንዘብ ያዥ በመሆንም ያገለግላሉ፡፡

አቶ ብርሃኑ አዱኛ ጫወታ እንደሚወዱ ይናገራሉ፡፡ የሚጫወቱት ጨዋታዎች መካከል የዓመት በዓላት ዘፈኖች፣ የስራ ዘፈኖችና ጌረርሳ ይገኙበታል፡፡ በተለይ ጌረርሳን በዓመት በዓላት፣ በአስትርእ ማርያም፣ በጥምቀት፣ በፋሲካ፣ በሰርግና በደቦ ጊዜያት እንደሚጫወቱ ይገልፃሉ፡፡ በጌረርሳው ገጠመኞቻቸውን ሁሉ ይገልፁበታል፡፡

አቶ ብርሃኑ የጌረርሳውን ክዋኔ የተማሩት ከአቶ መኮንን ደሜና ከአቶ ድሪባ ለታ ነው፡፡ አቶ ብርሃኑ የጌረርሳን ክዋኔ እንዴት እንደተማሩ ሲገልፁ፣

> አቶ መኮንን ደሜና አቶ ድርባ ለታ በየድግስ ቤቱ ጌረርሳ ሲከውኑ ብዙ ጊዜ አይቻቸዋለሁ፡፡ ሰዎች በተሰባሰቡበት እየከወኑ ሰዎችን ያስደስታሉ፣ ያዝናናሉም፡፡ ድግሱንም ያደምቁታል፡፡ ሰዎችም በጣም ስለሚወዱዋቸውና ስለሚያከብሩዋቸው ወደ ድግሳቸው ይጠሩዋቸዋል፡፡ እነሱ የሌሉበት ድግስ አይደምቅም ይባላል፡፡ እኔም በጣም ስለምወዳቸውና እነሱ የሚከውት ጌረርሳ በጣም ስለሚያስደስተኝ እነሱን አረአያዬ አድርጌአቸው ለመከተል ወደድኩ፡፡ ስለሆነም ጌረርሳ መከወኑን መለማመድ ጀመርኩ፡፡ ከጥቂት የልምምድ ጊዜያት በኋላ ክዋኔውን ቻልኩ (ብርሃኑ፣ 16/06/2004፣ 7፡00)፡፡

አቶ ብርሃኑ የነዚን የሁለቱን ከያንያን አረአያነት በመከተል በተለያዩ አጋጣሚዎች ጌረርሳ ይከውናሉ፡፡ ማህበረሰቡም በጣም ይቀበላቸዋል፣ አድናቆትም ይቸራቸዋል፡፡ እኔ መረጃ በምሰበስብበት ጊዜ ያየሁት ሁኔታ ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡

### 3.3. የአቶ ቸሩ ድንቁ ህይወት ታሪክ

አቶ ቸሩ ድንቁ በአደአ በርጋ ወረዳ ደኩ ቀርሳ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ጉኑፈታ/Gunnuffataa/ በተባለ ቦታ ተወለዱ፡፡ አባታቸው አቶ ድንቁ ዳሞታ ይባላሉ፡፡ እናታቸው ደግሞ ወ/ሮ ደርቢ ሬባ ናቸው፡፡ የተወለዱበትን ዓ.ም የማያስታውሱ ቢሆንም ዕድሜያቸው 42 ዓመት እንደሆነ ይነግረውኛል፡፡ አቶ ቸሩ ድንቁ ሁለት እህቶች ያላቸው ሲሆን እሳቸው ግን ለወላጆቻቸው ብቸኛ ወንድ ልጅ ናቸው፡፡

አቶ ቸሩ ድንቁ ወላጆቻቸውን ከብት በመጠበቅና ዕድሜያቸው የፈቀደውን የእርሻ ስራ ሲሠሩ ያደጉ ሲሆን ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በ1978 ዓ.ም ኢሉ ዳንሴ

አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመግባት እስከ ሦስተኛ ክፍል ተምረዋል፡፡ ከላይ እንደ ተጠቀሰው አቶ ችሩ ድንቁ ለወላጆቻቸው ብቸኛ ወንድ ልጅ በመሆናቸው ትምህርታቸውን ከሦስተኛ ክፍል በግቷረጥ ወላጆቻቸውን ለመርዳት ወደ ግብርና ለመመለስ ተገደዋል፡፡

በልጅነት ዘመናቸው ወላጆቻቸው ምንም የሌላቸው ደሃ በመሆናቸው ያደጉት በችግር ነበር፡፡ አቶ ችሩ ይህን የአስተዳደግ ሁኔታቸውን ሲገልፁ፡

> ልጅ ሳለሁ እናቴና አባቴ ምንም ሀብት አልነበራቸውም፡፡ በችግር ይኖሩ ነበር፡፡ ከትልቅና ረጅም ጊዜ ልፋት በኋላ አባቴ እህል እየነገደና እያረሰ፣ እናቴም ከእሱ ጋር እህል እየነገደች፣ አረቄም እያወጣች በመሸጥ ትንሽ ንብረት ማፍራት ቻሉ፡፡ ያች ትንሽ ንብረት እየረዳቻቸው አባቴ በሬዎችን መነገድ ጀመረ፡፡ ከዚህ ንግድ በሚያገኘው ትርፍ በሬ፣ ላምና ፍየሎችን ለመግዛት ቻሉ፡፡ የሚነግዱበት ገንዘብ አብዛኛውን በብድር ያገኙ ነበር፡፡ በገዙት በሬዎች እያረሱ፣ ያቺ ላምም እየረባችላቸው ትልቅ ንብረት አፈሩ፡፡ ጥሩ ኑሮም መኖር ጀመሩ፡፡ ከዚያ በፊት ድሆች ነበርን /ቸሩ፣ 15/06/2004/፣4፡00/፡፡



*ፎቶ3. በ15/06/2004 ዓ.ም ለአቶ ችሩ ድንቁ በቤታቸው ቃለ መጠይቅ ሲደረግ*

አቶ ችሩ ድንቁ ትዳር የያዙት በ1987 ዓ.ም ነው፡፡ ትዳር ሲይዙ ምንም ንብረት አልነበራቸውም፡፡ ካገቡ በኋላ ለዘጠኝ ዓመታት ለሰው እያረሱ በሚሰጣቸው ጥቂት

ገንዘብ ቤታቸውን አስተዳድረዋል፡፡ በቡና ቤት ተቀጥረው ሰርተዋል፡፡ የዘይት መጭመቂያ ፋብሪካ ውስጥ በጉልበት ሰራተኝነት ተቀጥረው ለአራት ዓመታት በመስራት ኑሮአቸውን ለማሻሻል ጥረት አድርገዋል፡፡ በምስራቅ ሸዋ ዞን ሞጆ አካባቢ በሰው ቤት ተቀጥረው ጤፍ አጭደው ባገኙት የጉልበት ዋጋ ኑሮአቸውን ለማሸነፍ ሞክረዋል፡፡ በሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ ውስጥ በጉልበት ሰራተኝነት ተቀጥረውም አገልግለዋል፡፡ ከነዚህ ስራዎች ባገኙት ገንዘብ ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ለመለወጥ ችለዋል(ቸሩ፣15/06/2004፣ 4፡00)፡፡

የአቶ ቸሩ እናትና አባት ከ32 ዓመታት በላይ አብረው ከኖሩ በኋላ አባታቸው በ1996 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ፡፡

አቶ ቸሩ አባታቸው ከሞቱ በኋላ የአባታቸውን መሬት በመውረስ አርሰው ኑሮአቸውን በማሻሻላቸው ለእናታቸው አንድ ባለ 42 ቆርቆሮ ቤት በሬጂ ከተማ ሰርተውላቸው እናታቸው በከተማ ይኖራሉ፡፡

አቶ ቸሩ ስድስት ልጆች ያላቸው ሲሆን ሦስቱ ወንዶች ሦስቱ ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡ እነዚህንም ልጆች ትምህርት ቤት አስገብተው በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች እያስተማሩ ይገኛሉ፡፡

አቶ ቸሩ ከልጅነት ዘመናቸው ጀምረው ጨዋታ የሚወዱ ሲሆን በዓመት በዓላት፣ በአስተርዮ ማርያም፣ በጥምቀት፣ በመስቀልና ሰዎች በሚሰበሰቡበት በማንኛውም አጋጣሚዎች ይጫወታሉ። የሚጫወቱት የጫወታ ዓይነቶች የተለያዩ ዘፈኖች፣ ጌረርሳና ሌሎች የሚያዝናኑ ቀልዶች ናቸው፡፡ አቶ ቸሩ በተለይ የውስጣቸውን ስሜቶችና ፍላጎቶች የሚገልፁት በጌረርሳ ነው፡፡ ያሳለፉትን የህይወት ውጣ ወረዶች በጌረርሳ ይገልፃሉ፡፡ የጌረርሳ መከወኑን ልምድ ያገኙት እንደ አቶ ብረሃኑ አጹኛ ሁሉ ከአቶ መኮንን ደሜና ከአቶ ድሪባ ለታ ነው፡፡ አቶ ቸሩ ይህንን ሲገልፁ፣

> አቶ መኮንን ደሜና አቶ ድሪባ ለታ በየድግስ ቤቱና ሰዎች በሚሰባሰቡበት ሌሎች አጋጣሚዎች ጌረርሳ ሲከውኑ ሕዝቡ በደስታና በፍቅር ሲቀበላቸውና ሲያደንቃቸው ሳይ መንፈሳዊ ቅናት ያድርብኝ ነበር፡፡ ምነው እንደነሱ በሆንኩ እያልኩ ነበር፡፡ በኋላ ሳይ እኔም እነሱ የሚያዜሙትን ጌረርሳ እየሸመደድኩ መለማመዱን ቀጠልኩ፡፡ ብዙም ሳልቆይ መከወኑን ቻልኩ (ቸሩ፣15/06/2004፣ 4፡00) ፡፡

አቶ ቸሩ ድንቁ በየድግስ ቤቱ ጌረርሳን እንዲከውኑ ይጋበዛሉ፡፡ ማህበረሰቡም በፍቅርና በአክብሮት ይቀበሏቸዋል፣ ሞራልም ይሰጧቸዋል፡፡

## 3.4. የአቶ ድሪባ ለታ ህይወት ታሪክ

አቶ ድሪባ ለታ ከአቶ ለታ ዶባና ከወ/ሮ ደስታ ደምሴ በአደአ በርጋ ወረዳ ደኩ ቀርሳ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ጐሮ ሻንቤ ጐጥ ውስጥ ኦዶ ጉምቢቹ /Oddoo Gumbichuu/ በተባለ ቦታ ተወለዱ፡፡ አቶ ድርባ ለታ ለወላጃቸው ሁለተኛ ልጅ ናቸው፡፡ ከሳቸው በፊት የነበራቸው ልጅ ስለሞተባቸው ወላጃቸው ለተወሰኑ ዓመታት በእንክብካቤ /በቅንጦት/ ነው ያሳደጓቸው፡፡ ነገር ግን በልጅነት ዘመናቸው የነበረው ስርዓት የዘውድ አገዛዝ በመሆኑ በአካባቢያቸው የነበረው የመሬት ባለቤት አቶ ድሪባንና ወንድማቸውን እንዲላላኩላቸው ያለወላጆቻቸው ፈቃድ ይወስዷቸዋል። ባለመሬቱ ያለልብስ ምግብ ብቻ እየሰጡዋቸው ጉልበታቸውን ያለ ዋጋ ይጠቀሙባቸው ነበር፡፡ ይደበድቧቸውም ነበር፡፡ አቶ ድሪባ ይህንን ሲገልፁ፡

> አንድ ጊዜ የመሬት በለቤቱ ለሰው መልዕክት እንድናገር ይልከኛል፡፡ እኔ በዚያን ጊዜ ልጅ ስለነበርኩ መልዕክቱን መናገሩን ረስቼ ከልጆች ጋር ስጫወት ውዬ ገባሁ፡፡ መልዕክቱን አለማድረሴን በመረዳቱ ባለመሬቱ ሰውነቴ እስኪላላጥ ከገረፈኝ በኋላ አባቴን ይጠራውና ልጆቼ እንዳይላላኩልኝ የምታደረገው አንተ ስለሆንክ ከዚህ ሰዓት ጀምረህ መሬቴን ለቀህ እንዲትሰደድ ብሎ አዘዘው፡፡ አባቴ ቄስና የአካባቢ ሽማግሌዎችን ቢልክበትም ውሳኔውን እንደማይለውጥ ይነግራቸውና አባቴን ከመሬቱ አባረረው። እኔና ወንድሜም ከቤቱ ተባረርን፡፡ ከዚያ በኋላ አባቴ ሌሎች ሰዎች በሰጡት ትንሽ መሬት ላይ ቤት ሰራና እስከ የዘውድ አገዛዝ ውድቀት ድረስ በችግር አሳደገን /ደሪባ፣ 20/06/2004፣ 5፡00/፡፡

የደርግ ስርዓት ስልጣን ሲይዝ የአቶ ድሪባ ለታ ወላጆች መሬት ሲከፋፈል ያገኙና ቀድሞ ወደ ነበረው ቀዬያቸው ወደ ኦዶ ጉምቢቹ ተመለሱ፡፡ በፊት የነበረው የችግር ኑሮ ያልፍና ተደላድለው መኖር ጀመሩ፡፡ በዚህ ጊዜ አቶ ድሪባና ወንድማቸው ትምህርት ቤት ቢገቡም አቶ ድርባ ለታ አንደኛ ክፍል እንኳን ሳያጠናቅቁ ያቋርጡና ቤተሰባቸውን ወደ መርዳት ተመለሱ፡፡



*ፎቶ4. በ20/06/2004 ዓ.ም ለአቶ ድርባ ሊታ ቃለ መጠይቅ ሲደረግ*

አቶ ድሪባ ለታ በ21 ዓመታቸው ትዳር ያዙ፡፡ የትዳር አጋራቸው ከነበረችው ከወ/ሮ ጌጤ ድሪባ ስምንት ልጆችን አፍርተዋል፡፡ ስድስት ወንድ ልጆችና ሁለት ሴት ልጆች አሏቸው፡፡ አቶ ድሪባና ወ/ሮ ጌጤ በትዳር ለ28 ዓመታት ከኖሩ በኋላ ወ/ሮ ጌጤ ድሪባ በ2000 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ፡፡ እንደ ባለቤታቸው የሚንከባከባቸው በማጣታቸው የተነሳ የነበራቸው ንብረት ይመናመንና የአቶ ድሪባ ለታ ልጆች የትውልድ ቀዬአቸውንና አባታቸውን ትተው ወደ ተለያዩ ከተሞች ተሰደዱ፣ ሌሎች ደግሞ በሰው ቤት በእረኛነትና በግብርና ሰራተኛነት ተቀጥረው መኖር ጀመሩ፡፡ አቶ ድሪባም ኑሮአቸው ባለቤታቸው በነበረች ጊዜ እንደነበረው ሳይሆንላቸው ሲቀር ለረጅም ጊዜ የኖሩበትን ቀዬ ትተው ሬጂ በተባለችው ከተማ ገብተው እየኖሩ ይገኛሉ፡፡ ከቀድሞ ባለቤታቸው ሞት በኋላ በ2003 ዓ.ም ሌላ ሚስት አግብተዋል፡፡

አቶ ድሪባ ለታ የሚተዳደሩት በግብርና ሥራ በመሆኑ በእዶ ጉምቢቹ ያላቸውን የእርሻ መሬት ሌሎች ሰዎች አርሰው ምርቱን እኩል ለመካፈል ሰጥተው እያሳረሱ ይገኛሉ፡፡ ሰፊ የአትክልት ቦታም ስላላቸው ቀይ ሽንኩርት፣ ቀይ ሥር፣ ቲማቲም፣ ጥቅል ጎመን፣ ቃሪያና ሌሎች የጓሮ አትክልቶች እያለሙ ይገኛሉ፡፡ እነዚህን አትክልቶች እያለሙ ያሉት በጉልበታቸው በመቆፈር ነው፡፡ ምንም የቀንድ ከብትም ሆነ የጋማ ከብቶች የላቸውም፡፡ በተጨማሪም ባለቤታቸው አረቄ እየነገዱ ኑሮአቸውን ይደጉማሉ፡፡

አቶ ድሪባ ለታ ዘፈን የሚወዱ ሲሆን ማንኛውንም ሥራ ሲሠሩ የሥራ ዘፈን፣ በዓመት በዓላት ደግሞ የበዓል ዘፈኖችን ይዘፍናሉ፡፡ ዘፈን ካለበት ቦታ የማይጠፉ ሲሆን ሰዎች ባይኖሩም ብቻቸውን ሆኖ የመዝፈንም ልምድ አላቸው፡፡ ጌረርሳንም በየአጋጣሚው እንደሚከውኑ ያስረዳሉ፡፡ ነገር ግን ሰዎች በሚሰባሰቡበት አጋጣሚዎች በዓመት በዓላት፣ በሰርግ፣ በደቦና በሌሎች ጊዜያት እንጂ ብቻቸውን ሆኖ አይከውኑም፡፡ "ጌረርሳን ከሰው ጋር ካልሆነ በስተቀር መከወን አመቺ አይደለም፡፡ በጌረርሳ ቁም ነገር ነው የሚገለፀው፡፡ ስለዚህ አድማጭ ያስፈልጋል" ይላሉ፡፡ አቶ ድሪባ ጌረርሳን ከልጅነታቸው ጊዜ ጀምሮ ይከውኑ ስለነበርና ጌረርሳን ለረጅም ዓመታት ሲከውኑ ስለቆዩ ልምዱን ከማን እንዳገኙ አያስታውሱትም /ድሪባ፣ 20/06/2004፣5፡00/፡፡ ነገር ግን ጌረርሳንና ሌሎች ዘፈኖችን ፈጥሮ በመከወን የሚተካከላቸው እንደሌሌና ባገኙት አጋጣሚ አዳዲስ ዘፈኖችንና ጌረርሳን በመፍጣር የተለያዩ አጋጣሚዎችን በመግለፅ ኀበዝ እንደሆኑ በ21/06/2004 ዓ.ም የተቀሩት አራቱ መረጃ ሰጪዎቹ አጫውተውኛል (አባተ፣ ብርሃኑ፣ ቾሩ፣ መኮንን፣ 21/06/2004፣ 5፡00)፡፡

አቶ ድሪበ ለታ በግምት የ55 ዓመት የዕድሜ ባለፀጋ መሆናቸውን ቢነግሩኝም የተወለዱበትን ዘመን /ዓ.ም/ አያውቁትም።

### 3.5. የአቶ መኰንን ደሜ ህይወት ታሪክ

አቶ መኰንን ደሜ ከአባታቸው ከአቶ ደሜ ጋዲሳና ከእናታቸው ከወ/ሮ ደሲ ድሮ ተወለዱ፡፡ የትውልድ ቦታቸው አደኣ በርጋ ወረዳ ደኩ ቀርሣ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ቀርሳ /Qarsaa/ በተባለ ቦታ ነው፡፡ አቶ መኰንን ደሜ ዕድሜያቸው 61 ዓመት እንደሆነ ቢናገሩኝም የተወለዱበትን ዓመተ ምህረት /የትውልድ ዘመናቸውን/ አያውቁትም፡፡ አቶ መኰንን ለወላጆቻቸው ሦስተኛ ልጅ ቢሆኑም ቃላቅ ወንድማቸው አቶ ጉንፋ ደሜ በደርግ ዘመነ መንግስት ዘምተው በጦር ሜዳ የተሰው ሲሆን ታናሻቸው አቶ አመንቴ ደሜ ደግሞ በዚሁ ቀበሌ እያሉ በህመም ምክንያት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ አቶ መኰንን ደሜ አሁን አንድ ወንድም ብቻ አላቸው፡፡



*ፎቶ5. በ18/06/2004 ዓ.ም ለአቶ መኮንን ደሜ በቤታቸው ቃለ መጠይቅ ሲደረግ*

አቶ መኩንን ደሜ በልጅነት ዘመናቸው በጥሩ እንክብካቤ አላደጉም፡፡ እስተዳደጋቸውን ሲገልፁ፡

> እኔ ስወለድ የነበረው ስርዓት የዘውድ አገዛዝ ነበር፡፡ አባቴ በትውልድ ቦታችን /ቀርሳ በተባለው ቦታ/ መሬት ገዝቶ ይኖር ነበር፡፡ በወቅቱ በቦታው የነበረው ባለሃብት አባቴ የገዛውን መሬት ተምቶት እንዲሰደድ አደረገው፡፡ አባቴም እኔንና ወንድሞቼን ይዞ ወደ እናቴ ወላጆች ቤት ገባ፡፡ እኔም እስከ 12 ዓመቴ ድረስ እዚያው "አቤቶ" በተባለ ቦታ በእናቴ ወላጆች ቤት አደኩ፡፡ ነገር ግን የእናቴ ወላጆች እንደኔ ወላጆች ድሆች ስለነበሩ ከዚህ በላይ ሊያስጠጉኝ አልቻሉም፡፡ ከዚያ በኋላ አባቴ ለአንድ ባለሃብት ሰጥቶኝ ምግብ ብቻ እየሰጡኝ እየተላላኩላቸው፣ ከዚያም አልፎ ከብት እያገድኩላቸው፣ እያረስኩላቸውና የማገዶ እንጨት እየለቀምኩላቸው አደኩ፡፡ እኔ ስራ ስለማልንቅ ወተት እንኳን እንጥላቸው ነበር፡፡ ልብስና ጫማ አልነበረኝም፡፡ የተቀዳደደ ልብስ ለብሼ ምንም ደመወዝ ሳይሰጡኝ በነፃ ለሰባት ዓመት አገለገልኳቸው፡፡ ይገርፉኝ፣ ያሰቃዩኝም ነበር /መኩንን፡18/06/2004፡3፡45/፡፡

አቶ መኩንን ደሜ በ19 ዓመታቸው ከሰው ቤት ወጥተው ወደ ወላጆቻቸው ቤት ተመለሱ፡፡ ወላጆቻቸውን በተለያዩ የግብርና ስራዎች ሲረዱዋቸው ከቆዩ በኋላ በ25 ዓመታቸው ትዳር ያዙ፡፡ ትዳር ሲይዙ ምንም ንብረት አልነበራቸውም፡ ከዚያ በኋላ ከባለቤታቸው ጋር በርትተው በመስራት ከአባቻቸው የተሰጣቸውን መሬት በሬ ከጎደኞቻቸው በመለመንና የአባቻቸውን በሬዎች በመጠቀም በማረስ መኖር ጀመሩ፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ አብዮት በመፈንዳቱ /የደርግ መንግስት የዘውድ

አገዛዝን ገርስሶ ስልጣን በመያዙ/ ጐዋ ከተባለ ቦታ መሬት ማግኘት ቻሉ፡፡ ያገኙትን መሬት በማረስ የተለያዩ የእህል ዘሮችን በመዝራትና አትክልት በመትከል፣ ባለቤታቸው ደግሞ አረቄ እያወጡና እየነገዱ ራሳቸውን ቻሉ፡፡

አቶ መኰንን ደሜ የዘውድ አገዛዝ እንደወደቀ በደርግ ዘመነ መንግስት የመሬት ኮሚቴ ሆኖ በመመረጥ መሬት ከባለሃብቶች እየተቀበሉ መሬት ለሌላቸው ለደሃ ገበሬዎች በማደል ሰርተዋል፡፡ በኢ.ሕ.ዴ.ግ ዘመነ መንግስት በቀበሌ ውስጥ ተመርጠው "ሸንጐ" በመሆን ለአምስት ዓመት አገልግለዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ የሀገር ሽማግሌ በመሆን የተጣላውን በማስታረቅና ማህበረሰቡ በሰላም አብሮ እንዲኖር በመምከር ላይ ይገኛሉ፡፡ ከማህበረሰቡ ጋር ማህበራዊ ጉዳዮች ላይም በስፋት እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡

አቶ መኰንን ደሜ የአሥር ልጆች አባት ናቸው፡፡ ትዳር ከያዙም 38 ዓመት ሆኗቸዋል፡፡

አቶ መኰንን ከጓደኞቻቸው ጋር ጌረርሳን መከወን ይወዳሉ፡፡ ይህን ሲናገሩ፣

> ጌረርሳ መጫወት በጣም ያስደስተኛል፡፡ እኔን ከሚመስሉ ጓደኞቼ ጋር እጫወታለሁ፡፡ የውስጤን /ሀሳቤን/ የሚገልፅልኝ ጌረርሳ ነው፡፡ ጌረርሳውን የምጫወተው በማንኛውም ቀን ሳይሆን በዓመት በዓላትና ሰዎች ተሰብስበው በሚጫወቱበት ጊዜ ነው፡፡ ስለራሴ ህይወት፣ ስለሀገር፣ ስለሌሎች ሰዎችም እያነሳሁ እጫወታለሁ /መኰንን፣ 18/06/2004፣4፡00/፡፡

አቶ መኮንን ደሜ ጌረርሳ መከወኑን የተማሩት ከአባታቸው ነው፡፡ አባታቸው አቶ ደሜ ጋዲሳ ድሮ ጌረርሳን በመከወን የሚተካከላቸው በአከባቢው አልነበረም፡፡ በየድግሱና ሰዎች በሚሰባሰቡበት ቦታ ሁሉ ጌረርሳን በመከወን የሚቀድማቸው የለም (መኮንን፣ 18/06/2004፣ 4፡00) ፡፡

## ምዕራፍ አራት

## 4. መረጃ ሰጪዎች የከወኑት ጌረርሳ ላይ የተደረገ የይዘት ትንተና

በዚህ ምዕራፍ አምስቱ መረጃ ሰጪዎቹ የከወኑት ጌረርሳ የቀረበ ሲሆን ያቀረቡት ጌረርሳ ምን ያህል ከህይወታቸው ጋር እንደሚሰምር ከህይወት ታሪካቸው ጋር በማገናዘብ ትንተና ተደርጓል፡፡ መረጃ ሰጪዎች በምን አጋጣሚ፣ የትና መቼ ጌረርሳውን እንደከወኑና የተከወነው ጌረርሳ ይዘት በከዋኞቹ ስም ርዕስ ተሰጥቷቸው እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 4.1. አቶ አባተ ኤጀርሳ የከወኑት ጌረርሳ ላይ የተደረገ ትንተና

በ19/06/2004 ዓ.ም ጠዋት በሁለት ሰዓት ተኩል (2:30) ወደ አቶ አባተ ቤት አቀናሁ፡፡ የአቶ አባተ ቤት የሚገኘው በደኩ ቀርሳ ቀበሌ ገበሬ ማህበር እንኔ ሰሪቲ በተባለ ቦታ ነው፡፡ ወደ አቶ አባተ ቤት ስቃረብ የዘፈን ድምፅ ተሰማኝ፡፡ ወደዚያ የሄድኩት ከመንገድ መሪዬ ከአቶ ሥዩም አዱኛ ጋር በመሆኑ እየዘፈኑ ያሉት አቶ አባተ ኤጀርሳ መሆናቸውን የነገሩኝ እሳቸው ናቸው፡፡ የአቶ አባተን በር በማንኳኳት ወደ ግቢያቸው እንደገባን አቶ አባተ በግቢያቸው ውስጥ በሚገኘው ድንጋይ ላይ ቁጭ ብለው ጌረርሳ ሲከውኑ አየን፡፡ በግቢያቸው ከእሳቸው ውጪ ማንም አልነበረም፡፡ ባለቤታቸው እቤት ውስጥ ናቸው፡፡ ግቢ ውስጥ እንደገባን ከአቶ አባተ ጋር ተዋወኩና ወደ ቤታቸው የመጣሁበትን ዓላማ ካስረዳኋቸው በኋላ ሲከውኑት የነበረውን ጌረርሳ ደግሞ እንዲከውኑልኝ ጠየኩዋቸው። ጌረርሳውን ከከወኑልኝ በኋላ ምን አነሳስቷቸው ሲከውኑ እንደነበር ጠየኩዋቸው፡፡ እሳቸውም፡

> አሁን በመንግስት የተነደፊው የልማት ስራ እየተሠራ ይገኛል፡፡ እኔ ግን ደሃ ስለሆንኩና ለሰው ጉልበቴን ሸጬ ሠርቼ በማገኘው ገቢ ስለምተዳደር በ18/06/2004 ዓ.ም የሚበላ ነገር በቤት ውስጥ ስላልነበረኝ ለሰው ሠርቼ ከዚያ በማገኘው የጉልበቴ ዋጋ እህል ሸምቼ ቤተሰቤን ለማስተዳደር ከልማት ሥራ ቀረሁ፡፡ ነገር ግን የጐጣችን ሃላፊዎች ከልማት ስራ በመቅረትህ 30 ብር ቅጣት ጥለንብሃል አሉኝ፡፡ እኔ ከልማት ሥራው ቀርቼ ትላንት ሰርቼ ያገኘሁት 20 ብር ብቻ ነበር፡፡ እሱንም ተጠቅሜበታለሁ፡፡ ዛሬ ግን ምንም በቤቴ ውስጥ ባይኖርም የግድ ወደ ልማት ሥራው መሄድ ይኖርብኛል፡፡ ካልሆነ ቅጣቱ ስልሳ /60/ ብር ይሆንብኛል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የምከፍለው አይኖረኝም፡፡ ከባለቤቴ ጋር ስለነገሩ ከተነጋገርን በኋላ ምንም አታስቢ ጐመንም ቢሆን በልተን ይህን ችግር እናሳልፋለን ብዬአት አበረታትቼአት ወደዚህ ወደ ደጅ ወጥቼ ጌረርሳውን መከወን

ጀመርኩ፡፡ ይህን ያደረኩት ሀዘኔን ለመርሳትና ለዚህ ችግር የዳረገኝን ያሳለፍኩትን ገጠመኞቼን እያስታወስኩ ነበር (አባተ፣ 19/06/2004፣2፡30)፡፡

አቶ አባተ በ19/06/2004 ዓ.ም የከወኑትን ጌረርሳ እንደገና በ21/06/2004 ዓ.ም በአቶ አዱኛ ጅማ ቤት ከውነውልኛል፡፡ የአቶ አዱኛ ጅማ ባለቤት ወ/ሮ ጥሩነሽ ኪዳኔ በ21/06/2004 ዓ.ም በቅድስት ድንግል ማርያም ስም የሚጠጡ የፅዋ ማህበር ነበራቸው፡፡ ማህበሩ ደርሶዋቸው ስለነበር በዕለቱ በቤታቸው ድግስ ነበር፡፡ በደኩ ቀርሳ ቀበሌ አይሉ በተባለ ቦታ በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ማህበርተኞች ተሰብስበዋል፡፡ በወቅቱ በቤቱ ውስጥ የነበሩት ሰዎች በቁጥር 30 ናቸው፡፡ ከነዚህም መካከል 19ኙ ሴቶች ናቸው፡፡ ሌሎች 11ዱ ደግሞ ወንዶች ናቸው፡፡ የተሰባሰቡት ሰዎች ዕድሜያቸው ከ25-65 ዓመት ውስጥ የሚገኙ ይመስላሉ፡፡ ማህበርተኞቹ የተሰበሰቡት ከ4፡00 /አራት ሰዓት/ ጀምሮ ነው፡፡ ማህበርተኞቹ በልተው ጠጥተው ካጠናቀቁና የተሰባሰቡበትን ጉዳይ ከጨረሱ በኋላ በስድስት ሰዓት (6፡00) ወጣቶቹ መዝፈንና ጌረርሳ መከወን ጀመሩ፡፡ እነዚህ ወጣቶች ጌረርሳ እየከወኑ እያለ ከማህበርተኞቹ አባላት መካከል የሆኑ በእድሜ ከፍ ያሉ ሰዎች የመረጃ ሰጪዎቼን ስም እየጠሩ ጌረርሳ እንዲከውኑ መጋበዝ ጀመሩ፡፡ እነዚህ ታዳሚያንና ከዋኞች ማህበራዊና ግለሰባዊ የሆኑ ጉዳዮችን እያነሱ መረጃ ሰጪዎቼን በማነቃቃትና በማበረታታት ጌረርሳ እንዲከውኑ አነሳስቷቸዋል፡፡ ይህን ያደረጉት ከመረጃ ሰጪዎቼ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮችን በማንሳት ነው፡፡ በተለይ አቶ አባተ ወንጀል በመስራታቸው ያገኛቸውን መንገላታትና ንብረት ማጣት በማንሳት አቶ አባተን ጌረርሳ እንዲከውኑ አድርጓቸዋል፡፡ በወቅቱ አምስቱ መረጃ ሰጭዎቼ በቦታው ስለነበሩ ሁሉም ጌረርሳን ከውነዋል፡፡ ከመረጃ ሰጪዎቼ መካከል ቀድሞ ክዋኔውን የጀመሩት ግን አቶ አባተ ኤጀርሳ ናቸው፡፡ በዕለቱ የጌረርሳና የዘፈን ክዋኔው እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ተኩል (11፡30) ድረስ የቆየ በመሆኑ በዚህ ጊዜ ነበር መረጃ ሰጪው በ19/06/2004 ዓ.ም የከወኑልኝ ጌረርሳ በድጋሚ የከወኑት፡፡ አቶ አባተ በነዚህ በሁለቱ ቀናት የከወኑት ጌረርሳ፣ መነሳሻ ምክንያቶቹና ይዘቶቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

4.1.1. በሰው ላይ ጉዳት አድርሰው ስለ መታሰር

የአቶ አባተ ወንድም አቶ ግርማ ኤጀርሳ ከ1985-1990 ዓ.ም በአካባቢያቸው በሚገኘው የኢሉ ደንሴ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዘበኛ ነበሩ፡፡ በ1990 ዓ.ም በአካባቢው አጠራር በተለምዶ በቅደሚ ሽር /የፋስካ ፍች ነገ ነው ሲባል/ የአካባቢው ሰዎች በጐች ኢሉን ደንሴ ትምህርት ቤት ግቢ ይገቡና በግቢ ውስጥ የነበረውን ችግኞች ያወድማሉ፡፡ በዚህ ጊዜ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር አቶ በለጠ ነጋሳ ይደርሱና አቶ ግርማን "ለምን የትምህርት ቤቱን ንብረት በጐቹ እንዲያወድሙ ታደርጋለህ" በማለት ተቆጡት፡፡ ቁጣው ወደ ጥል ተሸጋግሮ መደባደብ ጀመሩ። በወቅቱ አቶ አባተና ስድስት ወንድሞቻቸው ይደርሱና ለአቶ ግርማ በመደረብ በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ላይ ከፍተኛ የአካል ጉዳት ያደርሳሉ፡፡ ነገር ግን የአካባቢው ሰዎች ደርሰው በማስጣላቸው የመምህሩ ህይወት ይተርፋል፡፡ መምህሩም ጉዳት አድራሾቹን ከሰው አስፈረዱባቸውና ስምንቱም ወንድማማቾች ለሰባት ዓመታት /ከ1990 -1996 ዓ.ም/ አምቦ ማረሚያ ቤት ቆዩ፡፡

ይህ እስራት መነሻው የወንድማቸው የአቶ ግርማ ኤጀርሳ ከመምህሩ ጋር መጣላት በመሆኑ አቶ አባተ አጋጣሚውንና ለእስራት እንዴት እንደተያዙ እንደሚከተለው ጌረርሳን በመከወን ገልፀዋል፡፡

| | |
|---|---|
| Motobisi yaa bulee | አውቶብስ ግርጫው |
| Balaan kee na hinhanqatu | ያንተ ደፋ ደረሰኝና |
| Amma yaa Girmaa Ejoo | አንተ ግርማ ኤጀርሳ |
| Mana hidhaatan bulee | እስር ቤት አደርኩኝ |
| Waaqatu na baase ulee. | ከዱላ እግዚአብሔር አወጣኝ፡፡ |
| Boombiin mataan hidhaadhaa | የቦንብ አናቱ ታስሯል |
| Giddiitu manaa na baasee | ግዳጅ ከቤት አወጣኝ |
| Akka sangaa didaadhaa. | እንደ አበያ ሰንጋ፡፡ |

በማለት በወንድማቸው በአቶ ግርማ ኤጀርሳ ምክንያት /መነሻነት/ ወንጀል መፈፀማቸውንና እስር ቤት መግባታቸውን ገልፀዋል፡፡ ለእስራቱ ከቤት የወጡት በግድ መሆኑን "ከአበያ ሰንጋ" ጋር በመነፃፀር አሳይተዋል፡፡ ያልተገራ ሰንጋ ወደ እርሻ ወይም ወደ ገበያም የሚወሰደው በግድ በገመድ ታስሮ በመሆኑ ለእስር ከቤት የወጡት በግድ በፖሊስ ተይዘው መሆኑን በንፅፅር አመላክተዋል፡፡

እኚህ መረጃ ሰጪ በግድ ተይዘው ወደ እስራት በሚወሰዱበት ጊዜ በመንገድ ላይ እያሉ የተሰማቸውን ስሜትና ያጋጠማቸውን በጌረርሳ ሲያቀርቡ፡

| | |
|---|---|
| Hoggan Bargoo darbuu | በርጐን በማልፍበት ጊዜ፣ |
| Garaa furnoo bitadhee | ለሆዴ ፉርኖ /ዳቦ/ ገዝቼ |
| Gara funyoon hidhadhee | ወገቤን ጠበቅ አድርጌ፡፡ |
| Makiinaan ija qabaaree | መኪና ዓይን አለው ወይ |
| Shufeeriitu oofa malee | ሹፌሩ ይነደዋል እንጂ |
| Abuun kee mala qabaaree | አባተ ምን መላ አለው |
| Giddiitu oofa malee. | ግዳጅ ይነደዋል እንጂ፡፡ |
| Makiinaadha jedhanii | መኪና ነው አሉ |
| Kotteesaa gommaa godhee | እግሩን ጐማ አደርጐ |
| Garaasaa gongaa godhee | ሆዱን ሰፊ አድርጐ |
| Fuudhee biyyaa nabaase. | ከሀገር አወጣኝ ይዞ፡፡ |
| Raase kaa raase raasee | ነቀነቀ እንጂ ነቀነቀ |
| Shufeeriin marii raasee | ሹፌር መሪውን |
| Gommaan simintoo raasee | ጐማ አስፋልቱን |
| Gommaan gombisa hinqabu | ጐማ ከልካይ የለውም |
| Akkam goota yaa Abee | እንዴት ትሆናለህ አባተ |
| Garaan Luugama hinqabu | ሆድ ሉጋም የለውም |
| Akkam goota yaa qoonqoo | ሆዴ ምን ትሆናለህ |
| Qoonqootti akka abbaan godhe | ሆድ ባለቤቱ እንዳደረገው |
| Namseet akka waaq godhe. | ነፍስ እግዚአብሔር እንዳደረገው፡፡ |

አቶ አባተ ከላይ የተመለከተውን ወንጀል በመሥራታቸው በፖሊስ ተይዘዋል፡፡ ከፍተኛ ወንጀል በመሥራታቸው ከፍተኛ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው ገምተዋል፡፡ ለእስራት ተይዘው ከቤት ሲወጡ የመጀመሪያቸው ነው፡፡ ከዚህ በፊት እስር ቤትን አይተውት አያውቁም፡፡ ስለዚህ ወደ እስር ቤት በመኪና በሚጓዙበት ጊዜ ተጨንቀዋል፡፡ በተለይ በርጋ የተባለ ቦታ ሲደርሱ ከቤታቸው ርቀው የመታሰራቸው ጉዳይ የተረጋገጠ መሆኑን ተገነዘቡ፡፡ በርጋ የተባለው ቦታ የሚገኘው ከወረዳው ዋና ከተማ ከእንጭኒ ከአምስት እስከ እስር ኪሎ ሜትር በግምት አለፍ ብሎ ወደ ሆለታ ከተማ መሄጃ መንገድ ላይ ነው፡፡ ከእንጭኒ ከተማ እንዳለፉ አቶ አባተ ከዚህ

እስራት የሚያስጥላቸው ምንም አካል እንደሌሌ አውቁ፡፡ ይህን ደግሞ ጭንቀታቸውንና ፍራታቸውን አባሰባቸው (አባተ፣ 19/06/2004፣2፡30)፡፡ አቶ አባተ የጭንቀታቸውን ክብደት ለማስረዳት "ሆዴን በገመድ አስሬ" ብለዋል፡፡ ጉዞውም በመኪና መደረጉን ደግሞ "መኪና ነው አሉ፣ እግሩን ጐማ አድርጐ፣ ሆዱን ሰፊ አድርጐ፣ ከሀገር አወጣኝ ይዞ" በማለት ገልፀዋል፡፡ እኚህ ከዋኝ ስንቅ እንዲሆናቸው ዳቦ መግዛታቸውን፣ ስለሚበሉት ምግብ ማሰባቸውን ያመለክታል፡፡ ረሃብ እንኳን እንደምንም የሚችሉ ቢሆንም ስለ ነፍሳቸው ተጨንቀው ለእግዚአብሔር አደራ መስጠታቸውን ጌረርሳው ያስገነዝበናል፡፡

አቶ አባተ እስር ቤት ከገቡ በኋላ የእስር ቤቱን ሁኔታ፣ በውስጡ ያሉ ሰዎች ቁጥር ምን ያህል ብዙ እንደሆኑና በእስር ቤቱ ውስጥ የሚጠብቁዋቸው ሰዎች ምን እንደሚፈፅሙባቸው በጌረርሳ ገልጸዋል፡፡ ይህን ደግሞ፣

| | |
|---|---|
| Karchalleedha jedhanii | ከርቸሌ ይሉታል |
| Keessi isaa akka bool'atii | ውስጡ እንደ ጉድጓድ ነው |
| Namni isaa akka dagoondaatii. | ሰው እንደ ጉንዳን ነው፡፡ |
| Galgala gibuu jedhuu | ማታ ግቡ ይላሉ |
| Ganama wuxuu jedhuu | ጠዋት ውጡ ይላሉ |
| Rakkannee biyyaa baanee | ተቸግረን ከሀገር ወጣን |
| Akka waan harree taanee | እንደ አህያ ሆንን |
| Korokochaatti dhumnee. | በእስራት አለቅን በማለት |

ከውነዋል፡፡

በዚህ ከላይ በተመላከተው ጌረርሳ የእስር ቤቱን ሁኔታና ይዘት አስረድተዋል፡፡ እስር ቤቱ ውስጥ ከመሬት በታች እስር ቤት መኖሩን "ውስጡ እንደ ጉድጓድ ነው" በማለት አመላክተዋል፡፡ በተጨማሪም እስር ቤትና መቃብር ተመሳስለዋል፡፡ እስር ቤት የገባ ሰው እንደፈለገ ወጥቶ መግባት አይችልም፡፡ እንቅስቃሴው በእስር ቤት ግቢ ውስጥ ተገድቧል፡፡ በሌላ በኩል በእስር ቤት ብዙ ሰዎች ተፋፍገ የሚኖርበት በመሆኑ በየጊዜው በሽታ ይዛመታል፡፡ እስረኞች በየጊዜው ይሞታሉ፡፡ ይህ በመሆኑ እስር ቤት ከመቃብር ጋር ተመሳስሏል፡፡ እስረኛውም በሞተ ሰው ትይዩ ሆኖ ተገልጿል፡፡ በእስር ቤት ውስጥ ያሉ ሰዎች ብዛት ደግሞ "ከጉንዳን" ጋር

በማመሳሰል እንደ ጉዳንዳን እንደሚርመሰመሱ ለማሳየት ከዋኙ ተነፃፃሪ ዘይቤ ተጠቅመዋል፡፡

የእስር ቤቱ ጥበቃዎችም ጠዋት "ውጡ" ማታ ደግሞ "ግቡ" በማለት እንደሚያስቃዩዋቸው፣ እስራታቸውን ደግሞ ከአህያ እስራት ጋር በማነፃፀር /በማወዳደር/ ዘይቤያዊ በሆነ መልኩ እንደ እንስሳ እንደሚታዩ፣ በወቅቱ በእስር ቤቱ ውስጥ ሰብአዊነት የጐደለ አያያዝ እንዳለ አሳይተዋል፡፡

በመቀጠል አቶ አባት ወንጀል መስራት ሰውን ለከፋ ቅጣትና ውርደት እንደሚዳርግ

| | |
|---|---|
| Sanbata qotii laalii | በሰንበት እረሰና እይ |
| Waan cabbiin lafa godhuu | በረዶ መሬትን ምን እንደሚያደርግ |
| Wanjala godhii ilaalii | ወንጀል ሰርተህ እይ |
| Waan higgiin nama godhuu. | ህግ ምን እንደሚያደርግ፡፡ |
| Geeshee yoon mure maalii | ጌሽን ብቆርጥ ምን አለበት |
| Geesheen muka caakkaatii | ጌሽ የጫካ እንጨት ነው |
| Karchallee yoon bu'e maalii | ከርቸሌ ብወርድ ምን አለበት |
| Karchalleen biyya daanyaatii. | ከርቸሌ የዳኛ /ህግ/ ሀገርነው፡፡ |
| Ilmi abbaan qomaaxaa | አባቱ የቆመጠ |
| Na kabalee kophaasa. | ተማታኝ ለብቻ በማለት |

ገልጸዋል፡፡

እኒህ መረጃ ሰጪ የሚኖሩበት አካባቢ ያሉ ማህበረሰቦች ሰንበትን ያከብራሉ፡፡ ሰንበትን እንደ እረፍት ቀናቸው አይተው ለማረፍ ሳይሆን ሰንበት ከሠሩ እግዚአብሔር ስለሚቆጣ የዘሩትን እህል በበረዶ ያጠፋል፡፡ በሰንበት የሠሩትን ሰዎች ለረሃብ ያጋልጣል፡፡ ሰንበት የተከበረ ቀን በመሆኑ በሰንበት ቀን መስራት ሀጥያት ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው (አባተ፣ 19/06/2004፡2፡30)፡፡ እንግዲህ በሰንበት የተሠራ ሥራ እግዚአብሔርን አስቆጥቶ ቅጣት እንደሚያመጣ ሁሉ ወንጀልም ከፍተኛ ቅጣት ያመጣል፡፡ ስለዚህ ማንኛውም ሰው በተቻለው አቅም ወንጀል ከመስራት መቆጠብ እንዳለበት ሲሉ ይመክራሉ፡፡ ወንጀል መሥራት ቅጣት እንደሚያመጣና የሰውን ኑሮ እንደሚያበላሽ ከበረዶ እህልን ማውደም ጋር እያወዳደሩ አቅርበዋል፡፡ ሰንበት ከተሠራ እግዚአብሔር ተቆጥቶ በረዶ በመዝነብ እህልን አጥፍቶ የሰው ልጅን በረሃብ እንደሚፈጅ ሁሉ ወንጀል መሥራት ከፍተኛ

ቅጣት ወይንም ውርደት ያመጣል። ምክንየቱም የሳቸው ኑሮ እንዳልነበረ እንዲሆን ያደረገው ወንጀል በመሥራታቸው ነው፡፡ ወንጀልን ባይሠሩ ኖሮ ይህ አስከፊ ኑሮ አይገጥማቸውም ነበር፡፡

በተጨማሪም በእስር ቤት የታናቀ ሰው እንኳን በሰው ላይ እንደምስለጥን

| | |
|---|---|
| "Ilmi abbaan qomaaxaa | አባቱ የቆመጠ |
| Na kabala kophaasaa | ተማታኝ ለብቻ" በማለት አቅርበዋል፡፡ |

የስጋ ደዌ በሽታ ያለባቸውና በሽታው በአካላቸው ለይ ጉዳት ያደረሰባቸው ሰዎች ይህ ጥናት በተካሄደበት አከባቢ ከሌሎች ጋር አይጋቡም፡፡ በማኅበራሰቡ በሽታው በእግዝአብሔር ቁጣ የሚመጣ ተብሎ ይታመናል፡፡ በበሽታው የተያዙ ወይንም የሚያዙ ሰዎች እግዝአብሔር የተቆጣቸው ናቸው፡፡ በሽታው በዘርም ይተላለፋል ተብሎ ይታመናል፡፡ አሁን ማህበረሰቡ ስለበሽታው ያለው ግንዛቤ በመጠኑ ቢለወጥም በሽታው በዘር ይተላለፋል የሚል እምነት ግን ከማህበረሰቡ ሙሉ በሙሉ አልጠፋም፡፡ ስለዚህ በሽታው ያለባቸው ሰዎች ይናቃሉ፣ ከማህበረሰቡም ይገለላሉ (አባተ 21/06/2004፣ መኮንን 21/06/2004፣ ድርባ 21/06/2004)፡፡ ከዚህ ጌረርሳም እንደምንረዳው የተናቀ ሰው (ቆማጣ) ራሱ ተጫወተብኝ፣ በጥፊ መታኝ እያለ በእስር ቤት የቱን ያህል የሰው ነፃነት እንደሚረገጥ ያስረዳሉ፡፡

በእስር ቤት ሞትም አለ፡፡ ይህ መረጃ ሰጪው በእስር ቤት ለሰባት ዓመታት በመቆየታቸው እስረኞች እየሞቱ እሬሳቸው ሲወጣ ሲመለከቱ ስለነበር የሰው ነፍስ በማንኛውም ጊዜ /አጋጣሚ/ እንደምታልፍ፣

| | |
|---|---|
| Malkaan baaruu dildilaa | የባሩ ወንዝ ድልድይ አለው |
| Gaafa guutu hinbeekanii | መቼ እንደሚሞላ አይታወቅም |
| Nafseen dhiiraa billisaa | የሰው ነፍስ እንደጥንቸልናት |
| Gaafa duutu hin beekanii. | መቼ እንደምትሞት አይታወቅም |

በማለት ገልጸዋል፡፡

ጥንቸል በሣሮችና ቁጥቋጦ ውስጥ የሚትኖር እንሰሳ ናት፡፡ ይቺህ እንስሳ ባእድ ነገር ሲያጋጥማት በፍጥነት እየሮጠች ለማምለጥ ትሞክራለች፡፡ ነገር ግን የሚያባርራት እንሰሳ ይከተላት አይከተላት ሳታረጋግጥ ስለምትሮጥ ራስዋን ለባሰ አደጋ ታጋልጣለች፡፡ እየሮጠች ሜዳ ላይ ስለሚትወጣ በውሾች ተይዛ ትበላለች፡፡

ወይንም ልጆች አባረው ይዘው ይገድሏታል፡፡ በአንፃሩ የሰው ልጅ አስተውሎ አይቶ ራሱን ወንጀል ከመሥራት ካልቆጠበ ሊታሰር ይችላል፡፡ በእስር ቤት ውስጥ ደግሞ በበሽታ ሊያዝ ይችላል፡፡ ስለዚህ እንደጥንቸል በማንኛውም ሰዓት ሊሞት ይችላል፡፡ መረጃ ሰጪው በእስር ቤቱ እያሉ በማንኛውም ጊዜ ሊሞቱ እንደሚችሉ እያሰቡ እንደነበር ጌረርሳውና እሳቸው 19/06/2004 ዓ.ም የሰጡኝ ቃለ ምልልስ ያመለክታል።

### 4.1.2. በእስራቱ የተነሳ ስለንብረታቸው በወጪ ማለቅ

የአቶ አባተ እስራት ለረጅም ጊዜ የቆየ በመሆኑና ከእስራቱ በኋላ ለብዙ ዓመታት ፍርድ ቤት ስላመላለሳቸው ንብረታቸው ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል፡፡ አቶ አባተ እንደገለፁት እስራቱና ወደ ፍርድ ቤት መመላለሱ የነበራቸውን አንድ ጥማድ በሬ፣ ስምንት በጐች፣ ላምና የተከሉዋቸውን ባህር ዛፎች እንዲሸጡ አስገድዷቸዋል፡፡ አሁን ያላቸው ንብረት አንድ በሬ፣ አንዲት በግ፣ ትንሽዬ መኖሪያ ሳር ቤትና አንዲት ማሳ ብቻ ናቸው፡፡ ይህ ሁኔታ አቶ አባተ በርካሽ ዋጋ ጉልበታቸውን ሸጠው ሠርተው በሚያገኙት ገቢ ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሮ እንዲኖሩ አድርጓቸዋል፡፡ ለሰዎች እየተላላኩ እንዲኖሩ፣ ባለቤታቸው በሰው ቤት በሰራተኝነት ተቀጥራ እንድትሰራ ሆነ፡፡ አባታቸው የሰጣቸው አንዲት ማሳ እንኳን ለሰው እኝ /የመቀናጆ እርሻ/ ገብተው ለራሳቸው ሁለቴ ሲያርሱ ለሰው ደግሞ አንዴ በማረስ እንዲኖሩ አሰገደዳቸው፡፡ ይህን ሁኔታ እንደሚከተለው በጌረርሳ ተገልጿል፡፡

| | |
|---|---|
| Haroorechi hin bubbisuu | አሮሬቻ አይናፍስም |
| Birraa fakkaateet darbaa | ብራ መስሎ ያልፋል እንጂ |
| Deegaa namni hin dubbisu | ደሃን ማንም አያናግረውም |
| Ijaan ajjeeseet darbaa | በዓይን ገድሎት ያልፋል እንጂ |
| Deegaa olla dureessaa | ደሃ የሀብታም ጐረቤት |
| Yookaan kiraatu ajjeesaa | ወይ ክራይ ይገለዋል |
| Yoo kaan tiraatu ajjeesaa. | ወይ ስቃይ ይገለዋል፡፡ |
| Gaattiraan fiixa hinqabuu | ጥድ ጫፍ የለውም |
| Fiixa bantii isaattillee | የአናቱን ጫፍ እንኳን |
| Deegaan ulfina hinqabu | ደሃ ክብር የለውም |
| Mana lammii isaattillee | በወገኖቹ ቤት እንኳን |
| Ijoolleen gaashee hinjettu | ልጆች ጋሼ አይሉትም |

Dubartiin isaan hin jettuu. ሴቶች እርሶ አይሉትም፡፡

ደሃ በማህበረሰቡ ይናቃል፡፡ ማንም ሰው ጉልበቱን ከመጠቀም ውጪ ክብር ሰጥቶ መቀመጫ የሚለቅለት የለም፡፡ እንዲሁም ከሰው በታች ያስቀምጡታል፡፡ ይህ ከላይ የተመለከተው ጌረርሳ ደሃን ማንም እንደማያናግረው፣ በማንም ፊት እንደሚናቅ፣ በዓይን ብቻ ገርመም አድርገው በንቀት እንደሚያልፉት ያሳያል፡፡ ማንም ሰው ንግግሩን ከቁም ነገር እንደማይቆጥር፣ ምንም ያህል ቁም ነገረኛ እንኳን ቢሆን ተቀባይነት እንደሌለው ነው፡፡ ደሃን በብር በመግዛት ጉልበቱን ብቻ አሟጦ መጠቀምን እንጂ እንደ ሰው ማየትና አክብሮት መስጠት እንደሌለ ያሳያል፡፡ የሚሠራቸው ሥራዎች ከሚያገኘው የጉልበት ዋጋ ጋር የማይመጣጠን መሆኑን "ወይ ክራይ ይገለዋል፣ ወይ ስቃይ ይገለዋል" የሚሉት ስንኞች ያመለክታሉ፡፡ ደሃ ምንም ምርጫ ስለማይኖረው ያገኘውን ማንኛውንም ሥራ ሠርቶ ይኖራል፡፡ አማራጭማ ቢኖረው ኖሮ "ክራይ" አይገለውም ነበር፡፡

ደሃ በዘመዶቹና በልጆች ፊት እንኳን አክብሮት የሌለው መሆኑና ምን ያህል ዝቅ ተደርጎ እንደሚታይ ያመለክታል፡፡ የሰቶችም ለደሃ "እርሶ"ና የልጆች "ጋሼ" አለማለት በሰዎች ፊት ከመጠን በላይ መናቁን ይጠቁማሉ፡፡

እኚህ መረጃ ሰጪ በድህነታቸው የተነሳ በሰው ፊት ተንቀዋል፣ ተንቋሸዋል፡፡ በተላላቆች ፊት ቀርቶ በልጆች ፊት እንኳን አክብሮት አልነበራቸውም (አባተ፣ 19/06/2004፣2፡30)፡፡ ይህ ክብር ማጣትና መናቅ ደግሞ ምን ያህል እንደጐዳቸው ከላይ ከተመለከተው ጌረርሳ መረዳት ይቻላል፡፡

እስራቱ ያደቀቀው የአቶ አባተን ኑሮ ብቻ ሳይሆን የአባታቸውንም ጭምር ነው ፡፡ አባታቸው አቶ ኤጀርሳ ፊይሳ ልጆቻቸውን ከእስር ቤት ለማስፈታት ሲሉ የነበራቸውን ንብረት ሸጠዋል፡፡ ይህ የንብረት መሸጥ የሳቸውን ኑሮ ከነበረው እንዲያሽቆለቁል አድርጎታል፡፡ የሚበሉት ምግብ፣ የሚለብሱት ልብስ እንደ ዱሮ አይደለም፡፡ ይህንን ሁኔታ አቶ አባተ እንደሚከተለው ጌረርሳ በመከወን አሳይተዋል፡፡

Abbaabbaa turumbullee
Isa foon malee hin bullee

አባባ ቱሩንቡሌ
ያለስጋ የማያድር

| | |
|---|---|
| Yaa abbaa koo yaa Ejoo | አባቴ ኤጀርሳ |
| sa gaaratti galuu | በጋራ ላይ የሚኖር |
| Akka qeerransa dhaluu | እንደ ነብር የሚውል |
| Gaafa maarama sayyoo | በማርየም ሰዮ ቀን |
| Isa ciibsee garafuu | አስተኝቶ የሚገርፍ |
| Gaafa maarii waaqayyoo. | እግዚአብሔር የማረው ቀን፡፡ |
| Dirribni kee hin dacha'uu | ደራርበህ የማትለብሰው |
| Diriitu si dhibee laataa | ድር አንሶህ ነው ወይ |
| Surreen kee jilba hin darbu | ሱሪህ ከጉልበትህ አያልፍም |
| Birriitu si dhibee laata. | ብር አንሶህ ነው ወይ፡፡ |
| Yaa Ejoo gooba kormaa | ኤጆ ኩሩው ቁንኑ እንደ ኮርማ ሻኛ የምትንጎማለል |
| Sitti hintaane akka hormaa | አልተመችህም እንደሰው |
| Ejoo maaramiin fuullee | ኤጆ የማሪያም አጠገብ |
| Isa ilaalanii hin quufnee. | ታይቶ የማይጠገብ፡፡ |

አቶ አባተ ንብረታቸው ከማለቁ በፊት የነበረውን የአባታቸውን ኑሮ የገለፁት በልጅ ኢያሱ ዘመነ ንግስና ከተቋቋመው ጥርንቡሌ ወይም የከተማ ዘበኛ (ባሕሩ ዘውዴ፣2003) ኑሮ ጋር በማነፃፀር ነው፡፡ አቶ አባተ አያታቸው አቶ ፌይሳ ነግረውኛል ብለው እንደነገሩኝ በኢያሱ ጊዜ የተቋቋመው ቱሩንቡሌ ወይም የከተማ ዘበኛ በወቅቱ በጣም የተደራጀና /Modern Municipal Police (Ministry of Education, 2005)/ ከቤተ መንግስት ጋር ቅርበት የነበረው ነው፡፡ የቱሩምቡሌው አባላት በኑሮም የደላቸውና በቅንጦት የሚኖሩ ነበሩ፡፡ ይፈሩ፣ ይከበሩም ነበር፡፡ አቶ ኤጀርሳ ፌይሳ ልጆቻቸው ታስረው እነሱን ለማስፈታት ንብረታቸውን ሸጠው ከመጨረሳቸው በፊት የሚበቃቸውን ያህል ንብረት የነበራቸው፣ በጥሩ ሁኔታ የሚኖሩና ኩሩ ነበሩ፡፡ እንደቱሩምቡሌዎቹ ቤት በቤታቸውም ጮማ ይቆረጥ፣ ጠጅም ይጠጣ ነበር፡፡ ከራሳቸውም አልፎ ሰውንም መርዳት የሚችሉ ነበሩ፡፡ በሬዎቻቸውንና ፈረሳቸውን ለአካባቢያቸው ሰዎች ያውሱ ነበር፡፡ እህልም ቢሆን ለሰዎች በብድርም፣ በነፃም በመስጠት ለሰዎች ችግር ደራሽ ነበሩ፡፡ ነገር ግን የልጆቻቸው መታሰርና እነሱን ለማስፈታት ባወጡት ወጪ ምክንያት ራሳቸውንም እንዳይችሉ አደረጋቸው (አባተ፣ 21/06/2004፣6፡00)፡፡

አቶ ኤጀርሳ ፈይሳ ልጆቻቸው ከመታሰራቸው በፊት የሚበሉት ምግብና የሚለብሱት ልብስ ምቾት የሚሰጥ ነበር፡፡ ነገር ግን ልጆቻቸውን ከእስር ለማስፈታት ብዙ ወጭ በማውጣታቸውና የነበራቸው ንብረት በመመናመኑ የሚመገቡት ምግብና የሚለብሱት ልብስ እንደዱሮ ምቾት የሚሰጥ አይደለም፡፡ ሥጋ መመገብና ደራርቦ መልበስ ቀርቷል፡፡ በመሆኑም ልጃቸው አቶ አባተ የከወኑት ከላይ በተመለከተው ጌረርሳ ይህንን ሁኔታ በጥልቀት አሳይተዋል፡፡

#### 4.1.3. ስለጠመንጃ መሸጥ

ሌላው አቶ አባተ ጌረርሳ የከወኑበት አውድ በ12/07/2004 ዓ.ም በደኩ ቀርሳ ቀበሌ ጎዋ በተባለ ቦታ በአቶ ድዳ ዳዲ ቤት ከቀኑ ከስድስት ሰዓት (6፡00) ጀምረው ነው፡፡ በወቅቱ በአቶ ድዳ ዳዲ ቤት በቅዱስ ሚካኤል ስም የሚጠጣ የቅዱስ ሚካኤል መታሰቢያ የወንዶች የፅዋ ማህበር ነበር፡፡ ፅዋው ወንዶች ብቻ የሚጠጡት ቢሆንም በወቅቱ ሴቶችም ተጋብዟል፡፡ በቦታው 20 ወንዶችና ስምንት ሴቶች በአጠቃላይ 28 ሰዎች ነበሩ፡፡ የታደሙት የፅዋ ማህበሩ አባላት ዕድሜ በግምት ከ25-65 ይገመታል፡፡ እነዚህ የፅዋ ማህበሩ አባላት ወደ ተጠቀሰው ቤት መሰባሰብ የጀመሩት ከ4፡30 (አራት ሰዓት ከሰላሳ) ጀምሮ ሲሆን የፅዋውን ሥነ ሥርዓት ያጠናቀቁት በ6፡00 (ስድስት ሰዓት) ነው፡፡ የፅዋ ሥነ ሥርዓቱ እንደተጠናቀቀ የማህበሩን አባላት ሲያስተናግዱ የነበሩት ወጣት ወንዶችና ሴቶች መዝፈን ጀመሩ፡፡ እነዚህ ወጣቶች ሦስት ሴቶችና አምስት ወንዶች በአጠቃላይ ስምንት ነበሩ፡፡ ወጣቶቹ እየዘፈኑ እያለ የማህበሩ አባላት የሆኑ ጌረርሳ የመከወን ችሎታ ያላቸው ግለሰቦች ጌረርሳ መከወን ጀመሩ፡፡ ከነዚህ የማህበሩ አባላት መካከል አቶ አባተ፣ አቶ ብርሃኑና አቶ ቸሩ ነበሩ፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ከዋኞችና ታዳሚያን ሦስቱን መረጃ ሰጪዎቹን የሚያነቃቃ ጉዳዮችን በማንሳት ክዋኔ ውስጥ እንዲገቡ አድርጓቸዋል፡፡ ለምሳሌ የከዋኞችን ሕይወት የሚመለከቱ ጉዳዮችን በማንሳት ለክዋኔው አነቃቅቷቸዋል፡፡ ከወኞቹና ታዳሚያን አቶ አባተ በወንድማቸው ላይ በመደረብ በመምህር በለጠ ነጋሳ ላይ ያደረሱትን ጉዳት፣ መታሰራቸውንና እስር ቤት ያገኛቸውን መንገላታት በማንሳት በመኮርኮር ወደ ክዋኔ እንድገቡ አድርጓቸዋል፡፡ ከዚያ በኋላ መረጃ ሰጪዎቹም እርስ በርሳቸው እየተቀሳቀሱ ጌረርሳውን ከውነዋል፡፡ በዚህ የተነሳ ሦስቱ መረጃ ሰጪዎቹ በወቅቱ ጌረርሳ በመከወን ማህበራዊና ግለሰባዊ

ጉዳዮችን አንጸባርቀዋል፡፡ ከሦስቱ መካከል አቶ አባተ ኤጀርሳ የከወኑት ጌረርሳ ከነትንታኔው እንደሚከተለው በዚህና በሚቀጥለው ንዑስ ርዕስ ሥር ይገኛል፡፡

ከለይ እንደተገለፀው አቶ ኤጀርሳ ፊይሳ ልጆቻቸውን ከእስር ለማስለቀቅ ያላቸውን ንብረት ሸጠዋል፡፡ የሸጡት ንብረት ጠመንጃቸውንም ይጨምራል፡፡ ይህ ጠመንጃ /ምንሽር/ በመሸጡ የተከሰተውን ሁኔታ አቶ አባተ በ12/07/2004 ዓ.ም በከወኑት ጌረርሳ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡

| | |
|---|---|
| Osoleen nutti galte | ሸኮኮ ገባችብን |
| Gaagura moofaa taanee | ያረጀ ቀፎ ሆንን |
| Minishirii gurgurraan | ምንሽር ስንሸጥ |
| Obobeen nuti malte | ፊሪ ተመሳጠረብን |
| Wallaalaa doofaa taanee. | አላዋቂ፣ ሞኝም ሆንን፡፡ |

በማህበረሰቡ ጠመንጃ ከክብር ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ጠመንጃ ያለው ሰው ከመከበሩም በላይ ይፈራል፡፡ ሲናገር ይደመጣል፡፡ ሰዎች ለሽምግልና ይጠሩታል፡፡ ወንበር ይለቀቅለታል፡፡ በዚያኑ ያክል ጠመንጃውን ሲሸጥ እጁ ባዶ ሲሆን ይናቃል፡፡ ቀድሞ የነበረውን ክብሩን ያጣል፡፡ የተናገረው አይሰማም፡፡ ተቀባይነት ያጣል፡፡ ከጀግንነቱ ይልቅ ድህነቱ ጐልቶ ይሰማል፡፡ በሰው ላይ ተመሳጥረው ወንጀል የሚፈፅሙት ጥቂት ዋልጌዎች ሲሆኑ ጠመንጃን ከክብር ጋር ማያያዝ በማህበረሰቡ የተለመደ ነው (አባተ 12/07/2004፣ መኮንን 21/07/2004፣ ድርባ 21/07/2004)፡፡

ከላይ የተጠቀሰው ጌረርሳ አቶ ኤጀርሳ ጠመንጃቸውን በመሸጣቸው “ፊሪ” ተብሎ የሚናቁ እንኳን እንደተመሳጠሩባቸው፣ መፈራታቸውና ክብራቸው ምን ያህል እንደቀነሰ ያሳያል፡፡ ድሮ የነበራቸውንም ማንነት ማጣታቸውንም ያስገነዝበናል፡፡ ማንም ሰው በነገር እንደሚተናኮሏቸው ያመለክታል፡፡ ያረጀ ቀፎ የንብ መኖሪያና ማር የሚቀረጥበት መሆኑ ቀርቶ የተባይ ወይንም የአልባሌ ነገሮች (ሸኮኮ) መኖሪያ እንደሚሆን ሁሉ ጠመንጃ የሸጠ ሰው ክብሩና መፈራቱ ቀርቶ የማንም መጫወቻ ይሆናል፡፡ የአቶ አባተ ቤተሰብም ምንሽር በመሸጣቸው የነበራቸው ክብር እንደተጣለ ቀፎ ማርጀቱን ከጌረርሳውና ከአቶ አባተ ንግግር መረዳት ይቻላል፡፡ ይህን ከላይ የተጠቀሰውን የበለጠ የሚያስረግጥልን አቶ አባተ የከወኑት ጌረርሳ፣

| | |
|---|---|
| Yaa daamaa Ejoo Fayyee | የኤጆ ፈይሳ ዳማ |
| Daamaan daamaa gugsiitii | ዳማው የጉግስ ነው |
| Lafti keenya dur dubbii hin qabu | ድሮ መንደራችን ነገር የለውም |
| Amma hambaa dubbiitii. | አሁን የነገር ቋት ነው፡፡ |

ድሮ የነበረው መፈራትና ክብር አሁን ስለጠፋ አካባቢው የነገር ቋት መሆኑንና ሰላም መጥፋቱን የሚያሳይ ነው፡፡ ጠመንጃው ከተሸጠ በኋላ ለሁለት ጊዜያት ያህል ሌቦች አጥራቸውን በመስበር እስከ በጎች ጎራኖ /Gooraannoo/ በመግባት የአባታቸውንና የወንድማቸውን በጎች ሰርቀዋል፡፡ በየድግስ ቤቱ ጥል እንደሚያነሱባቸው ገልፀዋል (አባተ 12/07/2004) ፡፡

4.1.4. **ንብረታቸው በማለቁ የተከሰተው ማህበራዊና ስነ-ልቡናዊ ቀውስ**

የኑሮው መዳከም በአቶ አባተ ላይ ያመጣው ማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ተፅእኖ /ጉዳት/ ከፍተኛ ነው፡፡ ከማህበረሰቡ ጋር እኩል በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ እንዳይሳተፉ አድርጓቸዋል፡፡ በራሳቸው እንዳይተማመኑ (የበታችነት እንዲሰማቸው) ምክንያት ሆኗል፡፡ ይህን አጋጣሚ አቶ አባተ በ12/07/2004 ዓ.ም በከወኑት ጌረርሳ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

| | |
|---|---|
| Namni farda hinqabne | ፈረስ የሌላው ሰው |
| Hamaamota hindhaqu | ሰርገኝነት አይጠራም |
| Namni qotiyyoo hinqabne | በሬ የሌላው ሰው |
| Daboo namaa hindhaqu | የሰውን ደቦ አይሄድም |
| Namni kafana hinqabne | ልብስ የሌላው ሰው |
| Sargii namaa hindhaqu | የሰውን ሰርግ አይሄድም |
| Qismiitu gadi du'aa. | ቅስሙ ይሰበራል፡፡ |
| Takka taane baranaa | አንድ ሆንን ዘንድሮ |
| Durba ulfoofte taanee | ያረገዘች ሴት ሆን |
| Ija ba'aa dadhabnee | የሰውን ዓይን ማየት አቃተን |
| Saree dulloomte taanee | ያረጀች ውሻ ሆንን |
| Halkan dutuu dadhabne. | ለሊት መጮኽ ተሳነን፡፡ |

በዚህ ጌረርሳ ፈረስ፣ በሬ፣ ልብስ ማጣት ምን ያህል ከማህበራዊ ኑሮ እንደሚከለክል (ገለልተኛ እንደሚያደርግ) ተመላክቷል፡፡ ፈረስ የሌላው ሰው ፈረስ ካላቸው ጋር ሰርገኝነት መሄድ አይችልም፡፡ አያምርበትም፡፡ እሄዳለሁ ቢል እንኳን ሰዎች

አያስጠጉትም፡፡ ምክንያቱም ከፈረስ እኩል በመሄድ በሰርገኝነት መሳተፍ አይችልም፡፡ የሰርጉን ድምቀትም ስለሚያደበዝዝ ተቀባይነት የለውም፡፡ በማህበረሰቡ በአብዛኛው ሠርገኝነት የሚከደው በበቅሎ ነው፡፡ በብዛት ባይኖርም አልፎ አልፎ ፈረሶች ስላሉ በፈረስም ይከዳል፡፡ ነገር ግን ከነዚህ ከሁለቱ ውጪ በእግሩ ሠርገኝነት መሄድ የለም (አባተ 12/07/2004)፡፡

በሬ የሌለው ሰው ደግሞ የሰውን ደቦ መሄድ ያስቸግረዋል፡፡ ቢሄድ እንኳን ለሆዱ እንደሄደ ያስቆጥረዋል፡፡ ይህም ሌላ ማህበራዊ ችግር ነው፡፡ ልብስም ቢሆን ከአደባባይ ያስቀራል፡፡ ያለ ልብስ በዬትኛውም ማህበራዊ ጉዳይ ላይ መሳተፍ አስቸጋሪ ነው፡፡ ልብስ ማጣት በሰው ፊትም ያስንቃል፡፡ አቶ አባተ፣ ባለቤታቸውና ልጃቸው የሚለብሱት ሰዎች የሚሰጡዋቸው አሮጌ ልብሶች ናቸው፡፡ ለራሳቸው የተሻለውን ልብስ የሚገዙበት ገንዘብ የላቸውም፡፡ ስለዚህ ሰዎች በሚመፀውቱዋቸው አሮጌ ልብሶች መልበስ ግድ ሆኖባቸዋል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ቅስማቸውን ሰብረዋል፡፡ የበታችነት እንዲሰማቸው አድርጓቸዋል(አባተ 12/07/2004)፡፡ በአጠቃላይ በሬ፣ ፈረስና ልብስ ማጣት አቶ አባተ በማህበራዊ ኑሮ ላይ ከማህበረሰቡ ጋር እኩል እንዳይሳተፉ ምክንያት ሆኗል፡፡ ገለልተኛ አድርጓቸዋል፡፡

አቶ አባተ ከዚህ ማህበራዊና ስነ-ልቡናዊ ተፅእኖ ለመወጣት በ12/07/2004 ዓ.ም በከወኑት ጌረርሳ እንደሚከተለው ምኞታቸውን ገልጸዋል፡፡

| | |
|---|---|
| Nawwe kaa nawwe nawwee | ተመኟን ተመኘሁ |
| Qotiyyoo xamadamtee | የተጠመደ በሬ |
| Weenniif saaburaan hawwee | ዌኒና ሳቡራን ተመኘሁ |
| Qotiyyoo xamadamte | የተጠመደ በሬ |
| Gaafa daboo laalimee | በደቦ ቀን እይ እስቲ |
| Gaafa shiggaa laalimee | ሽጋ በሚታረስበት ጊዜ እስቲ እይ |
| Qotiyyoon hormaa | የሰው በሬ |
| kan ofii namaa hintaatuu | የራስ አይሆንም |
| Gaafa qonnaa laalimee | በእርሻ ቀን እስቲ እይ |
| Beeljoon hormaa | የሰው ቤልጂግ |
| Kan ofii namaa hintaatuu | የራስ አይሆንም |
| Gaafa tuksii laalimee | በተኩስ ቀን እስቲ እይ |

| | |
|---|---|
| Abbaan hormaa | የሰው አባት |
| Kan ofii namaa hin ta'uu | የራስ አይሆንም |
| Gaafa dubbii laalimee. | በነገር ጊዜ እስቲ እይ ፡፡ |

ከላይ እንደተገለፀው በሬ ለእርሻ አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ በማህበራዊ ኑሮ ላይ ለመሳተፍ ጥቅሙ ከፍተኛ ነው፡፡ አቶ አባተ ከመታሰራቸው በፊት እንደነበረው በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ አሁን አይሳተፉም፡፡ የሰውን ደቦ አይሄዱም፡፡ ምክንያቱም በሬ የላቸውም፡፡ ዌኒና ሳቡራ ድሮ የነበራቸው በሬዎች ናቸው፡፡ አሁን አንድ በሬ ብቻ ነው ያላቸው፡፡ ይህ ደግሞ እንደዱሮአቸው በማህበራዊ ኑሮ ላይ ሊያሳትፋቸው አልቻለም፡፡ ስለዚህ ከዚህ ተፅእኖ ለመላቀቅ እንደድሮ በሬ እንዲኖራቸው ይመኛሉ፡፡

በተጨማሪም እኚህ ከዋኝ ጠመንጃ እንዲኖራቸውም ይፈልጋሉ፡፡ ምክንያቱም ጠመንጃ በጀግኖች ጉራ እንደሚያሰልፍና ማንነትን ከፍ እንደሚያደርግ፣ አክብሮትን እንደሚያመጣ፣ መፈራትን እንደሚያጐናፅፍ ያውቃሉና፡፡ ስለዚህ ከዋኙ ከላይ የተመኙትን ቢያገኙ ከነበረባቸው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነ-ልቡናዊ ተጽእኖ እንደሚያላቅቃቸውና ከማህበረሰቡ እንደሚያስተካክላቸው ያስባሉ፡፡ ነገር ግን የተመኙትን ሊያገኙ አልቻሉም፡፡ በዚህ የተነሳ ከተጫናቸው ማህበራዊና ስነ-ልቡናዊ ተፅእኖም ሊላቀቁ አልቻሉም፡፡ ይህንን ሁኔታ ደግሞ

| | |
|---|---|
| Mataa koo guftaan haadee | ጐፈሬዬን ተላጨሁ |
| Luuccaa naa marga jedhee | ሉጫ ይበቅልልኛል ብዬ |
| Garaan koo guddaa yaadee | ሆዴ ትልቅ አሰበ |
| Barri naa darba jedhee. | ዘመኑ ያልፍልኛል ብሎ፡፡ |

በማለት ይገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ አቶ አባተ ከላይ በተጠቀሱት አጋጣሚዎች ጌረርሳ በመከወን በፈፀሙት ስህተት ያጋጠማቸውን እስራትና በእስራቱ የተነሳ የደረሰባቸውን መንገላታትና የንብረታቸው መሚጠፕ፣ ንብረታቸው በወጪ ማለቅ ምክንያት ደግሞ የደረሰባቸውን ማህበራዊና ስነ-ልቡናዊ ቀውስ አመላክተዋል፡፡

አቶ አባተ ጌረርሳ በመከወን የገለፁዋቸው አበይት ይዘቶች ከላይ የተመለከተው ሲሆን አቶ ብርሃኑ አዱኛ የከወኑት ጌረርሳ ከነትንታኔው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 4.2. አቶ ብርሃኑ አዱኛ የከወኑት ጌረርሳ ላይ የተደረገ የይዘት ትንተና

የካቲት 16 ቀን 2004 ዓ.ም መረጃ ሰጪዎቼ በሚኖሩበት አካባቢ ዓመት በዓል ነው። ኪዳነምህረት ትነግሳለች፡፡ ታቦት ይወጣል፡፡ በየሰው ቤት ድግስ አለ፡፡ ሰዎች ከቤተክርስቲያን መልስ በየሰው ቤት እየዞሩ ይጠጣሉ፣ ይበላሉ፣ ይዘፍናሉም፡፡ በእለቱ የሚጫወቱት ሰዎች ከወጣት እስከ አዛውንት ናቸው፡፡ በመሆኑም ከ16/06/2004 ዓ.ም ከቤተክርስትያን መልስ ሰዎች በየቤቱ እየዞሩ ሲዘፍኑ እኔም አቶ ድሪባ ጅማ ቤት ተገኘሁ፡፡ ይህ የሆነው በ8፡00 (ስምንት ሰዓት) ነው፡፡ በየመንደሩ እየዞሩ የሚዘፍኑ ሰዎች መጥተው በአቶ ድሪባ ጅማ ቤት ጨዋታ ጀመሩ፡፡ የአቶ ድሪባ ጅማ ቤት በደኩ ቀርሣ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ አይሉ በተባለ ቦታ ይገኛል፡፡ በዚህ ቤት የተሰበሰቡት ሰዎች ከወጣት እስከ አዛውንት ናቸው፡፡ የወንዶቹ ብዛት 18 ሲሆን ሴቶቹ ሰባት ናቸው፡፡ በአጠቃላይ 25 ሰዎች ናቸው፡፡ እድሜያቸው ከ14 እስከ 70 ይገመታል፡፡ እነዚህ ሰዎች የተለያዩ የዓመት በዓል ዘፈኖችን ከዘፈኑ በኋላ መሃል ላይ ጌረርሳ መከወን ጀመሩ፡፡ ከኔ መረጃ ሰጪዎች መካከል አቶ ብርሃኑ አዱኛና አቶ ቸሩ ድንቄ በቦታው ስለነበሩ ከሌሎች ሰዎች ጋር ጌረርሳን አዜሟል፡፡ እነዚህ ከዋኞች መረጃ ሰጪዎቼን ለክዋኔው የሚያነሳሱ ጉዳዮች በመከወን ክዋኔ ውስጥ እንድገቡ አድርጓቸዋል፡፡ ለምሳሌ ታዳሚያን አቶ ብርሃኑ ያደረጉትን የኦዶ ሻክሶ ጉዞ፣ በኦዶ ሻክሶ ያጋጠማቸውን ችግርና ከዚያ መልስ ኑሮአቸውን ለማሸነፍ ያደረጉትን ተጋድሎ አንስተው በመቀስቀስ ክዋኔ ውስጥ እንዲገቡ አድርጓቸዋል፡፡ ይህንን ሚና የተጫወቱ ታደሚያን ከአቶ ብርሃኑ ጋር ወደ የኦዶ ሻክሶ የተጓዙ ናቸው፡፡ እኔም በእንዲህ አይነት አጋጣሚ ጌረርሳ እንደሚከወን ስለማውቅ ታዘጋጅቼ ነበር የሄድኩት። ስለዚህ መቅረጸ-ድምጼን በመጠቀም አቶ ብርሃኑ አዱኛና አቶ ቸሩ ድንቄ የከወኑትን ጌረርሳ ቀዳሁ፡፡ የተቀዳው የአቶ ብርሃኑ አዱኛ ጌረርሳና ይዘቱ እንደሚከተለው ይገኛል፡፡

### 4.2.1. ስለ መጠጥ ጎጂነት

አቶ ብርሃኑ አዱኛ በ1985 ዓ.ም ትምህርታቸውን አቋርጠው በአደአ በርጋ ወረዳ ውስጥ ከሚትገኘው ከኦሎንኮሚ ከተማ አረቄ እያመጡ ይነግዱ ነበር፡፡ አረቄውን የሚነግዱት ከሁለት ጓደኞቻቸው ጋር ነበር፡፡ አረቄውን እየነገዱ እያሉ ራሳቸውም መጠጣትና መስከር ጀመሩ፡፡ ከሰዎች ጋርም መጣላት አመጡ፡፡ በዚህ ምክንያት አረቄ የሚነግዱበት ገንዘብም ከእጃቸው እየመነመነ መጣ፡፡ አቶ ብርሃኑ ንግዳቸው ልፋት እንጂ ውጤት እያጣ ሲመጣ አረቄ መጠጣትና መስከር ያመጣባቸው ኪሳራ መሆኑን ይረዱና ከመነገድ ውጪ መጠጣቱን አቆሙ፡፡ ከአረቄ ንግድ ያገኙ የነበረውን ትርፍ ያጠራቅሙና ቀስ በቀስ ፍየሎችን መግዛት ጀመሩ፡፡ የተገዙት ፍየሎች ረቡና ካረሱት እህል በተጨማሪ ሽጠው በሬ ገዙ፡፡ ይህ ደግሞ ኑሮአቸውን ማሻሻል ጀመረ፡፡ አቶ ብርሃኑም አረቄ መጠጣቱን በመተዋቸው የኑሮአቸው መሻሻል አስመልክተው በ16/06/2004 ዓ.ም በከወኑት ጌረርሳ እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡

| | |
|---|---|
| Eenyuuti dhuguu jaallataa | ማነው መጠጣት የሚወድ |
| Dhuguun ciisa feesisaa | መጣጥ ያስተኛል |
| Hunduu ciisa leellisaa | ጠጪ መተኛት ይወዳል |
| An jibbe tapha xinnoo | እኔ ጠለሁ ክፉ ጨወታ |
| Mana qublamee seenuu | አረቄ ቤት ገብቼ |
| Qubaan qabee haleeluu | አረቄውን መኮምኮም |
| Gola faradoo seenee | ወደ ፈረስ ቤት ገብቼ |
| Gala funyoo kajeeluu. | ኋላ ራስን መስቀል ከጀለኝ፡፡ |
| Qublameen qarshiin diinaa | አረቄ ለገንዘብ ፀር ነው |
| Kana birraa kuufatanii | ብራ ያጠረቀሙትን |
| Dadhabanii fidanii | ደክሞ ያመጡትን |
| Dafqa ofii cuunfanii | ላብን እንጠፍጥፈው |
| Qublamee farroo qollee | አረቄ የሰው ጠላት |
| Kan kabajaaf hin tollee | የሰውን ክብር አቃላይ |
| Mataa nama buusiftii | ራስን ዝቅ ታደርጋለች |
| Qaama namaa adoochitii | ሰውነትን አደንዝዛ |
| Sammuu nama doomsitii | አእምሮን አዶልዱማ |
| Nama nama tuffachiiftii. | ሰውን ታቃልላለች፡፡ |

| | |
|---|---|
| Ani beeka hojiishee | እኔ አውቃለሁ የእሷን ሥራ |
| Kana qollee narraa buuftee | ቆሌዬን ገፈፈችን |
| Akka ergamtuu namaa | እንደ ተላላኪ ሰው |
| Gola re'ee na bulchitee | ከሰው በታች አሳደረችኝ |
| Akka gaddeemtuu namaa | እንደ ውዳቂ ሰው |
| Sammuu koo na doomsitee | አእምሮዬን አደለደመችኝ |
| Baay'ee na Iyyoomsitee | ብዙ አደሃየችኝ |
| Olla kootiin na kuttee | ከጎረቤት አጣላችኝ |
| Fayyaa koo badduu baaftee. | ጤንነቴን አሳጣችኝ፡፡ |
| Dafeetan itti bare | ፊጥኝ አወቅሁባት |
| Akka isheen na doomsite | እንዳደነዘዘችኝ |
| Akka na iyyoomsite | እንደ አደሃዬችኝ |
| Dafeen irraa deebi'e | ቶሎ ከስዋ ታቀብኩኝ |
| Qalbii koos sassaabbadha. | ፀባዬንም አረምኩኝ፡፡ |

አረቄ ከጠጡና ከሰከሩ ሥራ መሥራት አይቻልም፡፡ ታሰንፋለች፤ ታስተኛለች፡፡ ወይምን ደግሞ ሰውን እረፍት ትከለክልና የማይገባውን ሥራ ታሠራለች፤ ከሰውም ጋር ታጣላለች፡፡ ከጎረቤት፣ ከጓደኛና ከዘመድ አዝማድ ታቆራርጣለች፡፡ ከዚያም አልፋ ለሞትም ልታደርስ ትችላለች፡፡ አዘውትሮ የሚጠጡ ከሆነ ደክመው ያፈሩትን ንብረት እንዲባክን ምክንያት ትሆናለች፡፡ መረጃ ሰጪው እንደነገሩኝ አረቄን ጠጥተው በመስከር ጥረው ግረው ያመጡትን ንብረት አውድመው ነበር፡፡ ከጎረቤታቸው ጋር በመጣላት ሰላምንም አጥተው ነበር፡፡ ከሰው ፊት የነበራቸውን አክብሮት አጥተው ነበር፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው መረጃ ሰጪው ከከወኑት ጌረርሳ እንደምንገነዘበው አረቄ ያለአግባብ አዘውትሮ መጠጣት ንብረት ከማሳጣቱም በላይ ጤናንም እንደሚያሳጣ ተመላክቷል፡፡ አእምሮን በማደንዘዝ ተገቢውን ሥራ እንዳይሠሩ ታደርጋለች፡፡ ያልሆነ ቦታ ታሳድራለች፡፡ ለተለያዩ በሽታዎች እንዲጻረት ምክንያትም ትሆናለች፡፡ መረጃ ሰጪው የታዘቡትን ሲገልጹ፡

> አረቄ እየጠጡ ሀብት ንብረታቸቸውን ያጡ ሁሌ በድህነት የሚኖሩ ብዙ ሰዎች በአካባቢዬ አሉ፡፡ ሁሌ ይበደራሉ፤ ብድሩን ግን አይመልሱትም፡፡ ነጋ ጠባ ከሰዎች ጋር ሲጣሉ ይታያሉ፡፡ ከቤትም

ሰላም የላቸውም፡፡ አረቄ ጠጥተው ሰክረው ገደል ገብተው የሞቱም አሉ፡፡ በመንገድ ላይ ወድቀው የያዙትን ገንዘብ የተነጠቁ አሉ፡፡ እኔ ራሴ አረቄ በመጠጣት ብዙ ጊዜ ራሴን አሰቃይቻለሁ፡፡ ንብረትም አጥቻለሁ፡፡ ነገር ግን ቶሎ ጥቅሟንና ጉዳቷን በመረዳቴ ራሴን መታደግ ቻልኩ፡፡ እኔ እጠጣ የነበረው ከማግባቴ በፊት ነበር፡፡ በትዳር እያለሁ ጠጥቼ ሰክሬ አላውቅም። ይህ የሆነው ላጤ በነበርኩ ሰዓት ጉዳቷን ስለተረዳሁ ነው (ብርሃኑ፣ 12/07/2004 ፡ 11፡30)፡፡

መረጃ ሰጪው በዚህ ጌረርሳ አረቄ መጠጣትና መስከር የሚያመጣውን ጉዳት በጥልቀት ገልጸዋል፡፡ ይህን አጋጣሚ የሚገልጹት በቁጭት ነው፡፡ ምክንያቱም ያኔ ሲጠጡበት የነበረውን ገንዘብ ቆጥበው ቢሆን ኖሮ ብዙ ይጠቅማቸው እንደነበር ያምናሉ፡፡

### 4.2.2. ስለ ኦዶ ሻክሶ ጉዞ

ሌላው አቶ ብርሃኑ አዱኛ በ16/06/2004 ዓ.ም በጌረርሳ የገለጹት ገጠመኛቸው ወደ ኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ጉጂ ዞን ኦዶ ሻክሶ ( ሲዳሞ) ለወርቅ ቁፋሮ የሄዱበትን አጋጣሚ ነው፡፡ ወደ ዚያ የሄዱት በ1987 ዓ.ም ነበር፡፡ የሄዱበት ምክንያት ኦዶ ሻክሶ በሚባል ቦታ ወርቅ እንደሚገኝና ብዙ ሰዎች ወርቅ ቆፍረው አውጥተው ሸጠው ብዙ ገንዘብ አግኝተዋል የሚል ወሬ በመስማታቸው እሳቸውም ወርቅ ቆፍረው ሸጠው ንብረት ለማፍራት ነበር። በመሆኑም ተነስተው ወደ ኦዶ ሻክሶ ሄደዋል፡፡ ይህን ወደ ኦዶ ሻክሶ ያደረጉትን ጉዞ በጌረርሳ ገልፀዋል፡፡ መጀመሪያ የገለፁት ለጉዞ ከቤታቸው የተነሱበትን ሁኔታ ነው፡፡ ይህም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| | |
|---|---|
| Ka'eetan biyyaa ba'ee | ተነስቼ ከሀገር ወጣሁ |
| Yaa biyya abbaa koo hinjennee | የአባቴ ሀገር አላልኩም |
| Yaa ija hindaaqqoo hinjennee | የዶሮ ይጪኽ አላልኩም |
| Yaa barii lafaa hinjennee | ንጋትም አልጠበኩም |
| Yaa marii firaa hinjennee | ዘመድን ላማክር አላልኩም፡፡ |
| Raase kaa raase raasee | ጠመዘዘ |
| Makiinaan gommaa raasee | ሹፌር መሪውን |
| Shufeerri marii raasee | አሽከረከረ መኪና ጎማውን |
| Fuudhee biyyaa na baase. | ወጣ ከሀገር ይዞኝ፡፡ |
| Surree naannechan hidhee | ወገቤን ጠበቅ አድርጌዋለሁ |

| | |
|---|---|
| Ni citaa hinyaadda'inii | ይላላል ብለሽ አታስቢ |
| Tulluu naanna'een dhufaa | ሀገርን ዞሬ እመጣለሁ |
| Yaa harmee yaa haadha koo | እናቴ እማምዬ |
| Ni du'aa hinyaadda'inii | ይሞታል ብለሽ አታስቢ፡፡ |

በማለት ከዘመድ አዝማድ ጋር ሳይመካሩ፣ ንጋትን ሳይጠብቁ መሄዳቸውን ገልፀዋል፡፡ ዘመድን ወይንም ጓደኛን ቢያማክሩ ከዓላማቸው ምክንያት ፈጥረው ሊያስቀሩዋቸው ይችላሉ፡፡ በዚህ ሰበብ ዓላማቸው ሊሰናከል ይችላል፡፡ ስለዚህ ማንንም ሳያማክሩ ወዳሰቡት ቦታ ሄደዋል፡፡

በጌረርሳቸው ለእናታቸውም መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡ ይሞታል ብለው እንዳይሰጉና እንዳይጨነቁ "ሀገር ዞሬ እመጣለሁ፣ ይሞታል ብለሽ አታስቢ" በማለት አበረታተዋል፡፡

ሲዳሞ እንደደረሱ ያጋጠማቸውን ሁኔዎች ደግሞ እንደሚከተለው በጌረርሳ ገልፀዋል፡፡

| | |
|---|---|
| Sidaamoo manni hinjiruu | ሲዳሞ ቤት የለም |
| Waaroo dhaabbatan malee | ዋሮ ውስጥ ማደር እንጂ |
| Taa'ii nyadhuun hin jiruu | ቁጭ ብለህ ብላ የለም |
| Taa'ii dhugiin hin jiruu | ቁጭ ብለህ ጠጣ የለም |
| Qarshii gaafatan malee. | ብር ይጠይቃሉ እንጂ፡፡ |

ኦዶ ሻክሶ ወርቅ የሚቆፈርበት ቦታ የነበረው ያልጠበቁት ነው፡፡ ኦዶ ሻክሶ ወርቅ የሚቆፈርበት ቦታ ቤት የለም፡፡ ወርቅ ቆፋሪዎች በፕላስቲክ፣ በማዳበሪያና በልብስ ጎጆ አይነት ነገር ብቻ ሰርተው እየኖሩ ወርቅ ይቆፍራሉ፡፡ በማይመች ኑሮ ውስጥ ሆኖ በጣም ጥልቀት ያለው ጉድጓድ በመቆፈር አፈሩን ካወጡ በኋላ አፈሩን ደግሞ በማዳበሪያ ጨምረው ወደ ወንዝ በማውሰድና በማጠብ ወርቅ ይፈልጋሉ፡፡ ወርቁ ከተገኘ ሸጠው ከዚያ የሚገኘውን ገንዘብ ለምግብና ለመጠጥ ያውላሉ፡፡ የተረፈውን ያጠራቅማሉ። ነገር ግን ትላልቅ ጉድጓዶችን ቆፍረው አፈሩን አግዘው አጥበው ወርቁን ሊያጡም ይችላሉ፡፡ ያለምንም ውጤት ወደ ትውልድ ቀዬም መመለስም አለ፡፡ ስለዚህ በኦዶ ሻክሶ መራብ፣ መጠማትና መታረዝ አለ፡፡ ብር ከሌለ ብላ፣ ጠጣ የሚል ሰው አይኖርም (ብርሃኑ፣ 17/06/2004፣ 11፡30)፡፡

አቶ ብርሃኑ አዱኛ እንዲህ ዓይነት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እያሉ ከጓደኛቸው ጋር ወርቅ መቆፈሩን ይቀጥላሉ፡፡ ወርቅም ያገኙና ሸጠው ገንዘብ በማግኘታቸው ይበረታታሉ፡፡ ነገር ግን ብዙም ሳይቆዩ ጓደኛቸው ይታመማል፡፡ ጓደኛቸውን በዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ማስታመም በራሱ ከባድና ትእግስት የሚጠይቅ ነበር፡፡ እንደምንም ጓደኛቸውን ሆስፒታል ውስደው በማሳከም አዳኑ፡፡ ነገር ግን ጓደኛቸውን አሳክመው ለማዳን የራሳቸውንና ጓደኛቸውን ገንዘብ በመጨረሳቸው ወደ ወርቅ ቁፋሮው ተመለሱና ሥራ ጀመሩ፡፡ ይህን ሁኔታ ሲገልጹ፡

| | |
|---|---|
| “Takka taane barasii | አንድ ሆነን ያን ዘመን |
| Warqiillee qoffarannee | ቆፍረን ወርቅ አገኘን |
| Waan jabduu yaallannee | ለኑሮአችን ትልቅ ነገር ሰራን” በማለት |

ጌረርሳ ከውነዋል፡፡

አዶ ሻክሶ የነበረውን አስቸጋሪ ኑሮ በትእግስትና በብልጠት ለማለፍ ደረጉትን ተጋድሎ ሲገልጹ ደግሞ

| | |
|---|---|
| Namni wayyaa balashee | ስስ ልብስ ያለው ሰው |
| Hinbulu biyya qorraa | አያድርም በብርድ ሀገር |
| Nan bule biyya qorraa | አደርኩኝ በብርድ ሀገር |
| Baaqqee koo dachafadhe | ስስ ልብሴን ለበስኩና |
| Namni qalbii yartuu | መጥፎ ፀባይ ያለው ሰው |
| Hin bulu biyya hormaa | አይኖርም በሰው ሀገር |
| Nan bule biyya hormaa | ኖርኩኝ በሰው ሀገር |
| Qalbii koo sassaabadhee. | ሀሳቤን አረምኩና፡፡ |

በማለት የራሳቸውን ፍላጎት ገድበው በእውቀትና በብልጠት በዚያ አስቸጋሪ ኑሮ ውስጥ ሲዳሞ እስከ አስር ወራት መኖራቸውን ገልጸዋል፡፡ ስስ ልብስ በብርድ ሀገር መኖር እንደማያስችል ሁሉ በሀሳብ መባከን በማያቁት ሀገር መኖር አያስችልም፡፡ ስለዚህ መረጋጋትና በብልጠት ችግሮችን መቋቋም ያስፈልጋል፡፡ አቶ ብርሃኑም ይህንን በመረዳት ራሳቸውን አረጋግተው አዶ ሻክሶ መቆየታቸውን ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን ከአሥር ወራት በላይ ጉጂ ዞን አዶ ሻክሶ ሊቆዩ አልቻሉም፡፡ ከኑሮው አስቸጋሪነት በተጨማሪ አቶ ብርሃኑ ታመሙ፡፡ ከዚህ በኋላ አዶ ሻክሶ መቆየት እንደማያዋጣቸው ከጓደኛቸው ጋር ይመካከሩና ወደ ትውልድ ቀዬአቸው ተመለሱ፡፡

ወደ ትውልድ ቀዬአቸው ለመመለስ ከጓደኞቻቸው ጋር ሲመካከሩ የነበረውን በጌረርሳ ሲገልፁ፡

| | |
|---|---|
| Ka'i kaa yaa dhiiroo | ተነስ ወንዱ /እንበሳዬ |
| Biyya abbaa ofii wayyaa | ያባት ሀገር ይሻላል |
| Abeet yaa biyya ofii | አቤት የራስ ሀገር |
| Biyya daadhii dhuganoo | ጠጅ የሚጠጡበት |
| Biyya coomaa muranoo | ጮማ የሚቆርጡበት |
| Biyya gaarii bulanoo. | ጥሩ የሚኖሩበት |

በማለት ትውልድ ቀዬያቸው ምቹ መሆኑን "ጠጅ የሚጠጡበት፣ ጮማ የሚቆርጡበትና ጥሩ የሚኖሩበት" በማለት ኦዶ ሻክሶ ከነበረው አስቸጋሪ ሁኔታ ጋር በማነጻጸር ገልፀዋል፡፡ አቶ ብርሃኑ ወደ ኦዶ ሻክሶ የሄዱት በቋሚነት እዚያ ለመኖር ሳይሆን ሠርተው ብር አጠራቅመው ወደ ትውልድ ቀዬአቸው ለመመለስ ነው፡፡

ኦዶ ሻክሶ በቆዩበት አሥር ወራት ውስጥ ያገኙትን ገንዘብ በህክምና በመጨረሳቸው ወደ ቤታቸው ከገቡ በኋላ በቀረቻቸው ጥቂት ገንዘብ ፍየል ገዙ፡፡ ያቺን ፍየል በማርባት፣ መሬት (ማሳ) በኮንትራት በመግዛትና በማረስ አዲስ ኑሮ ጀመሩ፡፡ ከአመታት በኋላ በ1988 ዓ.ም ያመረቱትን እህልና፣ ያረቡትን ፍየሎች በመሸጥ አንድ አነስተኛ በሬ ገዙ፡፡ ከዚያ በኋላ መሬት በኮንትራት በመግዛት አባታቸው ከሰጡዋቸው ሁለት የእርሻ ማሳዎች ጋር በማረስ ኑሮአቸውን ማሻሻል ቻሉ፡፡

### 4.2.3. ወሬ ትቶ በርትቶ ስለመስራት

አቶ ብርሃኑ በሚኖሩበት አካባቢ ያሉ አንዳንድ ሰዎች የእርሻ መሬት እያላቸው መሬታቸውን ለረጅም ጊዜ በኮንትራት በመሸጥና ሥራ በመተው ጊዜያቸውን በወሬ ያሳልፋሉ፡፡ በመሆኑም እነዚህ ሰዎች ቤተሰባቸውን በድህነት ያማቅቃሉ፡፡ ሁል ጊዜ ጊዜያቸውን በወሬ ሰውን በማጣላትና በማጋጨት ያሳልፋሉ፡፡ ይህን ሁኔታ በመገንዘባቸው አቶ ብርሃኑ በ21/06/2004 ዓ.ም በአቶ አጹኛ ጅማ ቤት ሁሉም መረጃ ሰጪዎች በሚገኙበት የሚከተሉትን ጌረርሳ ከወኑ፡፡

| | |
|---|---|
| Tuttuulanii fe'anii | ከምሮ ጭኖ |
| Tabba maaf komatanii | ዳገትን ለምን ያማሉ! |
| Tuttuulamanii taa'anii | ያለሥራ ተቀምጠው |

| | |
|---|---|
| Waaqa abbaa hinmatanii. | እግዜርን ያማርራሉን፡፡ |
| Itti ejjetanii qotanii | ረግጦ በማረስ |
| Xaafii gumbii guutanii | ጤፍን ድብኚት ሞልተው |
| Gurra abbaa ofii tolchuu | የአባትን ስም ማሳመር እንጂ |
| Yoo firri ofii dhufee | ዘመድ እንኳን ቢመጣ |
| Baksaa obaasanii | ንጥር ቅቤ አጠጥተው |
| Daadhii cirriqfachiisanii | ጠጅ አስጎንጭተው |
| Fira ofii gaggeessuu. | መሸኘት ነው እንጂ፡፡ |
| Yoo hoomtu mana hin jirree | ምንም ቤት ውስጥ ከሌለ |
| Raafuu funaannachaa | ጎመን እየለቀሙ |
| Imimmaan facaasaa | እንባን እያፈሰሱ |
| Irqifatanii boo'aniit | አምርረው በማልቀስ |
| Godadoo itti himachuu | ችግርን በማዋየት |
| Fira ofiituu naasisuu | ዘመድን ከማስደንገጥ |
| Boquu gadi cabsanii | አዝነው ከማሳዘን |
| Ija namaa qaana'uu | ቀና ማለትን ከመፍራት |
| Kanaafuu qotuu wayyaa. | ማረስ ይሻላል፡፡ |

ያለ ሥራ ቁጭ ብለው ወሬ ማውራት ከማዋረድና በድህነት ከማማቀቅ ውጪ ምንም ውጤት አያስገኝም፡፡ ነገር ግን በርትቶ መስራት ያስከብራል፡፡ የሚሠራ ሰው ቤቱ ሙሉ ነው፡፡ ቤት ሙሉ ከሆነ እንግዳ እንኳን ቢመጣበት አያሳፍርም፡፡ ምክንያቱም በመልካም ሁኔታ አስተናግዶ መሸኘት አይከብድምና፡፡

አቶ ብርሃኑ በሚኖሩበት አከባቢ ባለው ማህበረሰብ ዘንድ እንግዳን መቀበልና በጥሩ ሁኔታ አስተናግደው መሸኘት እንደ ትልቅ ነገር ይቆጠራል፡፡ እንግዳን የማይቀበል ደግሞ በማህበረሰቡ ጥሩ ግምት አይሰጠውም፡፡ይናቃል (ብርሃኑ፣ 12/07/2004 ፡ 11፡30)፡፡ ምንም በሌለበት ቤት እንግዳን መቀበል ደግሞ በጣም ያሳፍራል፡፡ ስለዚህ ጌረርሳው መሥራት (ለፍተው ኑሮውን ማሸነፍ) ይሻላል። ከወሬ ምንም አይገኝም፡፡ ወሬ በሰው ዘንድ ያስንቃል፡፡ ሥራ ግን ያስከብራል የሚል መልእክት ያዘለ ነው፡፡

ከዋኙ ደግሞ ሰውን ለሥራ ሲያነሳሱ፡

| | |
|---|---|
| Qoti yaa ilma namaa | እረስ የሰው ልጅ |

| | |
|---|---|
| Kan qotee dilbeeffatee | እርሶ አምርተው ያስገባ |
| Ija namaa hin qaana'uu | የሰውን አይን አያፍርም |
| Waaqni abbaa nama hindiduu | የአባት አምላክ እምቢ አይልም |
| Godhatan nama hin dhibuu. | ከሠሩ ችግር የለም፡፡ |

በማለት የሰው ልጅ በርትቶ ከሠራ የሰውን ዓይን አያይም። ራሱን ችሎ ክብሩን ጠብቆ ይኖራል፡፡ ሥራ ያስከብራል በማለት ይመክራሉ፡፡

የረሃብ መድሃኒት ምን እንደሆነ፣ የሰው ልጅ ከድህነት ለመውጣት ምን ማድረግ እንዳለበት በጌረርሳ ሲገልጹ፡

| | |
|---|---|
| Ani kaa mala beekaa | እኔ ዘዴ አውቃለሁ |
| Naggaadee wajjin tirfii | ከነጋዴ ጋር ትርፍ |
| Gabaree wajjin hirfii. | ከገበሬ ጋር እርፍ፡፡ |
| Beeka kaa beeka beekaa | አውቃለሁ አውቃለሁ እንጂ |
| Mala qoonqoo nan beekaa | የሆድን መድሃኒት |
| Qoricha beelaa beekaa | የረሃብን መድሃኒት |
| Gindii gaarii muradhee | ጥሩ ሞፈር መስራት ነው |
| Gindii jabaa xarabee | ጠርቦ ማስተካከል ነው |
| Hirfii jabaa itti galchee | ጥሩ እርፍ ማስገባት ነው |
| Maarashaa qarsiifadhee | ጥሩ ማረሻ አሰርተው |
| Qonyees nan dabalchiisee | ጥሩ መርገጥም ገዝተው |
| Iyyummaa amansiifadhe. | ድህነትን ማሳመን ነው፡፡ |
| Daarii lafaa jijjigsee | የመሬትን ዳር አፍርሼ |
| Xaafii kootu gad-jigsee | ጤፍ በገፍ አምርቼ |
| Mishingaa facaafadhee | ማሽላንም ዘርቼ |
| Xaafii dilbeechee galchee | ጤፍን በገፍ አምርቼ |
| Bonammoo makaradhe | በበጋ ጥሬ አምርቼ |
| Ganna tirfii gurguree | በክረምት ትርፉን ሸጬ |
| Waan guddaadhaaf shurshuree. | ለትልቅ እድገት አቅጂ፡፡ |
| Gindii jalatti kufuu | በርትቶ መስራት ነው |
| Midhaan taphatti hin dhufuu. | እህል በቀልድ አይመጣም፡፡ |

አንድ ሰው ጥሩ ኑሮ ለመኖር በርትቶ በብልሃት መሥራት አለበት፡፡ ካልሠራ ምንም ማግኘት አይችልም። የሰው ሥራ በእውቀት ካልታገዘ ደግሞ ልፋት ብቻ

እንጂ ውጤት አያመጣም፡፡ ስለዚህ አንድ ገበሬ ለእርሻ ከመነሳቱ በፊት ለእርሻ የሚሆኑ ቁሳቁሶችን በጊዜ ማዘጋጀት አለበት፡፡ ለእርሻ እንደሚመች አድርጎ ማሰናዳት ያስፈልጋል፡፡ ስራውንም በእቅድ መምራት አለበት፡፡ መቼ ምን መስራት እንዳለበት ማወቅ ብልህነት ነው፡፡ ከላይ የሰፈረው ጌረርሳ በእርሻ ጊዜ ማረስ፣ እርሻ በሌለበት ጊዜ ደግሞ ነግደው ትርፍ ማምጣት አስፈላጊ መሆኑን ያስረዳል፡፡ እህልን በበጋና በክረምት ሠርተው አምርተው በክረምት ትርፉን መሸጥ ያዋጣል፡፡ ምክንያቱም በክረምት የእህል ዋጋ ይጨምራል፡፡ በበጋ ግን የእህል ወቅት በመሆኑ እህል እንደ ክረምት ውድ አይደለም፡፡ ስለዚህ ወቅቱን ጠብቆ አምርቶ በክረምት መሸጥ አዋጭ መሆኑን ያመለክታል፡፡

አቶ ብርሃኑ ለፍተው አምርተው ጥሩ ምርት በማግኘታቸው የተነሳ ጌረርሳ እንደሚከውኑ፣ እንደ ሌሎች ሰዎች ለጉራ ብቻ እንዳልሆነ በ12/07/2004 ዓ.ም በአቶ ድዳ ዳዲ ቤት ከ6፡00-11፡30 በነበሩበት ጊዜ በከወኑት ጌረርሳ ሲገልጹ፣

| | |
|---|---|
| Ormi oftuuluun geerraraa | ሰዎች በጉራ ይሸልላሉ |
| Ani dilbeesseen geerraraa | እኔ አከማችቼ ነው የምሸልለው |
| Oduu maal ittiin godhuu | ወሬ ምን ይሰራልኛል |
| Kan ilma namaa salphisuu | ሰውን የሚያሳፍር፣ |
| Midhaan qotachuu wayyaa | አርሶ ማምረት ይሻላል |
| Isa du'aa fayyisuu | በሞተው እንኳን ነፍስ የሚዘራ |
| Kan qallaa furdisuu | የቀጠነውን የሚያወፍር |
| Kan salphaa boonsuu. | የቀለለውን የሚያስከብር፡፡ |
| Maal godhuufan odeessaa | ምን ለመስራት ነው የማወራው |
| Deegni biyyaa na balleessaa. | ረሀብ ከሀገር እንዲያወጣኝ ነው! |

ይላሉ፡፡

በዚህ ጌረርሳ ሥራ እንደሚያስከብር ወሬ ደግሞ እንደሚያስንቅፍ በመግለጽ ሰዎች ጠንክረው እንዲሠሩ ያበረታታሉ፡፡ አቶ ብርሃኑ እሳቸው የሚከውኑት ጌረርሳና ሌሎች የሚከውኑት ልዩነት እንዳለው፣ ሌሎቹ ለትዕቢት ወይንም ለጉራ ሲሆን እሳቸው ግን ሠርተው አምርተው ስኬታቸውን ለመግለፅ እንደሆነ አመላክተዋል፡፡ ያለሥራ ተቀምጦ ማውራት ከማስነቀፉም አልፎ ለድህነት እንደሚዳርግና እንጀራ ፍለጋ ከአገር አገር እንደሚያንከራትት ገልፀዋል፡፡

እኚህ ከዋኝ አርሰው አምርተው ራስን ለመቻል በሬ አስፈላጊ መሆኑን ደግሞ እንዲህ ስሉ ይገልፁታል፡፡

| | |
|---|---|
| Jiraadhu yaa qotiyyoo | ኑር አንተ በሬዬ |
| Situ daarii buqqisaa | አንተነህ ገልብጠህ የምታርስ |
| Situ gaarii mul'isaa | ጥሩ ነገርን የምታስገኝ |
| Situ xinnaa guddisa. | ትንሹን የምታሳድግ፡፡ |

በማለት በሬ ለእርሻ የጀርባ አጥንት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ያለበሬ እርሻን በተቀላጠፈ ሁኔታ መሥራት አይቻልም፡፡ ገበሬ በሬ ከሌለው እንደፈለገ አምርቶ ኑሮውን ማሸነፍ ይችልም፡፡ ስለዚህ አቶ ብርሃኑ በሬ ለራሳቸው የኑሮ ስኬት ከፍተኛ ድርሻ መውሰዱን በጌረርሳ አሳይተዋል፡፡

### 4.2.4. ስለ አባት ምክር

አቶ ብርሃኑ በጌረርሳ በ12/07/2004 ዓ.ም የገለጹት ሌላ ጉዳይ አባታቸው በመጀመሪያ እሳቸው እርሻ አንደጀመሩ እንዴት መስራት እንዳለባቸው የመከሩበትን አጋጣሚ ነው፡፡ ይህን ሲገልጹ፡

| | |
|---|---|
| Abbaabbatu na gorsee | አባቴ አሳየኝ |
| Abbabba guddicha koo | አባቴ ትልቁ |
| Situ beekaa dhukkuba koo. | አንተነህ የምታውቀው ህመሜን |
| Akka gootu naan jedhee | እንደምታደርገው አለኝ |
| Suuta jedhii lafa qoti | ቀስ ብለህ እረስ |
| Hojii barta naan jedhe | ስራ ትለምዳለህ አለኝ |
| Hoggaammoo lafa qottu | መሬትን በምታርስበት ጊዜ |
| Qibqibii qoti jedhe | ቅብቅቡን እረስ አለኝ |
| Yoo dura geerrartu | መጀመሪያ ስትሸልል |
| Dabeerotti geerrari jedhe | ካላዋቂ ጋር አድርግ አለኝ |
| Lolas ni barta jedhe. | ትግል ትለምዳለህ አለኝ፡፡ |
| Abbaabbaa guddicha koo | አባቴ ትልቁ |
| Situ beeka dhukkuba koo | የሚታውቀው ህመሜን። |

በማለት አባታቸው ሥራ የሚለመደው ቀስ በቀስ ከቀላል ሥራ ወደ ከባድ እየታደገ መሆኑን የመከሩትን ጌረርሳ በመከወን አቅርበዋል፡፡ አባት የልጁን ችግር

እንደሚረዳና ተከታትሎ በምክር እንደሚያግዝ "Situ beekaa dhukkuba koo /አንተነህ ህመሜን፣ በሽታዬን ያወክልኝ" በማለት ገልፀዋል፡፡

### 4.2.5. ስለልማት ሥራ

በተጨማሪም አቶ ብርሃኑ አዱኛ ከ01/06/2004 እስከ 30/07/2004 ዓ.ም ድረስ የሚቆይ በመንግስት የተነደፈ የልማት ሥራ ላይ ሰዎች እንዲሳተፉ ለመቀስቀስ በ12/07/2004 ዓ.ም ጌረርሳ ከውነዋል፡፡ ይህ ሥራ የውሃ ጉድጓድ በመስራትና አግድም ቦይ በመቆፈር ውሃን የማስቀረት፣ እርከን በመስራትና የተበሉትን መሬት በመጠገን አፈርን ከመሸርሸር የማዳን ሥራ ነው፡፡ ሥራው የሚሠረው ገበሬዎች በህብረት በመውጣት ነው፡፡ ይህ ሥራ እንዲቀላጠፍና የሚሠራው ሀገርን ለማልማት መሆኑን እንደሚከተለው በጌረርሳ ገልጸዋል፡፡

| | |
|---|---|
| Ka'i kaa yaa dhiiroo | ተነሱ ጎበዞች |
| Biyyattii misoomsinaa | ሀገራችንን እናለማለን |
| Iyyummaa balleessinaa | ድህነትን እናጠፋለን |
| Doomaa keenya baattannee | መቆፈሪያችንን ይዘን |
| Daagaa keenya buufannee | እርከንን እንሥራ |
| Bishaan keenya hidhannee | ውሃችንን አቅበን |
| Biqiltuu biqilchinee | ችግኝን አፍልተን |
| Iyyummaa fililchinee. | ድህነትን አጥፍተን፡፡ |

መረጃ ሰጪው አቶ ብርሃኑ አዱኛ የሚኖሩበት ደኩ ቀርሳ ቀበሌ ቆላማ አከባቢ አብዛኛው ቦታዎች ከ20 ዓመት በፊት በደን የተሸፈነ ነበር፡፡ ነገር ግን የአከባቢው ማህበረሰብ የእርሻ ማሳዎችን ለማስፋፋት ደኑን መንጥረው በማጥፋታቸው አከባቢው ተራቁተዋል፡፡ ይህ ነው የሚባል ደን አይታይበትም፡፡ በመሆኑም በአከባቢው ዝናብ ወቅቱን ጠብቆ አይዘንብም፡፡ ይህ ሁኔታ በአከባቢው የሚመረተውን ምርት እንዲቀንስ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ የአከባቢው ሙቀትም እንድጨምር ምክንያት ሆነዋል፡፡ ስለዚህ ይህን ሁኔታ ለመለወጥ የልማት ሥራዎች መሠራት አለባቸው፡፡ ችግኞች ማፍላትና መተከል አለባቸው፡፡ እርከንና የውሃ ማቆሩ ሥራ ማፋጠን ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ለማፋጠን ማህበረሰቡ በህብረት በመውጣት መሥራትና ያለውን ሁኔት መቀየር አለበት (ብርሃኑ፣ 12/07/2004፣ 11፡30)፡፡ አቶ ብርሃኑም

ይህን ሁኔታ በመረዳታቸው ከላይ የተመለከተውን ጌረርሳ በመከወን ማህበረሰቡ ለሥራ እንዲነሳሳ አደረጉ፡፡

በአጠቃላይ አቶ ብርሃኑ አዱኛ ከላይ የተመለከቱትን ጌረርሳ ከላይ በተመለከቱት አጋጣሚዎች በመከወን ኑሮአቸውን ለማሸነፍ ያደረጉትን ተጋድሎና ማህበረሰቡን ለሥራ ለማትጋት ያደረጉትን አስተዋፅኦ ገልፀዋል፡፡ በከወኑት ጌረርሳ ያነሷቸው አበይት ይዘቶች ወደ ኦዶ ሻክሶ ሄደው ሰርተው ለማግኘት ያቀዱትን ገንዘብ በህመማቸው ምክንያት አለማግኘታቸውንና ወደ ትውልድ መንደራቸው ከተመለሱ በኋላ ተግተው በመስራታቸው ኑሮአቸውን ማሻሻላቸውን ነው፡፡ በተጨማሪም ተግቶ መስራት ከድህነት እንደሚያላቅቅና እንደሚያስከብር ገልጸዋል፡፡

## 4.3. አቶ ቸሩ ድንቁ የከወኑት ጌረርሳና የይዘት ትንታኔው

አቶ ቸሩ ድንቁ በ16/06/2004 ዓ.ም በ8፡00 (ስምንት ሰዓት) አቶ ድሪባ ጅማ ቤት በመገኘት ጌረርሳ ከውነዋል፡፡ በወቅቱ 25 ሰዎች በቦታው ነበሩ። ከመረጃ ሰጪዎቹ ውስጥ ከአቶ ቸሩ ድንቁ ውጪ አቶ ብርሃኑ አዱኛ በቦታው ተገኝተዋል፡፡ በዚያ ቦታ የነበረው ሁኔታ የአቶ ብርሃኑ ጌረርሳ ሲተነተን የቀረበ በመሆኑ አልደገምም፡፡ አቶ ቸሩ ድንቁ በቦታው የከውኑት ጌረርሳ ከነመነሻ ምክንያቱ እንደሚከተለው ይገኛል፡፡

### 4.3.1. ብድር መመለስ ባለመቻል ስለመሰደብ

አቶ ቸሩ ድንቁ ንብረት ባላፈሩበት ዘመን ይበደሩ ነበር፡፡ ተበድረው ችግራቸውን ከተወጡ በኋላ ብድሩን መመለስ /መክፈል/ ያቅታቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ አበዳሪው ወደ ቤታቸው ይመጣና ገንዘቡን እንዲመልሱለት ይጠይቃል፡፡ አቶ ቸሩ ገንዘቡን መመለስ ባለመቻላቸው ጊዜ እንዲሰጣቸው በተማጽኖ አበዳሪውን ይጠይቃሉ፡፡ አበዳሪው ግን ገንዘቡን በቶሎ እንዲሰጡት ይጠይቅና ካልሆነ እንደሚከሳቸው ዝቶ፣ አስጠንቅቆና ተሳድቦ ወደ ቤቱ ይመለሳል፡፡

አቶ ቸሩ ከሰው ተበድረው ለመመለስ በየሰው ቤት እየዞሩ ቢጠይቁም ምንም ሳያገኙ ይቀራሉ፡፡ ይህ የሆነው በ1987 ዓ.ም ነው፡፡ አቶ ቸሩ በወቅቱ ያጋጠማቸውን በ16/06/2004 ዓ.ም በከወኑት ጌረርሳ በሚከተለው ሁኔታ ገልጸውታል፡፡

| | |
|---|---|
| Iyyummaan maal na hingoonee | ድህነት ምን ያላደረገኝ ነገር አለ |
| Rafuu na dadhabsiisee | እንቅልፍ ከለከለኝ |
| Raatuu na ifachiisee | ደደብን አሰደበኝ |
| Liqeeffachuun maal qaba | መበደር ነውር ነው ወይ |
| Yoo nama ganan malee | ሰውን ከካዱ እንጂ |
| Lammii gaddisiisan malee | ወገንን ካሳዘኑ እንጂ |
| Fira qaanessan malee. | ዘመድን ካሳፈሩ እንጂ፡፡ |
| Yoo harkaa qabaatan | ከእጅ ካለ |
| Hundu fira ofiitii | ሁሉም ዘመድ ነው |
| Yoo harkaa dhaban | ከእጅ ከሌላ |
| Hoomtuu nama hinyaadatu | ማንም ሰውን አያስታውስም |
| Guyyaanillee hin naanna'u | ቀን እንኳን አይዞርም |
| Guyyaan namaa hin dhihuu | ቀን አይመሽም |
| Halkan namaa hin bari'u. | ሌሊትም አይነጋም፡፡ |

አቶ ቸሩ በዚህ ጌረርሳ እንደገለፁት ድህነት እንቅልፍ ከልክሏቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቀን እንዳይመሽላቸው ሌሊት እንዳይነጋላቸው አድርጓቸዋል፡፡ ቀን ጊዜውን ጠብቆ የሚሄድና የሚመጣ ቢሆንም ለተቸገረ ሰው ከጭንቀቱ የተነሳ ይረዝምበታል፡፡ የሚመሽለትና የሚነጋለት አይመስለውም፡፡ ሌሊት እንቅልፍ፣ ቀን እረፍት አይኖሩም፡፡ ምክንያቱም አበዳሪው ከአሁን አሁን መጣብኝ እያለ ይጨነቃል፡፡ ሁል ጊዜ ስጋት አይለያውም፡፡ አቶ ቸሩም በወቅቱ የሚከፍሉት ገንዘብ ስለሌላቸው አበዳሪው ይከሰኛል፣ ከሰው ፊትም ያዋርደኛል ብለው ይሰጉ ነበር፡፡ ስለዚህ እንቅልፍ አጥተው ተጨንቀውም ነበር፡፡ አበዳሪው በመንገድ ላይ በመጣባቸው ቁጥር ይደነግጡ ነበር(ቸሩ፣ 16/06/2004)፡፡ ይህ በመሆኑ መበደር ኃጥያት ነው ወይ? /መበደር ምን ችግር አለው?፣ መበደር ያሰድባልን? በማለት ይጠይቃሉ፡፡ ምክንያቱም አበዳሪው ሰድቧቸዋል፣ አንቋሿቸዋል፡፡ በመሆኑም የማይበደር አይኖርምና አበዳሪውን እስካልካድኩኝ ድረስ ለምን አሰደባለሁ በማለት ምሬታቸውን ገልፀዋል፡፡

#### 4.3.2. ስለ ድህነት አስከፊ ገጽታ

አቶ ቸሩ ከለይ ከተጠቀሰው ችግር (ድህነት) ለመላቀቅ ያደረጉትን ትግል፣ የደረሰባቸውን ችግር ደግሞ በ21/06/2004 ዓ.ም በአቶ አዱኛ ጅማ ቤት ተገኝተው በከወኑት ጌረርሳ ገልፀዋል፡፡ በወቅቱ የነበረው ሁኔታ የአቶ አባተ ጌረርሳ ስተነተን የቀረበ በመሆኑ አሁን መድገም አስፈላጊ አይደለም፡፡ በአቶ አዱኛ ጅማ ቤት ከአራቱ መረጃ ሰጪዎቹ ጋር በመሆን የከወኑት ጌረርሳ የሚከተለውን ይመስል ነበር፡፡

| | |
|---|---|
| Raafuu nyaadhetanii | ጎመን በልቼ ነው ዘመኑን ያሳለፍኩት |
| Waan Charuu Dinquu ta'e hinbeektuu | አታውቅም ቸሩ ድንቁ የሆነውን |
| Daagussaa nyadheetanii | ዳጉሳንም በልቼ |
| Xaafii kiraa haameetanii | ጤፍ በኪራይ አጭጄ |
| Haati koo yaa ilma koo | እናቴ እማምዬ |
| Hinbadin naan jettee | ልጄ ሆይ አትጥፋ አለችኝ |
| Mudhiitti na hidhattee | ወገቧ ላይ አሰረችኝ |
| Daandii baaburaarraa na deebiftee. | ከመንገድ ላይ መለሰችኝ፡፡ |

ጎመን መብላት ያለ ቢሆንም ከሌሎች የምግብ አይነቶች ጋር ሳያፈረርቁ ብቻውን ለረጅም ጊዜ መብላት ድህነት ዬቱን ያህል ሥር የሰደደ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይህ መረጃም ሰጪ የችግር ጊዜውን ለማሳለፍ የቻሉትን አስከፊ ኑሮ ገፅታ ያመለክታል፡፡ በአከባቢው ጎመንን ሳያቋርጡ በተከታታይ ለረጅም ጊዜ መብላት የድህነት ምልክት ተደርጎ ይታመናል፡፡

በተጨማሪም ይህ መረጃ ሰጪ የሚኖሩበት ቦታ ዳጉሳ አይበላም፡፡ እንደ ማንኛውም ሳር ይቆጠራል፡፡ በአከባቢው በብዛት የለም፡፡ እንደቃርሚያ ተፈልጎ የሚገኝ ነው፡፡ በዚህ አካባቢ ዳጉሳን መብላት ሳርን እንደመብላት ይቆጠራል፡፡ ይህ ደግሞ ከክብት እኩል የሚያስቆጥር ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በዚያን ዘመን መረጃ ሰጪው (አቶ ቸሩ ድንቁ) በጣም ችግረኛ እንደነበሩ እንድንገነዘብ ያደርገናል፡፡ አቶ ቸሩ በድህነታቸው ምክንያት ከአቅም በላይ የሆነውን አስከፊ ችግር በቆራጥነት ችሎ እንዳለፉም እንረዳለን፡፡

#### 4.3.2.1. ወደ ሞጆ ሥራ ፍለጋ ስለመሄድ

ከላይ ከተጠቀሰው ጌረርሳ አቶ ቸሩ ከሀገር ለመጥፋት ሲሉ እናታቸው ከመንገድ እንደመለሷዋቸውም እንረዳለን፡፡ ነገር ግን እናታቸው ከመንገድ እንደመለሱዋቸው በዚያው አልቀሩም፡፡ ከትውልድ ቦታቸው ርቀው ሄደዋል፡፡ ይህን ጉዞ ያደረጉት ወደ ምስራቅ ሸዋ ሞጆ ወደ ተባለ ቦታ ነው፡፡ ወደ ሞጆ የሄዱት ተቀጥረው ጤፍ ለማጨድ ነበር፡፡ ተሳክቶላቸው ወደ ተመኙት ሄደዋል፡፡ በሄዱበት ቦታ ያጋጠማቸውን ደግሞ በጌረርሳ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡

| | |
|---|---|
| Ka'eetan biyyaa ba'ee | ተነስቼ ከሀገር ወጣሁ |
| Yeroon biyyaa ba'u | ከሀገሬ ስወጣ |
| Yaa abbaa koo hin jenne | አባቴን አላማከርኩም |
| Yaa haadha koo hin jenne | እናቴን አላማከርኳትም |
| Nan beela'e hin jennee | ይርበኛል አላልኩም |
| Nan dheebodhe hin jennee | ይጠማኛል አላልኩም |
| Mudhii koo jabeefadhee. | ወገቤን ጠበቀ አድርኩ፡፡ |
| Hoggaan majoodhaan ba'u | ሞጆ የደርስኩት |
| Baabura malee maaliree | ነው እንጂ በመኪና |
| Hoggaan of cinaa ilaalu | ዙሪያዬን ስመለከት |
| Kophaa koo malee maaliree | ነኝ እንጂ ብቸኛ። |
| Yaa haadha koon jedhee | ወይኔ እናቴ አልኩኝ |
| Yaa abbaa koon jedhee | ወይኔ አባቴ አልኩኝ |
| Of cinaadhaa dhabnaanii | ከጎኔ ሳጣቸው |
| Garaan na raase kaa | ሆዴ ተላወሰ |
| Akka gommaa makiinaa | እንደ የመኪና ጎማ |
| Keessa saa gongaa godhee. | ውስጡን ባዶ አድርገው፡፡ |
| Haadha koo haadhattittii | እናቴ እማምዬ |
| Ishee homaa hin dadhabnee | ምንም የማያቅታት |
| Ishee sabbata kuulaa | መቀነቷ የጠበቀ |
| Giiftii mana baksaadhaa | የምታበላ ንጥር ቅቤ |
| Kaatteetoo na dhaqqabdee | ሮጣ ደረሰችልኝ |
| Yaa ilma koo naan jettee | ልጄ ሆይ አለችኝ |
| Ka'i ni gallaa jettee | ተነስ እንግባ አለችኝ |
| Mudhiitti na hidhattee | ወገቧ ላይ አሰረችኝ |

| | |
|---|---|
| Lubbuu koo na baraartee | ህይወቴን ታደገችኝ |
| Tole yaa haadha koon jedhee | እሺ እናቴ አልኩኝ |
| Deebi'een garagalee. | ተመልሼ ገባሁኝ፡፡ |
| Yeroon deebi'ee galuu | ተመልሼ ቤት ስገባ |
| Ni boo'e kaa hiriyyaan koo. | አለቀሰ ጓደኛዬ፡፡ |

አቶ ቸሩ ድንቂ ወደ ምስራቅ ሸዋ ዞን ሞጆ አካባቢ የሄዱት በ1993 ዓ.ም ነበር፡፡ የሄዱበት ምክንያት ሥራ ፍለጋ ነው፡፡ ጤፍ አጨዳን ጨምሮ የተለያዩ ሥራዎችን ሠርተው ገንዘብ አጠራቅመው ወደ ትውልድ ቀዬአቸው ለመመለስ ነበር፡፡ ነገር ግን ለተወሰኑት ሳምንታት ብቻ በሞጆ ጤፍ አጨዳውን ከሠሩ በኋላ እናታቸው ወ/ሮ ድርቢ ሬባ ፈልገው አግኝተዋቸው ወደ ትውልድ ቤታቸው መልሰዋቸዋል፡፡ ሞጆ በነበሩበት ጊዜ ጤፍ አጭደው ያገኙትን ገንዘብ 400 (አራት መቶ) ብር ይዘው ገብተዋል(ቸሩ፣ 21/06/2004፣ 6፡00)፡፡

ከላይ የሰፈረው ጌረርሳ አቶ ቸሩ ሞጆ በነበሩበት ጊዜ ከጎናቸው አባቻቸውንና እናታቸውን ሲያጡ የተሰማቸውን ስሜት የሚገልጽ ነው፡፡ ምንም እንኳን አቅደው (አስበው) ቢሄዱም የሄዱበት ቦታ ከዚህ በፊት አይተው የማያውቁ በመሆኑ ተጨንቀዋል፤ ተጠበዋል፡፡ ይህን የጭንቀታቸውን ጥልቀት ለመግለጽ የሆዳቸው መላወስ ከሚጓዘው (ከሚሽከረከረው) የመኪና ጎማ ጋር በማነጻጸር አመልክተዋል፡፡ "ወይኔ አባቴ ወይኔ እናቴ" ማለትም በወቅቱ የነበረባቸውን ውጥረት ያሳያል፡፡

#### 4.3.3. አቶ ቸሩ ንብረት በማፍራት ክብር ስለማግኘታቸው

አቶ ቸሩ በወቅቱ ቢጨነቁም ወዲያው ወደቤታቸው አልተመለሱም፡፡ እናታቸው እስኪደርሱላቸው ድረስ በቦታው ቆይተዋል፡፡ ከላይ የተጠቀሰውን ገንዘብ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ቢያገኙም ከቤተሰብ ለመጀመሪያ ጊዜ በመለየታቸው አጋጣሚውን አልወደዱትም፡፡

ሞጆንም እንደጠበቁ አላገኙዋትም፡፡ ሞጆ የተቀበለቻቸው አልጋ በአልጋ ሆና አይደለም፡፡ በሞጆ ርቧቸዋል፣ ጠምቷቸዋል፡፡ በሞጆ ብቸኝነትም ተሰምቷቸዋል፡፡ ስለዚህ የእናታቸውን "የተመለስ" ትእዛዝ ተቀብለው ገብተዋል፡፡ ከሞጆ ባገኙት ገንዘብ ፍየሎችን በመግዛት አርብተው ላም ከዚያም በኋላ በሬ እስከ መግዛት ደርሰዋል፡፡ ከዚያም በዚህ ተበረታተው ሬጅ ከተማ ውስጥ በቡና ቤትና በዘይት

መጭመቂያ ፋብሪካ ውስጥ ተቀጥረው ሰርተዋል፡፡ እነዚህ ስራዎች በህይወታቸው ላይ ለውጥ አምጥተዋል፡፡ በሬ ጠምደዋል፤ ላሞችንም ገዝተዋል፡፡ ኑሮዋቸውም ተሸሽሏል(ቾሩ፣ 12/07/2004)፡፡ አቶ ቾሩ ኑሮአቸው ከተሻሻለ በኋላና በፊት በሰዎች ፊት /ዘንድ/ ያላቸው አክብሮት ወይንም ሰዎች እንዴት ሲመለከቱዋቸው እንደነበር አጋጣሚውን በ12/07/2004 ዓ.ም በአቶ ድዳ ዳዲ ቤት በመከወኑት ጌረርሳ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

| | |
|---|---|
| Dur qotiyyoo hin qabu | ድሮ በሬ አልነበረኝም |
| Inyiin qotadha malee | እኝ አርሳለሁ እንጂ |
| Dur niitii hin qabu | ድሮ ሚስት የለኝም |
| Si gabaan gala malee. | ወደ ባል የሞተባት ሴት እሄዳለሁ እንጂ፡፡ |
| Ergan qotiyyoo xamadadhee | በሬ ከገዛሁ በኋላ |
| Haadha manaas argadhe | ሚስትም ካገኘሁ በኋላ |
| Maatii koos horadhe | ልጆችም ካፈራሁ በኋላ |
| Guddinni kana caalu hin jiru | ይህን የሚያክል እድገት የለም |
| Xinnaa guddaan na waama | ትልቁም ትንሹም ይጠሩኛል |
| Yaa abbaa Girmaa naan jedhuu | የግርማ አባት ይሉኛል |
| Yaa Charuu noori jedhuuu. | ቾሩ ኖር ይሉኛል፡፡ |
| Dur immoo yaa jooraa jedhuu | ድሮ ዘዋሪ ይሉኛል |
| Eessaa dhufte naan jedhu | ከየት መጣ ይሉኛል |
| Har'a noorii as taa'i jedhu. | አሁን ኖር እዚህ ተቀመጥ ይሉኛል፡፡ |

ከላይ በተጠቀሰው ጌረርሳና አቶ ቾሩ ድንቂ ከነገሩኝ ታሪካቸው እንደምንረዳው ንብረት ባልነበራቸው ጊዜና ከማግባታቸው በፊት ኑሮአቸው በጣም አስቸጋሪ ነበር፡፡ በሬ ከመግዛታቸው በፊት በሰው ቤት እያገለገሉ የጉልበታቸውን ምትክ በሬ ለተወሰኑ የእርሻ ቀናት ብቻ ይሰጡዋቸው/ ያውሱዋቸው/ ነበር፡፡ ለራሳቸው ያርሱና አሁንም ለሰው እየሠሩ በሬውን ለጥቂት ቀናት ያገኙ ነበር፡፡ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ኑሮአቸውን ይገፉ ነበር። ከሰው ፊትም ክብር አልነበራቸውም፡፡ ማንም ሰው "ኖር" አይላቸውም፡፡ "ከየት መጣህ ደግሞ!" እየተባሉ በንቀት ይጠየቁ ነበር፡፡ መረጃ ሰጪው በሚኖሩበት አከባቢ "ኖር" የክብር መግለጫ ነው፡፡ እንዳውም " Namni noorii gabbata" ትርጉሙ " ሰው በኖር ይከበራል" ይባላል፡፡ የፍቅር መግለጫም ጭምር ነው (አቶ ቾሩ፣ 12/07/2004፣ 6፡10)፡፡

"ከየት መጣህ ደግሞ" ንቀት ነው:: የሰውን መምጣት መጥላትን ያሳያል:: ስለዚህ ሰው ሰውን ሲጠላ ወይንም ወደቤቱ መምጣቱን ሲጠላ ነው ይህንን አባባል የሚጠቀመው:: አቶ ቸሩም ደሃ በነበሩ ጊዜ "yaa jooraa" ማለት "ዘዋሪ" ተብለው እንደነበርና አሁን ንብረት ካፈሩ በኋላ ደግሞ

| | |
|---|---|
| Yaa abbaa Girmaa naan jedhuu | የግርማ አባት ይሉኛል |
| Yaa Charuu noori jedhuuu. | ቸሩ ኖር ይሉኛል:: |
| Har'a noorii as taa'i jedhu. | አሁን ኖር እዚህ ተቀመጥ ይሉኛል:: |

በማለት መቀመጫ ሰጥቷቸው በአክብሮት እንደሚያስቀምጡአቸው አጋጣሚውን በጌረርሳ ገልጸዋል::

#### 4.3.4. ስለልማት ሥራ

አቶ ቸሩ ድንቁ አባታቸው በ1996 ዓ.ም ከዚህ ዓ.ም በሞት የተለዩ ሲሆን የአባታቸውን ንብረት በመውረስ እያለሙ ይገኛሉ:: ያርሳሉ፣ ከብቶች ያረባሉ፣ አትክልቶችን ያለማሉ:: አሁን ከራሳቸው አልፎ ለናታቸው ሬጅ ከተማ ውስጥ 42 ሉክ ቆርቆሮ ቤት ሰርተውላቸው በከተማ ይኖራሉ:: አቶ ቸሩ አሁን እየሠሩ ያሉትን የልማት ሥራ በጌረርሳ የገለጹበት ሁኔታ፡

| | |
|---|---|
| Noori kaa noori noorii | ኖር እንጂ ኖር ኖር |
| Noori yaa hojii misooma | ኖር የልማት ሥራ |
| Yeroon misooma babal'ina | የልማት ጊዜ ዕድገት ነው |
| Qotanii qofforanii | አርሰው ቆፍረው |
| Callaa misoomaa argatu | የልማት ፍሬን ያገኛሉ |
| Yeroon darbe yaa baduu | ያለፈው ዘመን ይጥፋ |
| Yeroon bade yaa darbu | የጠፋው ዘመን ይለፍ |
| Kan dhufu yaanna malee | የሚመጠውን እናስባለን እንጂ |
| Yeroon misoomaa ni qonnaa | ጊዜው የልማት ነው እንረስ |
| Qofforreet aramannaa | ቆፍረን እናርም |
| Dubbii namaa hindhaqnu | የሰውን ነገር አናነሳም:: |
| Caccabaa galabaadhaa | የተሰባበረውን ገለባ |
| Horiitu nyaata malee | ከብቶች ይበሉታል እንጂ |
| Mana hin ijaarrannuu | ቤት አንሠራበትም |
| Tattaaffi misoomaa malee | ለልማት መፍጠን እንጂ |

| | |
|---|---|
| Dubbii darbee hin kaafnuu | የሰውን ነገር አንፈልግም |
| Jedheetan itti badee | ብዬ ጠፋሁበት |
| Yeroon gara misoomaa | ወደ ልማት ሥራ በጊዜ |
| Akka dirii ijji badee. | ውል እንደጠፋው ድር፡፡ |

አቶ ቸሩ ድንቁ በችግር ያሳለፉትን ጊዜ መርሳት ይፈልጋሉ። ምክንያቱም ያ ዘመን ደስታና ሰላም ያልነበራቸው ዘመን ነበር፡፡ ያን ዘመን ያሳለፉበትን ሁኔታ እያነሱ ጌረርሳ ሲከውኑ ከፊታቸው ሀዘንና ቁጭት ይነበባል፡፡ እሳቸውም ዘመኑን በሀዘን እንደሚያስታውሱ ነግረውኛል (ቸሩ 12/07/2004፣ 6፥10) ፡፡ ስለዚህ፡

"ያለፈው ዘመን ይጥፋ
የጠፋው ዘመን ይለፍ"

በማለት ዘመኑ አስከፊ የመከራ ዘመን በመሆኑ እንደገና አይምጣ፡፡ ከአእምሮዬ ይሰረዝ፡፡ አሁን ማሰብ ያለብኝ ስለልማት ሥራ ብቻ ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡ የልማት ሥራውን ስንሠራ ከሰው ከንቱ ነገር እንራቅ፡፡ ትኩረታችንን በልማት ሥራ ላይ ብቻ እናድርግ በማለት ማህበረሰቡንም ለሥራ ያነሳሳሉ፡፡ የሰውን ነገር በመተው እሳቸው ትኩረታቸውን ልማት እንዳደረጉ ያስረዳሉ፡፡ በማህበረሰቡ አንዳንድ ሰዎች ሰዎችን ከልማት ሥራ የሚያደናቅፉ አልባሌ ነገሮችን እያወሩ ሰውን የሚያጣሉ በመሆኑ ከዚህ አልባሌ ነገር መራቅ አለብን ብለው ይመክራሉ (ቸሩ፣ 12/07/2004፣ 6፥10) ፡፡

#### 4.3.5. ስለ አባታቸው ሞት

አቶ ቸሩ ድንቁ ለወላጆቻቸው ወንድ ልጅ እሳቸው ብቻ ናቸው፡፡ ሁለት እህቶች ያላቸው ቢሆንም እነሱም አግብተው ትዳር ይዘዋል፡፡ እናታቸውም ከላይ እንደተጠቀሰው በሬጅ ከተማ ውስጥ ይኖራሉ፡፡ አባታቸውም ስለሞቱባቸው ከባለቤታቸውና ልጆቻቸው ውጪ በሃሳብ የሚያግዛቸው፣ ችግራቸውንና ደስታቸውን የሚጋሩቸው የቅርብ ዘመድ የላቸውም፡፡ በመሆኑም አንዳንዴ ብቸኝነት ይሰማቸዋል፡፡ ይጨንቃቸዋልም፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ የሚከተሉትን ጌረርሳ ይከውናሉ፡፡

| | |
|---|---|
| Qarqabaa doobbii wayyaa | ለመጫኛ ዶቢ ይሻላል |
| Yoo cite baduu baatee | ተበጥሶ ካልጠፋ |

| | |
|---|---|
| Ilmaa tokkicha wayyaa | ወንድ ልጅ አንድ ይሻላል |
| Yoo du'ee baduu baatee. | ሞቶ ካልጠፋ፡፡ |
| Abbabba lafa biraa | አባዬ አባብዬ |
| Kan yaanni kee na biraa | ከኔ ጋር የሆነ ናፍቆትህ |
| Abbaabbaa qoma kittaa | አባቴ ክታ የምትለብስ |
| Hormaa beeljigii bittaa | ለሰው ቤልጂግ ትገዛለህ |
| Ana maa gara diddaa | ለኔ ለምን ሆድህ ይጨክናል |
| Abbaabbaa nugusa koo | አባቴ የኔ ንጉስ |
| Situ beekaa dhukkuba koo. | የምታውቀው ህመሜን፡፡ |
| Kombolcha goodaa jiruu | በሜዳ ውስጥ ያለ የኮምቦል እንጨት |
| Gaafa aduuf qorichaa | ለፀሐይ ጊዜ መድሃኒት ነው |
| Abba namarra jiruu | በህይወት ያለ አባት |
| Gaafa dubbiif qorichaa | ለችግር ጊዜ መድሃኒት ነው፡፡ |
| Abbaabbaa Nugusa koo | አባቴ የኔ ንጉስ |
| Situ beekaa dhukkuba koo. | የምታውቀው ህመሜን፡፡ |

ከላይ እንደተገለፀው አቶ ቸሩ ወንድም የላቸውም፡፡ ከአጎታቸውና በጉርብትና ካፈሩዋቸው ጓደኞች ውጪ በችግር ጊዜ የሚደርስላቸው ሰውም ስለሌላቸው አንዳንድ ጊዜ ብቸኝነት ይሰማቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ከላይ የተገለጸውን ጌረርሳ ይከውናሉ፡፡ አባታቸው በሕይወት ቢኖሩ ብቸኝነት እንደማይሰማቸው ይገልፃሉ፡፡ ምክንያቱም "አባት" በችግር ጊዜ ለልጁ መውጫ የሚፈልግለት፣ በሃሳብ የሚያግዝና መካሪም ነው፡፡ አቶ ቸሩ በዚህ ጌረርሳ የአባት ተገንነት ከዛፍን ጥላነት ጋር በማነፃፀር ገልፀዋል፡፡ ዛፍ -ሰዎች ከፀሐይ ቃጠሎ ለመሸሸ ይጠለሉበታል፡፡ ማንገደኛም ቢሆን በጥላው ሥር በማረፍ እረፍት ያገኝበታል፡፡ ለሚጠብቀው ጉዞም ጉልበቱን ያሰባሰብበታል፡፡ በመሆኑም አባትም ለልጁ በችግር ጊዜ በምክርም ሆነ በገንዘብ በመርዳት መከታ ይሆንለታል፡፡ ተሞክሮውን በማካፈል መላ ዘይዶ ከችግሩ እንዲላቀቅ ያደርገዋል እንጂ፡፡ የራስን ልጅ ችግር የሚረዳ በመሆኑ ልጁ ሲጨነቅ በጭንቀቱ ጊዜ አይለየውም፡፡ ጥላ ከለላ ይሆነዋል፡፡ አቶ ቸሩም አባታቸው በሕይወት ቢኖሩ መከታ እንደሚሆኑላቸው በማሰብ "የኔም አባት በህይወት ቢኖር አሁን ይረዳኝ ነበር" ይላሉ(ቸሩ፣ 12/07/2004፣ 6፡10)፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ አቶ ቸሩ ይህን ጌረርሳ እንደመፅናኛም ይጠቀሙበታል፡፡ ምንም ብቸኛ ቢሆኑም እንኳን ሞት እስካልመጣ ደረስ ወንድ አንድ ይሻላል እያሉ ራሳቸውን ያበረታታሉ፣ ብቸኝነታቸውን መርሳት ይሞክራሉ፡፡

ከላይ እንደተመለከተው አቶ ቸሩ በተለያዩ ሦስት አጋጣሚዎች ጌረርሳ በመከወን ያሳለፉትን የህይወት ውጣ ውረድ ገልፀዋል፡፡ በድህነታቸው የደረሰባቸውን መንገላታትና ስድብ፣ ባደረጉት ተጋድሎ ያሳዩትን የኑሮ መሻሻል፣ ያገኙትን ክብርና የአባታቸው ሞት ያደረሰባቸውን ተፅእኖ ገልፀዋል፡፡

## 4.4. አቶ ድሪባ ለታ የከወኑት ጌረርሳ ላይ የተደረገ ትንተና

አቶ ድሪባ ለታ በ21/06/2004 ዓ.ም ከአራቱ መረጃ ሰጪዎች ጋር ከ6፡00-11፡30 በአቶ አዱኛ ጅማ ቤት በመገኘት ጌረርሳ ከውነዋል። አቶ አባተ ኤጀርሣ የከወኑት ጌረርሳ ላይ ትንታኔ ሲካሄድ በዚሁ በተጠቀሰው በአቶ አዱኛ ጅማ ቤት የነበረው አጋጣሚ ላይ በመገኘት ነው። በዚሁ ዕለት አቶ ደሪባ ለታ በሕይወት ዘመናቸው ያጋጠማቸውን ገጠመኞችና የአሁኑን ኑሮአቸውን ጌረርሳ በመከወን አቅርበዋል። ካቀረቡት ገጠመኞቻቸው ውስጥ፣

### 4.4.1. ስለ ባለቤታቸው ሞት

አቶ ድሪባ ለታ በ21/06/2004 ዓ.ም ጌረርሳ በመከወን ከገለፁት ገጠመኞቻቸው መካከል የትዳር አጋራቸው የሞቱበትን አጋጣሚ ነው ። ባለቤታቸው ወ/ሮ ጌጤ ድሪባ ከአቶ ድሪባ ለታ ጋር በትዳር ለ28 ዓመት ከኖሩ በኋላ በህመም ምክንያት በ2000 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። አቶ ድሪባና ወ/ሮ ጌጤ ስምንት ልጆችን አብረው አፍርተዋል። አቶ ድሪባ ባለቤታቸው በመሞታቸው የተሰማቸውን ስሜት በተደጋጋሚ በከወኑት ጌረርሳ ገልፀዋል። ጌረርሳውን ሲከውኑ ሀዘን እየተሰማቸውና እምባቸው እየወረደ ነው። ጌረርሳውን ሲከውኑ አንገታቸውን ደፍተው ቀዝቀዝ ባለ ሁኔታ ወድያ ወድህ በመንቀሳቀስ ነው። የከወኑት ጌረርሳም እንደሚከተለው ቀርቧል።

| | |
|---|---|
| Si waamuu laataa | ልጥራሽ ወይ |
| Nan gatee laataa | ራሰኋት /ጠልኋት/ ወይ |
| Geexee too nan gatee laataa | ጌጤዬን ራሰኋት ወይ |
| Salaalettan badee laataa | ወደ ሰላሌ ጠፋሁ ወይ |

| | |
|---|---|
| Niitiin ofii yaa jaalee | የራስ ሚስት አንተ ሰው |
| Yoo du'an mataa namaa muratti | ሲሞቱ ፀጉሯን ትላጫለች |
| Nitii hormaa yaa jaalee | የሰው ሚስት አንተ ሰው |
| Yoo du'an sigabaa galfattii. | ሲሞቱ ውሽማ ታስገባለች፡፡ |
| Marga maltu jira | ምን ሳር አለ |
| Furaa maaltu jira | ምን ሳር አለ |
| Moo yaa fura gaarii! | አይ ጥሩ ሳር! |
| Nama maaltu jira | ምን ሰው አለ |
| Moo yaa nama gaarii! | አይ ጥሩ ሰው! |
| Si ilbaanyi yaa saree | ላንተ ይብላኝ አንተ ውሻ |
| Kan marqaa koo nyaattee | ገንፎዬን የበላህብኝ |
| Sii ilbaany yaa biyyee | ለአንተ ይብላኝ አንተ አፈር |
| Kan niitii koo nyaattee. | ሚስቴን የበላህብኝ፡፡ |

እንኳን ለ28 ዓመታት ለአንድ ሳምንት አብረው የኖሩት ሰው በሞት ከሰው ሲለይ ሀዘኑ ልብ ይሰብራል፡፡ በተለይ የትዳር አጋር ሲሆንማ ሀዘኑ መራር ይሆናል፡፡ ኑሮን ያመሰቃቅላል፡፡ ሞራል ይሰብራል፣ የመኖርን ተስፋ ያጨልማል፡፡ ስለሆነም ባለቤታቸው በመሞታቸው አቶ ድሪባ አዝነዋል፡፡ በየአጋጣሚው ስለባለቤታቸው ሳያነሱ አያልፉም፡፡ እኔ መረጃውን ስሰበስብ ባገኘሁዋቸው ጊዜያት ሁሉ ስለባለቤታቸው ሳያነሱ ያለፉበት ጊዜ የለም፡፡ ምክንያቱም ባለቤታቸው በመሞታቸው ኑሮአቸው ከነበረው አሽቆልቁሏል፣ ልጆቻቸው ተበታትነዋል፡፡ እሳቸውም ለረጅም ዘመናት ከኖሩበት ቀዬ ተፈናቅለዋል፡፡ ለዘመናት የኖሩበት ቤትም ፈርሷል፡፡ አቶ ድሪባ እንደ ነገሩኝ ኑሮአቸውን አደራጅተው ይመሩ የነበሩት ባለቤታቸው ናቸው፡፡ ባለቤታቸው ከሞቱ በኋላ ግን እሳቸው መምራት እንዳልቻሉና ጥቂት ጊዜያት ውስጥ ያፈሩት ንብረት መውደሙን ይገልፃሉ፡፡ በዚህ የተነሳ ልጆቻቸው ተበታተኑ፣ ቤታቸውም ፈረሰ (ድርባ ለታ፣ 21/06/2004)፡፡

መሆኑም አቶ ድሪባ ባለቤታቸው በጣም ደግ ሰው መሆናቸውን በመግለፅ የራስ ሚስት ሰው ሲሞት አዝና አልቅሳ እንደምትቀብር "የራስ ሚስት ሲሞቱ ፀጉሯን ትላጫለች" በማለት ገልጸዋል። ሌላ ሴት (ሌላ የውጭ ሴት ወይንም ፍቅረኛ) ግን ሰው ሲሞት ሌላ ወንድ እንደምታስገባና ስለሚቹ ምንም እንደማትጨነቅ "ሌላ ወንድ

ታስገባለች" በማለት ከራስ ሚስት ጋር በማወዳደር ሚስት ለባል አስፈላጊ እንደሆነች አመላክተዋል፡፡

በመቀጠል "ላንተ ይብላኝ አንተ አፈር" በማለት የባለቤታቸው መሞት መራር ሀዘን እንደሆነባቸው ገልፀዋል፡፡ ማንም ሴት ከራስ ሚስት ጋር እንደማትወዳደር በመግለፅ የተሰማቸውን ሀዘን ጥልቅ መሆኑን በ21/06/2004 ዓ.ም በከወኑት ጌረርሳ አሳይተዋል፡፡

### 4.4.2. በባለቤታቸው ሞት የተነሳ ስለልጆቻቸው መበተን

በመቀጠል ባለቤታቸው በመሞታቸው አቶ ድሪባ ለታና ልጆቻቸው ለረጅም ዘመን የኖሩበትን ቀዬ ለቀው መበታተናቸውን በሚከተለው ጌረርሳ ገልፀዋል፡፡

| | |
|---|---|
| Odoo kormi jiruu | ኮርማው እያለ |
| Effanni hin bookkisu | ወይፈን አያገሳም |
| Osoo kan du'e galee | የሞተ የሚገባ ቢሆን |
| Jiraan hin roorrisu | ያልሞተው አያቅራራም |
| Qe'een hin fokkisu. | ቀዬው አያስጠላም፡፡ |
| Yaa qeesii Goorgisii | የጊዮርጊስ ቄስ |
| Daawitii gombisii | ዳዊቱን ገልብጠው |
| Yaa qe'ee abbaa hinqabane | ባለቤት የሌለው ቀዬ |
| Situ ofirratti jibbee | አንተ ነህ የገፋሃው |
| Ta'iitii fokkisii | ተቀመጥ እንዳስጠላህ |
| Yaa qe'ee abbaa qabuu | ባለቤት ያለው ቀዬ |
| Situ ofirra bulchee | በራስህ ላይ አኑረሃል |
| Ta'iitii roorrisii. | ተቀመጥ እንደኮራህ፡፡ |
| Raase kaa raase raasee | ነቀነቀ ነቀነቅ |
| Odolchi gilaashii raasee | ፈረስ ግላሱን |
| Makiinaan gommaa raasee | መኪና ጎማውን |
| Qotiyyoon qambara raasee | በሬ ቀንበሩን |
| Maarashaan lafa raasee | ማረሻ መሬቱን እንደሚነቀንቀው |
| Gaddis garaa na raase. | እኔንም ሀዘን ሆዴን አላወሰው፡፡ |

ከላይ እንደተመለከተው አቶ ድሪባ ለረጅም ጊዜያት የኖሩበት ቤት እየፈራረሰ ይገኛል። የሚኖርበትና የሚንከባከበው ሰው የለም። አቶ ድሪባ ያንን ቀዬ ሲመለከቱ፣ የባለቤታቸውን ትዝታ ይቀሰቅስባቸዋል። በመሆኑም ቤቱን ማየትም የስጠላቸዋል። ስለዚህ ቀዬው ተንከባካቢ አቷል። በዚህ ምክንያት ነው ነዋሪ ያለውንና ነዋሪ የሌለበት ቀዬ በማነፃፀር የገለፁት። ነዋሪ ያለው ቀዬ ያስደስታል፡፡ ምክንያቱም ተንከባካቢ አለው። ይለማል፤ አትክልት ይተከልበታል፡፡ አበቦችም እየተተከሉ ቀዬው አስደሳች ይሆናል፡፡ ነዋሪ የሌለበት ግን በተቃራኒው ያስጠላል፡፡ ተንከባካቢ የለውም፡፡ አበቦች፣ አትክልቶች አይታዩበትም፡፡ ልጆች አይቦርቁበትም፡፡ ምንም የሚያማምሩ ነገሮች አይታይበትም፡፡ በአቶ ድሪባ ለታ መኖሪያ ለረጅም ጊዜ እየቦረቁ የኖሩበት ስምንት ልጆቻቸው ሌሎች ሰዎች ቤት በእረኝነትና በአራሽነት በመቀጠር ሌሎች ደግሞ አዲስ አበባን ጨምሮ ወደ ሌሎች ከተሞች በመጥፋታቸውና አቶ ድርባም ከተወለዱበት ጊዜ ጀምሮ ለ51 ዓመታት የኖሩበትን ቀዬ ለቀው ሬጅ ከተማ በመግባታቸው ቀዬው ነዋሪ አጥቷል፤ የሚያለማው የለም፡፡ በመሆኑም አቶ ድሪባ ለታ ሁለቱን ሰዎች የሚኖሩበት ቀዬንና ነዋሪ የሌለውን ቀዬ በማወዳደር ነው ነዋሪ ያለበት ማስደሰቱን፤ ነዋሪ የሌለበት ደግሞ ማስጠላቱን ያመለከቱት፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን "የሞተ ሰው ተመልሶ የሚገባ" ቢሆን ያልሞቱት ተበታትነው እንደማያስቸግሩ ገልጸዋል፡፡ ተፈጥሮ አትፈቅድም እንጂ ባለቤታቸው ተመልሰው የሚነሱ ቢሆን ልጆቻቸው ከተበተኑበት ተሰብስበው እንደሚገቡ ቀዬያቸውን እንደሚያሳምሩ ስለሚያስቡ ነው፡፡ ምክንያቱም የልጆቻቸው መበተን ዋና ምክንያት የእናታቸው ሞት ስለሆነ፡፡

አቶ ድሪባ የፈረሰውን ለረጅ ጊዜ የኖሩበት ቀዬ ሲመለከቱ ሀዘን ይሰማቸዋል፡፡ ሀዘናቸውን ከፈረስ ግላስ፣ ከመኪና ጎማ፣ ከበሬ ቀንበር መነቅነቅና ከማረሻ መሬትን መገልበጥ ጋር አወዳድረው ዜይቤያዊ በሆነ መልኩ ገልጸዋል፡፡ ከተሰማቸው ሀዘን ጋር ተወዳድረው የቀረቡት ነገሮች የፈረስ ግላስን ማራገብ፣ የመክና ጎማን ማሽከርከር፣ የበሬ ቀንበርን መነቅነቅና የማረሻ መሬትን መገልበጥ የሀዘናቸውን ክብደት የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በባለቤታቸው ሞት መጎዳታቸውን ለመግለፅ የተጠቀሙትን ቋንቋ የሚያሳይ ነው ፡፡

በተጨማሪም አቶ ድሪባ ባለቤታቸው ለቤታቸው ምሰሶ፣ ለኑሮአቸው መሠረት፣ ለቤተሰባቸው ሰብሳቢ መሆናቸውን፣

| | |
|---|---|
| Haadha warraatoo yaa giiftii | ባለቤቴ የኔ እመቤት |
| Daangulee morma looshaa | ቆንጅዬ ለግላጋዋ |
| Kan hortee qe'ee guutte | ወልደሽ ቤቴን የሞላሽ |
| Kan laatte garaa kaafte | አብልተሽ ያጠገብሽ |
| Jiitu harka baksaadhaa | እጅሽ ቅቤ ያበላኝ |
| Hutubaa mana kootii | ለቤቴ ምሰሶ የሆንሽ |
| Ammaartee namaa laatta | የምትሰጪ አፍሰሽ |
| Obaaftee nadha baafta | የምታረኪ አጠጥተሽ |
| Siif jechan alaa gala. | ላንቺ ስል ወደ ቤት እገባለሁ፡፡ |
| Hiriyyaan yoo na jibbe | ጓደኞቼ ቢጠሉኝ |
| Hawaasni yoo na nuffe | ማህበረሰቡም ቢያገልለኝ |
| Amajaajiin natti inaafe | ጠላቴም ቢዝትብኝ |
| Kan kee jaalalli itti fufe | ያንቺ ፍቅር አልተቋረጠም |
| Si duwwaatu natti lafe. | አንቺ ብቻ ነሽ ያዘንሽልኝ፡፡ |
| Maal godharee garuu | ምን ያደርጋል |
| Turtiin kees hindheeranne | ቆይተሽ አልረዘመም |
| Inaafaa isa guddaatu | ትልቁ ጠላት |
| Nu jidduu qaxxaamure | በመሃላች አቋርጦ |
| Si fudhatee deeme | አንችን ወስዶ ሄዶ |
| Utubaa mana koo jigsuun | የቤቴን ምሰሶ በማፍረስ |
| Qe'ee koo badduu baase | ቤቴንም በማውደም |
| Maatii koo gargar facaase. | ቤተሰቤን በታተነ፡፡ |
| Duuti maaluma na hingoonee | ሞት ምን ያላደረገኝ አለ |
| Booree haadha maatii | የቤተሰቤን ሰብሳቢ ምስቴን |
| Fuudhee manaa na jalaa baase | ከቤቴ በማውጣት |
| Anas qe'ee na baase. | እኔንም ከቤቴ አወጣኝ |

በማለት ገልጸዋል፡፡

አቶ ድሪባ ባለቤታቸው ለኑሮአቸው በጣም አስፈላጊ መሆናቸውን፣ ልጆችን ወልዳላቸው አባት ማድረጋቸውን በጌረርሳው ገልፀዋል፡፡ ባለቤታቸው ሰዎች ስጠሉዋቸውም እንደልተለዩዋቸው አፅናኝ፣ ተንከባካቢና ለቤተሰባቸው ሰብሳቢ መሆናቸውን፣ በመሞታቸው ልጆቻቸው መበተናቸውን አመላክተዋል፡፡ ከባለቤታቸው

ሞት በኋላ ኑሮ ስላልተመቻቸው እሳቸውም ለረጅም ዘመን የኖሩበት ቀዬ ለቀው ሄደዋል፡፡ የባለቤታቸው ሞት እጅጉን ኑሮአቸውን እንደባለሸባቸው ልጆቻቸውም ተወልዶ የኖሩበትን ቀዬ ጠልተው እንዲበታተኑ እንዳደረጋቸው "ሞት ምን ያላደረገኝ ነገር አለ" በማለት ያዩት ችግር ከባድ መሆኑን አስገንዝበውናል፡፡

### 4.4.3. ስለ ድህነት

አቶ ድሪባ ለታ አንድ ጊዜ ምንም የሌላቸው ደሃ ነበሩ፡፡ ይህም ዘመን ከ1982 እስከ1989 ዓ.ም ነበር፡፡ በዚህ ዘመን ለሰዎች በመሥረት በሚያገኙት ትንሽ ገቢ ቤተሰባቸውን ያስተዳድሩ ነበር፡፡ ያኔ ማንም ሰው እንደፈለገ ያዛቸው እንደነበር ይገልፃሉ። አቶ ድርባ ከዚህ ችግር ለመውጣት ወደ ጅማ ዞን ጎማ ወደ ተባለው ቦታ ቡና ለቀማ ሄደው ነበር፡፡ ወደ ጅማ የሄዱት በ1987 ዓ.ም ነው፡፡ ለሁለት ዓመት ጎማ ቆይተው ሠርተው ባገኙት ገንዘብ ወደ ትውልድ ቀዬአቸው ተመልሰው በሬዎችን በመግዛት ንብረት አፍርተዋል፡፡ ኑሮአቸውን ለውጠዋል፡፡ አቶ ድሪባ ጎማ ከመሄዳቸው በፊትና በኋላ የነበረውንና ያለውን አጋጣሚ በጌረርሳ ሲገልፁ፡፡

| | |
|---|---|
| Beela'ee raafuu nyaannaan | ርቦኝ ጎመን ብበላ |
| Distiin na akeekkattee | ድስት አስጠናቀቀችኝ |
| Daaree moofaa uffannaan | ተራቁቼ አሮጌ ብለብስ |
| Waarsaan na akeekkattee | ዋርሳ አስጠናቀቀችኝ |
| Waarsaan bishaanii galtii | ዋርሳ ከውሃ ስትገባ |
| Guullishaan itti darbadhee | ጉሊሻ ወረውርኩባት |
| Taw! Yaa moofaa jettee | ተው! አንተ አሮጌ አለችኝ |
| Hin jaallu qoosaa jettee | ቀልድ አልወድም አለችኝ |
| Harka koon sassaabadhee | እጄን ከሷ ሰበሰብኩኝ |
| Gommaattan tarkaaffadhe. | ወደ ጎማ ሄድኩኝ፡፡ |
| Yeroon Gommaadhaa galu | ከጎማ ስገባ |
| Farda boora bitadhee | ቦራ ፈረስ ገዛሁ |
| Caammaa shuulii bitadhee | ሹል ጫማ ገዛሁ |
| Qoobii buushii bitadhee | ቡሽ ቦርኔጣ ገገዛሁ |
| Kootiis suufii bitadhee | ሱፍ ኮት ገዛሁ |
| Noor yaa abba booraa jettee | ኖር አባቦራ አለችኝ |
| Nan jaalla qoosaa jettee. | ጨወታ እወዳለሁ አለችኝ፡፡ |

አንዳንድ ጊዜ በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ የአንድ ግለሰብ ማንነት ባለው ንብረት የሚለካበት ጊዜ አለ፡፡ ንብረት ያለው በለጠጋ የሚከበርበት፣ "እርስዎ" ተብሎ መቀመጫ የሚለቀቅለት ጊዜ አለ፡፡ ይህ ሰው ምንም ጥሩ ወይንም ክፉ ቢሆን መለኪያው ያው ንብረት በመሆኑ ይከበራል፤ ይፈራል፡፡ ንብረት የሌለው ደሃ ደግሞ ምንም እንኳን ጥሩ ሰው ቢሆን ያንን ጥሩነቱን ከራሱ አልፎ ለሰዎች የሚገልፅበት አጋጣሚ ስለሚያጣ፣ ማንም ሰው ስለማያስቀርበው እንደተናቀ ይኖራል፡፡ ማንነቱም ያው ሰዎች በምሰጡት ግምት ልክ ይሆናል፡፡ የሚለብሰው አልባሌ ነገር ከሆነማ እርሱን ከሚመስሉት ጋር እንጂ ሌሎች ከሱ በሃብት ከፍ ከሚሉት ጋር መቀራረብ አይችልም፡፡ ለጋብቻም ሆነ ለፍቅር ማንም አይጋብዘውም፡፡ ይናቃል፤ ይንቋሸሻል፡፡

ከላይ በተጠቀሰው አቶ ድሪባ በከወኑት ጌረርሳ እንደተገለፀው በለበሱት ልብስ መስደብ አለ፡፡ "ተው! አንተ አሮጌ" መባል አለ፡፡ እኒህ ከዋኝ ደሃ በነበሩት ጊዜ ተንቀዋል፡፡ ተሰድበዋል፡፡ ዋርሳቸውም ንቃቸዋለች፡፡

ዋርሳ (Waarsaa) በሰርግ ጊዜ ሙሽራው የሚለምነው የሙሽራ አጃቢ ነው፡፡ ዋርሳ ከሌሎች አጃቢዎች የሚለየው ለሙሽራው የቅርብ አገልጋይ በመሆኑ ነው፡፡ በሠርግ ጊዜ ለሙሽራው ፈረስ ይይዘለታል፡፡ዳቦ ይሸከማል፡፡ የሙሽሪትን ቁሳቁሶች በአህያ ጭኖ ወደ ሙሽራው ቤት የሚወስደው እሱ ነው። ሙሽራው ወደ ሙሽሪት ቤት ስሄድ ማር ይቆርጥለታል፡፡ በመልስ (ምላሽ) ቀን ደግሞ በግ ተሸክሞ ወደ ሙሽሪት ቤት የሚወስደውም እሱ ነው፡፡ ሰርጉ እስኪጠናቀቅ ድረስ ከሙሽራው አይለይም፡፡ ከምንዜዎች ይበልጥ ለሙሽራው የሚቀርብ እሱ ነው፡፡ የሙሽራ ፕሮቶኮል እየተከታተለ ያስተካክላል፡፡ ይህ ሰው ለሙሽሪት ዋርሳ ይሆናታል፡፡ እሷም ዋርሰው ናት፡፡

ይህ ዋርሳ የተበለ ሰው ከሙሽሪት ጋር ሠርጉ ካለፈ በኋላ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህን የሚያደርገው በድብቅ ነው፡፡ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን ካላደረገ ከብቶች አይረቡለትም፤ ጥገቶች /ጥጆች/ አያድጉለትም፡፡ ጆሮውም ይደፈናል ተብሎ ይታመናል፡፡ ብዙውን ጊዜ ለዋርሳነት የሚለመነው የሙሽራው የሥጋ ዘመድ (የአክስት ልጅ) ነው፡፡ ይህ የሚደረገው የግብረ ሥጋ ግንኙነትን ከሙሽሪት ጋር እንዳያደርግ ለመከልከል በማሰብ ነው፡፡ የሙሽራው ዘመድ ከሆነ

የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ ስለማይችል ጆሮው እንዳይደፈንና ከብቶች እንዳያልቁበት ሙሽሪትን መደገፍ አለበት ይባላል (ድርባ ለታ፣ 21/06/2004)፡፡

ይቺህ ዋርሳቸው የፍቅር ጥሪያቸውን ንቃ እንዳልተቀበለች ከዚያም ባለፈ "ተው! አንተ አሮጌ" በማለት መሳደቧን እንገነዘባለን፡፡ ይህ ደግሞ በድህነታቸው የተነሳ ነው፡፡ ከጎማ መልስ ንብረት ካፈሩ በኋላ ኑሮአቸው ሲለወጥ ግን ለፍቅር ጋብዛቸዋለች፡፡ ከሳቸው ጋር መጫወት እንደምትወድ ገልፃላቸዋለች፡፡ ይህ ሁኔታ ንብረት ሰዎች በማህበረሰቡ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረጉን የሚያሳይ ነው፡፡

### 4.4.4. ከኤድስ በሽታ ራስን ስለመጠበቅ

ይህ መረጃ ሰጪ ስለ ኤች አይቪ ኤድስ እውቀት አላቸው። በሽታው በማህበረሰቡ ላይ ማድረስ የሚችለውን ተፅእኖ ከባድ እንደሆነ ያውቃሉ። ስለዚህ የሰው ልጅ ከበሽታው እራሱን እንዴት መጠበቅ እንዳለበት ይመክራሉ። አቶ ድሪባ ለታ በ21/06/2004 ዓ.ም ከከወኑት ጌረርሳ መካከል ስለ ኤች አይቪ ኤድስ የከወኑት እንደሚከተለው ይገኛል።

| | |
|---|---|
| Adurreen midhaa hin nyaattu | ድመት እህል አትበላም |
| Hantuuta malee | አይጥን እንጂ |
| Ani marmaraa si hin geechuu | እኔ ምርመራ አልወስድሽም |
| Ni dhuuta malee. | ትሞችያለሽ እንጂ፡፡ |
| Dhufe kaa dhufe dhufe | መጣ መጣ |
| Saree hamaan dhufee | ክፉ ውሻ መጣ |
| Kan namni namarra | ሰው ከሰው |
| Hin dhoowwine dhufee | የማይከለከለው መጣ |
| Dhufe kaa dhufe dhufe | መጣ መጣ |
| Abiddi namatti qabatu dhufe. | ሰውን በሳት የሚያቃጥል መጣ፡፡ |
| Ati of eegi malee | አንቺ /አንተ/ ራስሽን/ህን ጠብቂ/ቅ/እንጂ |
| Yaa seefi yaa seefii | ሰይፍ አንተ ሰይፍ |
| Gandis namarraa hin eeguu | ቀበሌውም ሰውን አይጠበቅም |
| Aanaanis namarraa hin eeguu | ወረዳውም ሰውን አይጠበቅም |
| Obboleessi namarraa hin eegu | ወንድምም ሰውን አይጠበቅም |
| Obboleettiinis namarraa hin eegduu | እህትም ሰውን አትጠብቅም |

| | |
|---|---|
| Ati of eegi malee | አንቺ /አንተ/ ራስሽን/ህን ጠብቂ/ቅ/ እንጂ |
| Dhibeen hamaan dhufee | ክፉ በሽታ መጣ |
| Abbaan of eeguu qabaa | ባለቤቱ ነው ራሱን የሚጠብቅ |
| Of eeguun gaariidhaa. | ራስን መጠበቅ ጥሩ ነው፡፡ |
| Daariidha kan daariidhaa | ዳር ነው ዳር ነው |
| Qulqu'aalli lafaa daariidha | ቁልቁል ለመሬት ዳር ነው |
| Niitii dhirsaa gaariidhaa | ሚስት ለባል ጥሩ ናት |
| Dhirsis niitiidhaa gaariidhaa | ባል ለሚስት ጥሩ ነው |
| Ati of eegi malee. | አንቺ/አንተ ራስሽን/ህን ጠብቂ/ቅ እንጅ፡፡ |

ይህ መረጃ ሰጪ በሽታው በማህበረሰቡ ላይ እስከ ገጠር ድረስ ገብቶ ጉዳት ማድረሱን በመታዘባቸው የሰው ልጅ ለዚህ በሽታ ከሚያጋልጡ ነገሮች እንዲቆጠብ፣ ራሱን እንዲጠብቅ ሰው በሚሰበሰብበት ጌረርሳ በመከወን ይመክራሉ፡፡ ይህ በሽታ እስከ ጎረቤታቸው ድረስ ገብቶ ዘመዶቻቸውንና ሌሎች ሰዎችን ከጎራቤታቸው ገድሏል፡፡ ይህ የሆነው ማህበረሰቡ ስለ በሽታው ጥሩ ግንዛቤ ስለሌለው ነው፡፡ የመተላለፍያ መንገዱንም አያውቁትም፡፡ ከዋኙ ሰዎች በሚሰበሰቡበት ጊዜ በጨዋታ አጋጣሚውን እየገለፁ ይመክራሉ፤ ግንዛቤንም ያስጨብጣሉ፡፡ ይህን በሽታ አስፈሪነቱ ከሃይለኛ ውሻ፣ ከሰደድ እሳትና ከሰይፍ ጋር በመነፃፃር እየገለፁ መልዕክት ያስተላልፋሉ፡፡ ቀበሌ፣ ወረዳ፣ ወንድምና እህት ይህን በሽታ ከሰው መጠበቅ ወይም መከላከል የማይችሉና ሰው ግን ራሱን ከበሽታው ሊጠብቅ እንደሚችል ይመክራሉ፡፡ ያገባ ከራሱ ሚስት ጋር ብቻ ተወስኖ መኖር እንዳለበት “ቁልቁል” ለመሬት ዳር እንደሆነ ሁሉ ሚስትም ለባል ባልም ለሚስት ጥሩ በመሆናቸው አንድ ለአንድ መወሰን ተገቢ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

በተጨማሪም ለበሽታው ከሚጋብዙ ነገሮች ማህበረሰቡ ታቅቦ መኖር እንዳለበት ይመክሩ፡

| | |
|---|---|
| Qooda nadheen katama tana laaltu | የከተማ ሴት ከምታይ |
| Isheedhuma manaa tana hinyaltuu | የቤትህን አትመለከትም ወይ |
| Dirbadirii itti bittee | ድር በድር ገዝተህላት |
| Qaamarratti hinlaaltuu | ሰውነትዋ ላይ አታይም |
| Caammaa ammaa kana bittee | የዘመኑን ጫማ ገዝተህላት |
| Koomeerratti hinlaaltuu | እግሯ ላይ አታይም |

| | |
|---|---|
| Shaashii ammaa kana bittee | የዘመኑን ሻሽ ገዝተህላት |
| Mataarratti hinlaaltuu | በራሷ ላይ አታይም |
| Xilaa ammaa kana bittee | የዘመኑን ጃንጥላ ገዝተህላት |
| Harkarratti hinlaaltuu | በእጇ ላይ አታይም |
| Qooda magaala keessa kaattuu | ከተማ ውስጥ ከምትሮጥ |
| Kaatikaalaa dhugdee | ካትካላ ጠጥተህ |
| Qooda mataa keessa dhaantuu | ገብተህ ሚስትህን ራስ ራሷን ከምትቀጠቅጣት |
| Niitii deessee luqqeettutti baattu. | በወገቧ ላይ ልጅ ያዘለች ሴት፡፡ |

አንዳንድ ሰዎች በትዳር እያሉ ሌሎች ሴቶችን ከከተማ በመያዝ በሚስታቸው ላይ በመድረብ ይማግጣሉ፡፡ መድሃኒት ለሌለው በሽታም ይጋለጣሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ አረቂ እየጠጡ በመስከር ራሳቸውን መቆጣጠር ተስኗቸው ከሌሎች ሴቶች ጋር ይሽረሙጣሉ፡፡ በዚህ የተነሳ ከቤት ሰላም ያጣሉ፡፡ ከሚስቶቻቸው ጋር ይጣላሉ፡፡ ሚስቶቻቸውን ይደበድባሉ፡፡ በመሆኑም መረጃ ሰጪው ይህ ከሚሆን በራስ ብር ጠጥተው ሰክረው ከከተማ ሴቶች ጋር ማግጠው መድሃኒት የሌለው በሽታ ለቤተሰቦቻቸው ይዘው ከሚገቡ ቤት ላለችው ሚስት ጥሩ ጥሩ ነገር ገዝተው ከውጪ ማዬት የሚፈልጉትን እቤታቸው ውስጥ ማግኘት ይችላሉና ሰው መጠንቀቅ አለበት፣ የራሱን ትዳር ማክበር ይጠበቅበታል ሲሉ ይመክራሉ፡፡

#### 4.4.5. ሁለተኛ ባለቤታቸውን ያገኙበት አጋጣሚ

አቶ ድሪባ ለታ ከዚህ በታች የቀረበውን ጌረርሳ የከወኑት በ21/07/2004 ዓ.ም ሲሆን አውዱ እንደሚከተለው ነው፡፡ የአቶ ድሪባ ዋሚ በለቤት ወ/ሮ ጋድሴ አዱኛ በ21/07/2004 ዓ.ም በቅድስት ድንግል ማርያም ስም የሚጠጡ የፅዋ ማህበር ነበራቸው፡፡ማህበሩ ደርሷቸው ስለነበር በዕለቱ በቤታቸው ድግስ ነበር፡፡ በደኩ ቀርሳ ቀበሌ ጎዋ በተባለ ቦታ በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ማህበርተኞች ተሰብስበዋል፡፡ በወቅቱ በቤቱ ውስጥ የነበሩ ሰዎች በቁጥር 24 ናቸው፡፡ ከነዚህም መካከል 15ቱ ሴቶች ናቸው፡፡ የተሰባሰቡት ሰዎች ዕድሜያቸው ከ25-70 ዓመት የሚገመቱ ናቸው፡፡ ማህበርተኞቹ የተሰበሰቡት ከ4፡00 /አራት ሰዓት/ ጀምሮ ነው፡፡ ማህበርተኞቹ በልተው ጠጥተው ካጠናቀቁ በኋላ በስድስት ሰዓት ተኩል ወጣቶቹ መዝፈን ጀመሩ፡፡ ከመረጃ ሰጪዎቹ ውስጥ አቶ ድርባ ለታና አቶ መኮንን ደሜ በቦታው ነበሩ፡፡ አቶ ድርባ ለታ በዚህ ዕለት የከወኑት ጌረርሳ፣ መናሳሻ

ምክንያቶቹና ይዘቶቹ እንደሚከተለው በዚህና በሚቀጥለው ንዑስ ርዕስ ሥር ቀርበዋል፡፡

አቶ ድሪባ ለታ ከላይ በተጠቀሰው ዕለት በከወኑት ጌረርሳ የገለፁት ሌላው አጋጣሚ ሁለተኛ ባለቤታቸውን ያገኙበት አጋጣሚ ነው፡፡ የመጀመሪያ ባለቤታቸው ሞት ምክንያት የተበታተኑትን ልጆቻቸውን ፍለጋ አዲስ አበባ ከተማ ሄደው በመመለስ ላይ እያሉ በአዲስ አበባ ከተማ አስኮ ክፍለ ከተማ በሚገኘው መናኻሪያ ውስጥ አንዲት ሴት ያያሉ፡፡ እሳቸው ያዩት ሴት ብዙ ሸክም ስለነበራቸው ረድቷቸው መኪና ውስጥ አስገብተውላቸው ጎን ለጎን ተቀመጡ፡፡ በዚህ ጊዜ ይጠያየቁና አቶ ድሪባ ለታ ሚስታቸው በመሞታቸው ምክንያት ልጆቻቸው ተበታትነው ስለነበር እነሱን ፍለጋ አዲስ አበባ ሄደው መመለሳቸውን ይነግሩዋቸዋል፡፡ ሴትየዋም በበኩላቸው ባላቸው ይደበድባቸውና ያሰቃያቸው ስለነበር ጠፍተው እየሄዱ መሆኑን ይናገሩዋቸዋል፡፡ ይህንን ቃለ ምልልስ ያዳምጡ የነበሩ ተሳፋሪዎች እግዚአብሄር አገናኝቷቹዋልና ተጋቡ በማለት ሀሳብ ያቀርባሉ፡፡ እዚያው እንዲስማሙ ያደርጓቸዋል፡፡ አቶ ድሪባም በዚህ አጋጣሚ ሚስት ያገኙና ያገባሉ፡፡ የአሁኗ ባለቤታቸው የወ/ሮ መስቀሊ ጉርሙ የትውልድ ቦታ ሰሜን ሸዋ ዞን ደገም ወረዳ ያያ ሀሮ ቀበሌ ገ/ማህበር ነው (ድርባ፣20/07/2004)፡፡

ይህ በመሆኑ አቶ ድሪባ ለታ ብዙ ጊዜ ወደ ሰሜን ሸዋ /ሰላሌ/ ይመላለሳሉ፡፡ ይህንን ሚስታቸውን ያገኙበትን አጋጣሚና ወደ ሰሜን ሸዋ ያደረጉትን ምልልስ በጌረርሳ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡

| | |
|---|---|
| Maal na hingoone miilli koo | እግሬ ምን ያላደረገኝ ነገር አለ |
| Gumbichuu na kaasee | ከግምቢቹ አንስቶኝ |
| Finfinnee na baasee | አዲስ አበባ አወጣኝ |
| Niitii na badhaasee | ሚስትም አስገኝልኝ |
| maal na hin goone miilli koo. | እግሬ ምን ያላደረገኝ ነገር አለ |
| Dagam gubbaa na baasee | ደገም አደረሰኝ |
| Salaale gubbaa na deemsisee | ወደ ሰላሌ ወሰደኝ |
| Kuyyuu gubbaa na deemsisee | ወደ ኩዩ ወሰደኝ |
| Fiichee gubbaa na deemsisee | ወደ ፊቼም ወሰደኝ |
| Yaa miila koo sumatu naan deema malee | እግሬ አንተነህ የምታዞረኝ |

| | |
|---|---|
| Maal na godhe firri koo | ምን አደረጉኝ ዘመዶቼ |
| Homaa na hingoone firri koo | ምንም አላደረጉኝም ዘመዶቼ |
| Yeroon salaaletti baduu. | እኔ ወደ ስላሌ ስጠፋ፡፡ |

በማለት እግራቸው ከቦታ ቦታ እንደወሰዳቸው በዚህ አጋጣሚ ደግሞ ከሁለተኛ ባለቤታቸው መገናኘታቸውን በሚስታቸው ምክንያት ደግሞ ሰላሌ፣ ኩዩ፣ ደገምና ፊቼ ማየታቸውን ገልፀዋል፡፡

### 4.4.6. ስለልማት ሥራ

አቶ ድርባ ለታ በመንግሥት በተነደፈው የልማት ሥራ ላይ በመሳተፍ የውሃ ማቆሩንና የአፈር መንከባከቡን ሥራ መስራታቸውን የተሰጣቸውን ኃላፍነት መወጣታቸውን እንደሚከተሉት ጌረርሳ በመከወን ገልፀዋል፡፡

| | |
|---|---|
| Noorii noorii | ኖር ኖር |
| Maafan si kabajuu didaa | ለምን አላከብርም |
| Yaa hojii misoomaa | የልማትን ሥራ |
| Maa baddiree biyyeen koo | ለምን ይጠፋል አፈሬ |
| Bulbulamtee | ተጠርጎ |
| Maa baddiree biyyi koo | ለምን ይጠፋ ሀገሬ |
| Gurguramtee | ተሸጦ |
| Nan xaggana lafa koo | እጠግናለሁ መሬቴን |
| Maafan xagganuu didaa | ለምን አልጠግንም |
| Daagaas qoffaradhee | ድንጋዩን ፈልቅቄ |
| Hirkanas ijaarradhee. | እርከንንም ሠርቻለሁ፡፡ |

አቶ ደርባ የውሃ ማቆሩንም የአፈር እንዳይታጠብ እርከን ሥራውን መሥራታቸውን (ለተሠጠቸው መሬት እንክብካቤ ማድረጋቸውን) ገልጸዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉንም መረጃ ሰጪዎች የሚያሳስባቸው የዝናብ ማጥፋት ነው፡፡ በዚህ መረጃ ሰጪዎች ለዚህ ጥናት መረጃ በሚሰጡበት ጊዜ ማለትም ከየካቲት አጋማሽ እስከ መጋቢት መጨረሻ ድረስ በአካባቢው ማሽላ፣ ዘንጋዳና በቆሎ የሚዘራበት ወቅት ነው፡፡ ዝናቡ በሚጠበቅበት ወቅት ባለመዝነቡ የተነሳ ማህበረሰቡ ምርቱን እናጣለን በማለት በሥጋት ላይ ነው ያለው፡፡ እነዚህ ምርቶች በዚህ ቆላማ ስፍራ በብዛት ስለሚመረቱ ምርቱ ከጠፋ ህዝቡ ይራባል፡፡ ይህን

አጋጣሚ አቶ ድሪባ በ21/07/2004 ዓ.ም በከወኑት ጌረርሳ እንደሚከተለው በመግለፅ የዝናቡ መጥፋት ለልማት እንቅፋት መሆኑን ያመለከታሉ፡፡

| | |
|---|---|
| Roobi roobii | ዝነብ ዝነብ |
| Roobi yaa waaqayyoo | ዝነብ እግዚአብሔር |
| Maalumaaf roobuu diddaa | ለምንድነው የማትዘንበው |
| Ayyariitu naanna'uu didemoo | አየር አልዞር አለ ወይ |
| Lafatu nuuf na'uu didee | ወይስ መሬት አላዝንላችሁም አለችን |
| Maalumaaf roobuu diddaa. | ለምንድነው የማትዘንበው፡፡ |
| Yaa Waaqayyo maal laataa | እግዝአብሔር ለምን ይሆን |
| Yoo maal jenne nuuf naataa. | ምን ብንል ትራራልናለህ፡፡ |

ከ01-21/07/2004 ዓ.ም በዚህ በደኩ ቀርሳ ቀበሌ ቆላማ አከባቢ በየቀኑ ከንጋቱ ከ1፡00-1፡30 ቀሬ በከኒሳ /Qarree Bakkanniisaa/ ወደ ተባለ ጋራ ሕዝቡ ልጅ አዋቂ ሳይባል በህብረት በመውጣትና በማህበርና በዕድር በመሰብሰብ ዝናቡ እንዲዘንብላቸው በእግዚያታ ለእግዝአብሔር ፀሎት እያቀረቡ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በፊትም በተደጋጋሚ ጊዜ እንዲሁ ዝናቡ ወቅቱን ጠብቆ ባለመዝነቡ በዚህ አከባቢ የእህል እጥረት አጋጥሞ ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ እንደገና ይከሰታል በማለት በስጋት ላይ ይገኛሉ፡፡ ስለዚህ ችግሩ ደግሞ እንዳይከሰት ማህበረሰቡ በፀሎት ላይ ይገኛል፡፡ ምንም እንኳን በተደጋጋሚ ጊዜያት ፀሎት ቢያደርጉም ዝናቡ መምጣት አልቻለም፡፡ በመሆኑም ፀሎታቸው በእግዝአብሔር ዘንድ ደርሶ ተሰምቶ ምላሽ ባለማግኘታቸው ተስፋ ቆርጠዋል፡፡ ምን ብሎ ብለምኑ እግዝአብሔር እንደምሰማቸው ግራ ገብቷቸዋል(ድርባ፡21/07/2004)፡፡ ከዋኙ አቶ ድሪባ ለታ ፀሎት ከሚያደርጉት ሰዎች አንዱ ናቸው፡፡ በተደጋጋሚ ጊዜያት ፀሎት በማድረጋቸውና የሚጠብቁት ዝናብ ስላልመጣ ግራ ተጋብተዋል፡፡ ምን ማድረግ እንዳለባቸው አላወቁም፡፡ በዚህ የተነሳ

| | |
|---|---|
| Yaa Waaqayyo maal laataa | እግዝአብሔር ለምን ይሆን |
| Yoo maal jenne nuuf naataa. | ምን ብንል ትራራልናለህ" በማለት |

ግራ መጋባታቸውን ይገልፃሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ዝናቡ አልዘንብ ያለው

| | |
|---|---|
| Ayyariitu naanna'uu didemoo | አየር አልዞር አለ ወይ? |
| Lafatu nuuf na'uu didee | ወይስ መሬት አላዝንላችሁም አለችን? |

Maalumaaf roobuu diddaa. ዝናብ ለምን እምቢ አለ?

በማለት እግዝአብሔርን በመጠየቅ ግራ መጋባታቸውን ይበልጥ ይገልፃሉ፡፡

በተጨማሪም በዚሁ አካባቢ አንዳንድ ሰዎች በርትተው ወቅቱን ጠብቀው አይሰሩም፡፡ በመሆኑም ኑሮአቸው ከዘመን ዘመን ከችግር የተላቀቀ አይደለም፡፡ ስለሆነም ከዋኙ ህዝቡ በርትተው ከሠራ ድህነትና ረሃብ እንደማይኖርና ሥራ ከችግር እንደሚያወጣ

| | |
|---|---|
| Issee balloo issee balloo | እሰይ! እሰይ! |
| Yaa ijoollee oromiyaa | የኦሮሚያ ልጆች |
| Yaa ijoollee Ada'aa Bargaa | የአዳአ በርጋ ልጆች |
| Yaa ijoollee Dhakkuu Qarsaa | የደኩ ቀርሳ ልጆች |
| Issee yaa hojii misoomaa | እሰይ! የልማት ሥራ |
| Harkaan beekanii | በራሳቸው አውቀው |
| Osoo hojjetanii | ቢሠሩ |
| Namni maaf iyyoomaa. | ሰው ለምን ይደሃያል፡፡ |

በማለት ሰዎች ታጥቀው ተነስተው በልማት ሥራ ላይ መሳተፍ እንዳለባቸው በዚህ አጋጣሚ ያስገነዝባሉ፡፡ እውቀት ላይ የተመሰረተ ሥራ ከሡሩ ድህነት እንደሚጠፋ ይመከራሉ፡፡

በአጠቃላይ አቶ ድሪባ ከላይ በተጠቀሱት ሁለት አጋጣሚዎች ጌረርሳ በመከወን ስለባለቤታቸው ሞት በባለቤታቸው ሞት የተነሳ ስለልጆቻቸው መበተንና እሳቸው ለረጅም ጊዜ የኖሩበት ቀዬ ለቀው ስለመሄድ፣ ሁለተኛ ባለቤታቸውን በአጋጣሚ ስለማግኘትና በባለቤታቸው ምክንያት ሰላሌን ስለማየት፣ ስለልማት ሥራና የመሳሰሉትን ገልፀዋል፡፡

## 4.5. አቶ መኮንን ደሜ የከወኑት ጌረርሳ ላይ የተደረገ ትንተና

አቶ መኮንን እንደ አራቱ መረጃ ሰጪዎቹ በአቶ አዱኛ ጅማ ቤት በ21/06/2004 ዓ.ም በመገኘት ጌረርሳ ከውነዋል፡፡ በወቅቱ አቶ አዱኛ ጅማ ቤት የቅድስት ድንግል ማርያም መታሰቢያ የፅዋ ማህበር ነበር፡፡ አቶ መኮንን ደሜ በአቶ አዱኛ

ጅማ ቤት ጌረርሳ ሲከውኑ የቆዩት ከ6፡00 እስከ 11፡30 ሰዓት ነው፡፡ በዚያን ዕለት የከወኑት ጌረርሳ፣ መነሳሻ ምክንያቱና ይዘቱ እንደሚከተለው ነው፡፡

### 4.5.1. አቶ መኮንን ጠመንጃ መታጠቅ አትችልም ስለመባል

አቶ መኮንን ደሜ በ2002 ዓ.ም ሁለት ሄክታር የሚሆን የእርሻ ማሳቸውን ካላቸው በመቀነስ ትምህርት ቤት እንዲሠራበት ለቀበሌ ሰጥተው አንድ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተሰርቶበታል፡፡ የዚህ ትምህርት ቤት ስም "የደኩ ቀርሣ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት" ይባላል፡፡ የአቶ መኮንን ቤት ለትምህርት ቤቱ በቅርብ ርቀት ላይ በመገኘቱና የትምህርት ቤቱ የቦርድ አባላት የአቶ መኮንን ውለታ በማሰብ የትምህርት ቤቱ ዘበኛ አድርገው ቀጠራቸው፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ አንዳንድ የአካባቢ ሰዎች "አቶ መኮንን ደሜ ይጠጣሉ፤ ይሰክራሉ፡፡ ስለዚህ የትምህርት ቤቱ ዘበኛ ሆኖ ከቀጠሉና ጠመንጃ /የትምህርት ቤት መጠበቅያ መሣሪያ) ከተሰጣቸው በሚሰክሩበት ጊዜ በጠመንጃው በሰው ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ" በማለት የትምህርት ቤቱ ቦርድ ለአቶ መኮንን ደሜ ጠመንጃ እንዳይሰጣቸውና ከዘበኝነት እንዲያነሳቸው አመልክቷል በማለት ወሬ ይናፈሳል፡፡ ይህ ወሬ የአቶ መኮንን ጆሮ ይደርሳል፡፡ ይህ በመሆኑ አቶ መኮንን ተናደዋል፡፡ ይህን ንዴታቸውን ለመግለፅና የከሰሷቸውን ሰዎች በነገር ለመንካት እንዲህ በማለት ጌረርሳ ከውነዋል፡፡

| | |
|---|---|
| Maaluma yaa garaaree | ምነው አንተ ሆዴ |
| Halkan gaaruma yaaddaa | ለሊት ጥሩ ታሰባለህ |
| Guyyaa balleechaa maltaa | ቀን ቀን ጥፋት ታስባለህ |
| Raase kaa raase raase | አራገበ አራገበ |
| Garaan gilaasa raasee | ሆዴ ግለሱን አራገበ |
| Waanuma raasefan wallaalee | ለምን እንዳረገባ አላውቅም |
| Mee koottuu mee koottuu | ና እስቲ ና እስቲ |
| Mee koottu ittan badaa | ና እስቲ እጠፋበታለሁ |
| Yoo haraqee dhuganii | አረቂ ቢጠጡ |
| Rakataa fakkaatanii | ደሃ ቢመስሉ |
| Yaa Bokitee yaa bokitee | አንተ ቦክቴ |
| Giraaba gadi buutee | ቆላ የወረድክ ቦክቴ |
| Mana barumsaaf lafa kenninee | ለትምህርት ቤት መሬት ሰጠን |
| Mana barumsaaf waardiyyaa taanee | የትምህርት ቤቱ ዘበኛ ሆንን |

| | |
|---|---|
| Bokiteen qawwee hin qabattuu | መኮንን ጠመንጃ መያዝ አይችልም አሉኝ |
| Haraqee dhugdi jedhanii | አረቄ ይጠጣል አሉኝ |
| Nama sanyii hin qabne jedhanii | ዘመድ/ወገን/ዘር የለውም አሉኝ |
| Yaa haarrii Dame Gaaddisaa | እኔ ጀግናው የደሜ ጋዲሳ ልጅ |
| Iccitiin nutti dhuftee | ጥቃት መጣብኝ |
| Mee koottaa ala bullaa. | ኑ እስቲ ውጪ እንደር፡፡ |

አቶ መኮንን "ጠመንጃ መያዝ አትችልም" ስለተባሉ ንዴት አንገብግቧቸዋል፡፡ በማህበረሰቡ ጠመንጃ መያዝ አለመቻል ማለት ከፈሪዎች ወገን ያስመድባል፡፡ ክብርን ይነካል፡፡ ጠመንጃ የክብር መለኪያ፣ የማንነት መገለጫ ነው፡፡ መያዝ አትችልም መባል ደግሞ ያበሳጫል፣ ያንገበግባል፡፡ አቶ መኮንንም "ለትምህርት ቤት ማሠሪያ መሬት በመስጠቴ ምስጋና ሲገባኝ ክብር በመነካቴ፣ ዘር የለውም መባሌ ትክክል አይደለም" በማለት ንዴታቸውን ይገልፃሉ፡፡ ከዚያም ባለፈ "ኑ እስቲ ውጪ እንደር" በማለት እነዚያን ስም አጥፊዎችን ለመበቀል ይዝታሉ፡፡ የንዴታቸውን ጥልቀት ደግሞ "ሆዴ ግላሱን አራገበ" በማለት ይገልፃሉ፡፡

በተጨማሪም አቶ መኮንን "እስቲ ይታይ ያለብኝ ወንጀል ይመርመር፣ ከዚህ በፊት የሰራሁት ጥፋት" በማለት ጠላቶቻቸውን እንደሚከተለው ይተቻሉ፡፡

| | |
|---|---|
| Mee qulqulleessii natti himi | እስቲ አጥራና ንገረኝ |
| Yaa Siyyum Aduunyaa | አንተ ስዩም አዱኛ |
| Maaltu ijaaruu si sigate | ማነው ሥራ ያለህ |
| Mee nurraa dhoowwaa jedhaanii | "እስቲ ከልክሉልኝ |
| Mee Bokiin nama kassasee | ቦኪ ሰውን ከሶ ያውቃል ወይ? |
| Faayilli biiroo jiraa? | ፋይሉ ቢሮ አለ ወይ? |
| Mee fuudhaa jedhaanii. | እስቲ አውጡ" በላቸው፡፡ |
| Bokiin niitii isaa rukutee | ቦኪ ሚስቱን ደብድቦ |
| Gurri ishee duudaa dhaaree | ጆሮዋን መትቶ አደንቁሮ |
| Qaamni ishee hir'uudhaaree | አካሏን አጉድሏል ወይ |
| Miidhama himatteeree. | ጉዳቷን ተናግራለች ወይ፡፡ |
| Ijoollee Baaduu raaree | የባዱ ራሬ ልጆች |
| Hundumaa baaduu taanee | የተናጠ ወተት ሆንን |
| Hundumatu nu tuqata. | ማንም ያጣቅሰናል፡፡ |

አቶ መኮንን "ይሰክራሉ፤ በጠመንጃው በሰው ላይ ጉዳት ያደርሳሉ፤ ጠመንጃ መያዝ አይችሉም" መባላቸው ያለ አንድ ማስረጃ /ምክንያት/ የሰውን ስም ማጥፋት በመሆኑ አግባብነት እንደሌለው በመግለፅ" መኮንን ሰው ከሶ ወይንም ተከሶ ያውቃል ወይ? የራሱን ሚስት ሰክሮ መተው አካሏን አጉድሏል ወይ?" ብሎ በመጠየቅ የከሰሱዋቸውን ሰዎች ይተቻሉ፡፡ "እስቲ አጣሩ" በማለት የትምህርት ቤቱን ቦርድ ይጠይቃሉ፡፡

አቶ መኮንን ይህን ጌረርሳ ሲከውኑ በስሜት ሆነው እልህ እየተናነቃቸው ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ ነው፡፡ "እንደተናጠ ወተት/baaduu/" የማንም ተራ ሰው መጣቀሻ መሆናቸውን ይገልፃሉ፡፡ የማንም መቀለጃ ሆንኩ በማለት በምሬት እሮሮአቸውን ያሰማሉ፡፡ የትምህርት ቤቱ ቦርድ አባል የሆነው አቶ ስዩም አዱኛን "እስቲ አጣራና ንገረኝ የክሱ ምክንያት" በማለት ይጠይቃሉ፡፡

### 4.5.2. ስለ ወንድማቸው ሞት

አቶ መኮንን ደሜ ከዚህ በታች የተመለከተውን ጌረርሳ የከወኑት በ21/07/2004 ዓ.ም ከ6፡00-11፡30 በደኩ ቀርሳ ቀበሌ ጎዋ በተባለ ቦታ በሚገኘው በአቶ ድርባ ዋሚ ቤት በመገኘት ነው፡፡ ጌረርሳውን የከወኑበት ምክንያት ታላቅ ወንድማቸው አቶ ጎንፋ ደሜ በደርግ ዘመነ መንግስት በ1973 ዓ.ም በሚሊሻነት ተቀጥረው ዘምተው ነበር፡፡ አቶ ጎንፋ የዘመቱት የአንድ አካባቢ አብረው አደጎቻቸው ከሆኑት ከአቶ ግርማ ተፈራና ከአቶ በዪቻ ደበሌ ጋር ነበር፡፡ ሦስቱም ጓደኛሞች ጦርነት ላይ ብዙ ከቆዩ በኋላ በ1980 ዓ.ም በጦርነት ላይ እያሉ በጎንደር ክፍለ ሀገር ተሰውተዋል፡፡ አቶ መኮንን አሁን ያላቸው ወንድም አንድ ብቻ በመሆኑ ጥቃት በሚደርስባቸው ጊዜ ወንድማቸውን ስም እያነሱ ጌረርሳ ይከውናሉ፡፡ወንድማቸው ቢኖር ሦስት ቢሆኑ ማንም ሰው "ዘር የሌለው፣ ጠመንጃ መታጠቅ የማይችል፣ ሰካራም" ብሎ እንደማይሰድባቸው ይናገራሉ፡፡ በአጋጣሚው የከወኑት ጌረርሳ፣

| | |
|---|---|
| Waamuu laataa | ልጥራው ወይ |
| Takka waamuu laataa | አንዴ ልጥራው ወይ |
| Garaan na garagalee. | ሆዴ ባርባር ብሎኛል፡፡ |
| Si waamuu laataa | ልጥራህ ወይ |
| Yaa ijoollee Gondor | የጎደር ልጆች |

Yaa Gonfaa Damee — አንተ ጎንፋ ደሜ
Yaa Girmaa Tafarraa — አንተ ግርማ ተፈራ
Yaa Gonfaa hangafa koo — አንተ ጎንፋ ታላቄ
Yaa Gonfaa biyya hormaatii haftee. — በሰው ሀገር የቀረህ፡፡
Laali mee laali laali — እይ እስቲ እይ እይ
Qeerransa barruu laali — ነብር ቀለሙን እይ
Dhiira gaaddidduu ilaali. — ወንድ ጥላውን እይ

አቶ መኮንን ወንድማቸውና ጓደኞቹ በጦርነት ላይ የተሰውት ከረጅም ጊዜ በፊት ቢሆንም እስከሁን ሀዘን እንደሚሰማቸው ይናገራሉ፡፡ በጥቃት ጊዜ ወንድም ጥላ ከለላ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ ስለዚህ የወንድማቸው ሞት እንደ አዲስ በሀዘን ያስታውሳሉ፡፡ ወንድማቸው ዘምታው ለሀገራቸው ሲሉ መሰዋታቸውን ከጀግኖች ወገን እንደሚያስቆጥራቸው የወንድማቸውንና ጓደኞቹን ጀግንነት ከነብር ጋር እያወዳደሩ

"ነብር ቀለሙን እይ
ወንድ ጥላው እይ"

በማለት የወንድ ጥላው እንደሚያስፈራ ይገልፃሉ፡፡ ወንድማቸው በመሰዋቱና ከጎናቸው አለመኖሩ ግን ያሳዝናቸዋል፡፡

4.5.3. እናታቸው ወደ ጎንደር እንዲሄዱ አቶ መኮንንን ያዘዙበት ሁኔታ

አቶ መኮንን ደሜ ወንድማቸውን አቶ ጎንፋን ጎንደር ድረስ በመሄድ ሁለት ጊዜ ጠይቀቸዋል፡፡ እናታቸው ወ/ሮ ደሲ ድሮ አቶ መኮንን አቶ ጎንፋን ጎንደር ድረስ ሄደው እንዲጠይቁ ያበረታቱበትን ሁኔታ አቶ መኮንን በጌረርሳ ሲገልፁ፡

Waan naan jette haat too — እናቴ አለችኝ
Hirree koo qaqqabattee — ይዛ ትከሻዬን
Yaa ilma koo adaraa — ልጄ አደራ
Naan jette kaa haatitoo — እናቴ አለችኝ
Yaa ilma koo irruma aani jette. — አሸንፍ አንጂ አትሸነፍ አለችኝ
Naaf goote kaa gala — ስንቅ አደረገችልኝ
Qanqalatti — በስልቻ
Ilmi koo biyya hormaatti hafee — ልጄ በሰው ሀገር ቀርቶ

| | |
|---|---|
| Gadheen na dhaanuu mannaa | ፈሪ ከምገርፈኝ |
| Bineensi na nyaachuu wayya | ጅብ ብበላኝ ይሻላል |
| Daggalatti | በጫካ |
| Deemii barbaadi naan jette | ሂደህ ፈልግ አለችኝ |
| Anis ittuman badee | እኔም ጠፋሁበት |
| Akka dirii ijji bade. | ውል እንደጠፋው ድር፡፡ |
| Jawwe galaanni hin nyaatuu | ዘንዶ ወንዝ አይበላውም |
| Kanaaf daakee taphataa | ለዚህ ነው በውሃ የሚጫወተው |
| Gadhee garaan hin aaruu | ፈሪ አይናደድም |
| Obboleessas ajjeesanii | ብገሉበት ወንድም |
| Niitiis irraa fudhatanii | ብወስዱበት ሚስት |
| Gosas yoo ajjeesanii | ብገሉበት ወገን |
| Kanaaf nyaatee gabbataa. | ለዚህ ነው በልቶ የሚወፍር፡፡ |

የአቶ መኮንን እናት ሰንቅ አዘጋጅተው አቶ መኮንን ወደ ጎንደር መላካቸው ልጃቸውን እዲያመጣላቸውና ወገንን በማጣት ከሌሎች ከሚመጣው ጥቃት እንድታደጋቸው ነው፡፡

ልጄ በሰው ሀገር ቀርተው
ፈሪ ከምገርፈኝ
ጅብ ብበላኝ ይሻላል
በጫካ

ማለታቸው በሌሎች ሰዎች ከሚጠቁ ልጃቸው ማስፈራሪያ እንዲሆናቸው ነው፡፡ አቶ መኮንንም ወገን በማጣት ከሚደርስባቸው ጥቃት ለማምለጥ ወንድማቸው በህይወት ቢኖሩ እንደሚፈልጉ ቁጭታቸውን በ21/07/2004 ዓ.ም ይህንን ጌረርሳ በመከወን ገልፀዋል፡፡ “እኔ እንደ ፈሪ አይደለውም ጥቃት ያንገበግበኛል” በማለት ጌረርሳውን ከውነዋል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው አቶ መኮንን ደሜ በጌረርሳቸው አረቄ ይጠጣሉና ጠመንጃ እንዳይሰጣቸው ስለመባላቸውና ስለመሰደባቸው፣ ወንድማቸውን ለመጠየቅ ስላደረጉት ጉዞና ስለወንድማቸው ሞት ገልፀዋል፡፡

በአጠቃላይ ግለሰቦቹ ጌረርሳን በመከወን በሕይወት ዘመናቸው ያጋጠማቸውን ጉዳዮች፡ ደስታም ሆነ ሀዘን፣ ክፋም ሆነ በጎ፣ ምቾትም ሆነ ጭንቀትና የመሳሰሉትን ገጠመኞቻቸውን ገልጸዋል። ከያንያኑ ኑሮአቸውን ለማሸነፍ በጉልበት ሠራተኛነት

በመቀጠርና ከመንደራቸው ርቀው በመስራት ያገኙት ውጤት ገልፀዋል። በሂዱበት ቦታ የገጠማቸውን ችግር በጌረርሳቸው አንጸባርቀዋል። በዋረታቸው ኑሮቸቸውን ያሸነፉ ግለሰቦች የገኙትን የኑሮ መሻሻል ሲገልፁ ያልተሳካላቸው ደግሞ ያሉበት የኑሮ ጉስቁልናና ለዚህ አስከፊ ኑሮ ያበቃቸውን አጋጣሚዎች በጌረርሳ ገልጸዋል።

## ምዕራፍ አምስት

## 5. የአምስቱ ግለሰቦች ጌረርሳ የአከዋወን ሂደት

በ16/06/2004፣ 19/06/2004፣ በ21/06/2004፣ 12/07/2004ና 21/07/2004 ዓ.ም የአምስቱን ግለሰቦች የጌረርሳ አከዋወን ሂደት እንደ ተመለከትኩትና ግለሰቦቹን በተለያዩ ጊዜያት ጠይቄአቸው እንደተረዳሁት ጌረርሳውን ሲከውኑ ተራ በተራ ነው፡፡ ማንም ሰው እንደፈለገ ተነስቶ የሚከውን አይደለም፡፡ የራሱ የሆነ ሥርዓትና የአካሄድ ስልቶች አሉት፡፡ መጀመሪያ ልከውን የተነሳው ሰው ለተወሰነ ደቂቃ ከከወነ በኋላ ሌላ ከራሱ ዕድሜ ጋር የሚቀራረብ ሰው ይጋብዛል፡፡ ሳይጋበዝ በንሽጣ ተነስቶ ጌረርሳ መከወንም ይቻላል፡፡ ነገር ግን አንድ ከዋኝ ከእድሜው በጣም ከሚበልጥና በጣም ከሚያንስ ሰው ጋር ጌረርሳ አይከውንም፡፡ የማህበረሰቡ ስምምነት አይፈቅድም፡፡ ከዕድሜው በጣም የሚበልጥ ሰው በጌረርሳው ጠርቶ የሚጋብዝ ከሆነ እንደመዳፈር ይቆጠራል፡፡ ከዕድሜው በጣም ከሚያንስ ሰው ጋር ጌረርሳ የሚከውን ከሆነ ራሱን እንደ ማዋረድ ይቆጠራል፡፡ ስለዚህ አብረው የሚከውኑ ሰዎች ዕድሜ ተቀራራቢ መሆን አለበት፡፡ የግድ ደግሞ ዕድሜያቸው እኩል መሆን የለበትም፡፡ ለምሳሌ አቶ መኮንን ደሜ ዕድሜያቸው 61 ዓመት ነው፡፡ የአቶ ድርባ ለታ ዕድሜ ደግሞ 55 ዓመት ነው፡፡ የሁለቱ ከዋኞች ዕድሜ ተቀራራቢ በመሆኑ አብረው መከወን ይችላሉ፡፡ እኔ ጌረርሳ በሚሰብስብበት ጊዜ ሁለቱ በምልልስ መልክ ከውነዋል፡፡ ሌሎች ሶስቱ መረጃ ሰጪዎች ዕድሜ ተቀራራቢ በመሆኑ አብረው ከውነዋል፡፡ ስለዚህ በአብዛኛው ጌረርሳን አብረው በሚልልስ የሚከውኑ ሰዎች በዕድሜአቸው ተቀራራቢ የሆኑ ናቸው፡፡ በመሆኑም አቶ ብርሃኑ ከአቶ ቸሩና አቶ ቸሩ ከአቶ አባተ ጋር ጌረርሳ ከውነዋል፡፡ እነዚህ ከዋኞች አብረው ሲከውኑ ከልጅነት አሁን እስካሉበት ድረስ ያሳለፉት ገጠመኞቻቸውን በማንሳት ነው፡፡ አብረው የሠሩትንና ያጋጠማቸውን ሁሉ እርሰበርስ እያስታወሱ በጌረርሳ ገልፀዋል፡፡ እነዚህ ሦስቱ ከዋኞች ዕድሜያቸው ተቀራራቢ በመሆኑ ያለ ምንም ፍርሃትና መሽማቀቅ አብረው ጌረርሳ አዜመዋል፡፡



ፎቶ 6. አቶ ብርሃኑ አዱኛና አቶ ቸሩ ድንቁ በ21/06/2004 ዓ.ም በአቶ አዱኛ ጅጋ ቤት ጌረርሳ አብረው ሲከውኑ

ከላይ እንደተጠቀሰው ጌረርሳ አብዛኛውን ጊዜ የሚከወነው በምልልስ /dialogue/ መልክ ነው፡፡ ሁለት ሁለት ሆኖ ይከውናሉ፡፡ አንድ ሰው ሰዎች በተሰበሰቡበት ብቻውን መከወንም ይችላል፡፡ የሚከለክለው ማህበራዊ ስምምነት የለም፡፡ አብረው የሚከውኑት ሁለቱ ከዋኞች ከከዋኔ በኋላ ከመዳላ /Madaala/ ይጠጣሉ፡፡ መዳላ በጠላ ወይንም በአረቄ ወይንም ደግሞ በወትቱ በሚጠጣው መጠጥ የተሞላ ዋንጫ ነው፡፡ ከዋኞቹን ከመዳላ የሚያጠጡዋቸው ታዳሚያን ናቸው፡፡ ሁለቱ ከዋኞች ከዚህ ዋንጫ አብረው ይጎነጫሉ፡፡ ያቀረቡት ጌረርሳ የሚያቀያይማቸው እንኳን ቢሆን ይህ ዋንጫ ያስታርቃቸዋል፡፡ አብረው ከመዳላ ከተጎነጩ በኋላ በሁለቱ ከዋኞች መካከል ፍቅር እንጂ ጥል አይኖርም፡፡ ከመዳላ አብረው መጠጣት ማለት ፍቅርን እንደመጋራት ይቆጠራል፡፡

ከታች በሚገኘው ፎቶ እንደምትመለከቱት አቶ መኮንን ደሜና አቶ ድሪባ ለታ ጌረርሳ አብረው ከከወኑ በኋላ ከመዳላ ሲጠጡ የሚያሳይ ነው፡፡ ሁለቱ ግለሰቦች ጌረርሳ በመከወን በነገር ከተጎሻሸሙ በኋላ እንዳይጣሉ ታሚያን ከመዳላ ሊያጠጧቸው ነው፡፡ በምልልስ የከወኑት ጌረርሳ፡

አቶ መኮንን ደሜ የከወኑት፡

| | |
|---|---|
| Eessaree minishiriinii | ምንሽሩ ዬት አለ |
| Yaa Dirribaa lataa | አንተ ድሪባ ለታ |
| Eessaree domoftoriinii | ዶሞትፎሩ ዬት አለ |
| Meeqa tokkofte gaafa sanii | ስንት ተኮስክ ያን ዕለት |
| Gaafa qawwee kennitee galtuu | ጠመንጃ ተተምተህ ስትገባ |

Maalitti buute Qirbee
Erga qowwee fuutee hingalini.

ቅርቢ ለምን ወረድክ
ጠመንጃውን ይዘህ ካልገባህ።።

አቶ መኮንን ደሜ ከላይ በተመለከተው ጌረርሳ የአቶ ድሪባ ለታ በዘራፊዎች ጠመንጃ መቀማት በመግለፅ ስንት ነው የተኮስከው ጠመንጃውን ስተሙህ እያሉ በመተቸት ሲከውኑ አቶ ድሪባ ለታ በሚከተለው ጌረርሳ መልስ ሰተዋል።።በ1989 ዓ.ም አቶ ከግንደ በረት ወረዳ ቅርቢ ከሚባለው አከባቢ ጠመንጅ እያመጡ ይነግዱ ነበር።።ይህ በእንዲ እያለ በዚሁ ዓ.ም ሚያዚያ ወር ውስጥ ከግንደ በረት ወረዳ ጠመንጃ ይዘው ሲመጡ በመንገድ ላይ ሌቦች ጠመንጃውን ተቀሟቸዋል።። ይህ ነው የአቶ መኮንን ኪዊኔ መነሻ ምክንያት።።

| | |
|---|---|
| Amman tokkose maal sii godhaa | የፈለኩትን ያህል ብትከስ ምን አገበባህ |
| Dhiba kaa dhiba dhibaa | ያስቸግራል እንጂ ያስቸግራል |
| Maarashaan lafa dhibaa | ማረሻ መሬትን ይነቀንቃል |
| Daarri abbaa maatiit dhibaa | ማልበስ ብዙ የቤተሰብ ያለውን ያስቸግራል |
| Dudubbattuu jechatu dhibaa | ለለፍላፊ ቃሉ ያስቸግረዋል |
| Dirribaa maaltu dhibaa | ድሪባ ምን ያስቸግረዋል |
| Argatu calla nyaataa | ካገኘ ምርጥ ምርጡን ይበላል |
| Dhabu calleesaaf kaataa. | ካጣ ሠርቶ ለማግኘት ይጥራል።። |

አቶ ድሪባ ከለአግባብ ማውራት ችግር እንደሚያመጣ በቁጣ ለአቶ መኮንን የአፀፋ መልስ ሲሰጡ ሁለቱ ከዋኞች እንዳይጣሉ ታዳሚያን በ21/06/2004 ዓ.ም ከመዳላ እንዲጠጡ አድርጓቸዋል።።



ፎቶ 7. አቶ ድሪባ ለታና አቶ መኮንን ደሜ በ21/06/2004 ዓ.ም በአቶ አዱኛ ጅግ ቤት ጌረርሳ ብረው ከከወኑ በኋላ ከመዳላ ሲጠጡ

ሰዎች በተሰበሰቡበት ጌረርሳ የሚከውኑ ግለሰቦች ተቀምጠው አይከውኑም፡፡ የታዳሚያንን ስሜት ለመሳብና ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ጎልቶ እንዲሰማ የአካል እንቅስቃሴ ያደርጋሉ እንጂ፡፡ ሁለቱ አብረው የሚከውኑ ሰዎች ተራ በተራ ይነሱና በመንጉራደድ፣ ፊታቸውን በመጨምደድ፣ አይናቸውን በማጉረጥረጥና ጎንበስ ቀና በማለት ይከውናሉ፡፡ እንደ ጌረርሳውና እንደ የሚተላለፍ መልዕክት ሁኔታ የአካል እንቅስቃሴ ይደረጋሉ፡፡ ለምሳሌ አቶ አባተ ኤጀርሣ ያቀርቡት ጌረርሳ ከወንድሞቻቸው ጋር ሆኖ በሰው ላይ የአካል ጉዳት በማድረስ የደረሰባቸው እስራት፣ መንገላታት፣ የሃብት ንብረታቸው መውደምና በሰው ፊት ያላቸው ተቀባይነት መቀነስ በመሆኑ በአብዛኛ አሳዛኝ ገጠመኝ ነው፡፡ ስለዚህ አቶ አባተ ጌረርሳውን ሲከውኑ ፊታቸውን በመቋጠርና እጃቸውን በማወራጨት ከሚያስተላልፉት መልዕክት ጋር እንድሰምር በማድረግ ነው፡፡ ጭንቅላታቸውን በመንቅነቅና በአንድ እጃቸው ጆሮአቸውን በመያዝ ወዲያ ወዲህ በመሄድ የሀዘን ስሜት በማሳየት ነው፡፡ በ19/06/2004 ዓ.ም በቤታቸው ጌረርሳ ሲከውኑልኝ ግን በሁለት እጆቻቸው ግንባራቸውን በመያዝ ተቀምጠው ነው፡፡ ሲከውኑ የፊታቸው ደም ሥሮች ተገታትረው ይታዩ ነበር፡፡ በወቅቱ በስሜት ሆኖ እየከወኑ እንደሆነ ከሁኔታቸው ተረድቻለሁ፡፡

አቶ ብርሃኑ አዱኛ ከላይ በምዕራፍ አራት በስማቸው ሥር የቀረበውን አረቄ ስጠጡ በነበረበት ጊዜና ኦዶ ሻክሶ የሳለፉትን አስቸጋሪ ኑሮ በጌረርሳ ስገልፁ ከፊታቸው ቁጭትና ሀዘን ሲነበብ ሌሎቹን በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ በስማቸው ሥር የቀረበውን ጌረርሳ ሲከውኑ ደግሞ የአሸነፊነት ስሜት እየተነበበባቸው ወዲያ ወዲህ እየተንጎራደዱ ነበር፡፡

አቶ ቸሩ ድንቁም በበኩላቸው በልጅነትና ወጣትነት ዘመናቸው ያሳለፉትን ችግር ማለትም ብድር መክፈል ባለመቻላቸው መሰደባቸው፣ ካጋጠማቸው አስከፊ የኑሮ ሁኔታ ለመውጣት ያደረጉትን ተጋድሎና ሞጆ ሥራ ፍለጋ ሄደው ያጋጠማቸውን ችግር ጌረርሳ በመከወን ሲገልፁ የማዘን ስሜት ሲታይባቸው ባደረጉት ከፍተኛ ተጋድሎ ከችግራቸው መላቀቃቸውን ሲገልፁ ግን ከፊታቸው የደስታ ስሜት ይነበብ ነበር፡፡ ሁሉንም ከስማቸው ሥር የቀረበውን ጌረርሳ ሲከውኑ በመንጎራደድ ነው፡፡

አቶ ድሪባ ለታም በበኩላቸው ስለ ባለቤታቸው ሞትና ባለቤታቸው በመሞታቸው የልጆቻቸው ተወልደው ያደጉበት ቀዬ ለቀው መበተንና የሳቸውም ለ51 ዓመታት የኖሩበትን ቀዬ ለቀው መሄድ በጌረርሳ ስገልፁ አንገታቸውን ሰብረው እንባቸውን እያፈሰሱ በሀዘን ስሜት ወድያ ወዲህ እየሄዱ ሲሆን ሌሎቹን ጌረርሳዎች ሲከውኑ ግን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በደስታ ስሜት በመንጎራደድ ነው፡፡

አቶ መኮንን ደሜ ደግሞ ስለወንድማቸው በጦርነት ላይ መሞት በሀዘን ድምፃቸውን አለሳልሰው ፊታቸውን ኮስተር አድርገው ቀስ ብለው ወዲያ ወዲህ እየተንጎራደዱ ቢከውኑም ከትምህርት ቤቱ ዘበኝነት እንዲነሱ፣ ጠመንጃ እንዳይሰጣቸው የከሰሱዋቸውን ሰዎች በመተቸት ጌረርሳ ሲከውኑ ግን በስሜት በመሆን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው፣ አይናቸውን አጉረጥርጠውና ወዲያ ወዲህ የመሮጥን ያህል በመንቀሳቀስ ነው፡፡ ከፍታቸው የእልህ ስሜት ይነበባል፡፡ የከሰሱዋቸውን ሰዎችን ለመጋፈጥ ወደ ፊት የሚንደረደሩ ይመስላሉ፡፡

እነዚህ አምስቱ ከያንያን ጌረርሳውን ሲከውኑ ለክዋኔው ስሉ የተለየ አለባበስ አልተከተሉም፡፡ ነገር ግን አቶ አባተ ኤጀርሳ ጌረርሳውን ሲከውኑ የያዙትን ዱላ በመነቅነቅ በመወደርና ጎንበስ ቀና በማለት ሲሆን አቶ መኮንን ደሜ ደግሞ የያዙትን ጠመንጃ በተከሻቸው ላይ በማድረግና ፊት ለፊት በማነጣጠር የሰውነትን እንቅስቃሴ በማድረግ ከውነዋል፡፡ ነገር ግን ሌሎች ሦስቱ ከዋኞች ምንም ሳይይዙ ጌረርሳውን በጋለ ስሜት ከውነዋል፡፡

በአጠቃላይ ሁሉም ከዋኞች ስለታታሪነታቸው፣ ስለችግራቸውና ሌሎች መልዕክቶች በጌረርሳ ሲያስተላልፉ ከመልዕክት ጋር የሰውነት እንቅስቃሴያቸውን በማቀናጀት ሁኔታው በሚፈቅደው መሠረት ግርማ ሞገስ አላብሰው ነበር፡፡

## 5.1.የጌረርሳ ክዋኔ አጀማመር

የጌረርሳ ክዋኔ የራሱ የሆነ የአጀማመር ስልቶች አሉት፡፡ ከዋኙ ክዋኔውን በሚጀምርበት ጊዜ ማለት ያለበት ስንኞች አሉ፡፡ እነዚያን ስንኞች በመከወን ወደ ዋናው ክዋኔ ይገባል፡፡ እነዚህ ስንኞች የታደሚያንን ትኩረት በመሳብ ልብ ብለው እንዲያዳምጡ የሚያደርጓቸው ናቸው፡፡ ወደ ዋና ጉዳይም ለመግባት እንደ መንደርደርያ ያገለግላሉ፡፡

ነዚህ ከዋኞች ከላይ በምዕራፍ አራት የቀረበውን ጌረርሳ ሲከውኑ

| | |
|---|---|
| Geerar geerar naan jedhuu | ጌረርሳ ከዋኝ ጌሮ ነው ያለው |
| Namni geeraree hinbeeknee | ከውኖ የማያውቅ |
| Garaa haadhasaat jiraa. | በእናቱ ሆድ ነው ያለው፡፡ |

ማለት ጌረርሳን መከወን የሚጀምሩ ሲሆን ሌሎች እንዲከውኑ የሚጋብዙት ደግሞ፣

| | |
|---|---|
| Nawwe kaa nawwe nawwee | ተመኘሁ ተመኘሁ ተመኘሁ |
| Hiriyyaa na cinaa jiruu | ከጎኔ ያለው ጓደኛዬን |
| ________ tuquun hawwee. | ______መንካት ተመኘሁ፡፡ |

ማለት ይሆናል። መረጃ ሰጪዎቹ በቦዶ ቦታው እርስ በርስ እየተጠራሩ እንዲከውን ሚፈልጉትን ሰው ስም እየሞሉ፡

"ተመኘሁ ተመኘሁ ተመኘሁ
ከጎኔ ያለው ጓደኛዬን
ድሪባን መንካት ተመኘሁ"

የተበባሉ በመገባበዝ እርስ በርስ ስለሠሩት ሥራዎች፣ ስላሳለፉት ችግር፣ ለታታሪነታቸውና ሌሎች ጉዳዮች በጌረርሳ አስተላልፈዋል፡፡

ይም ደግሞ ከዋኙ

| | |
|---|---|
| Qamalee eegeen dabaa | ጦጣ ጅራቷ ይጠማዘዛል |
| Waanniin muka cabsitee | ጉሬዛ እንጨት ሰብወራለች |
| Dabareen kee maaf hafaa | ተራህ ለምን ይቀራል |
| Atis ilma dhalcitee. | አንተም ወንድ ልጅ ወልደሃል" |

ማለት ይጋብዛል፡፡
ንድ ልጅ መውለድ ማህበረሰቡን ከማንኛውም ስጦታ በላይ ያስደስተዋል፡፡ ማህበረሰቡ ወንድ ልጅ የአባቱን ቀዬ ይወርሳ፣ የቤተሰብን ስም ያስጠራል ወይም ተካላል፡፡ ማህበረሰቡንና ቤተሰቡን ከጠላት ይከላከላል፡፡ ጠላት ተበቅሎ የወገኑን ም ይመልሳል ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለዚህ ወንድ ልጅ መውለድ እንደ ትልቅ ር ይቆጠራል፡፡ አንድ ከዋኝም ወንድ ልጅ በመውለዱ ከሁሉም ቀድሞ ጌረርሳ ንዲከውን ይጋበዛል፡፡ ክብርም ይሰጠዋል (መኮንንና ድሪባ፣ 21/06/2004 ዓ.ም)፡፡ ጋባዡ ከዋኝ ደግሞ፣

| | |
|---|---|
| Geerari geerari jedhuu | ሽልል ሽልል ይሉኛል |
| Geerarii maal na gorsuu | መሽለልን ይመክሩኛል ወይ |
| Ana garaan hinobsuu. | እኔ ሆዴም አያስችለኝም፡፡ |

ገማለት ጌረርሳ መከወን ውስጤም ያዘኛል፣ የሰው ምክር አያስፈልገኝም ብሎ ገዋኔውን ይቀጥላል፡፡ ወይም ደግሞ፡

| | |
|---|---|
| Takka baroduu laataa | አንዴ ላግሳ ወይ |
| Narraa hinbareeduu laataa | ከኔ አያምርም ወይ |
| Takka bookkisuu laataa | አንዴ ላጌራ ወይ |
| Narraa hinfokkisuu laataa | ከኔ ያስጠላል ወይ |
| Mee takkan jedhee dhiisaa | አንዴ ብዬ ልተወው |
| Hiriyyaan garaa Ciibsaa. | ጌደኛዬን ላስደስት ይላል፡፡ |

ገመንጎራደድ ጌረርሳ መከወኑን ይቀጥላል፡፡መረጃ ሰጪዎች ከላይ የተመለከተውን ጌረርሳ አጀማመር ስልቶችን መረጃውን በሰበሰብኩበት አጋጣሚዎች ሁሉ ገመተግበር ከውነዋል፡፡

## 5.2. የታሚያን ሚና

ዋኞቹ ጌረርሳን በሚከውኑበት ጊዜ ከዋኞችን ለመበረታታት የታዳሚያን ሚና የጎላ በር፡፡ ታዳሚያን መበረታታት የሚገባውን የማህበረሰቡ እሴት እንዲበረታታ፣ ዋኞቹም እሴቱን እዲያከብሩ ለማድረግና ከዋኞች የሚያስተላልፉት መልዕክት ውነተኝነት ለማረጋገጥ (እውነት ነው ብሎ ለመመስከር) ከፍተኛ ሚና ጫውተዋል፡፡ ለምሳሌ በርትተው መሥራት (ማረስን)፣ ፈረስ መጋለብን (የግልቢያ ታዎች ሂደው በአደባባይ ከሰው ጋር መዋልን)፣ ጠመንጃን መያዝን (መታጠቅ)፣ መነገድን፣ ገንዘብን አለማባከንና ተናግሮ የማሳመን ችሎታን ማዳበርና ጥሩ ነው ሎ ማህበረሰቡ የሚያምናቸውን ማህበራዊ እሴቶችን መዳበርን አበረታተዋል፡፡ ወሬ ሰውን ማጣላትና ማህበረሰቡ ያልተገቡ ናቸው ብሎ የሚያምናቸውን ነገሮች ድረግ እንደሚያስነቅፍ ከዋኞች ጌረርሳ እየከወኑ እያሉ በመሃል በመግባት ዋኞቹ የመሰላሰልያ ጊዜ እንዲያገኙ በማድረግ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡ ዋኞቹ ውሸት እንደይናገሩ አስጠንቅቀዋል፡፡ መክረዋል፡፡ ታዳሚያን ይህንን ደርጉት ለጥቂት ደቂቃዎች የማሟሟቂያ ስንኞችን በመከወን ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ም ብሎ ከዋኞቹን አዳምጠዋል፡፡ ጌረርሳ ሲከወን ማውራት ያስነቅፋል፡፡ ስተቻል፡፡ ስለዚህ ጌረርሳ በሚከወንበት ጊዜ ማንም አያወራም፡፡ ነገር ግን በከዋኔ

መካከል ገብተው ለከዋኞቹ እረፍት በመስጠትና ለማበረታታት (ይህ ስለሚፈቀድ) የሚከተሉትን ስንኞች አዜመዋል፡፡

| | |
|---|---|
| Eemmoo yaa shoraa rooba | ኤሞ ያሾራ ሮባ |
| Maal yaada garaan gootaa. (x2) | የጀግና ሆድም ምን ያስባል፡፡ |
| Yaa nama qotuu beekuu | ማረስ የሚያውቅ ሰው |
| Akkatti qotuu beekuu | እንዴት እንደሚአርሰው! |
| Hirfii wawarraaqseetoo | እርፉን እየነቀነቀ |
| Farii daba dhoowweetoo. (x4) | ፈሩን እያስተካከለ፡፡ |
| Yaa nama yaabbii beekuu | ግልቢያን የሚያውቅ ሰው |
| Akkatti yaabbii beekuu | እንዴት እንደሚጋልብ! |
| Faanaa wawarraaqseetoo | መርገጡን እየነቀነቀ |
| Daalee dhaaba dhoowweetoo. (x4) | ፈረሱን እየኮረኮረ፡፡ |
| Yaa nama tuksii beekuu | ተኩስን የሚያውቅ ሰው |
| Akkatti tuksii beekuu | ተኩስን እንዴት እንደሚያውቅ! |
| Kilaashii daba dhoowweetoo | እላማውን እያስተካከለ፡፡ |
| Kilaashii wawarraaqseetoo. (x4) | ክላሹን እየነቀነቀ |
| Yaa nama nigdii beekuu | ንግድን የሚያውቅ ሰው |
| Akkatti nigdii beekuu | እንዴት እንደምንነግድ! |
| Birrii dadachaaseetoo | ብሩን እያጣጠፈ |
| Kiisii baha dhoowweetoo. (x4) | እንዳይባክን አድርጎ፡፡ |
| Yaa nama baaltii beekuu | ወሬን የሚያውቅ ሰው |
| Akkatti baaltii beekuu | እንዴት እንደሚያወራ! |
| Hidhii hiidhii wawarraqseetoo | ምላሱን እየላሴ |
| Lammii waldhabsiiseetoo | ወገንን እያጣለ |
| Olla addaan baaseetoo | ጎረቤትን እያለያየ |
| Nageenya dhabsiisee too. (x4) | ሰለሞን እያስጣ፡፡ |
| Yaa nama dubbii beekuu | ንግግርን የሚያውቅ ሰው |
| Akkatti dubbii beekuu | እንዴት እንደሚነገር! |
| Gaabii dadachaasee too | ጋቢን አጣጥፎ |
| Bilxii baha dhoowweetoo | ብልጥን መውጣት ከልክሎ |
| Gowwaa gala dhoowweetoo. (x4) | ሞኝን መግባት ከልክሎ፡፡ |
| Eemmoo yaa shoraa roobaa | ኤሞ ያሾራ ሮባ |
| Maal yaada garaa gootaa.(x2) | የጀግና ሆድ ምን ያስባል፡፡ |

በማለት በመሃል በመግባት ጥሩ ነው ብሎ ማህበረሰቡ የሚያምነውን ማህበራዊ እሴት አበረታተዋል፡፡ መጥፎ ልማድን ናቅፈዋል፡፡ ከዋኞቹም ከመጥፎ ነገሮች (ከወረኛነት) ራሳቸውን እንዲቆጥቡ አስጠንቅቀዋል፡፡ የሚከውኑት ጌረርሳ በእውነት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን መክረዋል፡፡

ታዳሚያን ከዋኞች ሚስጥራቸውን በጌረርሳ በሚገልፁበት ጊዜ በመሃል በመግባት በዜማ በተቻላቸው መጠን ሚስጥራቸውን እንዲጠብቁም አበረታተዋል፡፡ ከአቅማቸው በላይ ከሆነ እንጂ ምስጥራቸውን እንዳያወጡ መክረዋል፡፡ ምክንያቱ ሚስጥር ለተመረጠ ለልብ ጓደኛ እንጂ ለማንም ሰው አይናገርምና ነው፡፡

ይህን እንዲህ በማለት ከውነዋል፡፡

| | |
|---|---|
| Beeljigii malee kooltii hin hidhatinii (x2)<br>Yoo siigamte malee waa'ee hin himatini. (x2) | ቤልጂግ እንጂ ኮልት አትታጠቅ<br>ከአቅምህ በላይ ከሆነ እንጂ ሚስጥርህን አትናገር፡፡ |

በማለት ሚስጥር መጠበቅ አንዱ ማህበራዊ እሴት በመሆኑ ከዋኞች የራሳቸውን ሚስጥር እንዲጠበቁ፣ ከአቅማቸው በላይ ሲሆን ግን መፍትሄ ለመሻት እንዲናገሩ መክረዋል። ከዋኞችን አበረታተዋል፡፡ ሞራልም ይሰተዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ከዋኞች ሥጋታቸውንና ጭንቀታቸውን በሚገልፁበት ጊዜ አበረታተዋል፡፡ ለምሳሌ አንድ ከዋኝ ጠላቴ ይጎዳኛል ብሎ በሚሰጋበት ጊዜ ፍርሃቱ እንዲወገድ አድርገዋል፡፡ ሰው እውነተኛና ጥሩ ሰው ሆኖ መኖር አለበት እንጂ ሰው ይጎዳኛል ብሎ በመፍራት እንደማይገባ መክራዋል፣ አበረታተዋል፡፡ ለምሳሌ አቶ መኮንን ደሜ ጠመንጃ መያዝ አይችሉም ብለው የከሰሱዋቸው ሰዎች ከዚህ የበለጠ ይጎዱኛል ብለው በመስጋት ጌረርሳ በሚከውኑበት ጊዜ ታዳሚያን እንዲ በማለት መክረዋል፡፡

| | |
|---|---|
| Yaa daldu yaa daldu<br>Yaa olla qamalee (x2)<br>Woomtuu homaa nama hin gootu<br>Waaqa malee<br>Akkanumaan akkana taata malee<br>Nama hin sodaatin<br>Waaqa gurraacha malee. | አንተ ዘንጀሮ (x2)<br>የጦጣ ጎረቤት<br>ማንም ሰውን አይጎዳም<br>እግዚአብሄር እንጂ<br>ዝም ብለህ ትሰጋለህ እንጂ<br>ሰውን አትፍራ<br>እግዚአብሄር እንጂ፡ በማለት |

ከውናሉ፡፡ ከዋኙን ያደፋፍራሉ፡፡ ከላይ በቀረበው ጌረርሳ ውስጥ የመጡት "ዘንጀሮና ጦጣ" የሚሉት ቃላት የመጡት የጌረርሳውን ግጥም ምትን ለመጠበቅ ብቻ እንጂ የተለየ መልዕክት ለማምጣት እንዳልሆነ አምስቱም ከዋኞች 21/06/2004 ዓ.ም ገልፀውልኛል፡፡

በተጨማሪም ታዳሚያን ከዋኞችን አሞግሰዋል፡፡ በበለጠ በሞራል እንዲከውኑ አድርገዋል፡፡

ነዋኔውን እንዲቀጥል አደፋፍረዋል፡፡

| | |
|---|---|
| Varra ________ malee | የ _________ ቤተሰቦች እንጂ |
| Maaltu weessoo lama raasaa | ማን በቀን ሁለቴ ወተት ይንጣል |
| Veessoo lama raasaa | ወተት ይንጣል |
| ________ maree | _________እንጂ |
| Maaltu teessoo nama kaasaa | ማን ከመቀመጫ ያስነሳል |
| eesso nama kaasaa | ከመቀመጫ ያስነሳል |
| aa __________ mee shaallali | አንተ _________ ሽልል እስቲ |
| Mee maggali. | ተዝናና እስቲ፡፡ |

ባዶ ቦታ የሚሞሉት የከዋኞችን ስም ነው፡፡ እኔ መረጃውን በሚሰበስብበት ጊዜ ታዳሚያን የአምስቱን ግለሰቦች ስም እየተጠቀሙ ክብራቸውንና በማህበረሰቡ ላቸውን ተቀባይነት በመግለፅ ስያበረታቱ ተመልክቻለሁ፡፡ ታዳሚያን ከላይ ተገለፁትን ሲያዜሙ በህብረት ሆነው ነው፡፡ አቀማመጣቸውም ጎን ለጎን ሆነው ው፡፡

ታዳሚያን አንዱ የከዋኔ አውድ በመሆናቸው የክዋኔው ግብ መምታት ከፍተኛ ሚና ጫውተዋል፡፡ ታዳሚያን ባይኖሩ ከዋኞች ያደረጉት ክዋኔ አይኖርም ነበር፡፡ ክንያቱም የክዋኔ አነሳሽ በመሆንም አገልግለዋል፡፡ በዚህ የጥናት ሂደት ውስጥ ንደተረዳሁት አጋጣሚዎች ካልቀሰቀሱዋቸው በስተቀር በማንኛውም ጊዜ ከዋኞች ረርሳ መከወን አይችሉም፡፡ ከክዋኔ መነሳሻ አጋጣሚዎች ውጪ ክዋኔውም ሆነ ሜቱ አይመጣላቸውም፡፡ መረጃ ለመሰብሰብ ከዋኞቹ ጋ በሄድኩበት ጊዜ ሁሉ ረርሳ እንዲከውኑልኝ ጠይቄአቸው አረጋግጫለሁ፡፡ ከዋኞቹ ራሳቸው የሆና ጋጣሚ ከልቀሰቀሳቸው መከወኑ እንደሚከብዳቸው መረጃ ለማሰባሰብ ተገናኟዋቸው አጋጣሚዎች ደጋግሞ ነግረውኛል፡፡ ነገር ግን ታደሚያን ባሉበትና አጋጣሚዎቹ ውበት ባለው መልኩ ጌረርሳውን ከውነዋል፡፡ በመሆኑም ታደሚያን ክዋኔው ውበት በመስጠትም ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡

## ማጠቃለያ

ስነ-ቃል የማህበረሰቡን ብሎም የግለሰቦችን ህይወት ለማሳየት የጎላ ሚና ይጫወታል፡፡ ጥንት የሰው ልጅ ሀሳቡን በጽሑፍ መግለፅ ባልጀመረበት ጊዜ አንስቶ አሁን እስካለንበት ጊዜ ድረስ ስነ-ቃል የማህበረሰቡ ከዚያም አልፎ የግለሰቦችን እውቀት ከመግለፅም በዘለለ ፈር ማስያዥያና ተሞክሮ ማካፈያ በመሆን እያገለገለ ይገኛል፡፡ ማህበረሰቡ ተተኪውን ትውልድ ይቀርፅበታል፡፡ ትውልዱ መከተል ያለበትን ሞዴል (አርአያ) እየፈጠረ ለትውልድ መንገድ ያሳያል፡፡ ስነ-ቃል ማህበረሰቡ ወይም ግለሰቦች ያለፉበትንና አሁን ያሉበትን የአኗኗር ሁኔታ ለመገንዘብ ያስችላል፡፡ የማህበረሰቡ ወይም የግለሰቦች የህይወት ፍልስፍና፣ አስተሳሰብና ገጠመኞች በአጠቃላይ ግላዊ ወይም ማህበራዊ እሴት ይገለፁበታል፡፡ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች ከሚገለፁባቸው የስነ-ቃል ዓይነቶች መካከል በኦሮሞ ዘንድ ጌረርሳ አንዱ ነው፡፡

ጌረርሳ የግለሰቦች ከዚያም አልፎ የኦሮሞ ማህበረሰብ የህይወት ገጠመኞች ጥርቅም ነው፡፡ ግለሰቦች በህይወታቸው የጎዞ ሂደት ውስጥ ያጠረቃቀሙትን ገጠመኞች፣ ከገጠመኞቻቸው የቀሰሙትን እውቀት ወይንም የህይወት ተሞክሮ ይገልፁበታል፣ ያስተላልፉበታልም፡፡ ከ01/06/2004 እስከ 30/07/2004 ዓ.ም ድረስ በጌረርሳ ላይ ባደረኩት የመስክ ጥናት የተገነዘብኩት ይህንኑ ነው፡፡ ጥናቱ ያተኮረባቸው አምስቱ ግለሰቦች በጌረርሳ ያስተላልፉ የነበረው መልዕክት የህይወት ተሞክሮአቸው መሆኑ በጥናቱ ውስጥ ተገልጿል፡፡ ግለሰቦቹ ያጋጠሙዋቸውን ችግሮችና ኑሮአቸውን ለማሸነፍ ያደረጉትን ተጋድሎ በጌረርሳ አስተላልፈዋል፡፡ በተለይ አምስቱም ግለሰቦች ከነበረባቸው ድህነት ለመላቀቅ ከሚኖሩበት ቀዬ እስከመሄድ ድረስ ደርሰዋል፡፡ የሄዱበት ቦታም አስቸጋሪ ኑሮ አሳልፈዋል፣ ተርበዋል፣ ተጠምተዋል፣ ታርዘዋል፡፡ በተወለዱበት ቀዬም ቢሆን የተለያዩ ውጣውረዶችን አሳልፈዋል፡፡ ኑሮአቸውን ለማሸነፍና ሕይወታቸውን ለመለወጥ የተለያዩ ሥራዎችን ለመሥራት ጥረት አድርገዋል፡፡ ግለሰቦቹ እነዚህንና የመሳሰሉትን ገጠመኞቻቸውን ጌረርሳን በመከወን ገልፀዋል፡፡ በልፋታቸው ኑሮአቸውን የለወጡ ግለሰቦች አስቸጋሪውን ሁኔታ እንዴት እንዳለፉና አሁን ላሉበት ደረጃ እንዴት እንደደረሱም በጌረርሳቸው አመላክተዋል፡፡

ከያንያኑ በምዕራፍ አራት ውስጥ ከነትንታኔው የቀረበውን ጌረርሳ ሲከውኑ የታዳሚያንን ስሜት ለመሳብና ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ጎልቶ እንዲደመጥ ለማድረግ ከሚከውኑት ጌረርሳ መልዕክት ጋር የሰመረ የአካል እንቅስቃሴ አድርገዋል፡፡ እንደ ጌረርሳው መልዕክት ሁኔታ በመንጎራደድ፣ ፊታቸውን በመጨምደድ፣ አይናቸውን በማጉረጥረጥና ጎንበስ ቀና በማለት ከውነዋል፡፡ በአጠቃላይ አምስቱ መረጃ ሰጪዎች በህይወታቸው የጉዞ ሂደት ውስጥ ያጋጠማቸውን ጌረርሳ በመከወን በጥሩ ሁኔታ ገልጸዋል፡፡

ከዋኞቹ ጌረርሳውን በሚከውኑበት ጊዜ ከያንያኑን ለማበረታታትና ክዋኔው ሥርዓቱን ጠብቆ እንዲጓዝ ለማድረግ የታዳሚያን ሚና የጎላ ነበር፡፡ ከያንያኑ የማህበረሰቡን እሴት እንዲጠብቁ የማድረግ ሚናም ተጫውተዋል፡፡ ውሸት እንዳይናገሩ፣ ፍራትን እንዲያስወግዱና ምስጢራቸውን እንዲጠብቁ መክረዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ታዳሚያን ክዋኔ ውስጥ ተሳታፊ በመሆን ለክዋኔው ድምቀት ከመስጠታቸውም በላይ ከዋኞችን ለክዋኔ በማነሳሳት ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡ የከዋኞችን ስሜት ቀስቅሰው ክዋኔ ውስጥ የሚያስገባቸውን ጉዳዮች በማንሳት ከዋኞች በከፍተኛ ሞራል እንዲከውኑ አድርገዋል፡፡ ለምሰሌ ታደሚያን ከዋኞች የሰለፏቸውን ውጣ ውረዶች ማለት ከተወለዱበት መንደር ርቀው መሰደዳቸውን፣ ከሄዱበት ቦታ ያጋጠማቸውን ችግሮች፣ ችግሮቹን ለመቋቋም ያደረጉትን ተጋድሎ፣ ድህነትን ለማሸነፍ ከዋኞች ያደረጉትን ህልህ አስጨራሽ ትግል በማንሳት ከዋኞች ክዋኔ ውስጥ እንድገቡ አነቃቅቷል፡፡

# ዋቢዎች

ddis Tolesa. **The Historical Transformation of a Folklore Genre: The 'Geerarsa' as National Literature of the Oromoo in the Context of Amhara Colonization in Ethiopia.** Bloomington: Indeana University, PhD Dissertation, 1990.

auman, Richard. "Verbal Art as Performance"**American Anthropologist New Series.** Vol. 77, No.2 (1975), pp290-311.

_________. "Performance" **Folklore Cultural Performances, and Popular Entrtainments: a Communications-Centered Handbook**. (Ed.). Richard Bauman, New York: Oxford University press. 1992.

_________. "The Field Study of Folklore in Context" **Handbook of American Folklore**. (Ed.) Richard M.Dorson., Bloomington: Indiana University Press, 1983.

en-Amos, Dan. "Context" in Context" **Western Folklore**. Theorizing Folklore Toward's New Perspectives on the Politics of Culture. Vol. 52, No. 2/4, (1993), pp. 209-226.

rger, Harris M.and Giovanna P. Del Negro. "Bauman's Verbal Art and the Social Organization of Attention: The Role of Reflexivity in the Aesthetics of Performance" **Journal of American Folklore.** Vol. 115, No 455, (2002), pp. 62-91.

onner, Simon J. "Art, Performances and Praxis: The Rhetoric of Contemporary Folklore Studies" **Western Folklore.**Vol. 47, No.2, (1988), pp. 75-101.

eswell, John W. **Qualitative Inquiry & Research Design: Choosing Among Five Approaches.** 2nd ed.Thousand Oaks, London & New Delhi: Sage Publications, Inc, 2007.

rson, M. Richard. "Concepts of Folklore and Foklife Studies" **Folklore and Folklife: An Introduction.** Chicago and London: The Chicago University Press. 1972.

leral Democratic Republic of Ethiopia Central Agricultural Census Commission. **Ethiopian Agricultural Sample Enumeration, 2001/02 (1994 E.C.) Result for**

**Oromia Region: Statistical Report on Livestock and Livestock Products.** Part V. Addis Ababa: C.S.A. July,2003.

___________. **Ethiopian Agricultural Sample Enumeration, 2001/02 (1994 E.C.) Result for Oromia Region: Statistical Report on Area and Production of Permanent crops.** *Part iii.B* Addis Ababa: C.S.A. July,2003.

___________. **Ethiopian Agricultural Sample Enumeration, 2001/02 (1994 E.C.) Result for Oromia Region: Statistical Report on Area and Production of Temporary crops.** Part iii.A Addis Ababa: C.S.A. July,2003.

Federal Democratic Republic of Ethiopia Population Census Commission Centeral Statistical Agency. **The 2007 Population and Housing Census of Ethiopia Result for Oromiya Region: Statstical Report on Population Size and Characterstic.** Part 1. Addis Ababa: Branna Printing Enterprise, 2010.

Finnegan, Ruth. **Oral Literature in African.** Nairobi: Oxford University Press, 1970.

________. **Oral Poetry: It's Nature, significance and Social Context.** London: Cambridge University Press, 1977.

________. **Oral Tradition and the Verbal Arts: A Guide to Research Practices.** (ed.), Anthory Good, London and New York: Routledge Taylor and Francis Group, 1992.

Hufford, Mary. "Context" **Journal of American Folklore.** Common Ground: Key Words for the Study of Expressive culture, Vol. 108, No. 430, (1995), pp. 528-549.

Kapchan, Deborah A. "Performance" **Journal of American Folklore.** Common Ground: Key Words for the Study of Expressive Culture, Vol. 108, No, 430, (1995), pp. 479-508.

Lodico, Marguerite & etal. **Methods in Educational Research: From Theory to Practice.** 2nd ed. Sanfrancisco: John Wiley & Sons, Inc, 2010.

MacDonald, Donald A. "Field Work: collecting Oral Literature" **Folklore and Folklife: An Introduction.** (Ed). Richrd M. Dorson, Chicago and London: The University of Chicago Press, 1972.

Ministry of Education. **History Grade 10: Student Text Book.** (ed. By Girma Negash) Addis Ababa: Mega Publishing Enterprise, 2005.

Oromia Education Bureau (OEB) and Japan Internattional Cooperation Agency (JICA). **SMAPP Project: School Location Map of Adea Berga Woreda.** Addis Ababa: Baundery Project of JICA-EBO, 1998 E.C.

Sims, M.C. and Stephens M. **Living Folklore: An Introduction to the Study of People and Traditions.** Logan: Utah State University Press, 2005.

Vanderstoep, Scott W. & Deirdre D. Johnston. **Research Methods for Everyday Life: Blending Qualitative and Quantitative Approaches.** Sanfrancisco: John Wiley & Sons, Inc, 2009.

Alamaayyoo Hayileefaa. **Seenaa Oromoo Hanga Jaarraa 16**ffaa. Gul. 2ffaa , Finfinnee: Biiroo Aadaafi Turizimii Oromiyaa, 1998.

Iwunatu Admaasuu. **Xiinxala Geerarsa Bara Mootii Kumsaa Morodaa.** Waraqaa Eebbaa Digrii Jalqabaa Gamiisaan Guutuuf Qophaa'e. Dhaabbata Qo'annoofi Qorannoo Afaanota Itoophiyaatti Muummee Afaaniifi Ogbarruu Oromoo, Yunivarsiitii Addis Ababaa, Waxabajii, 2002.

Waajira Adaafi Tuurizimii A /A/ Bargaa. "**Seenaa Aanaa Ada'aa Bargaa.**" (ያልታተመ ተባዝቶ የተጠረዘ ሰነድ), 2004።

ሀይደር አማን። የአጋርፋ የአዳኞች ሙገሳ ግጥሞች ይዘት ትንተና። በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ክፍል የቀረበ ድግፅ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1998።

ባሕሩ ዘውዴ። የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983። አዲስ አበባ፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 2003።

ሽጉጤ ተሸመ። በጉጂ ጎሣ የቦሊቱ ጌረርሳ ግጥሞች። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፣ 1986።

አለም እሸቱ። መሰረታዊ የምርምርና የዘገባ አፃፃፍ። አዲስ አበባ፡ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡1997።

አምሳሉ አክሊሉ፡፡ አጭር የኢትዮጵያ ስነ-ፅሑፍ ታሪክ፡፡ (በእስቴንስል ተባዝቶ የተጠረዘ)፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣1976፡፡

ከባ መኮንን፡፡ በምስረቅ ወለጋ ዞን የጀርደጋ ጀርቴ ወረዳ የአዳኞች ሙገሳ ግጥሞች ይዘት ትንተና፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ክፍለ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፣ 1996፡፡

ወርቁ ደቻሳ፡፡ በወለጋ ክ/ሀገር፣ ሆሮ ጉዱሩ አውራጃ የኦሮሞ ብሔረሰብ ቀረርቶ ግጥሞች ትንተና፡፡ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ጽሑፍ ክፍል የቀረበ ድማጽ፣ አዲስ አበባ ዮኒቨርሲቲ፣ 1978፡፡

ገመቹ ገላልቻ። በወለጋ ክፍለ ሀገር፣ የደሌ ወበራ የኦሮሞ ብሔረሰብ የጌረርሳ /ጎሽ ገዳይ/ግጥሞች ከአደን ሥርዓቱ ጋር፡፡ ድማፅ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትየጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ የቀረበ፣ 1989፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ የስነ-ጽሑፍ መሰረታዊያን፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 2000፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ የሥነ-ቃል መምሪያ። አዲስ አበባ፣ ኢትዮ ጥቁር አባይ አታሚዎች፣ 1991፡፡

_________፡፡ "የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች አፋዊ ኪነተቃል ጥናት" የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ መፅሔት፡፡ ቁ.2፣ 1984፣ 3-26፡፡

http://www.ocha-eth.org. 10/09/2004 E.C. 2:30.

## የመረጃ ሰጪዎች አጭር ፕሮፋይል

| የመረጃ ሰጪዎች ስም | ፆታ | ዕድሜ | የትምህርት ደረጃ | የመኖርያ ቦታ | መተዳደርያ ቸው | ለማህበረሰቡ የሚሰጡት ግልጋሎት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አቶ አባተ ኤጀርሳ | ወንድ | 38 | ያልተማሩ | ደኩ ቀርሳ ቀበሌ ገ/ማህበር | ግብርናና የጉልበት ሥራ | |
| አቶ ብርሃኑ አዱኛ | ወንድ | 35 | እስከ 5ኛ ክፍል | ደኩ ቀርሳ ቀበሌ ገ/ማህበር | ግብርና | የጎጥና የዕድር ፀሐፍ |
| አቶ ቸሩ ድንቁ | ወንድ | 42 | እስከ 3ኛ ክፍል | ደኩ ቀርሳ ቀበሌ ገ/ማህበር | ግብርና | የጎጥና የዕድር ፀሐፍ |
| አቶ ድሪባ ለታ | ወንድ | 55 | ያልተማሩ | ሬጂ ከተማ | ግብርና | የሀገር ሽማግሌ |
| አቶ መኮንን ደሜ | ወንድ | 61 | ያልተማሩ | ደኩ ቀርሳ ቀበሌ ገ/ማህበር | ግብርናና ዘበኝነት | የሀገር ሽማግሌ |

# አባሪዎች

## አባሪ 1

1. የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች

ከሁሉም አስቀድሜ ለቃለ መጠይቁ ስለተባበሩኝ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

1. ስምዎ ማን ይባላል?
2. የተወለዱበት ቀን፣ዓመተ ምህረት ይንገሩኝ፡፡
3. የትውልድ ቦታዎስ ዬት ነው?
4. አሁንስ ዬት ይኖራሉ?
5. የወላጅዎን ሙሉ ስም ይንገሩኝ፡፡
6. የአስተዳደግ ሁኔታዎ ምን ይመስላል?
7. በልጅነትዎ ዘመን የወላጅዎ የኑሮ ሁኔታ ምን ይመስላል?
8. ቤተሰብዎ በምን ይተዳደሩ ነበር?
9. የቤተሰብ መጠን ምን ያህል ነበር?
10. በልጅነት ዘመንዎ ምን ዓይነት ጫወታ ይወዱ ነበር?
11. በምን አጋጣሚ ነው የሚጫወቱት?
12. በጫወታው ምን ምን ግላዊም ይሁን ማህበራዊ ጉዳዮች ትገልፁበት ነበር?
13. በልጅነት ዘመንዎ ወላጅዎን ምን ምን በመሥራት ይረዱ ነበር?
14. ተምረዋል? ከተማሩ የክፍል ደረጃዎን ይንገሩኝ፡፡ ዬት ተማሩ?
15. ካልተማሩ ለምን?
16. የጋብቻ ሁኔታዎን ይንገሩኝ፡፡ አግብተዋል? መች አገቡ?
17. ካላገቡ ለምን?
18. ስንት ልጆች አሉዎት? ልጆችዎ በምን ሁኔታ ለይ ይገኛሉ?
19. አሁን ያሉበት የኑሮ ሁኔታ ምን ይመስላል? በምን ስራ ይተዳደራሉ?
20. ከአከባቢ ማህበረሰብ ጋር ያለዎት ግንኙነት ምን ይመስላል?
21. ለማህበረሰቡ በተለያዩ የአላፍነት ደረጃዎች የሚተሰጡት አገልግሎት አለ? ምንድነው እሱ?
22. በህይዎት ዘመንዎ የማይረሱት ያሳዘነዎ ወይንም ያስደሰተዎ ነገር አለ? ይንገሩኝ እስቲ፡፡
23. በአሁኑ ጊዜ የሚትወዱት የጫወታ ዓይነት አለ? ምን ምን ናቸው?
24. መች መች ይጫወታሉ? ለምን ይጫወታሉ? ምን ዓይነት ግላዊም ይሁን ማህበራዊ ጉዳዮች ይገልፁበታል?
25. ጌረርሳን መከወን እንደሚወዱ ሰምቻለሁ፡፡ መች መች ይጫወታሉ?
26. ምን ለመግለፅ ይጫወታሉ?
27. ጌረርሳ መከወኑን ከማን ተማሩ?

# አባሪ 2

## 28.አምስቱ ግለሰቦች የከወኑት ትንታኔ ውስጥ ያልገቡ የጌረርሳ ስብስብ

### 2.1. አቶ አባተ የከወኑት ጌረርሳ

| | |
|---|---|
| Bara seetee barashee | ዘመኑ ዘመን መሰለህ |
| Fardatu garbuu lixee | ገብስ ውስጥ ገባ ፈረስ |
| Baratu darbuu didee | አላልፍ አለ ዘመን |
| Takka ala bulanii | አንዴ ውጭ ማደር ነው |
| Maalitti beekti dawween | ሞኝ ምን ታውቃለች |
| Tokkuun dhiira muranii | ወንድን እንዴ መቁረጥ ነው |
| Maalitti beekti gadheen. | ፈሪ ምን ታውቃለች፡፡ |
| Akkamiin karra banuu | እንዴት በሩን ይከፍታሉ |
| Gagagsaniiti malee | ገገግ አድርጎ እንጂ |
| Akkamiin dhiira ganuu | እንዴት ወንድን ይከዳሉ |
| Kakataniiti malee | ምለው ተገዝቶ እንጂ |
| Kakaksee karra hin banuu | ገገግ አድርጌ በርን አልከፍትም |
| Kakaksuun dhiisa malee | እተወዋለሁ እንጂ |
| Kakadhee dhiira hinganuu | ምዬ ወንድን አልከድም |
| Kakachuun dhiisa malee | እተወዋለሁ እንጂ፡፡ |
| xxxxx | |
| Ka'een goota faarsaa | ተነስቼ ጀግናን ላሞግስ |
| Goota oromoodhaa | የኦሮሞን ጀግና |
| Insiraa bishaanii | የውሃ እንስራ |
| Afaan dhidhiphinaa | አፉ ጠባብ ነው |
| Hennaan goota Faarsuu | ጀግናውን ሳሞግስ |
| Seesaan na jibbinnaa . | ፈሪ ልጠላኝ ነው፡፡ |
| Jabanaan cabe jedhee | ጀበናው ተሰበረ ብዬ |
| Buna dhuguu hindhiisuu | ቡና መጠጣትን አልተውም |
| Zabanni bade jedhee | ዘመኑ ከፋ ብዬ |

| | |
|---|---|
| Waa'ee garaakoo hindhiisuu. | የልቤን አልተውም፡፡ |
| xxxx | |
| Kan qotiyyoon na nyaatee | በሬው የወጋኝ |
| Kormi filaan na hindhiisuu | ቀንዳሙ ወይፈን አይተወኝም |
| Kan lammiin nanyaaree | ዘመዶቼ የጠሉኝ |
| Hormi silaa na hindhiisuu. | ሌሎች ሰዎች አይተውኝም፡፡ |
| Bara seetee Barashee | ዘመኑ ዘመን መሰለህ |
| Dhiiratu itillee hafee | አነጠፈ አልጋ ወንድ |
| Dubartiitu darbee rafee. | አልፋ ተኛች ሴት፡፡ |
| xxxx | |
| Gateettiin na rifataa | ትከሻዬ ይደነግጥብኛል |
| Kilaashiin hidhaa laataa | ክላሽን እታጠቃለሁ ወይ |
| Mudhii koo na rifataa | ወገቤ ይደነግጥብኛል |
| Zinnaaran hidhaa laataa | ዝናርን ይታጠቃለሁ ወይ |
| Harki koo na rifataa | እጄ ይደነግጥብኛል |
| Xalaatan qalaa laataa. | ጠላትን አርዳለሁ ወይ፡፡ |
| Duultu duulta yaa daalee | ከዘመትክ ትዘምታለህ እንጂ ፈረስ |
| Maaltu goodaa si lagaa | ዘመቻን ማን ይከለክለሃል |
| Duutu duuta yaa namsee | ከሞትሽ ትሞቺያለሽ እንጂ ነፍሴ |
| Maaltu du'a si lagaa. | ማን ሞት ይከለክልሻል፡፡ |
| Dinnicha maaliif nyaatu | ድንችን ለምን ያርሳሉ |
| Baraan ba'uufi malee | ለችግር ማሳለፊያ እንጂ |
| Ilma maaliif dhalchuuሌ | ጅን ለምን ይወልዳሉ |
| Maqaan falmuufi malee. | ስምን ለመትከል እንጂ፡፡ |
| xxxx | |
| Waaqni maa barii didaa | ለሊቱ ለምን አይነጋም |
| Waaqnibarii hindinnee | ለሊቱ መንጋቱን አልተወም |
| Tikseetu loon yaasuu didee | እረኛ ከብት አላሰማራ አለ እንጂ |
| Tiseen loon yaasuu hindinnee | እረኛ እምቢ አላለም |
| Boosettiitu qopheessuu didee | ሴቲቱ አላሰናዳ አለች እንጂ |
| Boosettii boolla qayyaa. | ሙያ የሌላት ሴት፡፡ |

| | |
|---|---|
| xxxxx | |
| Qoricha hoolaa coomtee | ለሰባች በግ መድሃኒት |
| Qaluudha malee maaliree | ማረድ እንጂ ምንድነው |
| Qoricha dhiira quuftee | ለጠገበ ወንድ መድሃኒት |
| Gobuudha malee maaliree | መቀጥቀጥ እንጂ ምንድነው፡፡ |
| Daldeessi maal nyaataree | ዝንጀሮ ምን ይበላል |
| Udaan baddeessaa malee | [illegible]ዴሳ ፍሬ እንጂ |
| Qallaan kee maal yaadaree | [illegible]ኄ ምን ያስባል |
| Du'aaf ajjeechaa malee. | ገድሎ መሞትን እንጂ፡፡ |

## 2.3. አቶ ብርሃኑ የከወኑት ጌረርሳ

| | |
|---|---|
| Irraan gadee tokkosee | ቁልቁል ተኩሼ |
| Jajjaba lixee laataa | ግንድ ውስጥ ገባ ወይ |
| Mirga malee geeraraan | ያለ አቅሜ ሽለልኩና |
| Taazzaba lixee laataa. | ትዝብት ውስጥ ገባው ወይ፡፡ |
| Xxxx | |
| Yaa guutee yaa guutamaa | አንተ ጉቴ አንተ ጉተማ |
| Na guute jadhee hinbeekuu | ሞላኝ ብዬ አላውቅም |
| Na guute dubbiin namaa. | ሞላኝ የሰው ነገርማ፡፡ |
| Indaaqqoo guutuu filuu | የአውራ ዶሮ |
| Baalliin lafa danqaraa | ክንፏ መሬት ይታከካል |
| Humna koo guutuu jiruu | ሙሉ ጉልበት እያለኝ |
| Hirree koo guutuu jiruu | ሙሉ ሰውነት እያለኝ |
| Maafan nama gabbaraa. | ሰውን ምን ያስለምነኛል፡፡ |
| Boqqooloo muktakkittii | አንድ እንጨት በቆሎ |
| Ni qorqo moo ni falfaluu | ይፈለፍላሉ ወይስ ይግጣሉ |
| Si jibbee namtakkittii | ባንድ ሰው መጠላት |
| Ni kolfu moo ni dallanuu | ይንቃሉ ወይስ ያኮርፋሉ |
| Maal abbaa sheet dallanuu | ለምንስ ያኮርፋሉ |
| Kolfaniit bira darbuu. | ስቆ ማለፍ ነው እንጂ፡፡ |
| Xxxx | |
| Jijjigaa mana gannaa | ፍርስራሽ የክረምት ቤት |

| | |
|---|---|
| Citaatu walittti qabee | ሣር ነው ያያያዘው |
| Saksaakkaa garaa lugnaa | ቦጭባጫ የፈሪ ሆድ |
| Zaqqiitu walitti qabee | ቀበቶ ነው ያያያዘው፡፡ |
| Xxxx | |
| Farda guddaa dulloomee | ላረጀ ፈረስ |
| Okeenyi darbaa taatee | ግጦሽ በእቅፍ ሆነች |
| Ilma namaa iyyoomee | ለደሀዬ ሰው |
| Nageenyi mamaa taatee | ነምታም በልክ ሆነች |
| Dubbiin daddarbaa taatee | ንግግርም ያላግባብ ሆነች፡፡ |

.4. አቶ ቸሩ ድንቁ የከወኑት ጌረርሳ

| | |
|---|---|
| Lagni hamaan gudarii | ትልቅ ወንዝ ጉደር ነው |
| Kan dheeraan hinceenee | ረጅም ሰው የማይሻገረው |
| Kan gababaan hindhaqqabnee | አጭር ሰው የመይደርስበት |
| Na qabe kaa dhibeen koo | በሽታዬ ያዘኝ |
| Na qabe kaa lapheerraa | ልቤን አስጨንቆ ያዘኝ |
| Kan firri namaa hin beeknee | ዘመድ የማያውቅ ለሰው |
| Kan abbaan guggubatuu. | አባቱን ብቻ የምጨነቅበት፡፡ |
| Xxxx | |
| Falaqqaqaa boqqoolloo | በቆሎ መሸልቀቅን |
| Lafa ciraattan baree | በቁጥቋጦ መሬት ለመድኩ |
| Falaqqaqee tokkosuu | ፈልቅቄ መተኮስ |
| Wajagiraattan baree | በወጅግራ ለመድኩ |
| Wajagiraa dheeraa koo | ወጅግራ ረጅሙ |
| Yaa gootatti reebaa koo | ለጀግና የሚያግዘው |
| Yaa lugnarraa dheessaa koo. | ከፈሪ የሚሸሸው፡፡ |

5. አቶ ድርባ ለታ የከወኑት ጌረርሳ

| | |
|---|---|
| Immaamiyyee haatitoo | እናቴ እማምዬ |
| Mataa na qaqqabattee | እራሴን ይዛ |
| Matumaan ooli jettee | በራስህ ዋል አለችኝ |
| Abbaabbaan koo na qaqqabee | አባቴም ይዞኝ |

| | |
|---|---|
| Miila koo na qaqqabee | እግሬን ይዞኝ |
| Miila naa ooli jedhee | በእግርህ እደር አለኝ |
| Hin oolu maafan oolaa | አልውልም ለምን እውላለሁ |
| Xiyyiitii shamatamee | ጥይት ተሸምተው |
| Hiriyyaa maraxamee | ጓደኛ ተመርጠው |
| Xiyyiitii shuushuu jedhee | ጥይት ሹሹ ብሎ |
| Hiriyyaa uu Jedhee. | ጓደኛ ሁሁ ብሎ:: |
| Xxxx | |
| Haati mucaa baalagee | የባለጌ ልጅ እናት |
| Garaa joobiraa laaltee | የአሞራን ሆድ አይታ |
| Qallaa koo Nyaate jettee | ልጄን በላብኝ ትላለች |
| Qallaa ishee maaltu nyaataa | ልጅዋን ማን ይበለዋል |
| Qallaa isheetu diina nyaatee. | እሱ ነው ጠለትን የበላው:: |
| Xxxx | |
| Beeka kaa beeka beekaa | አውቃለው አውቃለሁ |
| Hundattuu beeka beekaa | ሁሉንም አውቃለሁ |
| Beela'ees bulee beekaa | ርቦኝም አድሬ አውቃለሁ |
| Quufees bulfadhee beekaa | ጠግቤም አድሬ አውቃለሁ |
| Hidhees bulfadhee beekaa | አስሬም አሳድሬ አውቃለሁ |
| Hidhamees bulee beekaa. | ታስሬም አድሬ አውቃለሁ:: |
| Xxxx | |
| Kormaan hindaaqqoo akka jedhee | አውራ ዶሮ እንዳለ |
| Cuuccutii manaa hinbaasiin | ጫጩቶቹን ከቤት አታውጭ |
| Allaattiitu fudhata jedhee | አሞራ ይበላቸዋል አለ |
| Abbaan niitii boosettii waan jedhee | ሙያ የለላት ምስት ባል እንዳለ |
| Qayya hinulatin jedhee | ቀያ አትታጠኝ አለ |
| Yoon uladhe maal jennaan | ቀያ ከታጠንሽ |
| Yookaan shishinii gubdaa | ወይም ቀምስሽን ታቃጥያለሽ |
| Yookaan qaama kee gubdaa. | ወይ ሰውነትሽን ታቃጥያለሽ:: |
| Xxxx | |
| Lafa qotuu nu dagee | መሬት ማረስ ከልክሎን |
| Guraaroo magarfatee | አረም አበቀለ |

| | |
|---|---|
| Guraaroo sanuu nyaatee | ያንን አረሙን በልቶ |
| Gudeeda magarfatee | ሰውነትን (የመራብያ) አበቀለ |
| Gudeeda saniin lolee | በዚያ ሰውነት ታግሎ |
| Sariitii magarfatee | ሰራቲን አበቀለ |
| Sariitiin kophaa hinloluu | ሰራቲ ብቻውን አይታግልም |
| Qabata boosoo malee | በቦሶ ሰበብ እንጂ |
| Boosoon qayya hinulattuu | ቦሶ ቃያን አትታጠንም |
| Qabata koomoo malee | ኮሞ ምክንያት እንጂ |
| Boosettii garaa raachaa<br>Obboleettii billaachaa | ለሆዷ ያደረች ቦሶ<br>ያለ ቦታዋ የሚትውል |
| Maali yaa boosoo jennaan | ምነው ያለቦታሽ ዋልሽ ስትባል |
| Gurbeetu ns dide jettee | ልጁ እምቢ አለኝ አለች |
| Gurbeen maal ishee dida | ልጁ ምን እምቢ ይላታል |
| Isheetu baddeessaa didee | እስዋ ረስዋን ማጽዳት እምቢ አለች እንጂ፡፡ |

## 2.5. አቶ መኮንን የከወኑት ጌረርሳ

| | |
|---|---|
| Bosonuu kaattun argee | የሚትሸሽ ድኩላን አየሁት |
| Maali yaa bosuu jennan | ምነው ድኩላ ስላት |
| Eeboon dheessa naan jettee | ጦርን እየሸሸው ነው አለችኝ |
| Xiyyiitiin reeba jettee | ጥይትን አባርራለሁ አለችኝ፡፡ |
| Ni tolchite yaa bosuu | ጥሩ አደረግሽ ድኩላ |
| Xiyyitii kan reebenoo | የሚየባርሩት ጥይት ነው |
| Eeboo kan dheessanoo | የሚሸሹት ጦር ነው |
| Qawwee dhiiratu qabataa | ጠመንጃ ጀግና ነው የሚይዘው |
| Yoo ajjeesu tokkoonii | ብገድልም አንዴ ነው |
| Eeboo gadheetu baataa | ጦር ፈሪ ነው የሚይዘው |
| Dhiira kufe waraantii | የወደቀውን ወንድ ትወጋለች |
| Yoo waraantu sodaanii | የሚትወጋውም በፍሪሃት ነው፡፡ |

XXXX

| | |
|---|---|
| Jijjigaa mana hingodhuu | ፍርስራሽን ቤቴ አላደርግም |
| Hinuman diiga malee | እተወዋለሁ እንጂ |
| Yartuu hiriyyaa hingodhuu | ፈሪውን ጓደኛዬ አላደርግም |
| Hinuman dhiisa malee. | እተወዋለሁ እንጂ፡፡ |

# አባሪ 3

## የከዋኞች ፎቶ



የአምስቱ መረጃ ሰጪዎቹ



አቶ አባተ ኤጀርሳ በ21/06/2004 ዓ.ም በአቶ አዱኛ ጅግ ቤት ጌረርሳ ሲከውኑ



አቶ መኮንን ደሜ በ21/06/2004 ዓ.ም በአቶ አዱኛ ጅግ ቤት ጌረርሳ ሲከውኑ



አቶ ብርሃኑ አዱኛ በ21/06/2004 ዓ.ም በአቶ አዱኛ ጅማ ቤት ጌረርሳ ሲከውኑ



አቶ ድሪባ ለታ በ21/06/2004 ዓ.ም በአቶ አዱኛ ጅማ ቤት ጌረርሳ ሲከውኑ



አቶ ቸሩ ድንቁ በ21/06/2004 ዓ.ም በአቶ አዱኛ ጅማ ቤት ጌረርሳ ሲከውኑ



አቶ አባተ ኤጀርሳና ችሩ ድንቄ በ21/06/2004 ዓ.ም በአቶ አዱኛ ጅማ ቤት አብረው ጌረርሳ ከከውኑ በኋላ አቶ መኮንን መዳላ ሊያጠጡዋቸው ስሉ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የኔ ሥራ መሆኑንና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸው ተዛማጅ ጽሑፎችና መረጃዎች በትክክል በመጥቀስ የተጠቀምኩባቸው መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡ ግርማ አዱኛ

ፊርማ፡-------------------------

ቦታ፡ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ

ቀን፡ ጥቅምት 07 ቀን 2005 ዓ.ም